


www.ethipianorthodox.org

# ገድለ ሰማዕታተ ኢትዮጵያ



ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም እና ሐምሌ ፫፡ ፭፡ ፯፡ ፲ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም የተሰዉ የ፷፷ ሰማዕታት አጭር የሕይወት ታሪክ



www.ethipianorthodox.org

# ማውጫ

## መቅድም


### ክፍል አንድ

ገጽ

ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የተሰዉ ሰማዕታት አጭር የሕይወት ታሪክ 9

ሲቪል ባለሥልጣኖች . . . . . . 13

ወታደራዊ ባለሥልጣኖች . . . . . 71

### ክፍል ሁለት

ገጽ

ሐምሌ ፫ ፤ ፭ ፤ ፯ ፤ እና ፲ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ተወስደው የተሰዉ ሰማዕታት አጭር የሕይወት ታሪክ 111

### ክፍል ሦስት

ገጽ

የሰማዕታቱ ፍልሰተ አጽምና የቀብር ሥነ ሥርዓት . . . . . 131

በበዓሉ ዕለት የተደረጉ ንግግሮች . . 135


www.ethipianorthodox.org

## አዲስ አበባ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የታነፀው የ፷፷ ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት መታሰቢያ ወመዘክር ተመረቀ ።

ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም እና ሐምሌ ፫ ፣ ፭ ፣ ፯ ፣ እና ፲ ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በግፍ የተገደሉት ፷፷ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች አጽም ያረፈበት የመታሰቢያ ሐውልት ለሚኖች ቤተሰቦችና ወገኖች ፣ መንፈሳዊ አባቶች ፣ ታዋቂ አዛውንቶችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ተመርቆ ተከፍቷል ።

የመታሰቢያ ሐውልትና የታሪክ ሙዚየም የሆነው መካነ መቃብር በማናቸውም ጊዜ ለሕዝብ ክፍት ስለሚሆን ተተኪው ትውልድ የሰማዕታቱን ገድልና የደርግን መንግሥት ግፍ ለማስታወስ እንደሚረዳ ይታመናል ።

የሐውልቱን ምረቃ ቀን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው ይህ መጽሔት በፋሺስቱ ደርግ ባለቤቶቻቸውን ፣ አባቶቻቸውን ፣ ወንድሞቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ላጡ ሁሉ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ያመቁትን ሐዘን እንዲገልጹበትና በግፍ ለተገደሉት ሰማዕታት ቅድመ ታሪክ ወይም የታሪክ መግቢያ እንዲሆን በእያንዳንዱ ቤተሰብ የተዘጋጀ ማስታወሻ ነው ።

እነዚህ ሰማዕታት የኢትዮጵያ ነፃነት ክብርና ሕልውና ተጠብቆ ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የዘመናዊ ትምህርትና ጥበብ ተጠቃሚ እንድንሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉና ሕዝቡም በቀሰመው የእእምሮና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ሐገሩን እንዲገነባ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተጨባጭ የሆነ አስተዋፅኦ ያስመዘገቡ የሐገሪቱ አለኝታዎች ስለነበሩ ፣ ለሀገራቸው ዕድገትና ሁለንተናዊ የሥልጣኔ ሂደት ያከናወኑትን ተግባር በዚህ መጽሔት ውስጥ አጠቃልሎ ለማስፈር ያዳግታል ።

ሰላሳ ሶስተኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሐሪ ትሩማን "ሰዎች ታሪክን ይሠራሉ እንጂ ታሪክ ሰዎችን አይሠራም ፣ ዕድገትና መሻሻል ሊኖር የሚችለው ቆራጥ ትጉህና ብልህ የሆኑ መሪዎች በተሰጣቸው ዕድል ተጠቅመው የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ (ሕይወት) ወደ ተሻለ ሁናቴ መለወጥ ሲችሉ ብቻ ነው ።" እንዳሉት እነዚህ ሰማዕታት በተለያየ መስክ ታሪክ ሠርተው አልፈዋል ። ይህ የማይካድ ታሪክ በሰፊው ተመዝግቦ ለአንባቢያንና የኢትዮጵያን ታሪክ መገምገም ለሚሹ ሁሉ የሚቀርብበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።

መልካም ስምና መልካም ሥራ ከመቃብር በላይ መዋሉ በአበው ሲነገር የኖረ ሀቅ ነውና ።

ኢትዮጵያን ቀደም ብሎ ትወገዝበት ከነበረው የፊውዳል ሥርዓት ሙሉ በሙሉ አላቆ ጥፋት በማያስከትል የተመዛዘነ ሥልት ወደ ሀያኛው ምዕተ ዓመት የሥልጣኔ ዘመን ለማሸጋገር ሌት ከቀን በሚጥሩበት ጊዜ ሰማዕታቱ ተይዘው ለሰብአዊ መብትና ለፍትህ ልዕልና መከበር ላቋቋሙት ፍርድ ቤት እንኳ ሳያበቁ በግፍ መገደላቸውን የዛሬውም ትውልድ ሆነ መጪው ሊዘክረው የሚገባ እውነታ ነው ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ በመፈክርና በማያቋርጥ ፕሮፓጋንዳ ሸንግሎ በሥልጣን ኮርቻ ላይ የተቀመጠው የደርግ ጁንታ ፣ ታሪክና ትውልድ ሊዘነጋው የማይችል ጥፋት አድርሶ ጠፍቷል ። በ፲፯ ዓመታት ውስጥ (፲፱፻፷፯—፲፱፻፹፫) በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈፀመውን ግፍ ወደኋላ መለስ ብለን ስናጤን ሕሊናችንን የሚዘገንን ነው በከንቱ እንደ ጎርፍ የፈሰሰው የንጹሐን ደም ብቻ አይደለም ። ሐገሪቱን ከቶውንም ተመልሳ ማንሰራራት ወደማትችልበት የኢኮኖሚ የፖለቲካና የማህበራዊ ኑሮ አዘቅት ውስጥ ጥሏት በመጥፋት እጆችዋን ምፅዋት ወደሚለግሱ ባዕድ አገሮች ዘርግታ እንድትለምን ዳርጓታል ።

የቀድሞው ሥርዓት ለኢትጵያ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ሕይወት ኋላ ቀርነት ምክንያት ነው እየተባለ በአንዳንድ ክፍሎች ዛሬም በመወገዝ ላይ ቢሆንም ፣ ቀደም ሲል በአጼ ምኒልክ ኋላም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴና በግፍ በተገደ

www.ethipianorthodox.org

ሉት አጋሮቻቸውና የሥራ መሪዎቻቸው የተከ
ናወነው የሐገር ግንባታ ተግባር በኢትዮጵያው
ያንና በውጭ ሐገር ምሁራን እየተገመገመ የጎላ
ሥፍራና አድናቆት እያገኘ መጥቷል ።

በአንጻሩ የኢትዮጵያን እድገት በአጭር ጊዜ
ውስጥ ከፍ ወዳለ ግብ ለማድረስ "ሥር ነቀል
ለውጥ አማራጭ የሌለው አብዮታዊ ሂደት ነው"
በማለት ሕዝቡን አራዊቱን እጽዋቱን ያነድ
የነበረው የፋሽስቱ የደርግ ሥርዓት ያጠፋው
ጥፋት ወሬና ሥራ ለየቅል መሆናቸውን አስተ
ምሮናል ። ዳሩ ግን ሀገሪቱን አዲስ ሥርዓት ለማ
ላበስ በተደረገው ከንቱ ሙከራ የልምምድ
መስክ የነበረው ሕዝቡ ራሱ ስለነበር ለደረሰው
ጥፋት ተጠያቂው ማነው የሚለውንም ጥያቄ
ሳያስከትል አይቀርም ።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምናውቅለት እኛ ነን
በማለት በተግባር መግለጽ ለማይችልና ለማይ
ጨበጥ ጭፍን ዓላማ ተገዢ ሆነው ሲራወጡ
የተቀሰፉት አያሌ ወጣቶች የእሳት እራት የሆ
ኑት የሕዝቡን ምኞትና ማድረግ የሚቻለውን
መገንዘባቸው ብቻ አልነበረም ። በአስተሳሰብ
የመብሰል ሒደትና የልማት ሥራ በአጭር
ጊዜ ውስጥ ከግብ የማይደርስ እልህ አስጨራሽ
የሆነ ትዕግሥት እንዲሁም በቀና መንፈስ ላይ
የተመሠረተ የማያቋርጥ ትግል የሚጠይቅ መሆ
ኑን ለደርጉ አሽቃባጮችና ነፍስ ለማጥፋት
ይክለፈለፉ ለነበሩት ካድሬዎች የተከሰተላቸው
ይከተሉት የነበረው ርዕዮተ ዓለም በመስኮቦች
ሳይቀር የተወገዘ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪኩን ፤ ሃይማኖቱን
ባሕሉንና ጠቃሚ ነው የሚለውን ልማዱን ሳይ
ለቅ በተጠና ዕቅድ ይከናወን የነበረውን የዕ
ድገት እርምጃ አደናቅፎና አጨናግፎ በአባቶች
መቃብር ላይ ምንነቱን ያልተረዳውን የኮሚዩኒ
ስት ባንዲራ ያውለበልብ የነበረው ደርግ ፤ በብዙ
ድካምና ውጣ ውረድ የተገነባውን የሐገሪቱን
ፖለቲካ ፤ ማሕበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት እን
ዳልነበረ አድርጓል ።

የሐገራችን መለያና መታወቂያ የነበረው
ኢትዮጵያዊነት ራሱ ዛሬ ትርጉም አጥቶ አያሌ
ምሁራንን የሚያነጋግር ርዕስ እየሆነ ለመድረክ
በመቅረብ ላይ ነው ። የኢትዮጵያ ወግና ሥርዓት
ባህልና ልማድ ፤ ሰብአዊነትና ጨዋነት ፤ ትህ
ትናና ፈሪሃ እግዚአብሔር ብፁአነምድር በነበ
ሩት የደርግ ፋሽስቶች ተደምስሷል ። ይህ ነው
የሚባል ዓላማና ግብ የሌለው መንጋ ትውልድ
(አዲሱን ሰው)_ ለመፍጠር ይደረግ የነበረው
ዘመቻ ግን ሰው በላ ከመሆንና አገር ከማጥፋት
አላለፈም ።

ሰማዕታት የደከሙበትን ፤ ደርግና ጀሌ
ዎቹ ያፈራረሱትን መልሶ ለመገንባት እኛ የም
ንኮራባት እንጂ የምናፍርባት ኢትዮጵያ ሆና
እንዳትቀር ለማድረግ የአርቆ አስተዋይ የተቆ
ርቋሪ መሪዎችን ፤ የሰከኑ ምሁራንንና የመላውን
ሕዝብ ጥረት ይጠይቃል ።

አዎን ሰዎች ታሪክን ይሠራሉ እንጂ ታሪክ
ሰዎችን አይሠራም ። የደርግና የአበሮቹ ተልዕኮ
የጥፋትና የክፋት ስለነበረ ታሪክ የሚመዘ
ግብለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አጎናጽፌዋለሁ
ይል የነበረውንና በአጉል መፈክርና ፕሮፓጋንዳ
ታጅቦ በተውሶ ካባ የተከበበውን ከንቱ ርዕዮተ
ዓለም ብቻ ሳይሆን ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ
የፈጸመውን ኢሰብአዊ የሆነ ግፍና ጥፋት ይሆ
ናል ።

ኢትዮጵያን በትምህርትና በረጅም ዘመን
የሥራ ልምድ_የበሰሉ መሪዎቿን ፤ በዱር በገ
ደል እየተዋደቁ የአባቶቻችንን የጀግንነት ታሪክ
ሲያድሱ የቆዩትን ስመጥር አርበኞቿን ፤ በዓ
ለም አቀፍ የፖለቲካ መድረክ ተናግረው የሚደ
መጡትንና ተሟግተው የሚረቱትን ዲፕሎማ
ቶቿን ያሳጣት ደርግ የተባለው ጁንታ ያለ
ግፍና ጥፋት ማልማትን እንደማያውቅ ሥራው
መስክሮበታል ። ሐምሳ ዓመት ሙሉ በሰከነ
መንፈስ የተደከመበትን የተማረ ሰው ኃይል ፤
ብዙ ጥረት የተደረገበትንና አያሌ ጥሪት የፈሰሰ
በትን የማቴሪያል ሐብት የሕዝቡንም ሞራላዊና
ሥነልቦናዊ ንቃት አፈራርሶ ለትውልድ ሊተላ
ለፍ የሚገባውን ውርስና ቅርስ ጥቅም አልባ
አድርጎታል ።

ደርግ የእብሪት መፈክሩን እያቅራራ በግፍ
ከገደላቸው ከእነዚህ ሰማዕታት መካከል ዕድሜ
ያቸው ከሰልሳ ዓመት በላይ የሆኑ ጥቂት አልነ
በሩም ። ይህ የዕድሜ ጣራ በወለም ዘለም ዘመን
በመቁጠር የተገኘ የጊዜ ክምችት አይደለም ። የት
ራንስፖርት ፤ የመገናኛና የሕክምና አገልግሎት
ባልነበረበት ዘመን በእግርና በከብት እየተዘ
ዋወሩና ሐሩሩን ንዳዱንና የዱር አራዊቱን እየ
ተቋቋሙ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ያስከበሩትን
የሐገሪቱን የግዛት አንድነት ጠብቀው ለተተኪው
ትውልድ ያስረከቡበት ቁምነገርና ታሪክ እየሠሩ
የተጓዙበት የዕድሜ መስፈርት መሆኑ በግልጽ
መታወቅ አለበት ።

የደርግ ፋሽስቶች ያደረሱትን አሰቃቂና ትር
ጉም የለሽ ጭፍጨፋ ወደኋላ መለስ ብለን ስና
ስብ "የበደልነውን ሕዝብ ይቅርታ እንጠይቃ
ለን" በሚለው የለበጣ አነጋገር ይቅርና ፍጹም
ቅጣት እንኳ ለበደሉ በቂ ካሣ ሊሆን አይችልም ።
ዋናው ችግር የተበደሉት ሳይካሱ ፤ የሞቱት ይረ
ሳሉ ። ትላንት የተፈጸመው ግፍ ዛሬ ታሪክ መሆ
ን ይጀምራል ። ትላንት ያለአንዳች ፍርድ በግፍ
የጨፈጨፉትን ሕዝብ በግሬደር እያፈሱ በየፈ
ፋው ሥር በመሸጎጥ ለዱር አራዊት የዳረጉት
ወንጀለኞች ዛሬ እንለቀቅ ሲሉ መስማቱ እጅግ
ያስገርማል ። የገደሉት ሕዝብና እስከ ሕይወቱ
መጨረሻ እንዲናወዝና እንዲባክን ያደረጉት ትው
ልድ ገና ይፋረዳቸዋል ።

ኢትዮጵያን በድላችኋል ተብለው በሞት
እንዲቀጡ ሕሊና በሌላቸው ጋጠወጦች የተገ
ደሉት ባለሥልጣኖች ለኢትዮጵያ ዕድገትና ብል


www.ethipianorthodox.org

ጽግና ያደረጉት አስተዋጽኦ ሀገራችን በታሪክ እስከዛሬ ካስመዘገባቸው ሁሉ የላቀ እንደነበር አሌ አይባልም ።

ከ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በፊት በሰላም ይከናወን የነበረውን ሁለንተናዊ የሐገር ግንባታ ገቶና አፈራርሶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለ፲፯ቱ የድሕነት የስደት ፤ የዕልቂትና የሰቆቃ ዘመን የዳረገው የደርግ ሥርዓት ግን በሐገሪቱ ላይ ላደረሰው በደል መስፈርት ማግኘት ይሳናል ።

የደርግ መንግሥት የጥፋት ተልዕኮ ምን ይመስል እንደነበር ለመረዳት የባለሙያዎችን ማብራሪያ አይጠይቅም ። ጠባዩና ግብሩ የተሠራውን ማፍረስ ፤ የተመኘውን መንጠቅ ፤ አርሶ መለመን ፤ ተዋግቶ መሸነፍ ፤ ተከራክሮ መረታት ፤ ፎክሮ መሸሽ ፤ አጥፍቶ መጥፋት ስለነበር ኢትዮጵያ ዛሬ ከምትገኝበት ውድቀት መድረስዋ የሚያስገርም አይሆንም ።

"ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን የሀሰት መፈክር አንግቦ ኢትዮጵያን በደም ጎርፍ ያጥለቀለቃት የደርግ መንግሥት በይፋ የሚያውጀውና በተግባር የሚፈጽመው ተጣጥሞ ስለማያውቅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያተረፈው እልቂት ፤ ውርደትና ድቀት ብቻ ነው ።

ዛሬ ተመርቆ የተከፈተው የመታሰቢያ ሀውልት ለሁለት ዐቢይ ጉዳዮች የቆመ የታሪክ ማስታወሻ ነው ። በአንድ መልኩ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ፤ በዕድሜ ለጋ ከሆኑ ወጣቶች እስከ አረጋዊ አባቶች በአምባገነኑ የደርግ ዘመን በግፍ የተገደሉ መሆናቸውን መጪው ትውልድ በጥሞና እንዲያስታውስ የቆመ መታሰቢያ ነው ። በሌላ በኩል ያለሕዝብ ፈቃድ የጦር መሣሪያ አንግበው ሥልጣን የሚይዙ አምባገነኖች ሁሉ ከጥፋት ከእብሪትና ከሕገወጥ ተግባር ሌላ ለሐገር ለወገን ጥቅምና እድገት የሚቆረቆሩ እንደማይሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወዲሁ አበክሮ እንዲያስብበት እና የትላንቱ ታሪክ ነገም ሊደገም የሚችል መሆኑን እንዲገነዘብ የቆመ የመታሰቢያ ሐውልት ነው ።

www.ethipianorthodox.org

## ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የተሰዉ ሰማዕታት አጭር የሕይወት ታሪክ ።

ስድሳ ከፍተኛ የሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣኖች ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም መገደላቸውን ደርግ ያስታወቀው በሬዲዮ ኅዳር ፲፭ ቀን በጋዜጣ ደግሞ ህዳር ፲፯ ቀን ነበር ። ዝርዝር ሁኔታው እስከአሁን ስላልተገለጸ ፣ መንግሥት ወደፊት ያለውን መረጃ ይፋ እስከሚያደርግ ከዚያን እለት ጀምሮ እስከሬናቸው እስካረፈበት ቀን ድረስ ድርጊቱ ምን ይመስል እንደነበር በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል ።

እጅግ አሰቃቂ የሆነው የኅዳር ፲፬ ቀን ግድያ የተፈጸመው አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ውስጥ ሲሆን ፣ የደርግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የደህንነት አባላት በአስፈጻሚነት ፣ ሌሎች የደርግ አባሎችና ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የተወከሉ ሰዎች ደግሞ በታዛቢነት በቦታው ተገኝተው ነበር ። የአገዳደሉ ሁኔታ ፣ በግድያው የተካፈሉት ሰዎች የተተኮሰው ጥይት አይነትና ብዛት ሳይቀር በዝርዝር መመዝገቡ ታውቋል ።

ኅዳር ፲፬ የተገደሉት ባለሥልጣኖች እነማን ነበሩ! ከሲቪሎች ሁለት ጠቅላይ ሚኒስሮች ፣ አንድ ልዑል ፣ ፲፪ ሚኒስትሮች ፣ ፲፩ የጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎችና የአውራጃ ገዢዎች ፣ አንድ ፀሐፊና አንድ በግል እርሻ የተሰማራ ግለሰብ ናቸው ። ከወታደሩ ክፍል የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የልጅ ልጅ ፣ ፱ ሌፍቴናንት ጄኔራሎች ፣ ፫ ሜጀር ጄኔራሎች ፣ ፫ ብርጋዴር ጄኔራሎች ፣ ፫ ኰሎኔሎች ፣ ፯ የመስመር መኰንኖች ፪ የበታች ሹማምንቶች ነበሩ ። በእድሜ ክልል መስፈርት ከ፲፰ ዓመት ወጣት እስከ ፸፭ ዓመት አዛውንት ይገኙባቸዋል ።

ግድያው የተጀመረው ኅዳር ፲፫ ቀን ከሰዓት በኋላ ነበር ። ሌ/ጄኔራል አማን አንዶም እጃቸውን አልሰጥም በማለታቸው ቤታቸውን ከቦ የነበረው የደርግ ኃይል በታንክ ጭምር በከፈተው ተኩስ ቤቱ በተደረመሰበት ወቅት ጄኔራል አማንና ረዳቶቻቸው ተገደሉ ።

ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም/ ደግሞ የግድያው እንቅስቃሴ የተጀመረው ከምሽቱ ኡስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ነበር ። ዙሪያቸውን የተሸፈኑ የእስር ቤት መኪናዎች መጥተው ከታላቁ ቤተመንግሥት እስር ቤት አጥር በር ላይ ቆሙ ። ከሌሎች እሥር ቤቶች የሰበሰቧቸውን ሰዎች ከዙፋን አዳራሽ አካባቢ በሩ ላይ ወደቆሙት መኪናዎች ወሰዷቸው ።

ከዙፋን አዳራሽ ሥር ይገኝ የነበረውና ቁጥር አንድ ሁለት በመባል የታወቀው እስር ቤት በሮች በብርድልብስ ተሸፈኑ ።

መጀመሪያ ከሁለት ቁጥር ከዚያም ከአንድ ቁጥር በየተራ ስማቸው የተጠሩት እስረኞች ከየክፍላቸው እንደወጡ ሁለት ሁለት በካቴና ተቆራኝተው ውጭ ወደቆሙት የእስር ቤት መኪናዎች ተወሰዱ ። አንዳንድ ከህመም የተነሳ መቆም እንኳ የተሳናቸው አዛውንቶች መኪና ውስጥ የገቡት ጓደኞቻቸውን ተደግፈው ነበር ።

መኪናዎቹ ወደ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ገሰገሱ ። ከእስር ቤቱ ቅጥር ግቢ ሲደርስ ወደ አለም በቃኝ የሚወስደውን መንገድ ትተው ወደ ቀኝ ታጠፉ ። የተፈረደባቸው ወንጀለኞች በኤሌክትሪክ ወደ ሚገደሉበት ቤት አመሩ ። ቦታው በታጠቁ ወታደሮችና መትረየስ በጠመዱ ጂፖች ታጥሯል ። እስረኞቹ ከመኪና እየወረዱ ከተጠቀሰው ቤት አጠገብ እንዲሰበሰቡ ተደረገ ።

በቦታው ላይ ተገኝቶ ግድያውን ያስተባበረውና የመራው የደርግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር የነበረው ሻለቃ ራሱ ነው ።

የፓውዛ መብራት እስረኞቹ ፊት ላይ ተነጣጥሮ ስለነበር አካባቢውን መረዳት በማይችሉበት ሁኔታ ላይ እንደሆኑ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በሬዲዮ የተነገረውን መግለጫ የሚመስል

ጽሑፍ ተነበበና ዙሪያውን ተሰልፎ የቆመው የግድያ ጓድ ተኩስ ከፈተ ። የጥይቱ ናዳ በእስ ረኞቹ ላይ ወረደ ፤ ወደቁ ፤ ረገፉ ፤ ሬሳ በሬሳ ላይ ተከመረ ከፍተኛ ተኩስ በኋላ የሰማዕታቱ ፉከራና ሲቃ እርጭ አለ ።

ከታሰሩበት ሰንሰለት ጋር እንዳይቀበሩ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ስለነበር ፤ አንድ የወህኒ ቤት የበታች ሹም ከሬሳው መሀል ገብቶ ካቴ ናውን ከእጃቸው አወጣ ። የጄኔራል አማንና የሁለት ረዳቶቻቸው አስከሬን ከቀሩት ጋር እን ዲቀላቀል ተደረገ ።

በማግስቱ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የወህኒ ቤት እስረኞች ታዘው ጉድጓድ ሲቆፍሩ ዋሉ ። ቦታው ረግረግና ውሃ የሚተኛበት አረ ንቋ ነበር ። ምሽቱኑ የሰማዕታቱ አስከሬን አድሮ ከዋለበት ተነስቶ ከነልብሳቸው ጉድጓድ ውስጥ ተነባብሮ ተጣለ ። መጀመሪያ ኖራ ተረ ጨበት ፤ ከዚያም አፈር ለበሰ ።

ደርግ ኅዳር ፲፮ ቀን በራዲዮ እንዲሁም ኅዳር ፲፯ ቀን በጋዜጣ ባወጣው መግለጫ የሲቪ ል ባለሥልጣኖች ቁጥር ፳፱ ነበር ። በዚህ የታ ሪክ ማህደር የተመዘገበው የሲቪል ባለሥልጣ ኖች ቀጥር ፴፫ ነው ። ይህ የሆነበት ምክንያት በልዩ ልዩ የሲቪል ሥራ ላይ ተሰማርተው የነ በሩትን ከፍተኛ መኰንኖች እንደሲቪል በመ ቁጠር ነው ። እንዲሁም በደርግ ዘገባ የተገደሉት የጦርና የፖሊስ መኰንኖች ቁጥር ፴፮ ነበር ። ይህ ስሌት ማዕረጋቸውን እንጂ የነበሩበትን ሥራ ስላልተከተለ በወቅቱ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት አባል የነበሩትን ብቻ በመውሰድ ቁጥሩ ፳፯ ሆኖ ቀርቧል ።

የሕይወት ታሪካቸው ቅደም ተከተል የቀረ በው በተቻለ መጠን በዘመኑ የነበራቸውን ፕሮ ቶኮል ተከትሎ ነው ።



www.ethipianorthodox.org

## ሲቪል ባለሥልጣኖች

# ክቡር ፀሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ

## 1904-1967

ጎበዝ፡ ሰው — [illegible]፡
[illegible]፡ ጎበዝ፡
ሰው — [illegible]።

[illegible]



ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ለጋሲዮን የፕሬስ አታሼ በመሆን ሥራ ጀምረው በአገር ውስጥ በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች በሚኒስትርነትና በመጨረሻም ለ፲፫ ዓመታት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ለሀገራቸው ነፃነት ፣ አንድነት ፣ እድገትና ብልጽግና ለ፵፱ ዓመታት ያገለገሉ አስተዋይ መሪ ነበሩ ።

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በምሥራቅ ሸዋ አስተዳደር በአድአ ወረዳ ልዩ ስሙ ደምቢ በሚባል ሥፍራ ከአለቃ ሀብተወልድ ካብቴነህና ከወይዘሮ ያደግድጉ ፍልፍሉ መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፬ ዓ/ም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ የአማርኛ ትምህርት በአዲስ አበባ በሚገኘው በቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ፣ ዘመናዊ ትምህርት ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማሩ ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፲፯ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ግብፅ ሀገር ተልከው በሊሴ አሌክሳንድሪ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ተከታትለው በ፲፱፻፳፫ የፈረንሳይን ባኩሎሪያ በማዕረግ ተመረቁ ። ከእዚያም ወደ ፈረንሳይ አገር ሔደው በሶርቦን ዩኒቨርስቲ ከ፲፱፻፳፫—፲፱፻፳፰ ድረስ ሲማሩ ቆይተው በመጨረሻ በሕግ ትምህርት ሊሳንስ (ኤል ኤል ቢ) አገኙ ። በተጨማሪም ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በፐብሊክ ሎው እና በኢኮኖሚክስ ዲፕሎማ ደ ዶክትራ እንዲሁም በንግድና በፖለቲካ ሳይንስ ሰርተፊኬት ተቀብለዋል ።

ክቡርነታቸው በሊሴ አሌክሳንድሪ በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜ በግብጹ የኮፕቲክ ፓትሪያርክ በአቡነ ዮሐንስ ለትምህርት የተወሰዱት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ችግር ላይ ስለወደቁ በጊዜው የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና ባለሙሉሥልጣን እንደ ራሴ ከነበሩትና ከግብፅ ባለሥልጣኖች ጋር በመነጋገር ችግሩ እንዲፈታ አድርገዋል ።

ፈረንሳይ ሀገር ሶርቦን ዩኒቨርስቲ በትምህርት ላይ እንዳሉ ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣሊያ በመወረሯ በሊግ ኦፍ ኔሽን የኢትዮጵያ ዴሊጌሽን ዋና ጸሐፊ ፣ ከዚያም ፓሪስ በኢትዮጵያ ለጋሲዮን የፕሬስ አታሼ ፣ ከ፲፱፻፳፰—፲፱፻፳፱ ደግሞ አን

ደኛ ጸሐፊና ከ፲፱፻፳፱—፲፱፻፴፫ ጉዳይ ፈጻሚ በመሆን ሲሠሩ ኢጣሊያኖች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ይፈጽሙት የነበረውን ግፍ ለመላው ዓለም በማሳወቅ በአደረጉት ትግል ኢትዮጵያ የአውሮፓውያንን ድጋፍ እንድታገኝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ኢትዮጵያ ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላም ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ወደ እናት ሀገራቸው ተመልሰው ፣ ከ፲፱፻፴፮ እስከ ፲፱፻፶፪ ዓ/ም በጽሕፈት ሚኒስቴር ም/ሚኒስትር ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ም/ሚኒስትር ፣ እንዲሁም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል ። ከ፲፱፻፶፫ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር ሆነው ከመሥራታቸውም በላይ በተደራቢነት በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የአገር ግዛት ሚኒስቴር ሚኒስትር ነበሩ ።

ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ለሀገራቸው ነፃነትና አንድነት ገና በትምህርት ቤት ሳሉና በዚያም በተከታታይ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ካደረጉት ትግል በተጨማሪ ለእድገቷና ለብልጽግናዋ የፈጸሟቸው ተግባራት በርካታ ቢሆኑም ለአብነት ያህል ጥቂቱ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ተመልክቷል ።

እንግሊዞች ቀደም ብለው ይዘዋት የነበረውን ጋምቤላን ፣ ፈረንሳዮች ጅቡቲ ጠረፍ አጠገብ ያለችውን ውኃ ያለባትንና ስትራተጂክ የሆነችውን አፋምቦን ፣ እና እንግሊዞች ኦጋዴን ለቀድሞው ብሪትሽ ሶማሌላንድ የግጦሽ መሬት ብለው የያዙትን ሪዘርቭድ ኤሪያን እንዲሁም ለማስተዳደር ችሎታ የላችሁም ብለው የያዙትን የምድር ባቡር አስለቅቀዋል ። ኢጣሊያኖች ሲወጡ ከእንግሊዞች ጋር የነበረው ስምምነት የእንግሊዞችን የበላይነት የሚያንፀባርቅ በመሆኑ የኢትዮጵያን መብት በሚያስከብር መልክ እንዲለወጥ ፣ የሀገሪቱ የወሰን ክልል (በሱዳንና በሶማሊያ በኩል ያለው ሲቀር) ሌላው በሰላም ውሳኔ እንዲያገኝ አድርገዋል ።

ክቡር ፀሐፊ ትእዛዝ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት፣የአንድ ሀገር አስተዳደርና እድገት ሊጎለብት የሚችለው የተጠናከሩ ድርጅቶች ሲኖሩት መሆኑን በመገንዘብ ለእነዚህ መሠረት የሆነው ሕገ መንግሥት ተሻሽሎ እንደገና እንዲወጣ ፣ ከዚያም የፍትሐ ብሔርና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች ከነሥነ ሥርዓቶቻቸው ፣ የንግድና የባሕር ሕጎች ፣ የጠቅላይ ሚኒስትርና የሚኒስትሮች ሥልጣንና ተግባር የሚወስን ሕግ ፣ የዳኞች አሿሿምና በፍርድ አሰጣጥ ነፃነት ሕግ ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ሕግ ፣ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያና የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ ፣ የአገር አገዛዝ ደንብ ፣ የውትድርና አገልግሎት ሕግ ፣ ሌሎችም የአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሥራ ሂደት የሚያፋጥኑና ሥነ ሥርዓት የሚያስይዙ ሕጎች እንዲወጡ አድርገዋል ። በልማቱም መስክ የሁለተኛውና የሶስተኛው አምስት ዓመት ፕላን እንዲዘጋጅ የሕብረተሰቡ የሥራ ፍላጎት ከፍ እንዲልና የሥራ ፈቱ ቁጥር እንዲቀንስ በሰጡት አመራርና በአደረጉት አስተዋጽኦ በመንግሥትና በግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ይገኝ የነበረው ምርት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት በማሳደግና የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በማርካት ረገድ የታየው ኢትዮጵያ አስተማማኝ አቅጣጫ እንደያዘች የሚያመለክት ነበር ።

የኢንተርናሽናል ድርጅቶች በሀገር ውስጥ መቋቋም የኢኮኖሚ ጥቅምና ለአገር ክብር እንደሚያስገኝ በመገንዘብ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲቋቋምና ቻርተሩ እንዲፈረም ፣ ጽ/ቤቱም አዲስ አበባ እንዲሆን ፣ የአፍሪካ ኤኮኖሚክ ኮሚሽን ጽ/ቤትም አዲስ አበባ እንዲመሠረት አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ በኤኮኖሚ ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካ መስኮች በአገር ውስጥ አመራር በመስጠት በሚያካሒዱት የኃላፊነት ሥራ ብቻ ሳይወሰኑ በአያሌ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ላይ እየተገኙ ታሪካዊና መሠረታዊ የሆኑ ተግባራት አከናውነዋል ።

ለምሳሌ ያህል ፡—

ሀ/ ፓሪስ በተደረገው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ የሰላም ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታት ጋር በእኩልነት ደረጃ ተካፋይ እንድትሆን በአደረጉት ጥረት በአፍሪካ ውስጥ በቅኝ አገዛዝ ሥር የሚኖሩት አገሮች ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ፣ ኢጣልያን በቅኝ ግዛት የያዘቻቸውን ሀገሮች እንድትለቅና ለኢትዮጵያ ፳፭ ሚሊዮን ዶላር የጦር ካሣ እንድትከፍል ፡ እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን የጠላት ንብረት ኢትዮጵያ እንድትወስድ አስወስነዋል ።

ለ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በአሜሪካን ሀገር በሳንፍራንሲስኮ ከተማ በ፲፱፻፴፯ ሲረቀቅ ኢትዮጵያ የመንግሥታት ማኅበር መሥራች ሀገር እንድትሆን ከፍተኛ ጥረት አድርገው ይኸው በመሳካቱ ቻርተሩን በሚያዘጋጀው ጉባኤ ላይ ተካፍለው በመጨረሻ ቻርተሩን በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ፈርመዋል ።


www.ethipianorthodox.org

ሐ/ ከ፲፱፻፴፱—፲፱፻፵፩ አራቱ ታላላቅ መንግሥታት የኤርትራን ጉዳይ ለመመርመር በአደረጉት ጉባኤና ከእዚያም በኋላ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ በታየበት ጊዜ ፣ ኤርትራ ከእናት ሀገሯ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ተከራክረው በማሳመን አዎንታዊ የሆነ ውጤት አስገኝተዋል ።

መ/ የስዊስ ካናል ችግር በደረሰ ጊዜ የኢትዮጵያ መልእክተኞች መሪ በመሆን በለንደን ጉባኤ ላይ ከተካፈሉ በኋላ ወደ ፕሬዚዳንት ናስር ከተላኩት የአምስት ሀገሮች መልእክተኞች አንዱ ሆነው ተመርጠዋል ።

ሠ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አሥራ አምስተኛ ዓመቱን እስከአከበረበት ድረስ ፣ የኢትዮጵያ መልእክተኞች መሪ በመሆን በስብሰባው ላይ እየተገኙ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኮለክቲቭ ሲኩሪቲና በተባበሩት መንግሥታት ላይ ያላቸውን ጽኑ እምነት ግንዛቤ እንዲያገኝ አድርገዋል ።

ረ/ የአፍሪካ ነፃ መንግሥታት አራት ብቻ በነበሩበት ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት በ፲፱፻፶፭ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ በአንድ ድምጽ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠው ጉባኤውን መርተዋል ። በዚያን ጊዜ አንድ አፍሪካዊ ለዚህ ኃላፊነት ሲመረጥ እርሳቸው በታሪክ የመጀመሪያው ነበሩ ።

ሸ/ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአዲስ አበባ ውስጥ በአደረጋቸው የመሪዎች ስብሰባ ላይ አዘውትረው ተካፍለዋል ። በተለይም ከግንቦት ፲፬—፲፯ ቀን ፲፱፻፶፭ በተደረገው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ ላይ የሶማሊያ ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት የጎሣ ጉዳይ አንስተው ባሰሙት ንግግር "የሶማሊያ ዜጎች በኢትዮጵያ ፣ በፈረንሳይና በእንግሊዝ ግዛት ስር ይገኛሉ ። ኢትዮጵያ ያለ ሶማሊያ ሕዝብ ፈቃድ የሶማሊያን መሬት ነጥቃ ወስዳለች" በማለታቸው ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ የቀረበው ክስ መሠረተ ቢስ መሆኑን ጠቅሰው ኢትዮጵያ ታሪኳ የታወቀና ነፃነቷን ከሦስት ሺህ ዘመን አንስቶ የሕንድ ውቅያኖስን የሚያካብብ ለመሆኑ ታሪክ እንዲመሰክርላት ፣ በታሪክ ውስጥ የሶማሊያ መንግሥት የሚባል እንደሌለ ፤ በ፲፱፻፵፪ ስለቅኝ ሀገሮች ጉዳይ ተከፍቶ በነበረው ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያን መንግሥት በመወከል ተገኝተው ሶማሊያ በተቻለ ፍጥነት ነፃነቷን ማግኘት አለባት በማለት እንደተከራከሩ ፣ የአገር መስፋፋት ጥያቄ ማንሳት የሚቻል ከሆነ ኢትዮጵያ ታሪኳ በሚፈቅድላትና የጂኦግራፊ አቀማመጧ በሚመሰክርላት መሠረት ሶማሊያ ራስዋን ከኢትዮጵያ ግዛት እንደ አንድዋ አድርጋ እንደምትጠይቅ ሆኖም ኢትዮጵያ ከመሬቷ አንድ ጣት እንደ ማትሰጥ ይህንንም ዓይነት ፖሊሲ እንደ ማትከተል አስረድተው በማናቸውም ሀገር ጉዳይ ውስጥ ማንም ጣልቃ እንዳይገባ ፣ ጠቅላላ ወሰን እንዲከበር ፣ አለመግባባቶች በሰላም መንገድ እንዲያልቁ ፣ ለአፍሪካ አንድነት ጥረት እንዲደረግ ኢትዮጵያ አጥብቃ ስለምትጠይቅ የሶማሊያ መንግሥትም በዚህ ዓላማ ተመርቶ እንዲሠራ ያላቸውን ምኞት በመግለጽ ሰፊ መልስ ሰጥተዋል ።

ሰው በሥራው እንደሚታወቅ ሁሉ ክቡርነታቸው ለኢትዮጵያ አንድነት ፣ እድገትና ብልጽግና በትምህርት ላይ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ለአደረጉት አስተዋጽኦ በ፲፱፻፶ ዓ/ም የብላቴን ጌታነት ፣ በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የጸሐፊ ትእዛዝነት ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል ። እንዲሁም ከኢትዮጵያና ከውጭ አገሮች ልዩ ልዩ መንግሥታት ማለትም ፡—

ሀ/ ከኢትዮጵያ መንግሥት ፡— የንግሥት ሳባ ፣ የሥላሴ ፣ የዳግማዊ ምኒልክና የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኮርዶን ኒሻኖች ፤

ለ/ ከ፳፱ ሀገሮች ማለት በጠቅላላው ከ፴ በላይ የሆኑ ልዩ ልዩ የክብር ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ማዳም ኮሌትን በሕግ አግብተው ሲኖሩ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ በተፈጸመባቸው የግፍ ግድያ በተወለዱ በ፷፪ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌፍተናንት ጄኔራል

# አብይ አበበ

# 1908-1967

1- ዐቢይ፡

ሌፍተናንት ጄነራል አብይ አበበ በሰገሌ ጦርነት ቶራ መስክ ላይ በጀግንነት ሲዋጉ ከሞቱት ከሊቀ መኳስ አበበ አጥናፍሰገድና ከወ/ሮ ብርቅ ነሽ በሻህ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፰ ዓ/ም ተወለዱ ።

እናታቸው ወ/ሮ ብርቅነሽ አንድ ልጃቸውን ሳያንቀባርሩ በሥነ ሥርዓት ይዘው በማሳደግ የአማርኛን ትምህርት አለቃ መኰንን ደረሱ ዘንድ እንዲማሩ አደረጉ ። በኋላም ወጣቱ ዘመናዊ ትምህርት እንዲቀስሙ አጎታቸው ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ተፈሪ መኰንን ት/ቤት በአዳሪነት እንዲገቡ አድርገው በትምህርት ቤቱ ይሰጡ ከነበሩት ልዩ ልዩ የቀለም ትምህርቶች በተጨማሪ የፈረንሳይኛ ቋንቋና የዕደ ጥበብ ሙያ ተከታትለዋል ። ከዚህም በላይ የእስካውት ትምህርት ቤት እንደተቋቋመ ለተወሰነ ጊዜ ወደዚያው ተዛውረው ለአስተማሪው አስተርጓሚ በመሆን ጭምር ትምህርቱን ቀስመዋል ።

ወጣት አብይ ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ጊዜ በወቅቱ ሥርዓት መሠረት ቤተ መንግሥት ተራ በመግባት ያገለግሉ ነበር ።

የጀ/ አብይ የተፈጥሮ ምኞትና ፍላጎት የእርሻ ወይም የመካኒክ መሐንዲስ መሆን ነበር ። ዳሩ ግን የጊዜው ሁናቴ በሚያዘው መሠረት ከፍተኛ ደረጃ የደረሱት ተማሪዎች በተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ተመርጠው ፈተና ያለፉት ሁሉ ገነት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ትምህርት ቤት ይገቡ ስለነበር ጄኔራል አብይም ይህ ዕድል ገጥሟቸው ወታደር ሊሆኑ ተገደዱ ።

ጄኔራል አብይ ምክትል የመቶ አለቃ ሆነው ከተመረቁ በኋላ በዚያው ጦር ትምህርት ቤት



ለአሥር ዓመታት የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የነበሩት ክቡር ሌ/ጄ አብይ አበበ በተለያዩ ጊዜያት የሀገር ግዛት ሚኒስትር ፣ የፍርድ ሚኒስትር ፣ የመከላከያ ሚኒስትርና የኤርትራ ጠ/ግዛት እንደራሴ በመሆን ከ፴፫ ዓመት በላይ ሀገራቸውን ያገለገሉ በጎ አመለካከት የነበራቸው ታላቅ ሰው ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

አሰልጣኝ ከነበሩት ስዊድኖች ጋር በአስተማሪነት ተመድበው ሲያገለግሉ የመቶ አለቅነት ማዕረግ አገኙ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጠቅላይ ሠፈር አዛዥ ሻምበል በመሆን አዲስ ለተቋቋመው የራዲዮ መገናኛ ክፍል አሰልጣኝ ከነበሩት የስዊስ ተወላጅ ጋር ሲሰሩ ጠላት ኢትዮጵያን ስለወረረ ወደ ጦር ግንባር ዘመቱ ።

መቶ አለቃ አብይ ከወራሪው ኃይል ጋር ስለአደረጉት የአርበኝነት ተጋድሎ ራስ መስፍን ስለሺ የምስክርነት ቃላቸውን ሲሰጡ "ልጅ አብይ አበበ ከእኔ ጋር ሆኖ ለመንግሥቱ ለሀገሩና ለነፃነቱ በድካሙ ሳይመረር በሙሉ ልብ አገልግሏል ። ወደፊትም ለሀገሩ ታማኝ እንደሆነና ለነፃነቷም እንደሚጥር ያለፈ ሥራው ይመሰክርለታል" በማለት በጽሑፍ አረጋግጠውላቸዋል ።

ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ "ቀሪን ገረመው" በተሰኘው መጽሐፋቸው መቶ አለቃ አብይ አበበ በጦር ሜዳ ስላሳዩት አርአያነት ያለው ጀግንነትና ከጠላት ጋር በሚደረግም ትግል በፈጸሙት ፍትሐዊ ተግባር ሲያስረዱ እንደሚከተለው ጽፈዋል።

"- - - በዚህ የታሪክ ጉዞ ውስጥ ሊዘነጋ የማይገባ አንድ አብይ ነገር አለ ፤ ይኸውም ልጅ አብይ አበበ (ሌ/ጄኔራል) በአድናቆት የሚተረክለት ወጣት ሲሆን ሞረት ከባድ ውጊያ የተደረገ ዕለት ጀግኖች እስቲያደንቁት ድረስ ሲዋጋ ውሎ የማታ ማታ ግዙፍ ሰውነት ካለው ከአንድ ግድንግድ ወታደር ጋር ድንገት ተገናኘ ። ወታደሩ ወደ ወጣቱ በመጣ ጊዜ ወጣቱ በያዘው ጠብመንጃ ደግሞ ሊመታው ሲችል እሱ ባዶ እጁን ሆኖ እኔ በጠብመንጃ አልመታውም በማለት የያዘውን ጠብመንጃ ወደ መሬት ወርውሮ በመጣል ግብግብ ገጥመው በሚታገሉበት ወቅት ተራበተራ አንዱ በላይ አንዱ በሥር ሲገለባበጡ ከዚያ ከጠላት ወታደር ጭንቅላት የሚወርደው ደም የወጣቱን ሰውነት በደም ለውሶና አጨማልቆት ይታይ ነበር ። ያም ወታደር ደመነፍሱን ወደ ቅንጭብ ውስጥ ለመግባት እንደ እባብ በልቡ ሲሳብ - - ኃይሌ አያኖ የተባለ የሻለቃ መስፍን ባልደረባ በሩጫ ደርሶ ጊዜው ማን ያሸንፍ ማንስ ይጥል ይሆን? የሚባልበት ወቅት ባለመሆኑ ሁለቱም ወገኖች አልሸናነፍ ብለው በመታገል ላይ እንዳሉ ያን የጠላት ወታደር በመውዜር ጠብንጃ ነጥሎ በማዳፈን ወጣቱን አርበኛ ገላግሎታል ። ወጣቱ በፈጸመው አስደናቂ ተግባር አርበኞች እየተደነቁ ወደ ሠፈር ወስደው በደም የተበከለ ሰውነቱን በውሃ አነጹለት። "ይህ በመልኩ አወራረድ እጅግ የተዋበ የሰውነት ቅርጽ ያለውና በጣም ያማረ ወጣት አስተዳደጉ በጌትነት ሆኖ - - ያን የመሰለ አሰቃቂና አሳዛኝ ሁኔታ ያለአንዳች ቅሬታ ተቀብሎ በደስታ ከአርበኞች ጋር መከራን የተካፈለ ነው - - አስፈሪና አሰቃቂ በሆነ የጦር አውድማ መካከል ሲዋጋ ከዋለ በኋላ እንደገና ሰውነቱ በደከመበት ሰዓት ከአቅሙ በላይ የሆነ ይህን የመሰለ የጀብዱ ሞያ ሠርቶ ሲገኝ ወገንን ምን ያህል ያኮራና ያስደስት ይሆን ?

"የዚህን ትዝታ ከልባቸው ሳያጠፉ እያደነቁ የሚኖሩ በጦር ሜዳ የነበሩ የዓይን ምስክሮች በብዛት ይገኛሉ ።"

ወጣቱ አብይ አበበ ከ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ጀምሮ በዱር በገደሉ እየተዘዋወሩ በአርበኝነት ሲዋጉ ቆይተው ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፴ ዓ/ም ሱዳን ገቡ ። ከዚያም በእንግሊዝ አገር Bible College of Wales የተባለ ኮሌጅ ገብተው ለጥቂት ጊዜያት ሲማሩ ቆይተው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ።

ጄ/አብይ አበበ ከ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ጀምረው ለሚቀጥሉት ፴፫ ዓመታት ከፍ ባለ ትጋትና የመንፈስ ብርታት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች አገራቸውን አገልግለዋል ።

ከ፲፱፻፴፫—፲፱፻፴፬ የእልፍኝ አስከልካይ

ከ፲፱፻፴፬—፲፱፻፴፭ የወለጋ አገረ ገዥ ፤

ከ፲፱፻፴፭—፲፱፻፴፰ ራስ አበበን በጊዜያዊነት ተክተው የጦር ሚኒስትር ፤

ከ፲፱፻፴፰—፲፱፻፵ የጦር ተጠባባቂ ሚኒስትርና የአንደኛ ዲቪዚዮን የጦር አዛዥ ፤

ከ፲፱፻፵—፲፱፻፵፩ የጦር ምክትል ሚኒስትር ፤

ከ፲፱፻፵፩—፲፱፻፵፬ የጦር ተጠባባቂ ሚስትር

ከ፲፱፻፵፬—፲፱፻፵፯ የጦር ሚኒስትር ፤

ከ፲፱፻፵፯—፲፱፻፶ በፓሪስ አምባሳደር ፤

ከ፲፱፻፶ —፲፱፻፶፪ የፍርድ ሚኒስትር ፤

ከ፲፱፻፶፫—፲፱፻፶፭ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ፤

ከ፲፱፻፶፭—፲፱፻፷፭ በያዙት ሥራ ላይ የአገር ግዛት ሚኒስትር ፤

ከ፲፱፻፷፭—ሰኔ ፳፩ ድረስ የመከላከያ ሚኒስትር



www.ethipianorthodox.org

ጄኔራል አብይ በሕግ የሚያምኑና የሕግ ተገዥ ነበሩ ። ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል ብዙ ጊዜ አሳስበዋል ። የካቲት ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥራ እንዲረከቡ ሲጠየቁ ሕገ መንግሥቱ ተሻሽሎ በምክር ቤቱ ካልተመረጡ በስተቀር ችግር የሚገጥማቸው መሆኑን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በጽሑፍ ገልጸዋል ። ጃንሆይም ሐሳቡን ተቀብለዋል ።

ጄ/ አብይ አበበ የክብር ተከታይ በመሆን ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጋር መላውን ዓለም በመጎብኘት አገራቸውን ከማገልገላቸውም በላይ ብዙ ዕውቀት ገብይተዋል ። የሀገሪቱን ጉዳይ በሚመለከት በመሪዎችም ሆነ በሌላ አህጉራዊ ስብሰባዎች ላይ ተካፍለዋል ። ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ/ም ናይሮቢ ላይ በተሰበሰበው የአፍሪካ የመከላከያ ጉባኤ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ነበሩ ። እንደ አ አ ፲፱፻፶፫ ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋር በመሆን የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በመወከል በንግሥት ኤልሳቤጥ የዘውድ ንግሥ ላይ ተካፍለዋል ። ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የመጡትን አንዳንድ ታላላቅ መሪዎች የክብር ባልደረባ በመሆን አስተናግደዋል ።

ጄ/ አብይ አበበ በቅንነትና በታማኝነት ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ለአበረከቱት የረጅም ዘመን አገልግሎት ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከብዙ የመንግሥታት መሪዎች ልዩ ልዩ የሆኑ ፶ ታላላቅ ኮርዶን ሊሻኖች ተሸልመዋል ።

ጄ/ አብይ ከመንግሥት ሥራ ውጭ በማህበራዊ ኑሮም ከፍተኛ ተሳትፎ ነበራቸው ። በአሥመራ የሮተሪ ክለብ ፕሬዚዳንትና በአዲስ አበባ የበርካታ ድርጅቶችና ማህበሮች ፕሬዚዳንት ሆነው አገልግለዋል ።

ጄ/ አብይ የድርሰት ተሰጥዎም ነበራቸው ። "አውቀን እንታረም" በሚል ርእስ ያሳተሙት መጽሐፍ ትንቢታዊ ባሕርይ ያለው ነበር ። ካልታተሙት ውስጥ "እኔም ነበርኩ" የሚለው ጽሑፍ (ስለጣሊያን ጦርነት) የሚያወሳ ሲሆን አጫጭር የወል ግጥሞችን ያካተተና በሚቀጥሉት ርዕሶች ላይ ያተኮረ መጽሐፍ አዘጋጅተዋል ። "የሀሳብ ዘብዘብ ፣ ለምኞት መገዛት ፣ የሞት ሳቢሳ ፣ ሰው መሆን ፣ ሰውና ኑሮው ፣ አውቀው የሚደልሉኝ ፣ ሥነ ፍጥረት ፣ ተራራ ፣ ትልቅ ወርካ ፣ የትዕግሥት ተስፋ ፣ የሐሳብ ምርምር ፣ የእኔ ስሜት፣እንቁጣጣሽ፣የክረምት ምድጃ ፣ ውሻ ፣ ውዝዋዜ ፣ ይቅርታ ፣ የግል ምኞት ፣ ጥቁር አባይ ፣ የተሰኙ ግጥሞች ከመጻፋቸውም በላይ የራሳቸውን አጭር የሕይወት ታሪክ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ አስፍረዋል ። ከዚህም ሌላ "ተምረህ ሰልጥን" የሚል ባለ ሁለት ገቢር ተውኔት ደርሰዋል ።

ጄ/ አብይ ሌላ የማህበራዊ ገጽታ ነበራቸው ። በትርፍ ጊዜያቸው መጽሐፍ ማንበብን ፣ ፎቶግራፍ ማንሳትንና ማጠብን ፣ አደንን ፣ ዓሣ ማስገርንና ሌሎች የእስፖርት ዓይነቶችን ያዘወትሩ ነበር ።

ጄኔራል አብይ ስለ ሀገር ፍቅር ከአንድ ሰው ሊደረግ የሚገባውንና የሚፈለገውን ያላጓደሉና ችላ ያላሉ ፣ ብዙ ያወቁና የተረዱ ፣ ብዙም የቻሉና ያሳለፉ ትልቅ የትዕግሥት ጌታ ነበሩ ። ጄኔራል አብይ ሁሉንም አክባሪ ፣ ልዩነት የማያደርጉ ለሰው አዛኝና እግዚአብሔርን ፈሪ ነበሩ ።

ጄኔራል አብይ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ለኢትዮጵያ ሕዝብ በብዕራቸው የሚከተለውን ጽፈዋል ።

"በአጭሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምገልጸው እንደሚከተለው ነው ።

፩/ ሕሊናዬ ንጹሕ

፪/ እጆቼ ንጹሕ

ሆነው በአለኝ እውቀትና አቅም አገሬን በንጽሕና አገልግያለሁ ። በመከራውም ጊዜ አገልግያለሁ ። በሰላም ጊዜም አገሬን ሳገለግል በጉቦ አልተደለልኩም ፣ የሰው ንብረት አልቀማሁም ። በሰውም ላይ ግፍ አልሠራሁም ። ይህንንም ስል ክርስቲያን ነኝና ሐሰት ጨምሬበት እንደሆነ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ ። የሆነ ሆኖ ዳር ለማይወጣ ነገር ፣ እንዲህ አድርጎ አገርን ውርደት ላይ ለመጣል ፣ ንጹሕ ደም ለማፍሰስ - - - በከንቱ ሰው እንዲጠፋ ያደረጉትን ሁሉ እግዚአብሔር ፍርዱን ይስጣቸው ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር"

በማለት ጽፈው ፊርማቸውን አኑረዋል ። ሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በገዛ ፈቃዳቸው "ትፈልጉኛላችሁ ?" በማለት ጠይቀው በደርግ ቁጥጥር ሥር ዋሉ ። ከዚህ በኋላ አይተው ወደአልጠገቧቸው ልጆች አልተመለሱም ። ክቡር ጄኔራል አብይ አበበ ባለትዳር ፣ የሁለት ሴቶችና የአራት ወንዶች ልጆች አባት ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ልዑል ራስ

# አሥራተ ካሣ

# 1914-1967

ልዑል ራስ አሥራተ መድኅን ካሣ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፬ ዓ/ም በፍቼ (ሰላሌ) ከተማ ተወለዱ። አባታቸው የሸዋው ፣ የላስታውና የቤጌምድሩ መስፍን ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ዘ ዳርጌ ሲሆኑ እናታቸው ልዕልት ጽጌ ማርያም በሻህ ይባላሉ ።

ልዑልነታቸው በአባታቸው ቤት የአማርኛና የግዕዝ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ትዕዛዝ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ከሐረሩ መስፍን ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ጋር ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ ተደረገ ።

ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ ልዑልነታቸው አባታቸውን ተከትለው ወደ እንግሊዝ አገር ስደት ሄዱ ። እዛም እንደደረሱ "ባዝ" በምትባለው ከተማ ከሚገኘው ሞንክተን ኩምብ ከሚባለው ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርት ቀጠሉ ። በ፲፱፻፴፪ ዓ/ም የእንግሊዝ መንግሥት ኢትዮጵያን ከፋሽስት አገዛዝ ለማላቀቅ በወሰነበት ጊዜ ልዑልነታቸው የጦር ትምህርት እንዲያገኙ ተወስኖ ከካርቱም አጠገብ በሚገኘው "ሶባ" የጦር አካዳሚ ውስጥ የመኰንንነት ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራውን ጦር ተከትለው በድል አድራጊነት ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ።

በዚሁ ዓመት በሙሉ ኰሎኔልነት ማዕረግ የሰላሌ አውራጃ ገዥ ሆኑ ። በ፲፱፻፴፭ ዓ/ም በደጃዝማችነት ማዕረግ በልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰን ኃይለ ሥላሴ የቤጌምድር ገዥ ሥር የሰሜን እንደራሴ ተብለው ተመደቡ ። ልዑልነታቸው ከ፲፱፻፴፯ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፴፱ ወለጋን ከ፲፱፻፴፱ እስከ ፲፱፻፵፭ ዓ/ም አርሲን ፣ ከ፲፱፻፵፭



ልዑል ራስ አሥራተ መድኅን ካሣ የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ፣ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትና የተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች እንደራሴ በመሆን ለ፴፩ ዓመታት አገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

ዓ/ም እስከ ፲፱፻፵፰ ዓ/ም እንደገና ቤጌምድርና ስሜንን ፣ ከ፲፱፻፵፰ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፶ ዓ/ም ሸዋን ፣ በሙሉ በጠቅላይ አገረ ገዥነት አስተዳድረዋል ። ልዑል አባታቸው እንዳረፉ ልዑል ተብለው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኑ ።

በ፲፱፻፵፪ ዓ/ም ወደ መንበረ ማርቆስ የተላከው የኢትዮጵያ መንግሥት መልእክተኞች መሪ በመሆን ላገራችን ቤተ ክህነት ሙሉ ነፃነት ለማጎናጸፍ በተደረገው ጥረት በግብጽ በተደራጀው ስብሰባ ላይ በመገኘት የመጀመሪያውን ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ እንዲሰየም ስምምነት አደረጉ ።

ከ፲፱፻፶፫ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፶፯ ዓ/ም የሕግ መወሰኛ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ወቅት የኢትዮጵያ ፓርላማ በዓለም አቀፍ ፓርላማዎች ድርጅት (IPU) በአባልነት እንዲገባ ከማድረጋቸውም ሌላ ሕገ መንግሥቱ በተግባር እንዲውል ጥረታቸውና እምነታቸው ነበር ። በዚህም ሥራቸው እያሉ የአሜሪካንና የሜክሲኮን ፓርላማዎች ጎብኝተው ከሁለቱ ምክር ቤቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲፈጠር አድርገዋል ።

በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የመንግሥት ግልበጣ ከተደረገ በኋላ የወቅቱንና የሚከተለውንም ሁኔታ በመገምገም ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል ፣ ምክር ቤቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እንዲመርጥ ፣ የሚኒስትሮች ኃላፊነት ለምክር ቤቱ እንዲሆን ፣ ሕዝቡ በየአካባቢው የሚወያይበት ሸንጎ እንዲመሠረት ፣ ምክር ቤቱ መስተዳድሩን እንዲቆጣጠር ፣ ሕዝብና መንግሥት እንዳይራራቁ ፣ አመች ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያቀረቧቸው አስተያየቶችና ሐሳቦች ሕያው ምስክሮች ናቸው ።

በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ልዑልነታቸው በኤርትራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደራሴ ተብለው ተሹመው እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ድረስ ለሰሜኑ ኢትዮጵያ ግልጋሎታቸውን አበርክተዋል ። ኤርትራን በሚያስተዳድሩበት ዘመን በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም የራስነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

የግርማዊነታቸው እንደራሴ ሆነው ወደ ኤርትራ ከተዛወሩ በኋላ በክፍለ ሀገሩ ትምህርትና ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ፣ የሕዝቡ ጤንነት እንዲጠበቅና መንፈሳዊ እምነቱ እንዲበለጽግ ፣ ሐሳብ የመግለጽ መብቱ እንዲጎለብት ፣ በአጭሩ ኤርትራን ለማልማት ለተደረገው ጥረት በግንባር ቀደምትነት ያበረከቱት አስተዋጽኦ ራሱን ችሎ ወደፊት በሚታተም መጽሐፍ ይቀርባል ።

ከኤርትራም እንደተመለሱ የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሆነው ሲያገለግሉ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በአገራችን የተካሄደው ሰላማዊ ለውጥ አረመኔ በሆኑ አንዳንድ የደርግ መኰንኖች እጅ ስለወደቀ ለምርመራ ይፈለጋሉ ተብሎ ልዑልነታቸው በፈቃዳቸው እጃቸውን ቢሰጡም ፣ ጥቂት ወራት ከታሠሩ በኋላ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ፣ አለ አንዳች ፍትሕ ከ፶፱ አብሮ አደግ ጓደኞቻቸውና የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የሞት ጽዋ ተቀብለዋል ።

ልዑልነታቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜ ጀምሮ እስከ አረፉበት ጊዜ ድረስ አገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን ሠላሳ አራት ዓመት ሲያገለግሉ ከታላቁ የሰሎሞን ኒሻን አንስቶ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ መንግሥት ኒሻኖችን ሲሸለሙ ፣ ከአውሮፓውያንና ከአፍሪቃ መንግሥታት ከፍተኛ የክብር ሽልማቶችንም ተቀብለዋል ።

ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም የግርማዊት እቴጌ መነን አስፋወሰን የልጅ ልጅ ልዕልት ዙሪያሽ ወርቅ ገብረ እግዚአብሔርን በተክሊል አግብተው ሠላሳ ዓመት በቆየው ትዳራቸው ሰባት ልጆች አፍርተዋል ።


www.ethipianorthodox.org

# ራስ መስፍን ስለሺ

# 1897 - 1967

ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ በሐረርጌ ክ/ሀገር ወበራ አውራጃ ልዩ ስሙ ላፍቶ በተባለው ቀበሌ ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፰፻፺፪ ዓ/ም ተወለዱ ። አባታቸው ደጃዝማች ስለሺ ወልደሰማያት ፣ እናታቸው ወ/ሮ አስካለ ጋረደው ይባላሉ ።

ክቡር ራስ መስፍን በልጅነታቸው ዘመን በወላጆቻቸው ቤት አስተማሪ ተቀጥሮላቸው የአማርኛን ትምህርት ሲማሩ ቆዩ ። በወጣትነት ዕድሜያቸው በቤልጅግ አሰልጣኞች ይሰጥ የነበረውን ወታደራዊ ትምህርት አጠናቀው በክብር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ ማገልገል ጀመሩ ።

ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ የመንግሥት ሥራ ከጀመሩበት ከ፲፱፻፲፪ ዓ/ም ጀምሮ ሕይወታቸው በደርግ አረመኔ መኰንኖች እስከአለፈበት ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ድረስ ፶፬ ዓመት ሙሉ ለሀገራቸው እድገት ፣ ነፃነትና ክብር የታገሉ ጀግና አርበኛና ታላቅ ሰው ነበሩ ።

ፋሽስት ኢጣሊያ በ፲፰፻፹፰ ዓ/ም በዳግማዊ አፄ ምኒልክ መሪነት አድዋ ላይ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀል በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ኢትዮጵያን ወረረች ። ራስ መስፍን (ያኔ ሻለቃ) የክብር ዘበኛ የአንድ ክፍል የሻለቃ አዛዥ ሆነው ከንጉሠ ነገሥቱ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ማይጨው ዘምተው በተደረገው ታላቅ ጦርነት በሚያኮራ አኳኋን በቆራጥነት ተዋግተዋል ።

የኢጣልያን ፋሽስት ጦር ጊዜያዊ ድል አግኝቶ ወደ መሐል አገር በመግባቱ ራስ መስፍን ባፋጣኝ ጦር አደራጅተው በአዲስ አበባ ዙሪያና በሌሎችም ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች በመዘዋወር ፍልሚያውን ቀጠሉ ። በተለይም ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ከአዲስ አበባ ከተማ በስተ ሰሜን በኩል ዘልቀው በመግባት የጠላትን ጦር መግቢያና መውጫ ካሳጡት ስመጥር የአርበኛ መሪዎች አንዱ ራስ መስፍን አባ ተምትም ናቸው ።



ስመጥር ጀግናው አርበኛ ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ በአርበኝነቱ በሲቪል አስተዳደር ሚኒስትርነት ፣ እና በክፍለ ሀገር እንደራሴነት ሀገራቸውን ለ፶፱ ዓመታት በታማኝነት አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

ጀግናው ራስ መስፍን ስለሺ ከማይጨው ውጊያ አንስተው በልዩ ልዩ ሥፍራዎች እየተዘዋወሩ የጠላትን ጦር በመውጋት አያሌ ድሎች አስመዝግበዋል ። ከእነዚህም በሙሉ ፤ ጉራጌ ፣ ተጉለት ፣ መንዝ ፣ ሞረት ፣ መርሐቤቴ ፣ ይዳኖ ፣ ውልጮ ፣ ኪልቤ ፣ ጂማ ገነት ፣ ሜታ ፣ አጋምሣ ፣ ሙገር ፣ በጎጃም ውስጥ ፋግታ ፣ ወሣሜ በተባሉት ሥፍራዎች ከሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ፤ በኋላም በወለጋና በኢሉባቦር በተደረጉት ታላላቅ ጦርነቶች ከፍተኛ ድሎችን ከማስመዝገባቸውም በላይ ከነበልባሉ ውጊያ ውስጥ ገብተው ከፋሺስት ወታደሮች ጋር ሲታገሉ በተደጋጋሚ በጽኑ ቆስለዋል ።

ግንደበረት ካቺሴ ላይ በድፍረት ተጋፍጠው ሲዋጉ ከጠላት በተተኮሰ ጥይት የቀኝ አይናቸውን ቆስለዋል ። ይሁን እንጂ በጦርነቱ ውስጥ የሞቱ መስለው በማድፈጥ ያቆሰላቸውን ጠላት ተኩሰው ገድለውታል ። እንዲሁም በሌሎች በተለያዩ ሥፍራዎች በተደረጉ ውጊያዎች በእግራቸው ፣ በሽንጣቸውና በሌላውም የአካላቸው ክፍል ጽኑ የመቁሰል አደጋ ቢደርስባቸውም ከሞት ተርፈው የጠላት ጦር ፈጽሞ ከኢትዮጵያ እስከለቀቀበት ጊዜ ድረስ በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ በመዘዋወር በታላቅ ጀግንነት ተዋግተዋል ።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደ አገራቸው ሲመለሱ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ/ም የፊታውራሪነት ማዕረግ ተሰጥተው አርጆንና አካባቢውን እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ ። ጠላት የመጨረሻ ምሽጉ አድርጎ የነበረው ይህንን አካባቢ በመሆኑ እጅግ ከባድና እልህ አስጨራሽ የሆኑ ውጊያዎች አካሂደው ቁጥር ሥፍር የሌለው የጠላት ሠራዊትና መሣሪያ በመማረክ በአገር ውስጥ የቀረውን የመጨረሻ የጠላት ጦር እንዲደመሰስ ካደረጉት ጀግኖች አርበኞች ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ ግምባር ቀደም ነበሩ ።

ከ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ጀምሮ በሻምበልነትና በሻለቃነት ማዕረግ ሲዋጉና ሲያዋጉ ከቆዩ በኋላ ከ፲፱፻፴፬—፲፱፻፵፯ ደጃዝማች ተብለው የኢሉባቦርና የከፋ ጠቅላይ ግዛቶች ገዥ ሆነው ተሾሙ ። ከ፲፱፻፵፯—፲፱፻፶ የአገር ግዛት ሚኒስትር ሆነው እያገለገሉ ሳለ በእንግሊዝ ንግሥት ኤልሳቤጥ ሎርድ ቻምበርሊን ተብለው ተሰየሙ ። ከ፲፱፻፶—፲፱፻፷፯ ዓ/ም ራስ ተብለው የሸዋ ጠ/ግዛት እንደራሴና የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆነው አገልግለዋል ። በተጨማሪም የብርጌድየር ፣ የሜጀርና የሌተና ጄኔራልነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ በአገልግሎት ዘመናቸው ነገርን የመቁረጥ ተሰጥዎ የነበራቸው የፍትሕ ሰውናቸው። ፍርድ ለከሳሽና ለተከሳሽ እኩል እንደማያስደስት የተገነዘቡ ፤ ጉዳያቸውን በይደር ማንቀትና ነገርን በነገር ተርጉሞ በኮሚቴ እንዲታይ ማድረግ ውሳኔን ማቆየት ብቻ ሳይሆን ባለጉዳዮችን ማጉላላት በመሆኑ አድራጎቱን አጥብቀው ይቃወሙ ነበር ። የበታቾቻቸውንም ለቀልጣፋ ሥራ ፤ የሚያበረታቱና ለመልካም ውጤት የሚሾሙ የሚሸልሙ አለቃ ነበሩ ።

ገጠሬው ሕዝብ ከወረዳና ከአውራጃ ወደ ከተማ በቀላሉ መጥቶ ጉዳዩን እንዲፈጽም መጋቢ መንገድ ፣ በአካባቢውም ትምህርትና ጤና እንዲያገኝ ት/ቤቶችንና ጤና ጣቢያዎች ለማሠራት ከፍተኛ ዕቅድ ነበራቸው ። በእርሳቸው አነሳሽነትና አበረታችነት ሕዝቡ በበጎ ፈቃድ ገንዘብ አዋጥቶ ካሠራቸውና የአውራ ጎዳና ባለሥልጣን እንዲረከብ ከተደረጉት የጥርጊያና የጠጠር መንገዶች መካከል ከወልቂጤ ሆሣዕና ፣ ከሞጆ ኢጄሬና ከሰንቦ አረርቴ የተሠሩት የገጠር መጋቢ መንገዶች ከምኞታቸው ጥቂቶቹ ናቸው ።

ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ በማህበራዊ ኑሮአቸውም የተቸገረን ፣ የተራበንና የታረዘን የሚረዱ ቸርና ርኅሩኅ ሰው እንደነበሩ አብሮአቸው ከሠሩትና ከቅርብ ወዳጆቻቸው ይነገርላቸዋል ።

ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ በአርበኝነትና በሲቪል አስተዳደር ፶፬ ዓመት ሙሉ ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ላበረከቱት ከፍተኛ አገልግሎት ከአገር ውስጥና ከውጭ መንግሥታት አያሌ የጀብዱ ሜዳዮችና የክብር ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

ሀ/ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ፤

፩/ የአርበኝነት ሜዳይ ፣ ባለ አራት ዘምባባ
፪/ የስደተኝነት ባለ አንድ ዘምባባ
፫/ የጀብዱ የቅ/ጊዮርጊስ ሜዳይ ባለ ሁለት ዘምባባ
፬/ የቀ ኃ ሥ ሜዳይ ባለ ሁለት ዘምባባ
፭/ የቀ ኃ ሥ የድል ኮከብ ሜዳይ
፮/ የብሔራዊ አገልግሎት የወርቅ ሜዳይ
፯/ ባለአምበል የወርቅ ሜዳይ
፰/ የአሜድላ ኢዮቤልዩ መታሰቢያ ሜዳይ
፱/ የንግሥ በዓል መታሰቢያ ሜዳይ
፲/ የኢትዮጵያ የክብር ኮኮብ ኮርዶን ኒሻን ከነአምበሉ
፲፩/ የዳግማዊ ምኒልክ ኮኮብ ኮርዶን ኒሻን ከነአምበሉ
፲፪/ የሥላሴ ኮኮብ ኮርዶን ኒሻን ከነአምበሉ

ለ/ ከልዩ ልዩ ወዳጅ አገሮች መንግሥታት በጠቅላላው ፴፩ ልዩ ልዩ የክብር ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

ጀግናው ራስ መስፍን ስለሺ ለቆሰሉለትና ለተጋደሉለት ሀገር በወታደራዊ ደርግ የተከፈላቸው ወሮታ ጭካኔ የተሞላበት ሞት ነው ።

ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ ከቀድሞ ባለቤታቸው ከክብርት ወ/ሮ በዛብሽ አበበ ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ አፍርተዋል ። ከዚያም በኋላ ሕይወታቸው እስከአለፈ ጊዜ ድረስ አብረዋቸው ከኖሩ ባለቤታቸው ከክብርት ወ/ሮ የሺመቤት ጉማ አምስት ወንዶችና አራት ሴቶች ልጆች ያፈሩ ሲሆን በድምሩ የአሥራ ሁለት ልጆች አባት ነበሩ ።


www.ethipianorthodox.org

# ልጅ

# እንዳልካቸው መኰንን

## 1920-1967



ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኰንን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ፡ በሚኒስትርነት ፡ በተባበሩት መንግሥታት ቋሚ መልእክተኛነትና በአምባሳደርነት ሀገራቸውን ለ፴፫ ዓመታት ያገለገሉ ታዋቂ ዲፕሎማት ነበሩ ።

ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኰንን ከራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸውና ከወ/ሮ ዘውዲቱ መንገሻ ጳጉሜ ፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ/ም በአዲስ አበባ በየካ አውራጃ በመካከለኛ ወረዳ አቧሬ ተወለዱ ።

አባታቸው ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ጠላት አገራችንን ሲወር ወደ ውጭ ሀገር ከሄዱበት ጊዜ ጀምሮ ልጅ እንዳልካቸው አምስቱን የመከራ ዘመን ያሳለፉት በሰላሌ አውራጃ ልዩ ስሙ በቾ ጉራንዳ በተባለ ቦታ ከአያታቸው ከወ/ሮ አቦነሽ ተክለማርያም ጋር ነበር ። ወላጅ አባታቸው ጠላትን ድል መቶ ከሐገራችን ካስወጣው ሠራዊት ጋር እንደተመለሱ ልጅ እንዳልካቸው ከአያታቸው ጋር አዲስ አበባ ገቡ ።

ልጅ እንዳልካቸው የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሀገራቸው ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው መጀመሪያ በኤክስተር ኰሌጅ ቀጥሎም በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ሲማሩ ቆይተው በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም በፖለቲካ ኢኮኖሚ በኤምኤ ዲግሪ ከማዕረግ ጋር ተመረቁ ።

በ፲፱፻፵፬ ዓ/ም ወደ አገራቸው ተመልሰው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በአታሼነት የመንግሥት ሥራ ጀመሩ ። በዚሁ መሥሪያ ቤት የፕሮቶኮል ሹም ፣ የፖለቲካ ጉዳይ ዋና ዲሬክተርና ምክትል ሚኒስትር ሆነው ሠርተዋል ። ከዚያም በቅደም ተከተል በሕዝባዊ ኑሮ እድገትና በትምህርት ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የገዢዎች ቦርድ ሊቀ መንበር ፣ በእንግሊዝ ሀገር አምባሳደር ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ፣ በካቢኔ ሚኒስትርነት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሀገራቸው ቋሚ መልእክተኛ ፣ የፖስታ የመገናኛና የቴሌኮሙኒኬሽን ሚኒስትር በመጨረሻም በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ከየካቲት ፳፩ ቀን ጀምሮ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ለ፴፫ ዓመታት አገራቸውን በታማኝነትና በቅንነት አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# አቶ አበበ ረታ

## 1901-1967

ክቡር አቶ አበበ ረታ መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፩ ዓ/ም በትግራይ ክፍለ ሀገር በእንደርታ አውራጃ ፣ በሕገበሌ ወረዳ ፣ ልዩ ስሙ ሐርቆ በተባለ ሥፍራ ተወለዱ ። አባታቸው ሹም ባሕሪ ካህሣይ ፣ እናታቸው ወ/ሮ አዜብ ወ/ጊዮርጊስ ይባላሉ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በተወለዱ በት ሥፍራ ከፊደል እስከ ዳዊት ፣ በአባ ሐደራ ገዳም ምዕራፍ ፣ ጾመ ድጓና ጽጌ ፣ በሰቆጣ (የዋግ ሥዩማን ከተማ) ዝማሬንና መዋእለት ፣ የአቋቋም ይትበሃል ፣ ቅኔ ፣ ባጠቃላይ በጥንታዊውና ባህላዊ ሥርዓተ ትምህርት ጽዋትወ ዜማንና ትርጓሜ መጻሕፍትን ተምረዋል ።

ክቡር አቶ አበበ ረታ በ፲፱፻፳፫ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በስዊድን ሚሲዮን ት/ቤት ይሰጥ የነበረውን የእንግሊዝኛ ቋንቋና ሌላውንም ዘመ ናዊ ትምህርት በሚገባ ፈጽመው ለከፍተኛ ትምህርት ወደ እንግሊዝ ሀገር በመሄድ በቴዎሎጂ (ነገረ መለኮት) በከፍተኛ ማዕረግ ፣ እንዲሁም በብሪስቶል ዩኒቨርስቲ በፊሎሶፊና በኤኮኖሚክስ ጥናት በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቀዋል ።

ክቡርነታቸው ሥራን አሐዱ ብለው የጀመ ሩት ገና በትምህርት ላይ እያሉ በአሥራ ዘጠኝ ዓመታቸው ከክቡር ዋግ ሥዩም ከበደ ዘንድ ፀሐፊ በመሆን ነበር ።

ከፍተኛ ትምህርታቸውን በእንግሊዝ ሀገር በሚከታተሉበት ጊዜ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮ ጵያን ወረረች ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በስደት ላይ ሆነው ስለኢትዮጵያ ነፃነት በሚከራከሩበት ጊዜ ክቡርነታቸው የቅርብ ረዳት ሆነው ሲያገለ ግሉ ቆይተዋል ።

ክቡር አቶ አበበ ረታ በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በአገር ግዛት ሚኒስቴር የሕዝብ ጤና ጥበቃ ም/ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል ።

ክቡርነታቸው ጤና ጥበቃ ራሱን የቻለ አንድ የሚኒስቴር መ/ቤት ሆኖ ባገሪቱ ውስጥ ተግባሩን ማከናወን እንዳለበት ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ተነጥሎ እንዲቋቋም ተደረገ ።

በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም በለንደን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን አምባ ሳደርና መልእክተኛ ሆነው በመሾም በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። በ፲፱፻፵፫ ፓሪስ በተደረገው የተባበሩት መንግሥ ታት ጉባኤ የኢትዮጵያ መልእክተኞች መሪ በመ ሆን ተካፍለዋል ።

ከ፲፱፻፵፳—፲፱፻፷፭ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፣ በሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በእ ርሻ ሚኒስቴር ሚኒስትር እንዲሁም ከ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ጀምሮ የዘውድ አማካሪ በመሆን ለአገራቸው ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል ።

ክቡር አቶ አበበ ረታ ከመደበኛ ሥራቸው ውጭ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ፣ ጥንታዊና ባሕላዊ ቅርሶችን ለዘመኑ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲ ቻል በተደረገው ጥረት ሁሉ የጉባዔ ሊቀ መንበር በመሆን ያካበቱትን እውቀት በተግባር እንዲ ተረጎም አድርገዋል ።



ክቡር አቶ አበበ ረታ በሚኒስትርነትና በዘውድ አማካሪ ነት ፣ እንዲሁም በታሪክና በሃይማኖት ተመራማሪነት ሀገራቸውንና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በቅንነትና በታታሪነት ለ፵፯ ዓመታት ያገለገሉ ከፍተኛ የምርምርና የቋንቋ ሰው ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌ/ኰሎኔል ታምራት ይገዙ

## 1908-1967

ክቡር ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ጥር ፫ ቀን ፲፱፻፰ ዓ/ም ተወለዱ ። ወላጅ አባታቸው ባላም ባራስ ታፈሰ አደፍርስ ፣ እናታቸው ወ/ሮ ዘውዲቱ ይገዙ ይባላሉ ። በተጉለትና በቡልጋ አውራጃ ልዩ ስሙ አምቢስ በተባለ ቦታ የተወለዱት ክቡር ሌ/ኮሎኔል ታምራት የሕፃንነታቸውን ዘመን በወላጆቻቸው ቤት የሀገራችንን ትምህርት ሲከታተሉ አሳለፉ ። አያታቸው ክቡር ደጃዝማች ይገዙ በሀብቴ ወደ አዲስ አበባ አስመጥተዋቸው ታምራት ይገዙ በሚል ስያሜ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዘመናዊ ትምህርት እንዲከታተሉ አደረጉ ።

በዚሁ ትምህርት ቤት እንዳሉ የሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ሲቆረቆር በየትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ለዕጩ መኰንንነት ሲመለመሉ ፣ ክቡር ሌ/ኮሎኔል ታምራትም የተሰጠውን የመግቢያ ፈተና በማለፍ ጦር ትምህርት ቤቱ ገብተው ፣ በወቅቱ ይሰጥ የነበረውን የእጩ መኰንንነት ትምህርት አጠናቀው ዲፕሎም በማግኘት በመቶ አለቃነት ማዕረግ ተመረቁ ። ከዚያም በጦር ትምህርት ቤቱ በአሰልጣኝነት ተመድበው ሲሰሩ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም የሻምበልነት ማዕረግ ካገኙት ቀደምት መኰንኖች ሌ/ኮ ታምራት ይገዙ አንዱ ነበሩ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ወርራ የማይጨው ጦርነት እንደተፈታ አዲስ አበባን ለመያዝ የሚገሰግሰውን የጠላት ጦር ጣርማ በር ላይ አግዶ ለማቆም ከዘመተው ከገነት ጦር ባልደረቦች አንዱ ኮ/ታምራት ይገዙ ነበሩ ። የጠላት ጦር አይሎ አዲስ አበባን ለመያዝ ሲቃረብ ፣ በተለይምጠ ላት የገነት ጦር መኰንኖችን ለማደን ቆርጦ በመነሳቱ ፣ ሻምበል ታምራት



ክቡር ሌ/ኰ ታምራት ይገዙ በጠቅላይ ግዛት እንደራሴነት ፣ በም/ሚኒስትርነትና በዘውድ ም/ቤት አማካሪነት አገራቸውን ለ፴፰ ዓመታት በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

ይገዙ ውድ ሀገራቸውን ትተው ከአያታቸው ከክቡር ደጃዝማች ይገዙ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም መሰደድ ግድ ሆነባቸው ።

በስደት ላይ ሆነው በእሥራኤል የእንግሊዞች ኮሌጅ ገብተው ዘመናዊ ትምህርት በመማር ላይ እንዳሉ በስደት ላይ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ባቋቋሙት "ተስፋ ኮከብ ማኅበር" ዋና ፀሐፊ ነበሩ ። በወቅቱም ስደተኞችን መልምለው ወታደራዊ ትምህርት በመስጠት ጥራት ያለው አነስተኛ ጦር አዘጋጅተው ነበር ።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእንግሊዞች እርዳታ ኢጣሊያንን ከኢትዮጵያ ለማባረር ሱዳን መግባታቸው ሲሰማ ሻምበል ታምራት ይገዙ ኢየሩሳሌም ያሰለጠኑትን አነስተኛ ጦር ይዘው ወደ ሱዳን በመጓዝ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተቀላቀሉ ።

ሻምበል ታምራት ይገዙ በሱዳን የቀድሞ የገነት ጦር ትምህርት ቤት መኰንኖች ከነበሩት ጓደኞቻቸው ጋር እንግሊዞች ባቋቋሙት "ሶባ" በተባለ ጦር ትምህርት ቤት ከፍተኛ የጦር ሥልትና የውትድርና ትምህርት ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በጠቅላይ ጦር አዛዥነት ከሚመሩት ጦር ጋር ተሰልፈው ጎጃም ገቡ ።

ጎጃም ላይ ከሌሎች አርበኞች ጋር ተቀላቅለው በመዋጋት በመጀመሪያ አሜድላ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እንዲውለበለብ ተደረገ፤ ወደፊት በመግፋትና ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በአሸናፊነት አዲስ አበባ ገቡ ።

የጣሊያን ጦር ተባርሮ ኢትዮጵያ ነፃ ከወጣች በኋላ ሻምበል ታምራት በተለያዩ ሥፍራዎችና ማዕረግ ከፍ ያለ ኃላፊነት በሚጠይቅ ሥራ ላይ እየተመደቡ ሀገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

— በሻምበልነት ማዕረግ የጦር ሚኒስቴር ዋና ፀሐፊ ፤
— በሻለቅነት ፤ ኋላም በሌ/ኮሎኔልነት ማዕረግ የፖሊስ ሠራዊት ስታፍ ኦፊሰር ፤
— የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ዋና ዲሬክተር
— የፍርድ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተርና ኋላም ም/ሚኒስትር ፤
— የፖስታ ቴ. ቴ. ምክትል ሚኒስትር ፤
— የከፋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ፤
— የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴርና የፍርድ ሚኒስቴር ተጠባባቂ ሚኒስትር ፤
— የሐረር ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ
— የሰሜንና በጌምድር ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ
— በመጨረሻም የዘውድ ምክር ቤት አባል ነበሩ ።

ክቡር ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ከመደበኛ ሥራቸው ውጭ የወወክማና የኢትዮጵያ ፉትቦል ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በመሆን ለአያሌ ዓመታት አኩሪ አገልግሎት አበርክተዋል ።

ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ለብዙ ዘመናት ላበረከቱት አገልግሎት ከአነስተኛ ሜዳሊያ ጀምሮ እስከ ታላቁ የምኒልክ ኮርዶን ሊሻን ተሸልመዋል ።

በትርፍ ጊዜያቸው ክቡርነታቸው መጽሐፍ ማንበብን የሚወዱ ሰው ነበሩ ። የስደት ዘመናቸውን የምታወሳ "የስደት ኑሮ ታሪክና ትዝታ" በሚል ስያሜ የተለያዩ ግጥሞችን ያካተተች ምክር አዘል መጽሐፍ አሳትመዋል ።

ክቡር ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ በግፈኛው ወታደራዊ ደርግ በቁጥጥር ሥር ከቆዩ በኋላ ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር ካለ ፍርድ ተገድለዋል ።

ክቡር ሌ/ኮሎኔል ታምራት በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም ከክብርት ወ/ሮ ማርታ እምሩ ጋር በሕግ ተጋብተው የስምንት ወንዶችና የሁለት ሴቶች ልጆች አባት ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ

## 1899-1967



ከፍተኛ ባለ ሥልጣንና የሥራ ኃላፊነት ላይ ተመድበው ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን ፴ ዓመት ሙሉ ያገለገሉት ክቡር ደጃ/ክፍሌ እርገቱ ከ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ጀምሮ በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ባለ ሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ነበሩ ።

ክቡር ደጃ/ክፍሌ እርገቱ ጥር ፲፩ ቀን ፲፰፻፺፱ ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ ። አባታቸው አቶ እርገቱ ተክለአረጋይ በተጉለትና ቡልጋ የአ ማግርት ተወላጅ ሲሆኑ እናታቸው ወ/ሮ ወለተ ሚካኤል ቸሬ (አሁን እማሆይ) በመንዝና ይፋት የቀወት ባሻ ተወላጅ ነበሩ ።

ደጃ/ክፍሌ ከ፲፱፻፫ እስከ ፲፱፻፯ ዓ/ም በእናት አባታቸው ቤት የአማርኛ ትምህርት ከተማሩ በኋላ ከ፲፱፻፯ እስከ ፲፱፻፲፯ ዓ/ም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው በአሊያንስ ፍራንሴስ ት/ቤት የፈረንሣይኛ ትምህርት ተከታትለዋል ።

በ፲፱፻፲፯ ዓ/ም ወደ ውጭ አገር ከተላኩት ተማሪዎች አንዱ ሆነው በምድረ ግብፅ አሌክሳን ድርያ ሚሲዮን ሌይክ ፍራንሲዝ በተባለው ት/ቤት እስከ ፲፱፻፳ ዓ/ም ድረስ ሲማሩ ቆይተው የጠቅላላ ትምህርት ባካሎሪያ የተባለውን/ዲፕሎም ተቀ ብለዋል ።

ከላይ በተጠቀሰው ት/ቤት እንደገና እስከ ፲፱፻፳፪ ዓ/ም ድረስ ትምህርታቸውን ቀጥለው በሳይንስና ማቲማቲክስ ሁለተኛውን ባካሎሪያ ከአገኙ በኋላ ፣ በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ፈረንሣይ አገር ፓሪስ ሄደው ኮሌጅ ሳንት ባርብ የተባለው ት/ቤት ጦር አካዳሚ ለመግባት የሚያስችለውን የመሰ ናዶ ትምህርት ሲማሩ ቆዩ ።

ከ፲፱፻፳፬ እስከ ፲፱፻፳፮ ሐምሌ ወር ድረስ ፈረንሣይ አገር በሚገኘው ኤኮል ስፔሲያል ሚሊ ተሪ ደሰንሴር ከተባለው ጦር ት/ቤት ተመርቀውና በፈረንሣይ ጦር ሠራዊት ውስጥ የም/የመቶ አለቃ ማዕረግ የሚያሰጠውን ዲፕሎም ተቀብለው ነሐሴ ፲፱፻፳፮ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ።



www.ethipianorthodox.org

በውጭ አገር በትምህርት ላይ ሳሉ በስፖርተ ኛነት ፣ በእግር ኳስ ፣ በጦር ውርወራ ፣ በሩጫ ፣ በዋና ፣ በፈረስ ግልቢያ ፣ የወርቅ ፣ የብርና የነሐስ ሜዳይ ሽልማቶች አግኝተዋል ።

ክቡር ደጃ/ክፍሌ እርገቱ በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም የሻለቅነት ማዕረግ አግኝተው የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ሠራዊት የመድፈኛ ክፍል አዛዥ ፤ እንዲሁም በሕዳር ወር ፲፱፻፳፯ ዓ/ም በሙሉ ኮሎኔልነት ማዕረግ የክብር ዘበኛ ም/አዛዥ ሆነው ተሾሙ ።

በ፲፱፻፳፰ በክብር ዘበኛ ም/አዛዥነት በሰ ሜናዊ ጦር ግንባር ማይጨው ዘምተው ከፍ ባለ ጀግንነት ግዳጃቸውን የፈጸሙ ሲሆን በአምስቱ የጠላት ወረራ ዘመን በውስጥ አርበኝነት አገል ግለዋል ።

ከግንቦት ፲፱፻፴፫ ዓ/ም እስከ ሐምሌ ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ድረስ የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ አዛዥ በመሆን ሠራዊቱን እንደገና ማቋቋም ጀመሩ ። በዚህም ወቅት የወታደር ልዩ ልዩ ደንቦችና ሥርዓቶችን በአማርኛ አዘጋጅተዋል ።

ከሐምሌ ፲፱፻፴፫ ጀምሮ በከፋ ጠ/ግዛት ፣ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ፣ እንዲሁም በጦር ሚኒ ስቴር ሹም ሆነው ሠርተዋል ።

ከሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ/ም እስከ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፵፯ የሕዝብ ጸጥታ ጥበቃ ምክትል ሚኒስትርና የአገር ግዛት ሚኒስቴር ተጠባባቂ ሚኒስትር ነበሩ ።

ከግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ/ም እስከ ኅዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ/ም የሐረር ጠላቅይ ግዛት እንደ ራሴ ሆኑ ። ከኅዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ/ም እስከ ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ/ም በአገር ግዛት ሚኒስ ቴር የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሚኒስትር ዴ. ኤታ ሆነው አገልግለዋል ።

ከሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፶፰ እስከ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በሚኒስትርነት ማዕረግ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ዋና ሹም ነበሩ ።

ከኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም እስከ የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም የአገር ግዛት ሚኒስትር ፣ ከየካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በውጭ አገር የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደ ርና ልዩ መልእክተኛ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተ ዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ በጂቡቲና በሱማሌ በኩል ያለውን የወሰን ክልል ሥራ በኢት ዮጵያ መንግሥት ተወክለው ከፈረንሳዮች ጋር ከዳር እስከ ዳር ወሰኑን ተካልለዋል ። እንዲሁም በኬንያ በኩል ያለውን የወሰን ክልል ሥራ ከኬንያ መን ግሥት ጋር ተካልለዋል ። ከዚህ ሌላ የወወከማ ምክትል ፕሬዚዳንት ፣ የዓለም ስደተኞች መርጃ ኮሚቴ ም/ፕሬዚዳንትና የኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፈ ዴሬሽን ም/ ፕሬዚዳንት ፣ የኢትዮጵያ ሬስንግ ክለብ ም/ፕሬዚዳንትና የከሣቴ ብርሃን ማኅበር ሊቀ መንበር በመሆን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበ ርክተዋል ።

ክቡር ደጃ/ክፍሌ እርገቱ መጽሐፍ በማን በብ ፣ በፈረስ ግልቢያና በውሃ ዋና ትርፍ ጊዜያ ቸውን ማሳለፍ ይወዱ ነበር ።

ክቡር ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ ለረጅም ዘመን ቅን አገልግሎታቸው ልዩ ልዩ ሽልማቶች አግኝተዋል ። ከእነዚህም መካከል ፦ የኢትዮ ጵያ የድል ሜዳይ ፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሻን የመኰንን ደረጃ ፣ የውስጥ አርበኝነት ሜዳይ ባለ ፪ ዘንባባ ፣ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የጦር ሜዳይ (የጀብዱ) ባለ ፩ ዘንባባ ፣ የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን የመኰንን ደረጃ ፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሻን የታላቅ መኰንን ደረጃ ፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኮርዶን ኒሻን ፣ የንግሥት ሳባ ታላቅ ኮርዶን ኒሻን ይጉኙበታል ።

ከውጭ አገር መንግሥታትም በተለይ ከስዊ ድን ፣ ከፈረንሣይ ፣ ከፈረንሣይ ሳንት ባርብ ኮሌጅ ፣ ከኔዘርላንድ ፣ ከሱዳን (ሁለት ጊዜ) ፣ ከላይቤሪያ ፣ ከዩጎዝላቪያ ፣ ከፖላንይ ፣ ከጀርመን ፣ ከቡል ጋሪያ ፣ ከሩማንያ መንግሥትና ከሩማንያ ፓትርያ ርክ ፤ እንዲሁም ከቫቲካን መንግሥት የክብር ኒሻን ተቀብለዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ በወታደራ ዊው ደርግ በቁጥጥር ሥር ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ፷፯ ዓመታቸው ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ከሌሎች ባለሥልጣኖች ጋር ተገድለዋል ።

ክቡር ደጃ/ክፍሌ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም ወ/ሮ ጽጌ ድንግል ደስታን በሕግ አግብተው ምንዳዩ ክፍሌና ተሾመ ክፍሌ የተባሉትን ልጆች አፍርተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌ/ጄኔራል አሰፋ አየነ

# 1910-1967

ክቡር ሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ ከፊታውራሪ በየነ ጐሹና ከወይዘሮ የእልፍኝ አብተው ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፲ ዓ/ም ባሌ ጎባ ተወለዱ ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት ከተማሩ በኋላ ከ፲፱፻፳፯ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ/ም በቀ ኃ. ሥ. ገነት ጦር ትምህርት ቤት በወታደራዊ ሞያ ሰልጥነው በም/መቶ አለቃ ማዕረግ ተመረቁ ። ከዚያም በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም በሻምበልነት ማዕረግ የከባድ መሣሪያ አዛዥ ሆነው ተሾሙ ።

ከማይጨው ጦርነት በኋላ የፋሺስት ጦር ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ጣርማ በር ላይ ተመድ በው ጦራቸውን በጀግንነት በማዋጋት ግዳጃ ቸውን ተወጥተዋል ። የኢትዮጵያ ጦር ሲፈታ ክቡር ሌ/ጄኔራል አሰፋ አየነ ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ጎንደር ሄደው እዚያው ሳሉ ጠላት የኢትዮጵያ የጦር መኰንን መሆናቸውን ደርሶ በት በጎንደር ከተማ ለአንድ ዓመት ተኩል አሰ ራቸው ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ኢትዮጵያ ከጠላት ነፃ ስት ወጣ ሻምበል አሰፋ አየነ በፖሊስነት እንዲያገለ ግሉ ተመደቡ ። ከዚያም ወደ ጦር ሚኒስቴር በአስተዳደር መኰንንነት ተዛውረው የሚኒስቴሩ መ/ቤት ዘመናዊ መዋቅርና ይዘት እንዲኖረው ከአደረጉት መኰንኖች አንዱ ነበሩ ።



በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም በሻለቅነት ማዕረግ የኢትዮጵያ የአየር ኃይል አገናኝ መኰንን ሆነው ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ አየር ኃይሉን ታዋቂና አኩሪ ደረጃ እንዲደርስ የገነቡትና የመሩት ክቡር ሌ/ጄኔራል አሰፋ አየነ በመከላከያ ሚኒስ ቴር የጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹምና በመጨረሻም የት ራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በመሆን በጠቅላላው ለ፴፰ ዓመታት ሀገራቸውን ያገለገሉ አስተዋይ መኰ ንን ነበሩ ።

ሌ/ጄ አሰፋ በአገር ግዛት ሚኒስቴር የሕዝብ ፀጥታ ዲሬክተር ሆነው ባገለገሉበት ወቅት በጊ ዜው የፈረንሣይ ሱማሌ ይባል ከነበረው ከዛሬው ጂቡቲ ጋር የኢትዮጵያን ድንበር በመካለል ከፍ ተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ክቡር ሌ/ጄ አሰፋ አየነ በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም በሻ ለቅነት ማዕረግ የአየር ኃይል አገናኝ መኰንን ሆነው ተሾሙ ። በመደበኛ ሥራቸው ላይ ደር በው የአየር ኃይል ሁለተኛ ኮርስ እጩ መኰንኖች ጋር የበረራ ትምህርት ተምረው የበራሪነት ክንፍ ተቀብለዋል ። በተጨማሪ በዘመኑ ከነበሩት የአየር ኃይል አውሮፕላኖች ከተዋጊ እስከ መጓጓዣ አይ ሮፕላኖች በማብረር አገልግሎት ሰጥተዋል ።

ከ፲፱፻፵፱ እስከ ፲፱፻፶፱ የአየር ኃይሉ የትም ህርት መስጫ ተቋም እንዲስፋፋ ፣ የኢትዮጵያ ውያን የሰለጠነ የሰው ኃይልና መሠረታዊ መዋ ቅሩ (ኢንፍራስትራክቸር) በያመቱ እድገት እንዲ ያሳይ ባደረጉት ጥረት ኢትዮጵያውያን ከውጭ አሰልጣኞች ላይ ኃላፊነትን በሙሉ ለመቀበል ከመቻላቸውም በላይ የአየር ኃይሉን ድርጅታዊ ብቃት መሠረት ለመጣል ተችሏል ።

ከ፲፱፻፶፱—፲፱፻፶፰ ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ አየር ኃይሉን ዘመናዊ ለማድረግ ያካሄዱት ትግል ከፍተኛ ነበር ። በተለይም የውጭ አሰልጣኞች አየር ኃይሉ ፈጣን እድገት ሊያደርግና የጦር አው ሮፕላኖችም ሊደራጅ የሚችለው በውጭ ኃይል ሞግዚትነት ነው'' - - - በማለት መንግሥትን ሲያስፈራሩበት ለነበረው ግትር አመለካከት ክቡር ሌፍተናንት አሰፋ አየነ የሰጡት መልስ ''ባዕድ የሚያጠፋው ጥፋት እንደጎዳን ይቀ ራል ። ራሳችን በቅን ልቦና የምናጠፋው ግን የምንማርበት ስለሚሆን ለኛ የዘለቄታ ጥቅም አለው'' የሚል ስለነበረ ይህ አርቆ አስተ ዋይነታቸው በተግባር ሊተረጎም ችሏል ። ከዚህም በላይ ከሁለተኛው የዓለም ጦር



www.ethipianorthodox.org

ነት በኋላ ኢትዮጵያና አሜሪካ የተፈራረሙትን የጋራ መከላከያ ውል መሠረት በማድረግ አየር ኃይሉ በተራድኦ ፕሮግራም በዘመናዊ ጄት ተዋጊ አውሮፕላኖች እንዲታጠቅ በተደረገው ጥረት የሌ/ጄ አሰፋ አየነ ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነበር ።

ጄ/ አሰፋ ለአየር ኃይሉ የመሠረቱለት ሌላው የዘመናዊነት ባህርይ የአሠራር ስልት ወይም ሲስተም (Sistem) ነበር ። ሥራን በኃላፊነት የመወጣት ብቃት ሊመነጭ የሚችለው አንድ ሠራተኛ በአሠሪ ወይም በሹም እየተገፋ በመሥራት ሳይሆን ፣ ሠራዊቱ በዝርዝር የሥራ ድርሻውን ጠንቅቆ በማወቅ ፣ በየዕለቱ መፈጸም ያለበትን ተግባር ሁሉ በገዛ ራሱ አነሳሽነት አስቦ ለመሥራት የሚያስችለው ሥርዓት ሲዘረጋ ነው ። ይህንን መርህ ተመርኩዞ የኢትዮጵያ አየር ኃይል እንዲደራጅ ክቡር ሌ/ጄኔራል አሰፋ እውቀታቸውንና ሙሉ ኃይላቸውን በቅንነት የሰጡ አስተዋይ መሪ ነበሩ ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአየር ኃይሉን ምርጥ ፓይለቶችና ቴክኒሽያኖች እየተቀበለ እንደ አየር ኃይሉ ሁሉ የኢትዮጵያዊነት መሠረቱን እንዲጥል ክቡር ሌ/ጄ አሰፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

በ፲፱፻፷ ዓ/ም አካባቢ ነፃነታቸውን ለተቀዳጁ የአፍሪካ አገሮች በተለይም ለኬንያ ፣ ለሱማሊያ ፣ ለሱዳንና ለናይጄሪያ የወደፊት አየር ኃይሎች ጥንስስ የሚሆኑ ፓይለቶችና ቴክኒሻኖች በኢትዮጵያ አየር ኃይል እንዳይሰለጥኑ የውጭ ተጽእኖ ሀሳቡን አጨናግፎ ቢቆይም ጄኔራል አሰፋ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አዛዥ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ግን ተግባራዊ ሊሆን ችሏል ።

ሌ/ጄኔራል አሰፋ አየነ ለኦጋዴን የዘረጉት የአየር አገልግሎት መስመር በወር ሁለት ጊዜ ከድሬዳዋ በመነሳት ጂጂጋን ፣ ደገሐቡርን ፣ ቀብሪደሀርን ፣ ቀላፎን ፣ ጎዴን ፣ አዋሬን በቋሚነትና እንደ አስፈላጊነቱም ሌሎች ከተሞችን በማገናኘት ለክፍለ ሀገሩ ሕዝብ የትራንስፖርት ጠቀሜታ እየሰጠ ለብዙ ዓመታት ከቆየ በኋላ ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተረክቦ ቋሚ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል ።

ሌ/ጄኔራል አሰፋ እ አ አ ኦክቶበር ፲፱፻፷፩ የአሜሪካ አየር ኃይልን በጎበኙበት ወቅት በፈጠሩት ከፍተኛ መግባባት የኢትዮጵያ አየር ኃይል በፍጥነት እንዲያድግና ሱፐርሶኒክ አይሮፕላኖች እንዲያገኝ ከማድረጋቸውም በላይ ከበረራም ቴክኒሽያን ሥልጠና አልፎ ችሎታቸው የሚፈቅድላቸው የአየር ኃይሉ ባልደረቦች (በአገር ውስጥና) በአሜሪካ ዩኒቨርስቲዎች እየገቡ የዲግሪ ፕሮግራም እንዲከታተሉ ለማድረግ ችለዋል ።

አየር ኃይሉን ለሃያ ዓመታት ያህል በተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊነትና ብቃት ካለመታከት ካገለገሉና ከገነቡ በኋላ በሌተና ጄኔራልነት ማዕረግ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሆነው ተሾሙ ። በዚህ ኃላፊነት ሌ/ጄ አሰፋ አስተዋይነትን ፣ የመሥራትና የማሠራት ችሎታቸውንና ጠቅላላ የሥራ ልምዳቸውን በማካፈል የጊዜው የፖለቲካ ሁኔታ የፈቀደላቸውን ያህል ለሶስቱም የጦር ኃይሎች የተለየ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ክቡር ሌተና ጄኔራል አሰፋ በትምህርትና በታታሪነት የመሻሻል ለውጥ እንደሚገኝና ጊዜያዊ የችግር ማስታገሻ መፍትሔ ከመሻት ይልቅ ችግሩን ለዘለቄታ በሚያስወግድ ዘዴ ላይ ማተኮር እንደሚመረጥ አስተምረዋል ። በተግባርም እንዲታይ አድርገዋል ። በእርሳቸውም መመሪያና ትእዛዝ ብዙ የምርምር ፕሮጀክቶች ተዘርግተዋል። በሥራ ላይ እንዲውል ካደረጉት ጥናቶች አንዱ ፣ የሰለጠነው ዓለም አሁንም የሚጠቀምበት የወታደራዊ ሙያ የሥራ ችሎታ መቆጣጠሪያ (Military Occupational Specialists, MoS) ሲሆን በሥራቸው ላይ ደርበው ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በመተባበር ያስጠኑት በአገር ውስጥ ቀላል አውሮፕላን የመገጣጠም ጥናት ውሎ አድሮ ዛሬ "እሸት" በመባል የምትታወቀውን ቀላል አውሮፕላን ምርት ሊያስገኝ ችላል ።

ክቡር ሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ የላቀ አእምሮ የነበራቸው እንደበተ ርቱዕ ፣ በትምህርትና በሥራ የሚያምኑ ፣ ለሥልጣንና ለገንዘብ የማይጓጉ ፣ በኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት የማይናወጥ አቋም የነበራቸው አርቀው አሳቢ መሪ ነበሩ ።

ሌ/ጄኔራል አሰፋ "እውቀትና ጤና በዝተው የማይከብዱ ፣ በክምር የማይለኩና ምንም ጊዜ ለቅንጦት የማይውሉ ፀጋዎች ስለሆኑ በማንኛውም አጋጣሚ ልናስፋፋቸው ይገባናል" ይሉ ነበር ። በተለይም "ሰው ለቁም ነገር የሚበቃው እውቀትና ጨዋነት ሲኖረው ብቻ ነው ። ከድሃ ሕዝብ ላይ በሚሰበሰበው ገንዘብ ለሚካሄድ ድርጅት ኃላፊዎች በመሆናችን ምንም ዓይነት ገንዘብ ሆነ ንብረት እንዳይባክን የማድረግ የሕሊና ጭምር ከባድ ኃላፊነት አለብን" በማለት በመሪነት ብቻ ሳይሆን በመምህርነት ባህሪያቸው የአየር ኃይሉን ሠራዊት በበጎ አመለካከትና ሥነ ልቦናዊ ብቃት ኮትኩተው አሳድገዋል ።

በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በመንግሥት መናወጥ የተነሳ አዲስ የሥራ ድልድል ሲደረግ ክቡር ሌተና ጄኔራል አሰፋ አየነ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሆነው በመሾም ጥቂት ወራት እንደሠሩ ያለምንም ወንጀል ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተሰኘው የፋሺስቶች ቡድን በቁጥጥር ሥር ካቆያቸው በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ካለፍርድ በግል ገድሏቸዋል ።

ሌ/ጄ አሰፋ አየነ ከባለቤታቸው ከወ/ሮ አስቴር አሰፋ ሁለት ወንዶችና አራት ሴቶች ልጆች አፍርተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# አቶ ሙላቱ ደበበ

# 1920-1967

ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓ/ም በድሬዳዋ ከተማ ከአቶ ደበበ ገ/ሥላሴና ከወ/ሮ ፍቅሬ ወልደጻዲቅ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እስኪደርስ ድረስ እናታቸው ወ/ሮ ፍቅሬ ወ/ጻዲቅ ዘንድ በእንክብካቤ አደጉ ። ከዚያም አጎታቸው ክቡር አቶ ተፈሪ ሻረው ወሰዷቸው ። መጀመሪያ ተፈሪ መኰንን ኋላም አዲስ አበባ ንግድ ሥራ ት/ቤት ገብተው እንዲማሩ አደረጉ በንግድ ሥራ ት/ቤት ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ አምቦ እርሻ ኮሌጅ ገቡ ። ከዚያም ወደ ካናዳ ሄደው በጋር ባንትስ ኮሌጅ በፋይናንስና አስተዳደር ሙያ ተመረቁ ። በተጨማሪም አሜሪካን አገር ሄደው ከፍተኛ ትምህርት ተከታትለዋል ።

ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት መሥሪያ ቤቶች በከፍተኛ ኃላፊነት ተመድበው ለ፳፪ ዓመታት አገራቸውንና መንግሥታቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል።

በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም በእርሻ ሚኒስቴር

በኤፍ. ኤ. ኦ. (FAO)



ክቡር አቶ ሙላቱ ደበበ በሚኒስትርነትና በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ለ፳፪ ዓመታት አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ዶክተር

# ተስፋዬ ገብረ እግዚእ

# 1917-1967

ክቡር ዶክተር ተስፋዬ ገብረእግዚእ ከቀኛ ዝማች ገብረእግዚእ ስብሐትና ከወ/ሮ መና ተስፋ ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ ።

አባታቸው ቀኛዝማች ገብረእግዚእ ስብሐት ከልጅነታቸው ጀምሮ ያገር ፍቅር ያደረባቸው እና የኢትዮጵያን በኢጣሊያ መወረር ይቃወሙ ስለነበር ከትውልድ አገራቸው ከኤርትራ ወደ መሐል አገር መጥተው በሥራ ዓለም ተሠማሩ ። ፋሺስት ኢጣሊያ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ በራስ ሙሉጌታ አዝማችነት ወደ ሰሜን ዘምተው ከፋሺስቶች ጋር የሞት ሽረት ፍልሚያ ከአደረጉት ጀግኖች አንዱ ቀኛዝማች ገብረእግዚእ ናቸው ።

በኢጣሊያን ጊዜ አባታቸው በቁም እሥር ላይ በመቆየታቸው የዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚእ ትምህርት ለተወሰነ ጊዜ ቢተጓጎልም በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ጠላት ከአገራችን ከተባረረ ወዲህ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ቀጣይ ትምህርታቸውን ኮተቤ በሚገኘው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትለው ሰርቲፊኬት ተቀብለዋል ።

ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚእ ከወጣትነታቸው ጀምሮ ብሩህ አእምሮና ጽኑ ዓላማ የነበራ



ክቡር ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚእ የማስታወቂያ ሚኒስትር ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ ፣ በተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኛ ሆነው ለ፴ ዓመት ያገለገሉ አገር ወዳድ ምሁር ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

# ደጃዝማች
# አእምሮ ሥላሴ አበበ
# 1908-1967



አገራቸውን በጠቅላይ ግዛት እንደራሴነት ፣ በዋና ዲሬክተርነት ፣ በአውራጃ አስተዳዳሪነትና በአርበኝነት ለ፴፩ ዓመታት በታታሪነት ያገለገሉት ክቡር ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ ፣ በሥራ ችሎታቸውና በአመራራቸው የታወቁ ፣ የተወደዱና የተከበሩ የሀገሪቱ አለኝታ ነበሩ ።

ክቡር ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ ከልጅ አበበ ወልደሰማያትና የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ከሆኑት ከወ/ሮ አስካለ ጉግሣ መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፰ ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በቤተ መንግሥት ሥርዓትና ወግ በአያታቸው በወ/ሮ አጸደ ኃይሌ ቤት መምህር ተቀጥሮላቸው የአማርኛ ትምህርት ተማሩ ። አያታቸው ወ/ሮ አጸደ ኃይሌ ለንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ስለሰጧቸው በቤተ መንግሥቱ ደንብ እልፍኝ እያደጉ የዘመናዊውን ትምህርት እንዲማሩ በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ገብተው በጊዜው ይሰጥ የነበረውን የፈረንሣይኛ ትምህርት ተምረው በጥሩ ውጤት ተመርቀዋል ።

በ፲፱፻፳፪ ዓ/ም ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የክብር ዘበኛ መ/ቤቱን ለማቋቋም ከቤልጅግ መንግሥት የጦር አሠልጣኞች አስመጥተው ሥራው ሲጀመር አእምሮ ሥላሴም በወጣትነት ዕድሜ በጸሐፊነት ተቀጥረው እስከ ጠላት ወረራ ድረስ አገልግለዋል ።

በጀግኖች ልጆችዋ ደም ታፍራና ተከብራ በነፃነትዋ ኮርታ የኖረች ኢትዮጵያ አገራችንን ግፈኛው ፋሺስት ኢጣሊያ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም በወረረበት ጊዜ ወጣቱ አእምሮ ሥላሴ አበበም ጠላትን በዱር በገደሉ ለመፋለምና ከውድ አገራችን ለማባረር ቆርጠው ከተነሱት ኢትዮጵያውያን ጋር በማበር በዚያው ዘመን ወደ አርበኝነት ተሰማሩ ።

የኢትዮጵያ ጦር በማይጨው ሲፈታ ወጣቱ አእምሮ ሥላሴ በክቡር ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ናደው አዝማችነት በአርበኝነት ከተሰለፉበት ተመልሰው አዲስ አበባ በመግባት ፫ ቀንና ሌሊት በሚያስደንቅ ጀግንነት ተዋግተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

አዲስ አበባን ለቀው ከወጡ ወዲያ በቡልጋ ጭታ ቆላ ፥ በአርሲ ፥ በላንጋኖ ፥ በሲዳሞ ፥ በዳሎታ ወርግርግ በተባሉ አካባቢዎችና በልዩ ልዩ በረሃዎች እየተዘዋወሩ በመዋጋት የገጠማ ቸውን ችግሮች ሁሉ እየተጋፈጡ ከምባታ ገቡ ። እዚያ ዘመዶቻቸው ዘንድ ለአንድ ወር ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ወደ ኩሎ ኮንታ ጉዞ ለመቀጠል ሲነሱ አባታቸው ልጅ አበበ ወልደ ሰማያትና አጎ ታቸው ፊታ/ ታምራት ወልደ ሰማያት "ደብቀን እናስቀምጥህ አትሂድብን" ብለው ቢለምኑአቸው "እምቢ ለሀገሬ ከጠላት ጋር ከመዋጋት በስተቀር ተደብቄ መኖርን አልፈቅድም" ብለው ከክቡር ደጃ/ በቀለ ጋር ተቀላቅለው በኩሎ ኮንታና በጎፋ ተዘዋውረው እየተዋጉ በገለብ በረሃ በኩል አቋ ርጠው በወቅቱ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ወደነበረ ችው ኬንያ ተሰደዱ ። እዚያም በነበራቸው ከፍ ተኛ ችሎታና ቅልጥፍና ተመርጠው በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በስደተኞች መ/ቤት በዳኝነት ሥራ ተሠማ ርተው ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በሰፊው ረድ ተዋል ።

ቆራጡ አገር ወዳድ ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ ጠላት ከአገራችን እስከተባረረበት ጊዜ ድረስ አንድ ዓመት በአርበኝነት ፥ አራት ዓመት ደግሞ በስደት ያገለገሉ ሲሆን እነዚህም በሕጋዊ ምስክር ተረጋግጦላቸዋል ።

ጀግናው አእምሮ ሥላሴ አበበ ኢትዮጵያ ከፋሺስት ኢጣሊያ ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ ወደ እናት አገራቸው ተመልሰው ከ፲፱፻፴፬ እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ/ም ድረስ በተለያዩ መ/ቤቶችና የአገሪቱ ክፍሎች እየተዘዋወሩ ሰለቸኝ ፥ ደከመኝ ሳይሉ ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል ።

ከ፲፱፻፴፬ ዓ/ም ጀምሮ በክብር ዘበኛ ዋና መ/ቤት ፥ በገንዘብ ሚኒስቴር ፤ በሥራና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፤ ተዛውረው ፤ ሀ/ በክፍል ሹም ነት ፤ ለ/ በዋና ፀሐፊነትና ሐ/ በዋና ዲሬክተርነት ሠርተዋል ። በእነዚህ የኃላፊነት ቦታዎች ሥራ ወዳድና ትጉሁ የሕዝብ አገልጋይ ደጃ/ አእምሮ የሚቀርብላቸውን ማናቸውንም ሥራ "ይህ የበ ታች ነው ይመለስለት ወይም ይኸኛው የበላይ ድርሻ ስለሆነ ይቅረብ" የሚል አመለካከት ሳይ ኖራቸው ቆራጥና ቀልጣፋ ውሳኔ በመስጠት ሠር ተው አሠርተዋል ። ከዚህም በተጨማሪ የአንድን መ/ቤት የሥራ እንቅስቃሴ በሥርዓት መምራት የሚቻለው የመዝገብ ቤቶች አደረጃጀትና የፋይ ሎች አቀማመጥ ዘመናዊ ሥርዓት ሲኖራቸው መሆኑን በመገንዘብ በየተዘዋወሩባቸው ክፍሎች ሁሉ በቅድሚያ የመዝገብ ቤቶችን የውስጥ ደንብ አዘጋጅተው በመስጠት እያቋቋሙ የሚያሠሩ የሥራ መሪ ነበሩ ።

ክቡር ደጃ/ አእምሮ ሥላሴ አበበ ከአዲስ አበባ ውጭ ሲሾሙ የመጀመሪያው በባሕር ዳር አውራጃ በአስተዳዳሪነት ነበር ። "ወደ ተጠቀሰው ክፍል አልሄድ ብለው ያንገራግራሉ" ተብሎ የተ ፈሩት ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ ምንም ቅሬታና ተቃውሞ ሳይታይባቸው በወቅቱ አዲስ የተቆረ ቆረችውን የባሕር ዳርን ግዛት ተረክበው ብዙ ጊዜ ሳያባክኑ ከተማዋን በዘመናዊ እቅድ አስቀይ ሰውና አስሸንሽነው ከተሙ ። ይህ ጥሩ መሠረት እነሆ የባሕር ዳር ከተማ የዛሬ ቅርጽዋን እና እድ ገቷን ልትጎናጸፍ አስቻለ ።

በባሕር ዳር ላይ ባሳዩት የሥራ ውጤት ወደ ሐረርጌ ጠ/ግዛት ተዛውረው በረዳት እንደራሴነት እንዲሠሩ ሲደረግ የዚህ ዓይነት ሹመት በወቅቱ የተሰጠው ለመጀመሪያ ጊዜ ለደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ ነበር ። የተሾሙትም የተመሰከረለት የሥራ ችሎታ ያላቸው መሆኑ በጥናት ስለተረጋገጠና ዋናውን እንደራሴ በሥራ ይደግፋሉ ተብሎ በመ ታመኑ ነበር ። እንደተሾሙም ጠቅላላ የአስተ ዳደሩን ሥራ ተረክበው የጠ/ ግዛቱን ሹማምንትና ሠራተኞች በማስተባበር የሥራ እንቀሳቃሽ ሞተር በመሆን ሠርተው አሠርተዋል ። በእድገት ወደ ሌላ ቦታ ሲዘዋወሩም የሥራ መምህርና መሪ የነበ ሩትን ታላቅ ባለሞያ በማጣቱ ያላዘነ የዚያ ጠ/ ግዛት ነዋሪ አልነበረም ።

ደጃ/ አእምሮ ከ፲፱፻፶፬ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ድረስ አገልግሎት የሰጡት የጋሞ ጎፋ ጠ/ግዛት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነው ነበር ። ይህ ጠ/ ግዛት ኋላ ቀር ከሚባሉት አንዱ ከመሆኑም ሌላ ከዚያን ጊዜ በፊት አንድ የመንግሥት ሠራ ተኛ ሲያጠፋ እንደቅጣት ተቆጥሮ የሚዛወርበት በጠቅላላው አነጋገር "ሠራተኛ ካጠፋ ላከው ጋሞጎፋ" ተብሎ የሚታወቅ ነበር ። መንግሥት ይኸንን ሁኔታ ለመለወጥ በነበረው ፍላጎት ደጃ/ አእምሮ ሥላሴ አበበን የጋሞ ጎፋ ጠ/ግዛት እንደራሴ አድርጎ ሾማቸው ። ክቡርነታቸው ሹመቱን በበጎ በመቀበል ቤተሰባቸውንና የተደ ላደለ ኑሯቸውን ትተው በካኪ ልብስና በትጥቅ ብቻ ወደተሾሙበት ጋሞ ጎፋ ሄዱ ።

እዚያም እንደደረሱ ቅድሚያ የሥራ ፕሮግ ራማቸው አውራጃዎችንና ወረዳዎችን መጎብኘት ነበር ። በወቅቱ አርባ ምንጭ በጫካና በቆንጥር ተሸፍና አገኙ ። ይሁንና በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም የጠ/ ግዛቱ ርዕሰ ከተማ ቀድሞ ከነበረበት ከጨንቻ ወደ አርባ ምንጭ አዛውረው በድንኳን ኑሮ የማ ልማቱን ተግባር ተያያዙት ።

የአውሬ መፈንጫ የነበረውና የሰው ልጅ ረግጦት የማያውቀው የአርባ ምንጭ ከተማ ከም ንጣሮ አንስቶ በማስተር ፕላን አስጠንቶ እስከ ማስቀየስና ማስሸንሸን ድረስ ከተፈጸሙት ሥራ ዎች ጥቂቱ ፤

ሀ/ በጠ/ ግዛቱ ያለውን ሕዝብ በማስተባበር የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችንና ተቋ ሞችን አሠርተዋል ።

ለ/ ከወላይታ ሶዶ እስከ አርባ ምንጭ ያለውን የመኪና መንገድ አሠርተው አርባ ምንጭ ከአዲስ አበባ እንዲገናኝ አድርገዋል ።



www.ethipianorthodox.org

ሐ/ በጠ/ግዛቱ ርዕሰ ከተማና በሌሎች ሁለት አውራጃዎች በድምሩ ሶስት የአይሮፕላን ማረፊያዎች አሠርተው በሳምንት ሁለት ቀን አይሮፕላኖቹ እንዲያርፉ ተደርጓአል ።

መ/ የስልክ መስመሮች ተዘርግተዋል ።

ሠ/ የኤሌክትሪክ መብራት ገብቶቷል ።

ረ/ የሬዲዮ መገናኛዎችን በአውራጃዎችና በወረዳዎች አቋቁመዋል ።

ሰ/ ከአርባ ምንጭ ጎፋ ፣ ፈለገ ነዋይ ፣ ጋርዱላ ፣ ጊዶሌ ፣ ጋሞና ጨንቻ የመኪና መንገዶችን አሠርተዋል ።

ሸ/ ለቱሪስቶች መስሕብ የሚያገለግለውን የነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ እንዲቋቋም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ከማድረግ ሌላ ወደዚያ የሚያደርሰውን የእግዜር ድልድይ መንገድ በብዙ ድካም አሠርተዋል ።

ቀ/ የአርባ ምንጭ ኃይሌ ደጋጋ ፩ኛና በሲቀላ የሚገኘውን አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሠሩ አድርገዋል ።

በ/ በጫሞና በአባያ ሐይቆች የሚንቀሳቀሱ ማለትም ከጎረቤት ጠ/ግዛት ከሲዳሞ ዲላና ከጋርዱላ ጉማይዱ የሚያገናኙ ጀልባዎች እንዲመደቡ ሆኖ ለጠ/ ግዛቱ ሕዝብ አገልግሎት እንዲያበረክቱ ተደርጓል ። ይህ አገልግሎት ሊዘረጋ የቻለው በባለታሪኩ ታታሪነትና አርቆ አስተዋይነት ፣ ባጭር ታጥቆ ፣ ሌት ተቀን ፣ ያለዕረፍት በመሥራትና በመታገል እንደነበረ እንኳንስ ተጠቃሚው የአገሬው ሕዝብ ቀርቶ የግድያውን ተግባር የፈጸመባቸው ፣ አፋኙና ፋሺስቱ ፣ አረመኔ የደርግ መንግሥት የደረሰበትና በኋላ በአድራጎቱ የተጸጸተበት እንደነበር ይነገራል ። ክቡር ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ በችሎታቸው ፣ በአመራራቸውና በእምነታቸው በበላዮቻቸውና በበታቾቻቸው እንዲሁም በሚያስተዳድሩት ሕዝብ ዘንድ እጅጉን የታወቁና የመወደድና የመከበር ጸጋ የተጎናጸፉ ታላቅ የሀገሪቱ አለኝታ ነበሩ ። በዚህ የላቀ አገልግሎታቸው በየጊዜው የሚከተለውን ሹመትና ሽልማት አግኝተዋል ።

ሹመት

— በ፲፱፻፴፭ ዓ/ም የሻምበልነት ማዕረግ ፤

— በ፲፱፻፶ ዓ/ም የፊታውራሪነት ማዕረግ ፤

— በ፲፱፻፶፱ ዓ/ም የደጃዝማችነት ማዕረግ

ሽልማት

— የኢትዮጵያ ክብር ኮከብ ኮርዶን ኒሻን ፤

— የዳግማዊ ምኒልክ የመኰንን ደረጃ ኒሻን ፤

— የአራት ዓመት የስደተኛ ሜዳይ ፤

— የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሜዳይ ባለ አንድ ዘንባባ ፤

— የአንድ ዓመት የአርበኝነት ሜዳይ ፤

— የድል የኮከብ ሜዳይ ተሸልመዋል ።

ክቡር ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ እንኳን ወገኖቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ቀርቶ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት ዓይን የመመልከትና ሁሉንም የመርዳት ተሰጥኦ የየዕለት ተግባራቸው እንዲሆን ከእግዚአብሔር በልዩ የተወሃዳቸው ዕድለኛ ሰው ነበሩ ። ይህንንም ያሳደጓቸውና ያስተማሯቸው ፣ ሥራ በማስያዝ ለታላቅ ደረጃ ያበቋቸው እጅግ ብዙ በሕይወት ያሉ ሰዎች የሚናገሩላቸው ወደር የማይገኝላቸው ንቁና ደግ ሰው ነበሩ ።

ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ "ራሴን ልጥቀም ፣ ልበልጽግ ፣" የሚል የራስ ወዳድነት ጠባይ እና ባሕሪ ጨርሶ በሕሊናቸው የሌለ የዘወትር ተግባራቸው "ሀገሬን ፣ ሕዝቤን በቅን ላገልግል" ከማለት በስተቀር "ሰለቸኝ ፣ ደከመኝ" ማለት የማያውቁ ለሀገሪቱ ቆመዋል ከሚባሉት ወገኖች አንዱና ግምባር ቀደም ነበሩ ።

በረሃ ፣ ነፋሻ ፣ ቀዝቃዛ ሳያማርጡ በተመደቡባቸው ልዩ ልዩ አገሮች ሁሉ በቆራጥነት እየተዘዋወሩ አገር የሚለማበትን ፣ ሕዝቡ ሠርቶ የሚበለጽግበትን ፣ እቅድ እየተለሙ ያለአንዳች ዕረፍት የሚሠሩና የሚያራምዱ እግዚአብሔርን ፈሪ ፣ ንጉሠ ነገሥታቸውን አክባሪ የሆኑ የሀገሪቱ ታማኝ ዜጋ ነበሩ ።

ሰው ሆኖ ሞት ለማንም የማይቀር የተፈጥሮ ግዴታ ቢሆንም ፣ እኝህን ውድ የሀገሪቱን አገልጋይ ላገር እድገትና ግንባታ በመሥራት ላይ እያሉ ሰው በላው አረመኔ ወታደራዊ የደርግ መንግሥት ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በፈቃደኝነት በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ካደረገ በኋላ ካለ ፍርድ ከሌሎች ፶፱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና ጓደኞቻቸው ጋር ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ገድሏቸዋል ።

ክቡር ደጃ/ አእምሮ ሥላሴ ባለትዳርና የሁለት ሴቶችና የአራት ወንዶች ልጆች አባት ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ደጃዝማች ወርቅነህ ወ/አማኑኤል

# 1912 - 1967

ክቡር ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል ኅዳር ፺ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓ/ም በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ልዩ ስሙ ጐሮ ጉቱ በሚባል ሥፍራ ተወለዱ ። አባታቸው ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል ሐዋስ ፤ እናታቸው ወ/ሮ ወሰን የለሽ መሸሻ ይባላሉ ።

ዘመኑ ፡ ቦታውና ሁኔታው በሚፈቅደው መሠረት በሥርዓትና በእንክብካቤ በዚህ ሥፍራ ከወንድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው ጋር አደጉ ። ዕድሜያቸውም ለትምህርት ሲደርስ በወላጆቻቸው ቤት የፊደልንና የቋንቋን ትምህርት በአባታቸው አማካኝነት ተማሩ ። ደጃዝማች ወርቅነህ የኢጣሊያ ፋሺስት ወረራ እስከተጀመረበት ጊዜ ድረስ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተው በወረራው ምክንያት አቋረጡ ።

ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል ከማይጨው ጦርነት መልስ ከአባታቸው ጋር አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይኖሩ ነበር ። አባታቸውና ታላቅ ወንድማቸው ካፒቴን ጥግነህ ወልደ አማኑኤል ከሌሎች አርበኞች ጋር በመሆን ወረራውንና የኢጣሊያንን ጦር በልዩ ልዩ መንገድ ሲዋጉ ቆይተዋል ።

የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ/ም አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በግራዚያኒ ላይ በጣሉት የቦምብ አደጋ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተፈጠረው እልቂት ፤ የግራዚያኒ ጦር በመጀመሪያ ደጃዝማች ወልደ አማኑኤልንና ልጆቻቸውን እንዲታሠሩ አደረገ ። ደጃዝማች ወልደ አማኑኤልን ወዴት እንዳደረሳቸው ባይታወቅም ደጃዝማች ወርቅነህን በአዲስ አበባና በናኩራ እሥር ቤቶች



ክቡር ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደአማኑኤል በምክትል ሚኒስትርነት ፤ በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባልነትና በጠቅላይ ግዛት እንደራሴነት ለሠላሳ ዓመታት አገራቸውን በታማኝነት አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

እንዲማቅቁ አድርጎ እስከ ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ድረስ በእሥር ላይ አቆያቸው ።

የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ክቡር ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል ከሌሎች እስረኞች ጋር በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ከናኩራ እስር ቤት ተለቅቀው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በሕይወት ከተረፉት ከሌሎች እህቶቻቸው ፣ ወንድሞቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ጋር ለመገናኘት በቅተዋል ።

ደጃዝማች ወርቅነህ በጠላት ወረራ ምክንያት የተጎዳች አገራቸውን መልሶ ለማቋቋም በተደረገው ጥረት ተካፋይ በመሆን ከ፲፱፻፴፯ ዓ/ም ጀምሮ በመንግሥት ሥራ ላይ በመሰማራት አቅማቸውና ችሎታቸው በፈቀደ መጠን እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ። በየጊዜው በኃላፊነት ተመድበው የሠሩባቸው መ/ቤቶች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው ።

ከ፲፱፻፴፯ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፴፱ ዓ/ም በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በሕግ አፈጻጸም መጠባበቂያ ጽ/ቤት ዋና ፀሐፊ

ከ፲፱፻፴፱ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፵ ዓ/ም የድሬዳዋ ጉምሩክ ሹም

ከ፲፱፻፵ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፵፩ ዓ/ም የአዶላ ወርቅ ማዕድን ኃላፊ

ከ፲፱፻፵፩ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፵፪ ዓ/ም የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ፀሐፊ

ከ፲፱፻፵፪ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፵፫ ዓ/ም የድሬዳዋ አውራጃ አስተዳዳሪና የድሬዳዋ ከተማ ማዛጋጃ ቤት ሹም

ከ፲፱፻፵፫ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፵፱ ዓ/ም በሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር መ/ቤት

ከ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የአዲስ አበባ ከተማ ም/ከንቲባ ፣

ከ፲፱፻፶፫ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በግቢ ሚኒስቴር ም/ሚኒስትር

ከ፲፱፻፶፱ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ

ከግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም እስከ ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ፣ በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል ።

ደጃ/ ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል ላበረከቱት አገልግሎት የሚከተሉትን የኒሻን ሽልማቶች ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከውጭ ሀገር መንግሥታት ተቀብለዋል ። የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የታላቅ መኰንን ደረጃ ፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የአዛዥ መኰንን ደረጃ ፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የመኰንን ደረጃ ፣ የአሚድላ መታሰቢያ ሜዳይ ፣ ፲፭ ልዩ ልዩ የውጭ አገር መንግሥታት ኒሻኖች ፣ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም አጋማሽ ላይ በኢትዮጵያ በተነሳው ለውጥ ነገሩ ለሀገር የሚበጅ እና የሚጠቅም ከሆነ በማለት እንደ ሌሎች ጓደኞቻቸው እጃቸውን በሰላም ሰጥተው በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ያለፍርድ በግፍ ተገድለዋል ።

ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል ከቀሰሙት ዘመናዊ የቀለም ትምህርት ሌላ ፈረንሣይኛ ፣ ጣሊያንኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ይናገሩ ነበር ።

ክቡር ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ/ም ከወ/ብሩኬ አለማየሁ ጋር በሕግ ተጋብተው ሰባት ልጆች አፍርተዋል ። አራት የልጅ ልጆችም አይተዋል ።

www.ethipianorthodox.org

# ደ/ች ሰለሞን አብርሃም
# 1905-1967

ክቡር ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃም ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፭ ዓ/ም በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ሐማሴን አውራጃ ልዩ ስሙ ፀሎተ በሚባል ሥፍራ ተወለዱ ።

ከ፲፱፻፲፯ እስከ ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ድረስ የትግሪኛና፣የአማርኛ፣የአረብኛና፣የኢጣሊያንኛ ቋንቋዎች በማጥናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ፣ የሁለት ዓመት ልዩ ከፍተኛ ኮርስ በመውሰድ ትምህርታቸውን አጠናክረዋል ።

ከ፲፱፻፴፭ ዓ/ም ጀምሮ በተለያዩ አስተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሶስት ዓመት ያህል ማታ ማታ ከተማሩ በኋላ ፣ በፍርድ ሚኒስቴር መ/ቤት ይሰጥ የነበረውን የሕግ ትምህርት ተምረው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ። ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ማታ ማታ እየተማሩ ለሁለት ዓመት ያህል የሕግ ትምህርት ተከታትለዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃም በተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች ለረጅም ጊዜ አገልግለዋል ።

ሀ/ ከሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፴ እስከ ግንቦት ወር ፲፱፻፴፱ ዓ/ም ድረስ በፍርድ ሚኒስቴር ዲሬክተር፤

ለ/ ከሰኔ ወር ፲፱፻፴፱ እስከ ሰኔ ወር ፲፱፻፵፫ ዓ/ም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠባባቂ ዳኛና የወንጀል ክፍል ዲሬክተር ፤

ሐ/ ከሐምሌ ወር ፲፱፻፵፫ እስከ ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ፤

መ/ ከሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፩ ጀምሮ እስከ መጋቢት ፳፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ/ም ድረስ በአገር ግዛት ሚኒስቴር የሂሳብና የፔርሶኔል ዋና ዲሬክተር ፤



ክቡር ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃ በኤርትራ ክ/ሃገር ልዩ ስሙ ፀሎት በሚባል ሥፍራ በ1905 ዓ.ም. ተወለዱ ። በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሲያገለግሉ ቆይተዋል ። በደርጉ መንግሥት ተይዘው በተገደሉበት ወቅት የወሎ ክ/ሀገር እንደራሴ ነበሩ ።

ሠ/ ከመጋቢት ፳፩/፲፱፻፶፫ እስከ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ/ም ድረስ በአገር ግዛት ሚኒስቴር በረዳት ሚኒስትር ማዕረግ የርስትና ውል ክፍል ሹም ፤

ረ/ ከሐምሌ ፳፬ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ/ም ጀምሮ በያዙት ሥራ ላይ ም/ሚኒስትር ፤

ሰ/ ከታህሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፷፬ ዋ/ም በአገር ግዛት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴታ ፤

ሸ/ ከ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ጀምሮ የወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ሆነው ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን ለ፴፯ ዓመታት በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።

በዚህ ጊዜ በተለይ እየታዘዙ ከሚያከናውኗቸው ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ነበሩ ። የአጋዴንን ክፍለ ግዛት ጠቅላላ የልማት ተግባር ማጥናት፣የጎለልቻን የእርሻ ልማት ማጥናት ፣ የጎዴን ልማት ማቋቋም ፣ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትና በፈረንሣይ ሪፑብሊክ መንግሥት መካከል ኅዳር ፪ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ/ም ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ በተዘረጋው የምድር ባቡር ኩባንያ ስምምነት ውል መሠረት የምድር ባቡርን ክልል ጉዳይ ማጥናት ፣ የዱር አራዊት አስተዳደርና ጥበቃ ቦርድ ሊቀመንበር ሆነው የጥናት ሥራ ማካሄድና የመሬትን ይዞታ ለማሻሻል በተዋቀረው ኮሚቴ ውስጥ አገር ግዛት ሚኒስቴርን ወክለው በመሳተፍ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ለረጅም ዘመን ቅን አገልግሎታቸው መታሰቢያ እንዲሆን ፤

ሀ/ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የዳግማዊ ምኒልክ የፈረሰኛ ደረጃ ኒሻን ፤

ለ/ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ አዛዥ መኰንን ኒሻን ተሰጥቷቸዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ከተገደሉት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አንዱ ሲሆኑ ባለትዳርና የ፲ ልጆች አባት ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ደ/ች ወርቁ እንቁሥላሴ

## 1915-1967



በአርበኝነት ፣ በእንደራሴነት ፣ በዋና ዲሬክተርነትና በአውራጃ አስተዳዳሪነት ሀገራቸውን ለ፴፱ ዓመታት ያገለገሉት ክቡር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ ዕውቅ አስተዳዳሪ ነበሩ ።

ክቡር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፲፭ ዓ/ም አዲስ አበባ ተወለዱ ። አባታቸው ግራዝማች ዕንቁሥላሴ ባንቲዳኝ ፣ እናታቸው ወ/ሮ ፍቅርተ ኃይለ ሥላሴ ይባላሉ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በወላጆቻቸው ቤት በትምህርት ተኮትኩተው አድገዋል ።

ጠላት ሀገራችንን በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ሲወር ከአባታቸውና ከወንድሞቻቸው ጋር በተጉለትና ቡልጋ ፣ በመርሐቤቴና በእንሳሮ በመዘዋወር ፭ቱን ዓመት በአርበኝነት ከመፋለማቸው በላይ ግራርጌ በሚባለው ስፍራ ቆስለዋል ።

ጠላት ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ከ፲፱፻፴፫ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በቤተ መንግሥት ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር ፣ በክብረ መንግሥት አውራጃ ዲሬክተርነት ፣ በማረቆና ጉራጌ አውራጃ አስተዳዳሪነት እንዲሁም በወለጋ ፣ በኢሉባቦርና በሲዳሞ ጠ/ግዛቶች በዲሬክተርነት ፣ በመጨረሻም በባሌና በኢሉባቦር ጠ/ግዛቶች በእንደራሴነት አገልግለዋል ።

ክቡር ደጃ/ ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ ከአርበኝነት መልስ በአገር ግንባታ በተሠማሩበት ፴፩ ዓመታት ዘመናዊ አስተዳደርንና የልማት አውታሮችን በመዘርጋት የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባሮች ፈጽመዋል ።

ሀ/ በክብረ መንግሥት ፣ በወለጋ ፣ በኢሉባቦርና በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛቶች ዘመናዊ የአስተዳደር ሥልት በመቀየስና ሕዝቡን ለልማት በማነቃቃት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ለ/ በማረቆና በጉራጌ አውራጃ አስተዳዳሪነታቸው ዘመን ዝዋይ ለአውራጃው ርዕስ ከተማ



www.ethipianorthodox.org

ሆና እንድትቆረቆር አድርገዋል ። በማረፊና በአርሲ ጎሣዎች መካከል ለዘመናት ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ይሆን የነበረውን የፀጥታ ችግር ለማቃለል የመጀመሪያው ሙከራ ካደረጉት ባለሥልጣኖች አንዱ ነበሩ ። ሕዝቡን በማስተባበር ከዓለምገና እስከ ሶዶ ከዚያም እስከወላሞ ሶዶ ያለውን ጥርጊያ መንገድ አስከፍተዋል ። ከእነዚህም ሌላ ትምህርት ቤቶችን ፣ ጤና ጣቢያዎችን ፣ ክሊኒኮችና ዘመናዊ ቢሮዎችን በአውራጃው ውስጥ አሠርተዋል ።

ሐ/ ከ፲፱፻፶፭ እስከ ፲፱፻፶፰ ዓ/ም በባሌ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ በነበሩበት ዘመን የፀጥታ ችግሮችን ከማቃለላቸውም በላይ የጠቅላይ ግዛቱ መገናኛ በአየር ብቻ ስለነበር ጥርጊያ መንገዶችን አሰርተዋል ። ከገናሌ ፣ ጎባ ከጎባ ዋቢ ፣ ከጊኒር ስራሮ ፣ ከዋቢ ኤልከሬ ራይቱ ፣ ጭረቱ ፣ ዶሎና ጉላ ፣ ከጎባ በጉሮና በበርበሬ ወረዳ በኩል እስከ ዶሎ መና አባ ርሶ ፣ አንጌቱ ድረስ ያሉትን ጥርጊያ መንገዶች አሰርተው ለተሽከርካሪዎች ክፍት እንዲሆኑ አድርገዋል ።

መ/ የኢሉባቦር ጠ/ግዛት እንደራሴ ሆነው ከ፲፱፻፶፰ እስከ ፲፱፻፷፯ ድረስ በጎሬ አውራጃ ውስጥ ያሉትን መንገዶች በማስቀየስ የግዛቱ ዋና ከተማ ከነበረው ከጎሬ ጋር እንዲገናኝ አድርገዋል ። ከጎሬ ሞቻ አውራጃ ከዚያም እስከ ከፋ ጠ/ግዛት ቦንጋ ድረስ ያሉትን ጥርጊያ መንገዶች ለመክፈት ከፍተኛ ጥረት አድርገው ከጎሬ ማሻ ፣ ከማሻ ቴፒ ፣ ከቴፒ ወደ ቦንጋ የሚያወጣውን መንገድ አበራ እስከተባለው የከፋ ወሰን ድረስ አስቀይሰው ጥርጊያ መንገድ አስከፍተዋል ። በተጨማሪም በየመንገዶቹ ባሉት ከፍተኛ ጅረቶች ላይ በሕዝብ መዋጮ የተገዙ ዘጠኝ የብረት ድልድዮች እንዲዘረጉ አድርገዋል ።

ሕዝቡ በልማት ሥራ እንዲሳተፍ ለማድረግ በጉባኤ ካስመከሩ በኋላ በራሱ ደንብ የሚስተዳደር አንድ የኢሉባቦር "የልማት ድርጅት" በ፲፱፻፷ ዓ/ም እንዲመሠረት አድርገዋል ። ድርጅቱን በሊቀ መንበርነት እየመሩ ፣ በእውቅ መሐንዲሶች እየተጠና ፣ የባሮ ቀላ ፣ የጊዳቼና የዳበና ድልድዮች እንዲሠሩ ከማድረጋቸውም ሌላ ዶዘሮችና ግሬደሮች ተገዝተው የውስጥ መንገዶች እንዲከፈቱ አድርገዋል ። ይህ የልማት ድርጅት ከስዊድን ተራድኦ ድርጅት ጋር በመተባበር ብዛታቸው ከ፳ ያላነሱ ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ፲ የጤና ጣቢያዎችና ክሊኒኮች እንዲሠሩ ከማድረጉም በላይ ሶስት ፴ ሰው የሚጭኑ አውቶቡሶች ተገዝተው የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ አድርገዋል ። የጠ/ግዛቱን የአስተዳደር አገልግሎት ለማሻሻል ቀደም ሲል በ፩ አውራጃ ፣ በ፲፯ ወረዳና በ፳ ምክትል ወረዳዎች ተዋቅሮ የነበረውን በማቀራረብ "ሶርና ገባ" የተባለ አዲስ አውራጃ በመክለልና በ፴፩ ወረዳዎች እንዲዋቀሩ አድርገዋል ። በዚህም ምክንያት ሕዝቡ ተቀራርቦ ችግሩን በጋራ ለማስወገድ ችሏል ።

ሰ/ ከ፲፰፻፹፭ ጀምሮ የጠቅላይ ግዛት ርዕስ ከተማ ሆኖ የቆየው ጎሬ ሊስፋፋ የማይችልና ለማኅበራዊ ኑሮ እድገት ተስማሚ ሆኖ ባለመገኘቱ ቀደም ሲል ከተደረገው ጥናት በመነሳት የጠ/ግዛቱን ዋና ከተማ ከጥቅምት ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ጀምሮ ወደ መቱ እንዲዛወር አድርገዋል ።

የመቱ ከተማ በማስተር ፕላን መሠረት ተቀይሶ ግንባታው እንዲጀመር ከማድረጋቸውም በላይ በቻይና መንግሥት ተራድኦ አንድ ዲዚል (በናፍታ) የሚሠራ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያ ለከተማው አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል ። በክቡር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ አሳሳቢነት የተጀመረው ለሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫነት በበቾ በኩል ያለው የሶር ፏፏቴም የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ጥናት ዛሬ ለፍሬ በቅቶ አገልግሎት እየሰጠ ነው ።

ክቡር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ለአበረከቱት አገልግሎት የሚከተሉትን ማዕረጎችና ሽልማት ተቀብለዋል ።

— በ፲፱፻፵፪ የቀኛዝማችነት ማዕረግ

— በ፲፱፻፶፭ የፊታውራሪነት ማዕረግ

— በ፲፱፻፷፪ በደጃዝማችነት ማዕረግ ተሾመው የኢትዮጵያን የክብር ኮከብ አዛዥ መኰንን ኒሻን ተሸልመዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ ሕዝቡን ለማገልገል የነበራቸውን ከፍተኛ ምኞት ከግብ ለማድረስ በጥረት ላይ እንዳሉ የመንግሥት ለውጥ በመደረጉ በግፈኛው ወታደራዊው የደርግ መንግሥት ሜራ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ተይዘው ለ፭ ወራት ያህል ከታሰሩ በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ያለ ፍርድ በግፍ ተገድለዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ሥላሴ ሲስተር ሙሉመቤት ወልደማርያምን በሕግ አግብተው ስምንት ልጆች አፍርተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ደጃዝማች ለገሠ በዙ

# 1922-1967



ከ፲፱፻፷፩ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፷፯ የወሎ ክፍለ ሀገር እንደራሴ የነበሩት ክቡር ደጃዝማች ለገሠ በዙ በሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር ፥ በጡረታ ኮሚሽንና በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከፍ ባለ ሥልጣን ደረጃ ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን ለ፳፱ ዓመታት በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ለገሠ በዙ በአርሲ ክፍለ ሀገር ልዩ ስሙ ቱሉ ኩቼ ማርያም ተብሎ በሚጠራው ሥፍራ ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ/ም ተወለዱ ። አባታቸው ባሻ በዙ ጐጃና እናታቸው ወ/ሮ ሙሉ ነሽ ወልደማርያም ይባላሉ ።

ያገር ወግና ባህል በሚፈቅደው መሠረት በቤተ ክህነት የሚሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት በወላጆቻቸው ቤት ተምረው ዘመናዊ ትምህርት በተፈሪ መኰንንና በተግባረዕድ ት/ቤቶች አጠናቀቁ ። ለትምህርት ከፍ ያለ ጉጉት ስለነበራቸው በሥራ ዓለም እያሉ በብሪትሽ ካውንስል ኢንስቲትዩትና በኮርስፖንደንስ እያጠኑ ዕውቀታቸውንና የሥራ ችሎታቸውን አሻሽለዋል ።

ደጃዝማች ለገሠ በዙ ወደ ሥራው ዓለም የተሠማሩት በ፲፱፻፴፱ ዓ/ም በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀጥረው በተከታታይ በፀሐፊነት ፥ በዋና ፀሐፊነት ፥ በም/ዋና እንስፔክተርነትና በዋና እንስፔክተርነት እስከ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ/ም ድረስ በማገልገል ነበር ።

ደጃዝማች ለገሠ በዙ የጡረታ ኮሚሽን ሲቋቋም መሠረታዊ ጥናት እንዲደረግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ከማበርከታቸውም በላይ አሁን በሀገራችን የሚሠራበትን መመሪያ መሠረት ጥለ



www.ethipianorthodox.org

ዋል ። ከጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ/ም እስከ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም ባለው ጊዜ የጡረታ ኮሚሽን ኮሚሽነር በመሆን መ/ቤቱን በትጋትና በኃላፊነት ሲመሩ ቆይተዋል ።

ከሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም እስከ ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም በም/ሚኒስትርነት ማዕረግ የምርጫ ቦርድ መሥሪያ ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅና የቦርድ ሊቀ መንበር ነበሩ ።

ደጃዝማች ለገሠ በዙ ከጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም እስከ ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ድረስ በአገር አስተዳደር ሚኒስትር ዴኤታ ተብለው ብዙ የሚታወሱበት ቁም ነገር ሥራ በማበርከት "ሥራቸው እንደመልካቸው ያማረ" በመባል ምስጉን ሊሆኑ በቅተዋል ።

ክቡር ደጃዝማች ለገሠ በዙ በሠሩባቸው መ/ቤቶች ሁሉ ከፍተኛ የሥራ ድርሻ ያበረከቱ መሆናቸውን የሥራ ጓደኞቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ሕዝብ የመሰከረላቸው ታታሪ ሰው ናቸው ። በሠሩ ባቸው መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ጥራት ያለውን ሕጋዊ ሥራ በመሥራት ፣ መመሪያዎችንና መግለጫ ዎችን በመስጠት ፣ መዛግብትን በማቋቋም ፣ ሠራ ተኞን በማሰልጠን የታወቁ ከመሆናቸውም በላይ በልዩ ልዩ ኮሚቴዎችም ሰብሳቢና አባል በመሆን አገልግሎት ሰጥተዋል ።

በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም አንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ስለእርሳቸው በሰጡት አስተያየት "በጠባዩ የተ ወደደ ፣ ታዛዥነትና የሥራ ችሎታ ያለው ፣ የማ ይሰለች ፣ አብዝቶም የሚያጠና ታማኝነቱ የተረ ጋገጠ ወጣት ነው" በማለት የተናገሩት ደጃ/ ለገሠ በዙ በሠሩባቸው ሁሉ በተግባር ተረጋግ ጧል ።

ደጃዝማች ለገሠ ትምህርታቸውን ለማሻሻል በነበራቸው ጉጉት በማታ ት/ቤቶችና በልዩ ልዩ ኢንስቲትዩቶች በመከታተል በእንግሊዝኛ ፣ በአ ካውንቲንግና በኦዲቲንግ ከፍተኛ ትምህርትና ልምድ ያካበቱ ሰው ነበሩ ። ጠቅላላ ትምህርትና የሥራ ልምድ ለመቅሰም በአውሮፓ ፣ በአሜሪካ ፣ በእሥራኤልና በአፍሪካ ልዩ ልዩ አገሮች ተዘዋ ውረው ለሥራቸውና ለአገለገሉባቸው መ/ቤቶች የሚጠቅሙ እውቀት ገብይተዋል ።

ክቡር ደጃ/ ለገሠ በዙ በአገልግሎት ዘመና ቸው ለአደረጉት አስተዋጽኦ ማስረጃ እንዲሆኑ ፤

— የኢትዮጵያ የክብር ታላቅ መኰንን ከነፕላኩ

— የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሻን የመ ኰንን ደረጃ ባለአምበል

— የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን የመኰንን ደረጃ ባለአምበል ተሸልመዋል ።

ክቡር ደጃ/ ለገሠ በዙ ከሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ጀምረው የወሎ ክፍለ ሀገር እንደራሴ ሆነው ለብዙ ዓመታት የነበረውን የወሎ ድርቅ ችግር ለመፍታት ጥረት በማድረግ ላይ እንዳሉ በወታደራዊው ደርግ በቁጥጥር ሥር ውለው ለስ ድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ካለፍርድ በጭካኔ ተገድለዋል ።

ደጃዝማች ለገሠ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ወ/ሮ ክብረ ወርቅ ስንቁን በሕግ አግብተው ሁለት ወንድ ልጆችና ሰባት ሴት ልጆች አፍርተዋል ። ሕፃናቱ ለአቅመ አዳም ሳይበቁ አባታቸው በመገደላ ቸው ወ/ሮ ክብረ ወርቅ ስንቁ አስተያየታቸውን ሲሰጡ "ቤተሰብ ላይ የደረሰውን በደል የወለደ ይፍረድ ፤ ታሪክም የ፲፯ቱን ዓመት ግፍ አይዘነ ጋውም" ብለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# አፈንጉሥ አበጀ ደባልቅ

## 1905-1967



ክቡር አፈ ንጉሥ አበጀ ደባልቅ ፥ ለ፵፩ ዓመታት በአርበኝነት፣የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ችሎት ፍርድ አጣሪ ጉባኤ ፕሬዚዳንትና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል በመሆን አገራቸውን አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

ክቡር አፈንጉሥ አበጀ ደባልቅ በ፲፱፻፫ ዓ/ም በደብረብርሃን አውራጃ ፣ በደነባ ወረዳ ፣ በጅሩ ምክትል ወረዳ ግዛት ፣ በመንታ ወፍጮ ከአባታቸው ከአቶ ደባልቅ ባንቲና ከእናታቸው ከወይዘሮ ታዩ ጭንቆሎ ተወለዱ ።

ወቅቱ በሚፈቅደው መሠረት በቤተክህነት የሚሰጠውን ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ ለአጭር ጊዜ በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤት በምስጢር ክፍል በአንደኛ ፀሐፊነት አገልግለዋል ። በዚህም ወቅት በ፲፱፻፳፪ ዓ/ም በተደረገው የቋና ዘመቻ ፣ አባታቸው ቀደም ሲል አርፈው ስለ ነበር የአባታቸውን ትጥቅ ይዘው በመዝመት ታግለዋል ።

ከ፲፱፻፳፰ እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ ፣ ለሀገር ነፃነትና ክብር ሲሉ ፣ በአምስቱ ዓመታት ፣ በዱር በገደል ሕይወታቸውን በማጋፈጥ በተለያዩ የጦር ሜዳ ዎች በተለይም በጎጃም ፣ በትግራይ ፣ በግሼና አንጾኪያ የአርበኝነት አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

የጠላት ወራሪ ጦር ተሸንፎ ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ፣ ወደ ሥራ ዓለም ተመልሰው ፣ ከ፲፱፻፴፬ እስከ ፲፱፻፵፩ ዓ/ም በሸዋና በወሎ የወ ረዳ ዋና ፀሐፊ ፣ በቤጌምድር ጠ/ግዛት ምክትል ዋና ፀሐፊ ፣ በአዲስ አበባ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት አንደኛ ፀሐፊ ፣ የአስተዳደር ፍ/ቤት ዳኛና ፕሬዚዳንት በመሆን ሠርተዋል ። ኋላም ወደ ፍርድ ሚኒስቴር ተዛውረው የከፍተኛ ፍርድ ቤት አስተዳዳሪና የጠቅላይ ፍ/ቤት ምክትል አፈንጉሥ በመባል አገልግለዋል ። ከ፲፱፻፵፩—፵፯ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዙፋን ችሎት ፍርድ አጣሪ ጉባኤ መጀመሪያ በምክትል ፕሬዚ ዳንትነት ኋላም በፕሬዚዳንትነት ተሾመው ቅን አገልግሎታቸውን ከማበርከታቸውም በላይ ሚያ ዝያ ፲፱፻፵፯ ዓ/ም የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሆነው ተሾመው ነበር ።

ክቡር አፈንጉሥ አበጀ ደባልቅ ፣ ሕይወታ ቸው በደርግ ሰለባ እስከጠፋበት ድረስ ለኢትዮጵ ያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሐቀኝነት ፣ በቅንነት ፣ በጦር ሜዳ አርበኝነት ጭምር አገልግለዋል ። ክቡርነታቸው ለሀገር የነበራቸው ፍቅር ፣ በአርበ ኝነትም ሆነ በሰላሙ ጊዜ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችና የሥራ ቦታዎች ተዘዋውረው ላበረከ ቱት የላቀ ተግባር ከተሸለሟቸው ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ውስጥ ሀ/የቅድስት ሥላሴ የወርቅ የክብር ኮከብ ለ/ የዳግማዊ ምኒልክ የፈረሰኛ የወ ርቅ የክብር ኮከብ ፣ ሐ/ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የፈረሰኛ የወርቅ የክብር ኮከብና መ/ የ፲፱፻፴፫ ዓ/ም የአሜድላ ፳፭ኛ ዓመት መታሰቢያ ይገኙ ባቸዋል ።

ክቡር አፈንጉሥ አበጀ ደባልቅ በአገልግሎት ዘመናቸው በሰላምም ሆነ በጦርነት ኢትዮጵያን ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ፡ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ፣ በሰፊው ያውቁ ስለነበር በአንድ ክፍለ ሀገር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወገንነትና አንድነት እንዲሁም ደህንነት አጥብ ቀው ያምኑ ነበር ። የነበሯቸው ወዳጆች ብዛትና ዓይነት ከትንሽ እስከ ትልቅ መሆኑ ይህንኑ የሚ ያሳይ ነበር ።

የክቡር አፈንጉሥ አበጀ ችሎታና ለሥራ የነ በራቸው ፍቅር ከልዩ የተፈጥሮ ተሰጥኦ ፣ ከጠንካራ ባሕርይና ከሰፊ የሥራ ልምድ የመነጨ ነበር ። ሕይወታቸው የሚታወሰው ኢትዮጵያን በእውነትና በቆራጥነት ስላገለገሉ ብቻ ሳይሆን ፣ በሩህሩህነ ትና በደግነትም የታወቁ ክርስቲያን ስለነበሩ ነው ። ሰማዕትነታቸው በደርግ የግፍ አገዳደል ይከተም እንጂ የተጀመረው በአዋቂ እድሜ በፈ ጸሙአቸው ብዙ መልካም ሥራዎች ስለነበር ፣ ሕይወታቸው ለዘመናቸው ትውልድ አንድ ዓይ ነት መታሰቢያ ነው ። ለመጪውም ትውልድ አር አያነት አለው ።

ክቡር አፈንጉሥ አበጀ ደባልቅ የመጀመሪያና የመጨረሻ የነበሩት ባለቤታቸውን ወ/ሮ አሰፋሽ ክፍለ ዮሐንስን በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም አግብተው ከ፵ ዓመት በላይ አብረው በመኖር ሁለት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ልጆች ተክተዋል ።

---

www.ethipianorthodox.org

# ብላታ አድማሱ ረታ

## 1916-1967



የግቢ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ የነበሩት ክቡር ብላታ አድማሱ ረታ ፴፪ ዓመታት መንግሥታቸውንና አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

ክቡር ብላታ አድማሱ ረታ ከእናታቸው ከወ/ሮ አይናለም አየለና ከአባታቸው ከአቶ ረታ እንግዳ በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በደራ ወረዳ በታላቂቱ ደብር ሻሚ ማርያም በ፲፱፻፲፮ ዓ/ም ተወለዱ ።

ታዋቂ ሠዓሊ የነበሩት አጎታቸው አቶ አገኘሁ እንግዳ ከፈረንሣይ አገር እንደመጡ የእናትና አባት ፈቃድ ጠይቀው እያስተማሩና እያሳደጓቸው ሳለ ለሥራ ጉዳይ ወደ ግርማዊነታቸው ሲሄዱ ክቡር ብላታ አድማሱ ረታን ለማስተዋወቅ ይዘዋቸው ቀረቡ ። ንጉሠ ነገሥቱም ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ አደረጉ ።

ወጣት አድማሱም የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአማርኛና በፈረንሣይኛ ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ በቤተ መንግሥት ሥራ እንዲጀምሩ ተደረገ ።

ብላታ አድማሱ በመደበኛ ትምህርት ቤት ከቀሰሙት እውቀት ሌላ ቋንቋ የማወቅ ብርቱ ፍላጎት ስለነበራቸው በግል ጥረታቸው ጣልያንኛ ፣ አረብኛና በመጠኑም እንግሊዝኛ ቋንቋ ለመናገር ችለዋል ። በትርፍ ጊዜያቸው ተላምደው ሄሊኮፕተር ያበሩም ነበር ።

ብላታ አድማሱ ከሚታወቁባቸው በጎ ሥራዎች በየክፍለ ሀገሩ ለሚገኙ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ማሠሪያ የገንዘብ እርዳታ ከመስጠታቸውም በላይ ንዋየ ቅድሳት እየገዙ ሃይማኖትን ለማጠናከር ያደርጉት የነበረው ከፍተኛ ጥረት አንዱ ነው ። ለምሳሌ ያህል ለሻሚ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥራ ረድተዋል ፣ ንዋየ ቅድሳትም ለግሠዋል ። ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ክሊኒክ አሠርተዋል ከዚህም በላይ ከየክፍለ ሀገሩ ለትምህርት ፍለጋ የሚመጡ ረዳት የሌላቸውን ልጆች በማሰባሰብና እርዳታ እየሰጡ በማስተማር ራሳቸውን እንዲችሉ አድርገዋል ።

ከግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ጋር ባላቸው የቅርብ ግንኙነትም ፍትሕ የጎደለባቸው በትክክል እንዲታይላቸው ፤ በተለይም በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ለታሠሩት ምሕረት እንዲደረግላቸውና ከእሥራት አስፈትተዋል ።

ክቡር ብላታ አድማሱ ረታ በመንግሥት ሥራ ለ፴፱ ዓመታት በታማኝነትና በቅንነት ላበረከቱት የረጅም ጊዜ አገልግሎት ብላታ ተብለዋል ፤ በግቢ ሚኒስቴርም ሚኒስትር ደኤታ ነበሩ ። ከአገር ውስጥና ከውጭ መንግሥታት ከተሸለሙት አያሌ ኒሻኖች የሚከተሉት ይገኙበታል ።

በ፲፱፻፵፯ ዓ/ም የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ፣ ከስዊድን ፣ ከዴንማርክና ከኒውዚላንድ ፤ በ፲፱፻፶ ዓ/ም ከኒዘርላንድ ፣ በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ከቤልጅግ በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም የዳግማዊ ምኒልክ የመኰንን ደረጃ፤ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ከጆርዳን ፣ ከማላጋሲ ፤ በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም ከሴኔጌል ፣ ከኖርዌይ፣ ከሃይቲ ፤ በ፲፱፻፷ ዓ/ም ከቤልጅግ ፤ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ከእስፔን ፤ በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ከሱዳንና ከግብፅ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ከሞሮኮ ከጀርመን ፣ ከግሪክ ፤ የክብር ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

ክቡር ብላታ አድማሱ ረታ ለአገራቸውና ለወገናቸው ታማኝ ፣ ርህራሄ የተሞላባቸው ፣ ሥራቸውን አክባሪ ፣ ስለቸኘ ደከመኝ የማይሉ ሰው ነበሩ። ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን የሚያፈቅሩ ሰው ሆነው ሳሉ በሥራቸው ባህሪና የሥራ ውጥረት በዓመት በዓልም እንኳን ለረጅም ሰዓት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ዕድል አልነበራቸውም። ከሥራ ወዳድነታቸው የተነሣም በማናቸውም ሰዓት ከሥራ ገበታ ላይ የማይለዩ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም እጅግ የሚወዱዋቸው ሰው ነበሩ ።

በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በጥር ወር እናታቸው በጠና ታመው ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ከሄዱ በኋላ የሕዝብ አመጽ የተደረገና ወታደራዊው ደርግ በመንግሥት መድረክ ላይ ብቅ ያለ ቢሆንም የቅርብ ዘመድ የሆነ ሁሉ ሁኔታው አስከፊ ስለሆነ ወደ ሱዳን አገር ይሂዱ ቢሏቸው "አገሬንና ንጉሠ ነገሥቴን ትቼ አልሄድም ፣ የሞት ጽዋ ካለ አብሬ እቀምሳለሁ" በማለት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ። እንደተመለሱም በወታደራዊ ደርግ ለ፮ ወር ያህል በቁጥጥር ሥር ውለው በሕክምና ላይ እንዳሉ የሥራ ጓደኞቻቸው ከነበሩት ፶፱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በግፍ በጭካኔ ተገድለዋል ።

ክቡር ብላታ አድማሱ የሕግ ባለቤታቸውን ወይዘሮ ኢትዮጵያ ውብነህን በተክሊል አግብተው ፪ ወንድና ፪ ሴቶች ልጆች አፍርተዋል ።


www.ethipianorthodox.org

# ኰሎኔል ሰለሞን ከድር

## 1919 - 1967



ክቡር ሌ/ኰሎኔል ሰለሞን ከድር በተለያዩ ወታደራዊና የሲቪል መ/ቤቶች በሚኒስቴር ደኤታና በሌሎች ማዕረጎች ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን ለ፳፩ ዓመታት ያገለገሉ እውቅ መሪና አስተዳዳሪ ነበሩ ።

መስከረም ፲፱ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ/ም በኢሉባቦር ክ/ሀገር በጎሬ ከተማ ከአቶ ከድር ሃናና ከወይዘሮ ማዘንጊያ ነጋሽ ተወለዱ ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጎሬ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ት/ቤትና አዲስ አበባ ተፈሪ መኰንን ት/ቤት እንደአጠናቀቁ ወታደር ለመሆን በነበራቸው ፍላጎት ክብር ዘበኛ የጦር አካዳሚ ገብተው በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም በከፍተኛ ማዕረግ ተመረቁ ።

የሥራ መጀመሪያ የሆናቸውን በተመረቁበት አካዳሚ ለሁለተኛ ጊዜ ለተመለመሉት ዕጩ መኰንኖች አሰልጣኝ ሆነው በመመደብ የመልካም መኰንንነትና የመሪነት አርአያ በማስቀሰም ለሶስት ዓመት ያህል አስተምረው አስመርቀዋል ። በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም በኮሪያ ለዘመተው ለሁለተኛ ሻለቃ የመረጃ መኰንን ሆነው በሰሩበት ወቅትም በአሳዩት የጦር ስልትና ጀግንነት ለጦሩ መልካም ስም ካሰጡት አንዱ ነበሩ ።

ከኮሪያ መልስ የክብር ዘበኛ የዘመቻ መምሪያ መኰንን ሆነው በትምህርት ከቀሰሙትና በተግባር ባካበቱት ልምድ ተደግፈው በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ታላቁን የውጊያ ትርኢት በካራሎ ተራራ ላይ በ፲፱፻፴፯ ዓ/ም አደራጁ ። በዚህ ተራራ ላይ በከባድ መሣሪያ ፣ በመድፍ ፣ በታንክና በአየር ኃይል የተደገፈ ውጊያ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በተገኙበት አሳይተው ለራሳቸው ታላቅ ምስጋና ፣ ለጦሩ ከፍ ያለ አድናቆትንና ከበሬታን አስገኝተዋል ።

የክቡር ሌ/ኮሎኔል ሰለሞን ከድር ከፍ ያለ ችሎታና ትጋት በቅርብ ይከታተሉ የነበሩ ባለሥልጣኖች በተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊነት ያጩዋቸው ነበር ። መጀመሪያ በ፲፱፻፴፰ ዓ ም በቶኪዮ ለተባበሩት መንግሥታትና ለኢትዮጵያ ጦር ዋና አገናኝ ሆነው ተሾሙ ። ቀጥሎም በዋሽንግተን የመጀመሪያው ሚሊቴሪ አታሼ በመሆን በአሜሪካና በኢትዮጵያ ወታደራዊ ተቋሞች መካከል የነበረውን ግንኙነት በይበልጥ እንዲጠናከር የበ

www.ethipianorthodox.org

# አቶ ተገኝ የተሻወርቅ

## 1926 - 1967

በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የማስታወቂያ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ሆነው በተሾሙ ማግሥት በ፴፩ ዓመታቸው የደርግን ግፍ ቀማሽ ከሆኑት ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለሥልጣኖች አንዱ ክቡር አቶ ተገኝ የተሻወርቅ አገራቸውን ማገልገል የጀመሩት በ ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ገና በጠዋቱ የኢትዮጵያን ሄራልድ የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በመሆን ነበር ።

ወቅቱ ከሚጠይቀው የሥነ ጽሑፍ ዘይቤና አቀራረብ ወጣ በማለት ጋዜጣው ለሕብረተሰቡ የማሳወቅ ፣ የማስተማርና የማዝናናት ተግባሩን እንዲፈጽም በአደረጉት ያላሰለሰ ጥረት በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም የፕሬስ መምሪያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ ። የፕሬስ መምሪያ በአንድ ጋዜጣ የሥራ ሂደት ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን በማስታወቂያ ሚኒስቴር ሥር የሚታተሙትን ጋዜጦች ፣ መጽሔቶችና መጽሐፎች ሁሉ የሚያደራጅ ፣ የሚመራና የሚቆጣጠር ድርጅት ነበር ።

አቶ ተገኝ የተሻወርቅ የነበራቸውን የሥነ ጽሑፍ ተሰጥኦ በትምህርት ፣ በንባብና በድርሰት ውድድሮች አዳብረው ባካበቱት ሰፊ ልምድ ፣ በሕዝባዊ ባሕሪያቸው ጭምር በመታገዝ ፣ የኢትዮጵያን ፕሬስ አምስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊና የጽሑፍ ጥራቱ እንዲሻሻል ፣ አገልግሎቱም በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ አድር



ክቡር አቶ ተገኝ የተሻወርቅ የማስታወቂያ ም/ሚኒስትር ፣ የፕሬስ መምሪያ ዋና ሥራ አስኪያጅና የኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው አገራቸውን ለ፲፰ ዓመታት ያገለገሉ ስመጥር ጋዜጠኛ ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

ገዋል ። ከ፭ እስከ ፲ በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ብቻ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ በነበረባት ሀገራችን ሥነ ጽሑፍን ማስፋፋት አስቸጋሪ መሆኑ ቢታወቅም ጋዜጦች ተነባቢ ፣ ቀስቃሽ እና አስተማሪ ሊሆኑ በቅተዋል ።

ባሳዩት የሥራ አመራር ብቃት ፣ ኃላፊነትን የመቀበል ችሎታና በራስ አነሳሽነት ሥራን በትጋት የመሥራትና የማሠራት ባሕሪያቸው ነበር አቶ ተገኝ የተሻወርቅ በ፲፱፻፸፮ ለም/ሚኒስትርነት ሹመት የበቁት ።

ነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፳፮ ዓ/ም በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ወበራ አውራጃ ልዩ ስሙ ሞሌ በሚባል ሥፍራ ተወለዱ ። አቶ ተገኝ አባታቸው አቶ የተሻወርቅ ዘርፉ ፣ እናታቸው ወ/ሮ ደብሪቱ ጌጡ ይባላሉ ።

አቶ ተገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በደሴ ከተማ በወይዘሮ የሺ እመቤት ትምህርት ቤት ፣ የሁለተኛ ደረጃን ደግሞ ኮተቤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቀቁ ። ከዚያም ለከፍተኛ ትምህርት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ገብተው በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም የባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ በማግኘት ተመረቁ ። የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት በዚህ አላበቃም ። በ፲፱፻፶፪ ዓ/ም አሜሪካን አገር ከሚገኘው ስመጥር ቦስተን ዩኒቨርስቲ ገብተው በጋዜጠኝነት ሙያ ማስተር ኦፍ ሳይንስ ዲግሪ በ፲፱፻፶፫ ተቀብለዋል ።

አቶ ተገኝ የተሻወርቅ በተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ ከክፍላቸው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ፤ በተለይም በድርሰት ውድድሮች አሸናፊ በመሆን የተለያዩ ሽልማቶችን ያገኙ ነበር ።

ብሩህ የሥነ ጽሑፍ ሰው የነበሩት አቶ ተገኝ የተሻወርቅ ሥራ ከጀመሩበት ከ፲፱፻፵፬ ዓ/ም ጀምሮ በአሜሪካ ፣ በምዕራብ እና በምሥራቅ አውሮፓ ፣ በሶቭየት ሕብረትና በሩቅ ምሥራቅ እየተዘዋወሩ ኢትዮጵያን ለዓለም ሕብረተሰብ ሲያስተዋውቁና ለሀገራቸው ይጠቅማሉ ብለው ያሰቧቸውን ዕውቀቶች ሁሉ በመቅሰም እና በማሰባሰብ ለሥራ ጓደኞቻቸው አካፍለዋል ። በእነዚህ የሥራ ጉብኝቶች ስለኢትዮጵያና ስለ ጋዜጠኝነት ሙያ ካነጋገሯቸው ታላላቅ መሪዎችና የሥነ ጽሑፍ ሰዎች በዘመኑ ብዙ ይነገርላቸው የነበሩ የቻይና እውቅ መሪ ቸርማን ማኦ ሴቱንግና ጠቅላይ ሚኒስትር ቹንኤን ላይ ይገኙበታል ።

ክቡር አቶ ተገኝ የሀገራቸውን ሥነ ጽሑፍ ያፈቅሩ ስለነበር በመላ ኢትዮጵያ በመዘዋወር ጥንታዊ ጽሑፎችን በተለይም ስለቀደምት የግጥም ጽሑፎች ከማሰባሰባቸውም በላይ ጸሐፊዎች ስለሀገራቸው ሁኔታ ፣ ባሕልና ልማት በበሳል ብዕራቸው ቀርጸው ለሕዝብ እንዲያሳውቁ የሚያበረታቱና ራሳቸውም ይጽፉ ነበር ።

አንድ አምስት ዓመት በቁጥጥር ሥር ቆይተው ከደርግ እሥር ቤት የተለቀቁት ከፍተኛ ባለሥልጣን ስለክቡር አቶ ተገኝ ችሎታና አስተዋይነት ሲናገሩ ፤

"ይህ ኢትዮጵያዊ ወጣት እንደስሙ ትርጓሜ በኢትዮጵያ ለጊዜው ፍላጎት ተስማሚ አገልግሎት ለማቅረብ በወቅቱ የተገኘ ፣ በትምህርት የበለጸገ ፣ በሥራ ልምድ የዳበረ ሙሉ የአገር አገልግሎት ችሎታ ያለው ሰው ነበር ።

"በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በእሥር ቤት ሳለን ፣ በኢትዮጵያ ፷ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ላይ የተፈጸመው ኢሰብአዊ እና ኢፍትሐዊ የሆነ የግፍ ግድያ ከመፈጸሙ በፊት ከሐረርጌ ፫ኛ ክፍለ ጦር የእስር ቤቱን አያያዝ ለማጥናት የተሰየመው ቡድን እስር ቤቱን ጎብኝቶ ላቀረበው ጥያቄ አቶ ተገኝ የተሻወርቅ የእሥር ቤቱን ኢሰብአዊ አያያዝ በዝርዝር ካስረዳ በኋላ አንድ የማይረሳ ትምህርታዊ ማስጠንቀቂያ እንዲህ ሲል ሰጥቷል ። "እናንተ ወታደሮች ይኸ ሁሉ ግፍ የሚሠራው በእናንተ ስም ነው ። እኛ የሚደርስብንን በትዕግሥት እንቀበላለን ። እናንተም ከፍርድ የምታመልጡ አይምሰላችሁ" ብሏል ። ሟቹ በዚህ አቋሙ የራሱን ጽርሐ ባሕሪይ ከማሳየቱም በቀር ለአገር አገልግሎት ወደፊት ለሚነሳው ትውልድ ሕይወቱን መስዋዕት እንዲያደርግ የሚያዘጋጀው ነው ።

ክቡር አቶ ተገኝ የተሻወርቅ ሥራ በጀመሩ በ፲፪ ዓመታቸው ፣ በተወለዱ በ፴፩ ዓመት በፋሺስቱ ጁንታ ከሌሎች ፶፱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር ለአጭር ጊዜ በቁጥጥር ሥር ከቆዩ በኋላ ካለፍርድ ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ተገድለዋል ።

ክቡር አቶ ተገኝ የተሻወርቅ ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፷ ዓ/ም ወ/ሮ ሶፊያ ይልማን በሕግ አግብተው ያሬድ ተገኝ የሚባል አንድ ወንድ ልጅ ተክተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ልጅ ኃይሉ ደስታ

## 1922-1967



ልጅ ኃይሉ ደስታ በመከላከያ ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስ ትርነት በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ም/ፕሬዚ ዳንትነት ። እንዲሁም በተለያዩ መ/ቤቶች በከፍተኛ ኃላፊ ነት ለ፳፮ ዓመታት አገራቸውን በቅንነትና በታማኝ ነት ያገለገሉ ሀገር ወዳድ ነበሩ ።

የልዑል ራስ ካሣ የልጅ ልጅ የነበሩት ልጅ ኃይሉ ደስታ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ/ም በሸዋ ክ/ሀገር በሰላሌ አውራጃ ፍቼ ከተማ ተወለዱ ። አባታቸው ደጃዝማች ደስታ ተሰማ ፣ እናታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ ይባላሉ ።

ልጅ ኃይሉ ደስታ በልዑል ራስ ካሣ ቤት የአማርኛንና የግዕዝን ትምህርት እንደጀመሩ ፋሺ ስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረሩ ከአያታቸው ከልዑል ራስ ካሣ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ ጋር ገና የስድስት ዓመት ሕፃን ሳሉ ወደ ኢየሩሳሌም ተሰደዱ ።

ኢየሩሳሌም በነበሩበት ጊዜ ቀደም ሲል ጀምረውት ከነበረው የአማርኛ ትምህርት ጋር የአረብኛንና የእንግሊዝኛን ቋንቋ ሲማሩ ቆዩ ። በኋላም ከእናታቸው ጋር ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይኖሩ በነበረበት ባዝ በተባለው ቦታ ከን ጉሣውያን ቤተሰብ ልጆች ጋር ትምህርታቸውን ቀጠሉ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው የእንግሊዝኛ ፣ የፈረንሳይኛና የአረ ብኛ ትምህርት ተማሩ ። የኢትዮጵያ ነፃነት ሲመ ለስ በኢየሩሳሌም ከነበሩት የኢትዮጵያ ስደተኞች

www.ethipianorthodox.org

# ፊታውራሪ
# አምዴ አበራ
## 1925-1967

ፊታውራሪ አምዴ አበራ ከክቡር ደጃዝማች አበራ ካሣና ከክብርት ወይዘሪት ሆይ ከበደች ሥዩም ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ/ም አዲስ አበባ እንጦጦ ገነተ ኢየሱስ ተወለዱ ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም አገራችን በኢጣሊያ ፋሺስት ጦር ተወራ አባታቸው ክቡር ደጃዝማች አበራ ካሣ ከወንድማቸው ከክቡር ደጃዝማች አስፋ ወሰን ካሣ ጋር ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ/ም በጠላት እንደተገደሉ ፣ የፊታውራሪ አምዴ አበራ እናት ክብርት ወይዘሪት ሆይ ከበደች ሥዩም በእንሳሮና በመርሐቤቴ እየተዘዋወሩ ከጠላት ጋር ሲዋጉ የሶስት ዓመት ሕፃን የነበሩት አምዴ አበራ ሰላሌ ውስጥ ጎሐ ጽዮን ጣየ ከተባለ ሥፍራ በአንድ ግለሰብ ቤት እንዲቆዩ ተደረገ ።

በዚህ ሥፍራ እንዳሉ ከሞግዚታቸው ጋር በፋሺስት ኢጣልያ እጅ ወድቀው መጀመሪያ ኢጣሊያን አገር አዚናራ እሥር ቤት ተወሰዱ ። የእናታቸው አባት ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻና ባለቤታቸው ልዕልት አፀደ አስፋው በኢጣሊያ ፋሺስት ቁጥጥር ሥር ውለው ወደ ሮማ ተወስደው ስለነበር ሕፃኑ ከእነሱ ጋር አምስቱን የኢጣልያ ፋሺስት የመከራ ዘመን እዚያ እንዲያሳልፉ ሆነ ።

ጠላት ከኢትዮጵያ ተባሮ በስደት ከቆዩት አያታቸው ከልዑል ራስ ካሣ ኃይሉና ከእናታቸው ከስመ ጥሩዋ የአርበኞች ጦር መሪ ከክብርት ወይዘሪት ሆይ ከበደች ሥዩም ጋር ሲገናኙ ፊታ/ አምዴ ገና የስምንት ዓመት ልጅ ነበሩ ።

ፊታውራሪ አምዴ አበራ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አዲስ አበባ በተፈሪ መኰንን ት/ቤትና



ፊታውራሪ አምዴ አበራ ከተመደቡበት የመንግሥት ሥራ ይልቅ ሀገራቸውን በበለጠ ለመጥቀም እንደሚችሉ ባመኑበት በእንስሳት እርባታ ሥራ ተሰማርተው ከፍተኛ አርአያነት ያለው ተግባር የፈፀሙ ሀገር ወዳድ ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

አቃቂ አድቬንቲስት ሚሲዮን ትምህርት ቤት አጠናቀቁ ። የሁለተኛ ደረጃን ትምህርት እንግሊዝ አገር በሚገኘው ባይብል ኮሌጅ አፍ ሳውዝ ዌይል ዝ ከጨረሱ በኋላ ፣ እዚያው እንግሊዝ አገር በሚ ገኘው በስመ ጥሩው ሳንድረኸርስት ሮያል ሚሊ ቴሪ አካዳሚ ገብተው የሚሰጠውን ከፍተኛ የጦር ትምህርት በመከታተል በምክትል መቶ አለቃነት በተለይ በታንከኝነት ሙያ ተመረቁ ።

ፊታውራሪ አምዴ አበራ ከውጭ አገር ትምህ ርታቸውን ጨርሰው በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም ወደ ሀገራ ቸው እንደተመለሱ በመኰንንነት መነሻ ማዕረግ በመከላከያ ሚኒስቴር ተመደቡ ። በምድር ጦር አንደኛ ክፍለ ጦርና ቀጥሎም በሆለታ ገነት ጦር አካዳሚ ከፍተኛ የጦር መኰንኖችን የሙያ መሻ ሻያ ኮርስ ሲያስተምሩ ቆዩ ። በዚህ ሙያ በአሳዩት ንቃትና ታታሪነት ፣ በአገር አስተዳዳሪነት ቢመ ደቡ የበለጠ እንደሚጠቅሙ ስለታመነበት በ፲፱፻ ፴፱ ዓ/ም በፊታውራሪነት ማዕረግ የመርሐቤቴና የሰላሌ አውራጃ ገዥ ሆነው እስከ ፲፱፻፵፪ ዓ/ም አገለገሉ ።

ፊታውራሪ አምዴ አበራ በጦር ሠራዊትና በአገር አስተዳደር ሲሰሩ በገጠር ያለውን ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ተገንዝበው ኖሮ በወቅቱ ከተሰማሩ በት የአገረ ገዥነት ከሚሰጡት አገልግሎት ይልቅ በገጠር ካለው ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው የግል ሥራ እየሠሩ የሚያውቁትን ቢያሳውቁ ለሀገርና ለወገን ይበልጥ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ እም ነት ስላደረባቸው የአገረ ገዥነት ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀቁ ።

በ፲፱፻፵፪ ዓ/ም አነስተኛ ካፒታል ይዘው በዚያው በሰላሌ አውራጃ ፍቼ ከተማ አጠገብ አምስት ሄክታር ውሃ ካብ መሬት ገዝተውና አራት ጋሻ መሬት ከባለስርት ተኮናትረው የአካባቢው ገበሬዎች ለወተት ከሚጠቀሙባቸው ከብቶች ጊደሮች ከዝተው ሥራ ጀመሩ ። እነዚህን ጊደ ሮች ከምርጥ ዘር ኮርማዎች ጋር በማዳቀል ባገ ኙት ጥሩ ውጤት ተበራትተው ከቀንድ ከብት እርባታ ሌላ ምርጥ ዘር በጎችንና ፈረሶችን ማር ባት ጀምረው ነበር ። ይኸንኑ ልምዳቸውን ለአካ ባቢው ገበሬ ለማካፈል በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት ምርጥ ዘር ኮርማዎችን በማሠራጨትና ምክር በመስጠት ገበሬው ዘመናዊ የእርባታ ዘዴ ቀስሞ የበለጠ ምርቱን አሳድጎ እንዲጠቀም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ።

ፊታውራሪ አምዴ አበራ የጀመሩት እንስ ሳት ርቢ ሥራ ከእንስሳት እርባታ ኤክስፐርቶችና ከመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ከፍተኛ አድናቆት አግኝቷል ። ሥራው ከፍተኛ ወጭ ፣ ብዙ ድካ ምና እለታዊ ትጋት የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ በማና ቸውም በኩል ጉድለት ሳያሳዩ ያስፋፉት የእንስ ሳት እርባታ ሥራ በአርአያነትም ሆነ በምርቱ ውጤት የአገራችንን የእርሻ ሀብት የሚያሻሽል ሆኖ በመገኘቱ ለብሔራዊ ሽልማት ብቁ ስለ አደረጋቸው በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የወርቅ ኒሻንና ዲፕሎማ ከአሥር ሺህ ብር ጋር ተሸልመዋል ።

ፊታውራሪ አምዴ አበራ በእንስሳት እርባታ ላስገኙት የላቀ ውጤትና ለአካባቢው ገበሬ ላበረ ከቱት አርአያ ሽልማቱን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ሲቀበሉ በአደረጉት ንግግር "የተሠ ማራሁበት ሥራ ከፍተኛ ድካምና ረጅም ጊዜን ስለሚጠይቅ እኔ ሠርቼ እጨርሰዋለሁ በማለት ሳይሆን ያለውን ችግር ትንሽ እንኳ ቀርፌ ለት ውልድ ለማስተላለፍ ኢትዮጵያዊነቴና ምኞቴ አስገድዶኝ ነው" ካሉ በኋላ "ሥራውን እያሻ ሻልሁ ከማስፋፋት አላቋርጥም" ብለው ታታሪ ነታቸውን ያረጋገጡ ሰው ነበሩ ።

ፊታውራሪ አምዴ አበራ በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም ወይ ዘሪት ብሩክታዊት ከፍሌን በሥርዓተ ተክሊል አግብተው ሲኖሩ ባለቤታቸው ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ልጅ ሳይወልዱ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩዋቸውም የገቡትን ቃል ኪዳን ጠብቀው እስከ ዕለተ ሞታቸው ሌላ ሚስት ሳያገቡ ኖሩ ።

ፊታውራሪ አምዴ አበራ የአገረ ገዥነቱን ሥራ ትተው የግል ልማት አቋቁመው በምሳሌነ ቱና በውጤቱ ለአገር የሚጠቅም ሥራ እየሠሩ ፲፩ ዓመት ከቆዩበት ሥራ ላይ ፋሺስት ደርግ ነሐሴ ወር ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በቁጥጥር ሥር ከአዋለ ቸው በኋላ ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም አገራች ውን በተለያየ መስክ ከአገለገሉና የማይረሳ ውለታ ከነበራቸው ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር ያለ ፍርድ በጭካኔ ተገድለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ፊታውራሪ ታደሰ እንቁሥላሴ

# 1923-1967

ፊታውራሪ ታደሰ እንቁሥላሴ ስንዳኝ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ተወለዱ ። በአርበኝነት ከታወቁት ወንድሞቻቸው ጋር አድገው የመጀመሪያ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርት ተምረዋል ።

ፊታውራሪ ታደሰ ሥራ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በመንግሥት መሥሪያ ቤትና በአውራጃ አስተዳዳሪነት ለ፳፭ ዓመታት አገልግለዋል ። ከ፲፱፻፵፩ እስከ ፲፱፻፶፩ ዓ/ም በገንዘብ ሚኒስቴር ፣ ከ፲፱፻፶፩ እስከ ፲፱፻፶፱ የባሌ ጠቅላይ ግዛት ዋና ፀሐፊ ፣ ከ፲፱፻፶፱ እስከ ፲፱፻፷፪ የዋሽ ጠ/ ግዛት የፀጥታ ሹም ፣ ከ፲፱፻፷፪ እስከ ፲፱፻፷፮ በከፋ ጠ/ ግዛት የሊሙ አውራጃ ገዥ ሆነው አገራቸውን አገልግለዋል ።

ፊታውራሪ ታደሰ እንቁሥላሴ በወታደራዊ የደርግ መንግሥት በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ተገድለዋል ።

ፊታውራሪ ታደሰ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነበሩ ።



ለ፳፭ ዓመታት አገራቸውን በታታሪነት ያገለገሉት ፊታውራሪ ታደሰ እንቁሥላሴ ከ፲፱፻፷፪ እስከ ፲፱፻፷፮ በከፋ ጠ/ግዛት የሊሙ አውራጃ ገዥ ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ፊታውራሪ
# ደምሴ አላምረው

# 1919 - 1967

ፊታ/ ደምሴ አላምረው ከአባታቸው ከደጃዝማች አላምረው ቢሰውርና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘውዲቱ ይልማ በ፲፱፻፲፱ ዓ/ም በጎጃም ጠቅላይ ግዛት በአጋምና ጊዮርጊስ ቀበሌ ተወለዱ ።

በወቅቱ ወግና ሥርዓት መሠረት የአማርኛን ትምህርት በመማር ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም የጣሊያን ፋሺስት አገራችንን በመውረሩ ትምህርታቸውን አቋርጠው በለጋ ዕድሜያቸው ከአርበኞች ጋር ወደ ጫካ ገቡ ። በዚህን ጊዜ ጠላትን በመዋጋት ባደረጉት ተጋድሎ የፊታውራሪነት ሹመት ከማግኘታቸውም በላይ ፊታውራሪ ዲጋ የሚል የጦር ሜዳ የቅጽል ስምም ተሰጥቷቸዋል ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ወራሪው የኢጣሊያን ጦር ተሸንፎ የኢትዮጵያ ነፃነት ሲከበር በመንግሥት "ሌባ አዳኝ" ተብለው ዘራፊዎችንና ቀማኞችን እንዲቆጣጠሩ በጎጃም ተሾሙ ። በዚያን ጊዜ ነበር ፊታውራሪ ደምሴ አላምረው በጎጃም ሕዝብ ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ሊታወቁ የበቁት ። ያን ጊዜም ነበር እረኞች በየሜዳው ፤

ደምሴ አላምረው የሌባው መጋኛ
አንተ ደከምክ እንጂ በሬ እንቅልፉን ተኛ

እያሉ ይዘፍኑላቸው የነበር ።

ይህንን መንግሥት የጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት በመወጣታቸው ወዲያውኑ የወረዳ ገዥ ፣ ብዙም ሳይቆዩ የአውራጃ ገዥ በመሆን በተለያዩ አውራጃዎች አገልግለዋል ። በመጨረሻም በኢሉባቦር ጠ/ ግዛት የጎሬ አውራጃ ገዥ ነበሩ ።

ፊታውራሪ ደምሴ አላምረው በተወለዱ በ፵፰ ዓመታቸው ከሌሎች ፶፱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ በፋሺስቱ ደርግ ካለፍርድ በግፍ ተገድለዋል ።

ፊታ/ ደምሴ አላምረው ባለትዳርና የአሥራ ሶስት ልጆች አባት ነበሩ ።



ፊታውራሪ ደምሴ አላምረው በአርበኝነትና በአውራጃ ገዥነት አገራቸውን ለ፳፱ ዓመታት ያገለገሉ አርበኛ ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org



www.ethipianorthodox.org

# አቶ ኃይሉ ተክሉ

## 1932-1967

አቶ ኃይሉ ተክሉ ከአባታቸው ከአቶ ተክሉ ይታጠቁና ከእናታቸው ከወ/ሮ እህትብሎ ገብረ ኢየሱስ ሚያዝያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ/ም በመናገሻ ማርያም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በጊዜው ይሰጥ የነበረውን የአማርኛ ትምህርት በመናገሻ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲከታተሉ ቆዩ ። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአሁኑ ጊዜ መድኃኔ ዓለም ትምህርት ቤት በሚባለው ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ በቀድሞው ንግድ ሥራ ት/ቤት ገብተው ይሰጥ የነበረውን ትምህርት አጠናቀዋል ።

ትምህርታቸውን እንደጨረሱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተቀጥረው እስከ ታሠሩበት ጊዜ ድረስ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሲያገለግሉ ቆይተዋል ።

አቶ ኃይሉ ተክሉ ቀደም ሲል በመንግሥት በተመሰረተባቸው የወንጀል ክስ ለብር ፪ ሺህ (ሁለት ሺህ) የሚበቃ ዋስ ጠርተው ተለቅቀው በቀጠሮ ላይ እንዳሉ የወታደራዊው ደርግ ስልጣን ጨብጦ ያለ በቂ ምክንያት ግለሰቦችን ከቤታቸው እየወሰደ ያስር በነበረበት ወቅት በጥቅምት ወር ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከቤታቸው ተወስደው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከ፶፱ ባለሥልጣኖች ጋር ያለፍርድ በግፍ ተገድለዋል ።



አቶ ኃይሉ ተክሉ ትምህርታቸውን በቀድሞ ንግድ ሥራ ት/ቤት አጠናቀው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቀጥረው በአገር ውስጥና በውጭ አገር አገልግለዋል ።


www.ethipianorthodox.org

ሀገር መምህራን ከሞላ ጎደል በ፲፱፻፳፰ በኢትዮ ጵያውያን አሰልጣኞች ሊተኩ በቅቷል ። የሠራ ዊቱም ብዛትና የጦሩ ድርጅት ከግብፅ ቀጥሎ በቀይ ባሕር ላይ ተወዳዳሪ አልነበረውም ። የባሕር ኃይሉ መኰንኖች ኮሌጅ እስከ የበታች ሹማምንት ማሰልጠኛ እንዲሁም ከጦር ስልት ስልጠና እስከ የባሕር ሀብት ልማት በቂ ትምህርት መስጠት የሚያስችል ሙሉ ድርጅት እንዲኖረው ተደር ጓል ። ከዚህም በላይ የባሕር ኃይሉ ለማናቸውም ዓይነት መርከቦች መጠገኛ በመሣሪያም ሆነ በሰው ኃይል የተሟላ ድርጅት ነበረው ። ዘመናዊ የአሠራር ሥልት በመዘርጋትም ለባሕር ኃይሉና ለሀገሪቱም የሚበጅ ሥርዓት እንዲለምድ አድር ገዋል ። ባለሙያዎችን በመምረጥና በተገቢው ቦታ ላይ በማሠራት በነበራቸው ከፍተኛ ተሰጥኦና ብስለት የባሕር ኃይሉን እድገት አፋጥነዋል ፤ ስመ ጥርም እንዲሆን ረድተዋል ።

"ቀዝቃዛ ጦርነት" በመባል ይታወቅ የነበ ረው የሁለቱ ኃያላን መንግሥታት ፍጥጫ ተጋግሎ በነበረበት ወቅት ፣ ከባላንጣዎቹ ኃያላን መንግ ሥታት ብቻ ሳይሆን ከአያሌ ሀገሮች ጋር ሀገራቸ ውንና የባሕር ኃይሉን ሳያሰልሱ ያስተዋወቁ ታላቅ ዲፕሎማትም ነበሩ ።

በየጊዜው በሶቭዬት ህብረት ፣ በእንግሊዝ ፣ በአሜሪካ ፣ በፈረንሳይ ፣ በኢጣሊያና በፖርቱጋል ፣ ወዘተ - - - በሚደረጉት ዓመታዊ የባሕር ኃይል ቀናት ላይ ሀገራቸውን ወክለው በመገኘት ጠቃሚ ልምዶችን ቀስመዋል ። በአንፃሩ ሪር አድሚራል እስክንድር የኢትዮጵያን ዓመታዊ የባሕር ኃይል ቀን ለተከታታይ ፲፰ ዓመታት በማዘጋጀት በወ ቅቱ አሉ የሚባሉት የባሕር ኃያላን አገሮች ታላላቅ የጦር መርከቦች ፣ ከፍተኛ የባሕር ኃይል መኰ ንኖችና የሀገር መሪዎች በተገኙበትና በተሳተፉ በት የውጊያ ልምምድ በማሳየት ቁጥሩ ውስን ግን የሙያ ብቃቱ የላቀ የባሕር ኃይል ሠራዊት የገ ነቡ ፣ ኢትዮጵያም በቀይ ባሕር ላይ ያላት ባለቤት ነት በተግባር እንዲታወቅና እንዲከበር ያደረጉ ታዋቂ አዛዥ ነበሩ ። በዚህም ምክንያት ኢትዮ ጵያ ከምን ጊዜውም በላይ በቀይ ባሕር ላይና በአካባቢው አገሮች ዘንድ ሊኖራት የሚገባውና የሚችለው ፖለቲካዊና እስትራቴጂክ ጠቀሜታ ግንዛቤ ከማግኘቱም በላይ ተግባራዊነቱም ተረ ጋግጦ ነበር ።

ከዚህም በተጨማሪ እጅግ አወዛጋቢና አሻሚ በሆነውና ድርድሩም እስከ አሁን ውሳኔ ባላገኘው የባሕር ሕግና የባሕር ሀብት አጠቃቀም" ጉባኤ ላይ በተለያዩ ዓመታት ኢትዮጵያን ወክለው የተላኩትን ዴሌጌሽኖች በመምራትና ሥራቸው ንም በቅርብ በመከታተል አስፈላጊውን ድጋ ፍና አመራር ሲሰጡ ቆይተዋል ። በዚህ አኳያ የአገ ሪቱ ዘላቂ ጥቅም የሚጠበቅበትን አቋም በማዳበር ያልተቆጠበ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ክቡር አድሚራል እስክንድር ከሀገራቸው ቋንቋ ሌላ በእንግሊዝኛ ፣ በፈረንሳይኛና በኢጣል ያንኛ በነበራቸው ከፍተኛ ችሎታ ፣ ከሰው ጋር በቀላሉ የመተዋወቅና የመግባባት ባሕሪ በተለ ይም ለሀገር ልማትና እድገት በነበራቸው በጎ ምኞትና ጉጉት እንዲሁም ለመንግሥታቸውና ለንጉሠ ነገሥታቸው በነበራቸው ሙሉ ታማኝ ነትና ታዛዥነት የመንግሥታትና የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ መልእክተኛ በመሆን በአምስቱም ክፍላተ ዓለማት አጫጭር የሥራ ጉብኝት አድርገው በልዩ ልዩ መስክ የወዳጅ ሀገሮችን ድጋፍ ለማስ ገኘት ችለዋል ።

በግል ኑሯቸውም ፈሪሐ እግዚአብሔር ያደ ረባቸው ፣ በሥራ ቦታ ታታሪ ፣ ዲሲፕሊን አክ ባሪና ቂም በቀል የማያውቁ ፣ በሥራ ጓደኞቻቸው ዘንድ የተወደዱና የተከበሩ ናቸው ።

አድሚራሉ በወታደራዊና በሲቪል መስኮች ለሀገራቸው ላበረከቱት የላቀ ተግባር በየጊዜው በየደረጃው ከመቶ አለቅነት ፣ ኮማንደርነት ፣ ከዚያም ኮሞዶርነትና ሪር አድሚራልነት ማዕረግ በግርማዊ ጃንሆይ ከመሾማቸውም በላይ የተለያዩ ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ተሸልመዋል ። ከዚህም በላይ በሥራ አጋጣሚ ከጎበኟቸው ሀገሮች መሪ ዎች ማለትም ከዩጎዝላቪያ ፣ ከኢጣሊያ ፣ ከፈረን ሳይ ፣ ከእንግሊዝ ፣ ከሶቪዬት ሕብረት ፣ ከሕንድ ከታይላንድ ፣ ከአውስትራሊያ ፣ ከፖርቱጋል ፣ ወዘተ - - - ከፍተኛ ምስጋና ፣ ሜዳሊያዎችና ብርቅ ሽልማቶች አግኝተዋል ።

ምንም እንኳን ሪር አድሚራል እስክንድር የየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ወታደራዊ እንቅስቃሴ ሲጀ መር ከኢትዮጵያ ውጭ የመሆን ዕድል የነበራቸው ቢሆንም ለሀገራቸውና ለቤተሰባቸው በነበራቸው ፍቅር ፣ ለመንግሥታቸውና ለንጉሠ ነገሥታቸው በነበራቸው ታማኝነትና ሙሉ እምነት እንዲሁም በሥራ ሪኮርዳቸውና በራሳቸው ንጽሕና በመተ ማመን የሀገር ውስጥ ሁኔታ አስተማማኝ ፣ የራሳ ቸውም ዕጣ ግልጽ በአልነበረበት ወቅት በገዛ ፈቃዳቸው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት እጃቸውን ሰጥተዋል ።

ሆኖም ፋሺስታዊው ወታደራዊው ደርግ "ለምርመራ" ብሎ የሀገሪቱን ከፍተኛ ባለሥል ጣኖች አሰባስቦ እስር ቤት አጉሮ ካቆያቸው በኋላ ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ያላንዳች ፍርድ ፷ ባለሥልጣኖችን በግፍ ሲገድሉ አድሚራል እስክ ንድርም በተወለዱ በ፶ ዓመታቸው "ልጅም እንደ አባት" እንዲሉ በሰማዕታትነት ተሰው ተዋል ።

በአሁኑ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ ልዑላን ቤተሰብ ፣ ዘመድ ወዳጅና የአዲስ አበባ ሕዝብ እንዲሁም የውጭ አገር እንግዶች በተገኙበት አጽማቸው ከሌሎች ፷፯ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በድብቅ ከተቀበረበት ተቆፍሮ ወጥቶ በቅድ ስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀው የመታ ሰቢያ ሐውልት በክብር እንዲቀመጥ ተደርጓል ።

ሪር አድሚራል እስክንድር ደስታ ወ/ሮ ሣራ አማኑኤልን በሕግ አግብተው ነዓሚ እስንክ ድር የምትባል ሴት ልጅ ተክተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌ/ጄኔራል ድረሴ ዱባለ

## 1911-1967

ክቡር ጄኔራል ድረሴ ዱባለ በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ጨርጨር አውራጃ ቁኒ ወረዳ በዴሳ ከተማ ህዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፲፩ ዓ/ም ተወለዱ ። አባት አቶ ዱባለ ወልደአማኑኤል ፣ እናት ወ/ሮ ላቀች ይልማ ይባላሉ ።

ድረሴ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ አያታቸው ከተከሉት ቄስ ትምህርት ቤት ወቢ ማርያም ደብር ይገባሉ ። ፊደል በቆጠሩ በመንፈቅ ዳዊት ይደግሙና በወላጆቻቸው ይሸለማሉ ፤ እናት የአንገት ጌጥ ፣ አባት የእጅ ጠባብ ይገዙላቸዋል ። ድረሴ ካህን ለመሆን ቅኔና ዜማ ለመማር ፍላጎት ያድርባቸዋል ። ሆኖም የአጋጣሚ ጉዳይ ይሆንና አሰበ ተፈሪ መንግሥት ት/ቤት እንዲገቡ ይደረጋል ።

እዚያም ድረሴ ትጉህ ተማሪ ሆኑ ፤ በክፍል ጥሩ ውጤት በማምጣት ይሸለማሉ ፤ ከትምህርት ውጭ በቲያትርም ተሳትፎ ያደርጋሉ ።

ፋሺስት ኢጣልያ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ኢትዮጵያን ሲወር ድረሴ ከጓደኞቻቸው ጋር በበዴሳ እየተዘዋወሩ በትምህርት ቤት ስለሀገር ፍቅር የተነገራቸውን ሁሉ ማስረዳት ገቡ ። ወታደሩ ወደ አጋዴን ሲዘምት ባቡር ጣቢያ እየጠበቁ የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር እየዘመሩ ማበረታታት ቀጠሉ ። ድረሴ ከሁለት ጓደኞቻቸው ጋር ከቀኛዝማች ዋጋዬ ዋልተንጉሥ ጦር ሠራዊት ጋር ጨርጨር ውስጥ ይቀላቀሉና ባሌ ይዘምታሉ ። ጠላት በማየሉና ሠራዊቱ እልቂት ስለደረሰበት ይበተናል ።

ድረሴ ከፊ/ በዕደማርያም ጦር ጋር ይደባለቁና ወደ እንግሊዝ ሱማሌ ለመግባት ጉዞ ሲደረግ ሠራዊቱ ጠላት እጅ ይወድቅና ይማረካሉ ። ድረሴም አፍደም ተወስደው ይታሰራሉ ። ከአንድ ዓመት ከመንፈቅ እሥራት በኋላ ይለቀቃሉ ።

ፋሺስት ኢጣሊያ በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ከኢትዮጵያ ሲባረር ድረሴ አሰበ ተፈሪ መንግሥት ት/ቤት የተማሩት እንግሊዝኛ ይጠቅማቸውና ሐረርጌ ለገባው የእንግሊዝ ጦር አስተርጓሚ ሆነው ይቀጠራሉ ። ከዚያም ጥቂት ገንዘብ እንዳገኙ ወደ በዴሳ ይመለሱና እናታቸውንና ወንድማቸውን በሕይወት ያገኛሉ ። ትንሽ እንደሰነበቱ በ፲፱፻፴፬ ዓ/ም አዲስ አበባ ይመጡና ከሶስተኛ ሻለቃ ጦር ሰፈር በሲቪልነት አስተርጓሚ ሆነው ይቀጠራሉ ። ድረሴ ምኞታቸው ወታደር መሆን ኖሮ ለእንግሊዛዊ የቅርብ አለቃቸው ስለፍላጎታቸው ያስረዳሉ ። እሱም እዚያው ቢቆዩ የውትድርና ትምህርት ማግኘት እንደሚችሉ ይነግራቸዋል ። እሳቸውም ምክሩን ይቀበሉና ለሁለት ወራት የውትድርና ትምህርት እንዲማሩ ይደረጋል ።

ድረሴ በሥልጠናው አንደኛ ይወጡና በአሥር አለቅነት ማዕረግ ይመረቃሉ ። ከዚህ በኋላ ከሶስት ጓደኞቻቸው ጋር ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ይላኩና በ፲፱፻፴፭ ዓ/ም በምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ሰርተፊኬት ከግርማዊ ጃንሆይ ይቀበሉና ሥራ ይመደባሉ ። የድረሴ ትምህርት በዚህ አላበቃም ። በሥራ ላይ እንዳሉ በተለያዩ ጊዜያት ለከፍተኛ የጦር ትምህርት ተመርጠው ወደ አሜሪካን ተልከው ፎርት ሌበን ወርዝ ኮሌጅ የአዛዥነትና የጄኔራል እስታፍነት ትምህርት ከመከታተላቸውም በላይ በፎርት ናክስ ኬንታኪ በበላይ መኰንንነት ዲፕሎም ተቀብለዋል ። ለአያሌ ጊዜያት በውጭ አገር ልዩ ልዩ የጦር ድርጅቶችንና ተቋሞችን ጎብኝተው ከፍተኛ እውቀትም ቀስመዋል ።

ድረሴ ዱባለ በም/መቶ አለቅነት እንደተመረቁ ሥራ የጀመሩት በነገሌ ቦረና ሶስተኛ ሻለቃ ተመድበው ነበር ። እዚያም መጀመሪያ በመቶ አዛዥነት በተከታታይም በሻምበል አዛዥነት ፣ በትምህርት ክፍል መኰንንነትና የሻለቃው አዛዥ ረዳት መኰንን ሆነው ሠርተዋል ።



ለ፴፮ ዓመታት አገራቸውንና ጦሩን በቅንነትና በታማኝነት ያገለገሉት ክቡር ሌተና ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ለፖሊስ ሠራዊት እድገትና መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ መኰንን ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌ/ጀኔራል ደበበ ኃይለ ማርያም

## 1908-1967

ክቡር ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃ/ማርያም ከወ/ሮ አስካደች አጥናፍሰገድና ከቀኛዝማች ኃ/ማርያም ኢብሳ ኅዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፰ ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ በሀገራችን ባህል መሠረት በወላጆቻቸው ቤት ሆነው የአማርኛ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ገብተው በመማር ላይ እንዳሉ ፋሺስት ኢጣሊያ ሀገራችንን በግፍ በመውረሩ ትምህርታቸውን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን አቋርጠዋል ።

በ፲፱፻፳፱ ዓ/ም ጠላት አዲስ አበባ ሲገባ ጄኔራል ደበበ ከአርበኛው ከደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ጋር በሜታ አቦ አውራጃና ከዚያም ልዑል ራስ እምሩ ወደነበሩበት ወደ ጅማ ጠ/ ግዛት ሄደው በየቦታው በተደረገው ጦርነት ተካፍለዋል ።

የራስ እምሩ ጦር ሲፈታ በመጀመሪያ በግንደ በረት ፣ በኋላም በጎጃም በአርበኝነት ሲታገሉ ቆይተው ወደ ሱዳን ተሰደዱ ። ቀጥሎም ሱዳን ከኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ጦር ጋር በመቀላቀል ተዋግተው በድል አድራጊነት ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል ።

ክቡር ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃ/ማርያም በሀገር



ክቡር ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃ/ማርያም በአርበኝነት ፣ በአውራጃ አስተዳዳሪነት ፤ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የእልፍኝ አስከልካይነት ፣ በክብር ዘበኛ ዋና አዛዥነት ፣ በም/ጦር ዋና አዛዥነት እንዲሁም የኤርትራ ክ/ሀገር ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በመሆን ለ፴፫ ዓመታት ሀገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋ ።



www.ethipianorthodox.org

ውስጥና በውጭ ሀገር እንደሚከተለው ተምረዋል ።

— የብሔራዊ ትምህርት በወላጆቻቸው ቤት

— የአካዳሚክስ ትምህርት በተፈሪ መኰንን ት/ቤት

— የእጩ መኰንንነት ኮርስ በካርቱም (ሱዳን)

— የከፍተኛ አዛዥነት (የእስታፍ ኮሌጅ) ኮርስ በገነት ጦር ት/ቤት (ሆለታ)

ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃይለማርያም በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው ላገራቸው ላበረከቱት ቅንና ከፍተኛ አገልግሎት የሚከተለውን የማዕረግ እድገት አግኝተዋል ።

፩/ በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም በም/መቶ አለቅነት ማዕረግ የጦር ሚኒስቴር በጀት ኃላፊ ፤

፪/ በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም በሻምበልነት ማዕረግ በትግራይ ጠ/ግዛት የራስ አበበ አረጋይ ልዩ ፀሐፊና የጠ/ግዛቱ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ፤

፫/ ከ፲፱፻፴፰ እስከ ፲፱፻፵፩ በሻለቅነት ማዕረግ የቀድሞው ፩ኛ ክ/ጦር የአሁኑ ፬ኛ ክ/ጦር የአስተዳደር መኰንን

፬/ ከ፲፱፻፵፪ እስከ ፲፱፻፵፮ በሌ/ኮሎኔልነት ማዕረግ የድሬዳዋ ፣ ኢሳና ጉርጉራ አውራጃ ገዥ ፤

፭/ ከ፲፱፻፶ እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በሌ/ኮ ቀጥሎም በሙሉ ኮሎኔልነት ማዕረግ የግርማዊ ን ነ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ እልፍኝ አስከልካይ ፤

፮/ ከ፲፱፻፶፫ እስከ ፲፱፻፷፪ ዓ/ም በብ/ጄኔራልነት ቀጥሎም በሜ/ጄኔራልነት ማዕረግ የክብር ዘበኛ ጦር ዋና አዛዥ ፤

፯/ ከ፲፱፻፷፪ እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ/ም በሌ/ጄኔራልነት ማዕረግ የምድር ጦር ዋና አዛዥ ፤

፰/ ከ፲፱፻፷፬ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ድረስ የኤርትራ ጠ/ግዛት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በመሆን ሀገራቸውንና ወገናቸውን አገልግለዋል።

ክቡር ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃ/ማርያም ለሀገራቸው ላበረከቱት ከፍተኛ አገልግሎት ከ፶፩ ያላነሱ ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ከሀገር ውስጥና ከውጭ መንግሥታት የተሸለሙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

፩/ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የክብር ኮከብ ባለ አንገት ኮርዶን ፤

፪/ የዳግማዊ ምኒልክ ባለአንበል የመኰንንነት ደረጃ ፤

፫/ የአርበኝነት ሜዳይ ባለሁለት ዘንባባ ፤

፬/ የዳግማዊ ምኒልክ ረጅም ዘመን አገልግሎት የወርቅ ሜዳይ ፤

፭/ የእንግሊዝ መንግሥት በአፍሪካ የጦር ሜዳ ኒሻን ፤

ክቡር ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃይለማርያም በአርበኝነትና በከፍተኛ ሥልጣን ሀገራቸውን ያገለገሉ ቅን ፣ ርህሩህና እጅግ ደግ ሰው እንደነበሩ አብረዋቸው የሠሩና የሚያውቋቸው ሁሉ ይመሰክራሉ ።

ክቡር ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃይለ ማርያም በየካቲት ወር ፲፱፻፴፰ ዓ/ም ወ/ሮ ሶስና አበበ አረጋይን በሕግ አግብተው ሰባት ልጆች አፍርተዋል ።

ፋሺስቱ ወታደራዊ ደርግ በኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ ማግስት ከቁጥጥር ሥር አውሎ ሕዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ከገደላቸው የቀድሞ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አንዱ ክቡር ሌተና ጄኔራል ደበበ ኃይለማርያም ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌ/ጄኔራል
# አሰፋ ደምሴ

## 1911-1967

ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር በመዘጋጀት ላይ መሆኗ እንደታወቀ ፣ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዘመናዊ ትምህርት በመከታተል ላይ የነበሩት ሌፍተናንት ጄኔራል አሰፋ ደምሴ ለሀገሪቱ ወቅታዊ ጥያቄ ፈጣን መልስ ለመስጠት ታስቦ በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም ወደተቋቋመው የገነት ጦር ትምህርት ቤት ተመርጠው እንዲገቡ ተደረገ ።

በሀገራችን የመጀመሪያው በሆነው የእጩ መኰንንነት ትምህርት ተሳታፊ ከሆኑት ወጣት ኢትዮጵያውያን አንዱ ክቡር ሌ/ጄኔራል አሰፋ ደምሴ በገነት ጦር ትምህርት ቤት እንዳሉ ጠላት ሀገራችንን በመውረሩ ትምህርታቸውን አቋርጠው ከጀግናው ደጃዝማች ፍቅረማርያም አባ ተጫን ሠራዊት ጋር ተሰልፈው ለሀገራቸው ነፃነት ወረራን መከላከል ተያያዙ ። የደጃዝማች ፍቅረማርያም ጦር ሐምሌ ወር ፲፱፻፳፰ በሾላ በኩል አዲስ አበባ ገብቶ ጠላትን ለማጥቃት ባደረገው ሙከራ ጄኔራል አሰፋ ደምሴ ሶስት ቀናት ሙሉ በጀግንነት ተዋግተው ቆስለዋል ። በዚህ ውጊያ ወቅት ለፈጸሙት የጀግንነት ተጋድሎ ባለአንድ ዘንባባ የቅዱስ ጊዮርጊስ የጀብዱ ሜዳይ ተሸልመዋል ።



ክቡር ሌፍተናንት ጄኔራል አሰፋ ደምሴ በአርበኝነት ፣ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እልፍኝ አስከልካይነት እና በጦር አዛዥነት አገራቸውን ለ፴፱ ዓመታት ያገለገሉ መኰንን ነበሩ ።

ከዚያም የአርበኝነት ትግላቸውን በመቀጠል ወደ ሸንኮራ አምርተው ባልጭ በተባለ ቦታ ከጠላት ጋር በተደረገው ከባድ ጦርነት ላይ ከተካፈሉ በኋላ ወደ አርሲ ሄደው ከደጃዝማች በቀለ ሀብተ ገብርኤልና ከቀኛዝማች ኃይሌ አባ መርሳ ሰዎች ጋር ተቀላቅለው በከምባታ ፣ በኩሎ ኮንታ ፣ በጎፋና በባኮ እየተዘዋወሩ ሲዋጉ ቆይተው በ፲፱፻፳፱ ዓ/ም ወደ ኬንያ መሰደድ ግድ ሆነባቸው ። ኬንያ በስደት በቆዩበት ጊዜ በስደተኛው ሰፈር በልዩ ልዩ የአስተዳደር ሥራ አገልግለዋል ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአገር ውስጥ የነበረውን የአርበኞችን ትግልና በውጭ የሚገኘውን ሠራዊት ከእንግሊዝ ጦር ጋር አስተባብረው ፋሺስት ኢጣሊያን ከሀገራችን ለማስወጣት ባደረጉት ጥረት ቀደምት ትኩረት የተሰጠው በሶማሌ ላንድ፣ በጂቡቲና በኬንያ በስደት ከነበሩት ኢትዮጵያውያን መካከል መልምሎ ሱዳን አገር ሶባ በተባለ ሥፍራ በጊዜያዊነት በተቋቋመው የቅዱስ ጊዮርጊስ ጦር ትምህርት ቤት በጦር ስልት ማሰልጠን ነበር ። ከኬንያ ወደ ሱዳን ተዛውረው ጦር ትምህርት ቤቱ እንዲሰለጥኑ ከተደረጉት ወጣቶች አንዱ ሌ/ጄኔራል አሰፋ ደምሴ ነበሩ ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሚመራው የጊዲዮን የጦር ኃይል ከሱዳን እስከ መሐል አገር ባደረገው ረጅም ዘመቻ ክቡር ጄኔራል አሰፋ ደምሴ በግንባር ከተሰማራው የሶባው የጦር ትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን በድል አድራጊነት አዲስ አበባ በመግባት የኢትዮጵያን ነፃነት አብስረዋል ።



www.ethipianorthodox.org

በወረራው በአርበኝነት ፡ በነፃነቱ ትግል በአ ጥቂነት ፡ ከጦር ግንባር ያልተለዩት ጄኔራል አሰፋ ደምሴ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ያቋረጡትን የእጩ መኰንንነት ትምህርት በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ቀጥለው በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ከገነት ጦር ት/ቤት በም/መቶ አለቃነት ማዕረግ ተመረቁ ።

ከዚያም በተከታታይ ለአገራቸውና ለመንግሥታቸው በሰጡት አገልግሎት ከ፲፱፻፴፩ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፴፭ ዓ/ም የወታደር ፖሊስ አዛዥ ፡ ከ፲፱፻፴፭ እስከ ፲፱፻፴፰ አላማጣ የነበረው የ፲ኛ እግረኛ ሻለቃ አዛዥ ፡ ከ፲፱፻፴፰ እስከ ፲፱፻፵ አድዋ የነበረው ፮ኛ እግረኛ ሻለቃ አዛዥ ፡ ከ፲፱፻፵ እስከ ፲፱፻፶ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ም/ እልፍኝ አስከልካይ ነበሩ ። ከዚያም በ፲፱፻፶ ዓ/ም የአዲስ አበባ አውራጃ ገዥ ፡ በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም በመከላከያ ሚኒስቴር የድርጅት (ሎጂስቲክስ) መምሪያ ኃላፊ ፡ በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በደብረ ብርሃን የ፫ኛ እግረኛ ብርጌድ አዛዥ እንዲሁም በዚሁ ዓመት የግርማዊ ን. ነ. ቀ. ኃ. ሥ. ዋና የእልፍኝ አስከልካይ ሆነው ተሾሙ ።

በ፲፱፻፶ ዓ/ም የአዲስ አበባ ዙሪያ አውራጃ ገዥ በነበሩበት ጊዜ በተፍኪ የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ በአካባቢው ያለውን ሜዳ በማጥለቅለቁ በዚያ የነበረው ሕዝብ ቤቱና ንብረቱ በውኃ ስለ ተወሰደበት ለረጅም ቀናት እዚያው ከሕዝቡ ጋር በመቀመጥ የሕዝቡን ችግር እየተካፈሉ በመኖር ለታረዘና ንብረቱ ለተወሰደበት እንዲረዳ በማድረግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ክቡር ሌ/ ጄኔራል አሰፋ ደምሴ ከ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ከወጣት ዘመናቸው ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ለ፴፱ ዓመታት አገራቸውን ፡ ንጉሠ ነገሥታቸውንና የኢትዮጵያን ሕዝብ በአርበኝነት ፡ በጦር አዛዥነትና በተለያዩ የአስተዳደር ዘርፎች በማገልገል አኩሪ ተግባር ፈጽመዋል ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም የምክትል መቶ አለቃ የሆኑት አሰፋ ደምሴ በየጊዜው ባሳዩት ታታሪነትና የኃላፊነት ምግባር በ፲፱፻፴፩ ሻምበል ፡ በ፲፱፻፴፮ ሻለቃ ፡ በ፲፱፻፵፪ ሌ/ ኮሎኔል ፡ በ፲፱፻፶ ሙሉ ኮሎኔል ፡ በ፲፱፻፶፭ ብርጋዴር ጄኔራል ፡ በ፲፱፻፶፰ ሜጀር ጄኔራልና በ፲፱፻፷፫ ሌፍተናንት ጄኔራል ለመሆን በቅተዋል ። በተጨማሪ አያሌ የጦር ሜዳይ ሽልማቶችንና የክብር ኒሻኖችን ከአገር ውስጥና ከውጭ መንግሥታት አግኝተዋል ።

## የአገልግሎትና የጦር ሜዳይ ሽልማቶች

—የአንድ ዓመት የአርበኝነት ሜዳይ

—የቅዱስ ጊዮርጊስ ባለአንድ ዘንባባ የጀብዱ ሜዳይ

—የ፭ ዓመት የስደት መታሰቢያ ሜዳይ

—የድል ኮከብ ሜዳይ

—የ፳፭ ዓመት የጀብዱ መታሰቢያ ሜዳይ

—የዳግማዊ ምኒልክ የረጅም ዘመን አገልግሎት ሜዳይ

—የዳግማዊ ምኒልክ የ፲፭ ዓመት አገልግሎት ሜዳይ

—የእንግሊዞች የጦር ሜዳይ መታሰቢያ ሜዳይ

—የእንግሊዞች የአፍሪካ ስታር ሜዳይ

## የክብር ኒሻን ሽልማቶች

—የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ታላቅ ኮርዶን

—የዳግማዊ ምኒልክ ታላቅ መኰንን

—የኢትዮጵያ ክብር ኮከብ ታላቅ መኰንን

—የዳግማዊ ምኒልክ ኮማንደር (አዛዥ መኰንን)

—የኢትዮጵያ ክብር ኮከብ (አዛዥ መኰንን)

—የዳግማዊ ምኒልክ የመኰንን ደረጃ (ኦፊሰር)

—የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የመኰንን ደረጃ (ኦፊሰር)

ከእነዚህ በተጨማሪ ከኔዘርላንድ ፡ ከኢጣሊያን ፡ ከታይላንድ ፡ ከጆርዳን ፡ ከቤልጅግና ከስፔን መንግሥታት በጠቅላላው ስድስት ታላቅ ኮርዶን ኒሻኖች እንደዚሁም ከኖርዌ ፡ ከላይቤሪያ ፡ ከፖላንድ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ከሞሮኮ ፡ ከአይቮሪኮስት ፡ ከሴኔጋል ፡ ከኢንዶኔዥያ ፡ ከማሌዥያ ፡ ከሩማንያ ፡ ከማላጋሲ ፡ ከኮሪያ ፡ ከሱዳን ፡ ከጀርመን ፡ ከሊባኖስ ፡ ከካምቦዲያ ፡ ከሃይቲ ፡ በጠቅላላው ፳፫ (ሃያ ሶስት) የክብር ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

በከፋ ክፍለ ሀገር ሊሙኮሣ በተባለ ቦታ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፩ ዓ/ም ከፊታውራሪ ደምሴ አባውሌና ከወይዘሮ ማንያህልሻል ብሩ የተወለዱት ሌ/ ጄኔራል አሰፋ ደምሴ በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን የሕፃንነት ጊዜያቸውን ያሳለፉት በታላቁ ቤተ መንግሥት እንክብካቤ እየተደረገላቸው የአማርኛ ፡ የሥነ ሥርዓትና የሥነ ምግባር ትምህርት እየተከታተሉ ነበር ።

ክቡር ሌ/ጄ አሰፋ ደምሴ በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ በፋሺስቱ ወታደራዊ ደርግ በቁጥጥር ሥር ውለው በእሥር ቤት ከቆዩ በኋላ ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ካለፍርድ በጭካኔ ተገድለዋል ። ኃያሉ አምላክ ነፍሳቸውን ከጻድቃንና ከሰማዕታት ጋር እንዲያኖረው እንማጸናለን ።

ሌ/ጄኔራል አሰፋ ደምሴ ወ/ሮ አልማዝ መላኩን በሕግ አግብተው ሶስት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ልጆች አፍርተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌ/ጀኔራል አበበ ገመዳ

# 1909-1967



ክቡር ሌተና ጀኔራል አበበ ገመዳ የክብር ዘበኛ አዛዥ ፤ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዩ ኤታ ማጆር ሹም ፣ የተለያዩ ክፍለ ጦሮች አዛዥና የአጋዴን አስተዳዳሪ ሆነው ለ፵ ዓመታት አገራቸውን በታማኝነት ያገለገሉ መኰንን ነበሩ ።

ክቡር ሌ/ ጀኔራል አበበ ገመዳ ከአቶ ገመዳ አባታጠቅና ከወ/ሮ ንጋቷ ወልደ አረጋይ በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ልዩ ስሙ መንዲዳ በተባለ ሥፍራ በ፲፱፻፱ ዓ/ም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የአማርኛ ትምህርት አጠናቅቀው በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዘመናዊ ትምህርት በመማር ላይ ሳሉ ፣ አገራቸውን በውትድርና ሙያ ለማገልገል ወሰኑ ። በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም በጊዜው ተቋቁሞ በነበረው የክብር ዘበኛ ጦር ማሠልጠኛ ተቋም ተቀጥረው ይህንኑ ጦር ለማሰልጠን ለመጡት የቤልጂግ መኰንኖች አስተርጓሚ ሆኑ ። ከዚያም ወደ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ገብተው በምክትል መቶ ዕልቅና ማዕረግ ከተመረቁ በኋላ በውትድርና ሙያ አገልግሎታቸውን ቀጠሉ ።

የኢጣሊያን ፋሺስት አገራችንን በወረረበት ዘመን በክብር ዘበኛ ውስጥ ከነበሩት ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ስለአገራቸው ነፃነትና ስለወገናቸው ክብር አስፈላጊውን ግዳጅ ፈጽመዋል ።

ጠላት ከአገራችን ከተባረረ በኋላ በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በሻምበልነት ማዕረግ በ፲ኛው ሬጂመንት ውስጥ በመደልደል ሐረር ይገኝ የነበረውን ሬጂመንት በማቋቋም ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።



www.ethipianorthodox.org

በ፲፱፻፴፯ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ፩ኛ ክፍለ ጦር ተዛወሩ ። በኋላም ፬ኛ ክፍለ ጦር ተብሎ ይጠራ ከነበረው ክፍለ ጦሩ የአስተዳደር መኰንን ሆነው ሲሰሩ የሻለቅነት ማዕረግ አገኙ ።

በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር ትምህርት ቤት ተልከው በወቅቱ ይሰጥ የነበረውን የካዴት ማሰልጠኛ ኮርስ በ፩ኛነት በመፈጸም ከግርማዊነታቸው እጅ ሽልማት ተቀብለዋል ።

ከዚህ በኋላ የመምሪያ መኰንንነት ኮርስ ተከታትለው ትምህርቱን በሚገባ ፈጽመዋል ።

በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም የ፲፪ኛ ብርጌድ አዛዥ ሆነው ወደ አሥመራ ተዛውረው በማገልገል ላይ እንዳሉ የሌ/ኮሎኔልነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

በዚሁ አገልግሎታቸው ላይ እንዳሉ በአዲስ አበባ ጉምሩክ ውስጥ የሥራ ችግር በመፈጠሩ በረዳት ሚኒስትርነት ማዕረግ ወደዚህ መ/ቤት ተዛውረው ለተወሰነ ጊዜ ሥራውን ከሠሩ በኋላ በጥብቅ የክፍለ ጦር አዛዥነት ወደ አሥመራ ተመልሰው ሲያገለግሉ የኮሎኔልነት ማዕረግ አግኝተዋል ። በዚህ ሥራ ላይ እንዳሉ በካራ ቆሬ ግዛት ውስጥ አለመግባባት ስለተፈጠረ አበበ ገመዳ ተልከው ሕዝቡን በማስታረቅና ሰላም እንዲወርድ በማድረግ ከፍ ያለ ሚና ተጫውተዋል ። በኋላም ወደ አሥመራ ተመልሰው የብርጋዴር ጄኔራልነት ማዕረግ ተሰጥቷቸው የ፪ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው ቅን አገልግሎታቸውን ሲሰጡ ቆይተዋል ።

ክቡር ጄኔራል አበበ ገመዳ በእነዚህና በሌሎችም ችግሮች በተፈጠረባቸው ቦታዎች ተጠርተው ችግሩን በማስወገድ በሚፈጽሙት ተግባር አስተዋይና ወሳኝ አዛዥ መኰንን መሆናቸውን አረጋግጠዋል ።

ሌ/ጄኔራል አበበ ገመዳ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ለከፍተኛ የአዛዥነትና የመምሪያ መኰንንነት ትምህርት ወደ አሜሪካን አገር ተልከው ትምህርታቸውን አጠናቀው ከተመለሱ በኋላ የሜጄር ጄኔራልነት ማዕረግ አግኝተው የ፫ኛው ክፍለ ጦር አዛዥና የኦጋዴን አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ ።

በ፲፱፻፷ ዓ/ም በሌተና ጄኔራልነት ማዕረግ ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው የክብር ዘበኛ አዛዥና የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዩ ኤታ ማጆር ሹም በመሆን እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም አገልግለዋል ።

በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የወታደር እንቅስቃሴ ሲጀመር ዓላማው ለኢትዮጵያ የማይበጅ መሆኑን በመገንዘብ እንቅስቃሴውን ለማክሸፍ "እጄን አልሰጥም" በማለት ተቋቁመው በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ "ጥያቄያቸው በዳኝነት ይታያል ፤ እጅህን ስጥ" ብለው በማለት ስለላኩባቸው ለወታደራዊው ደርግ እጃቸውን ሊሰጡ በቅተዋል ።

ሌ/ጄኔራል አበበ ገመዳ በትምህርትና በውትድርና ለአዛዥነት አመራር ችሎታቸው በተሰጣቸው ከፍተኛ ዲፕሎምና ሌላ ከኢትዮጵያ መንግሥት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ተሸልመዋል ።

ሀ/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ባለ አንበል የአገልግሎት ደረጃ ኒሻን ፤

ለ/ የዳግማዊ ምኒልክ የፈረሰኛ የአገልግሎት ደረጃ ኒሻን ፤

ሐ/ የቅዱስ ጊዮርጊስ ባለ ፪ ዘንባባ ኒሻን ፤

መ/ የድል ኮከብ ኒሻን ፤

ሠ/ የዳግማዊ ምኒልክ የብርና የወርቅ ሜዳይ ኒሻን ፤

በተጨማሪም ከአሜሪካ ፣ ከእሥራኤል ፣ ከጀርመን ፣ ከእንግሊዝ ፣ ከፈረንሳይ ፣ ከዩጎዝላቪያና ናይጀሪያ የክብር ኒሻኖችና ሜዳዮች ተሸልመዋል ።

ሌ/ ጄኔራል አበበ ገመዳ ከረጅም ጊዜ ቅን አገልግሎት በኋላ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ስመጥር በሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ በተፈጸመው የወታደራዊው ደርግ አሰቃቂና የግፍ ግድያ የሞት ጽዋው ተካፋይ ሆነው ሕይወታቸውን አጥተዋል ።

ክቡር ሌ/ ጄኔራል አበበ ገመዳ ወ/ሮ ተናኘ ተገኜን በሕግ አግብተው ዶ/ር ልኡልሰገድ አበበ ፣ ወ/ሪት ሶፊያ አበበ ፣ ወ/ሪት ፀዳይ አበበና አቶ ነብዩ አበበን አፍርተዋል ።

ከ፲፱፻፵፱—፲፱፻፶፩ ዓ/ም በመከላከያ ሚኒስቴር ለሁለት ዓመታት የሚሰጠውን የሕግ ትምህርት ተከታትለው በዲፕሎማ ተመርቀዋል ። እንዲሁም ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችና ኅብረተሰቡን በሚጠቅሙ በጎ ተግባሮች ላይ ተሳትፈዋል ። ከእነዚህም በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተለያዩ ብሔረሰቦችን በማስተባበር ከዓለም ገና እስከ ወላሞ ሶዶ የመንገድ ሥራ ድርጅት በማቋቋምና በፕሬዚዳንትነት በመምራት ኅብረተሰቡ የነበረበትን ከፍተኛ የትራንስፖርት እጦት በማቃለል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም መጨረሻ ኒውዮርክ በሚገኘው ኮንስ ስኩል አስተባባሪነት በተዘጋጀው ትምህርታዊ ጉብኝት ላይ በዌስት ፖይት ፣ በዋሽንግተን በሚገኘው የአሜሪካን ጦር ሠራዊት በብሔራዊ ጦር ኮሌጅ የተካሄደውን ጥናታዊ ጉብኝት ተከታትለዋል ። ከ፲፱፻፶፮—፶፯ ዓ/ም ወደ ቀድሞው አገር ግዛት ሚኒስቴር ተዛውረው በረዳት ሚኒስትርነት ማዕረግ የፀጥታ ሚኒስትር በመሆን አገልግለዋል ። በተጨማሪም እስራኤል አገር ሄደው የመረጃ አጠንቃቀርና አስተዳደር ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ የፀጥታ ሚኒስቴር መ/ቤትን በአዲስና በዘመናዊ መልክ እንዲደራጅ አድርገዋል ።

በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም በብርጋዲየር ጄኔራልነት ማዕረግ የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ሆነው ተሹመው በመሥራት ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በኢራን እንዲሁም በ፲፱፻፷ ዓ/ም በሜጀር ጄኔራልነት ማዕረግ በጃፓን በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም በሌ/ጄኔራልነት ማዕረግ በካናዳ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም በእሥራኤል አገር የዓለም አቀፍ ፖሊስ ሠራዊት ስብሰባ ላይ ተካፍለው ሲመለሱ በጀርመን አገር ጥናታዊ ጉብኝት በማድረግ የፖሊስ ሠራዊቱ ከጀርመን እርዳታ የሚያገኝበትን መንገድ አመቻችተዋል ።

ከዚህም ጎን ለጎን በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም በጡረታ የተገለሉ የፖሊስ ባልደረቦችን በማስተባበር በሰቲትሁመራ የሰሊጥ እርሻ ላይ እንዲሳተፉ ማህበር በማቋቋም በአርበኝነት የተዋጉበትን ሥፍራ በልማት እንዲበለፅግ ተጠዋሪዎችም እራሳቸውን እንዲረዱ ዘመናዊ እርሻ በማቋቋም ለሀገራቸው ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም የተቋቋመውና በፕሬዚዳንትነት የሚመሩት ከዓለም ገና እስከ ወላሞ ሶዶ የመንገድ ሥራ ድርጅት ካለባቸው የመንግሥት ተደራራቢ ሥራ በተጨማሪ በቀጥታ በመሳተፍና በማስተባበር በሕዝብ መዋጮና የጉልበት ድጋፍ ብቻ የበጋና የክረምት መንገድ በማሠራት ኅብረተሰቡ ይደርስበት የነበረው ከፍተኛ የመገናኛ ችግር ከማቃለላቸውም በላይ የአውቶቡስ አክሲዮን ማህበር በማቋቋም ኅብረተሰቡ በልማቱም በኩል ከፍተኛ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ አድርገዋል ። በዚህም ተወዳዳሪ የሌለው ተግባር በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ድርጅቱን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት ተሸላሚ እንዲሆን አድርገውታል ።

ሌ/ ጄኔራል ይልማ ሺበሺ የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ሆነው በሠሩባቸው ዓመታት ያካበቱትን የረዥም ጊዜ የሥራ ልምድና እውቀት በሚገባ በሥራ ላይ በማዋል ኢትዮጵያ ዘመናዊ በሁሉም መስኩ የተደራጀ የፖሊስ ሠራዊት እንዲኖራት አድርገዋል ። በአዛዥነት ዘመናቸውም ዘመናዊ ኮሌጅ ፣ ዘመናዊ የፖሊስ ሠራዊት ተጨማሪ ሆስፒታል ከነሙሉ መገልገያ መሣሪያዎቹ ፣ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የፖሊስ አቪዬሽን በማቋቋም የአይሮፕላን አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል ። ከዚህም በተጨማሪ የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ በሞት በሚለዩበት ጊዜ የሟች ቤተሰቦችን የሚረዳ የሕይወት መረዳጃ ማህበር ወይም ኢንሹራንስ አቋቁመዋል ። ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ የፖሊስ ሠራዊቱን በሲቪል ሥራ ማለትም በልማት በማሳተፍ ለሀገራቸው የልማት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ክቡር ሌ/ጄኔራል ይልማ ሺበሺ በደርግ ተይዘው በግፍ ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር እስከተገደሉበት ድረስ ለአምስት ዓመታት በአርበኝነት ፣ ለ፴፩ ዓመታት በሲቪልና በውትድርና የአገልግሎት ዘመናቸው ከልጅነት እስከ እውቀት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በዱር በገደሉ ወጥተው ወርደው በውጭም ዓለም በተሳተፉባቸው ተግባራት ሁሉ የሀገራቸውን ክብርና ጥቅም ከሁሉም በላይ በማስቀደም በቅንነት አገልግለው ታሪክና ትውልድ የማይረሳው አኩሪ ተግባር ፈጽመዋል ። ለዚህም ቅንና ከፍተኛ አገልግሎታቸው ከሀገር ውስጥና ከውጭ መንግሥታት ከ፳፩ የሚበልጡ ልዩ ልዩ ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ተሸልመዋል ።

<u>ከሀገር ውስጥ ፡—</u>

ሀ/ የኢትዮጵያ የ፭ ዓመት የአርበኝነት ባለ አራት ዘንባባ ኒሻን ፤

ለ/ የኢትዮጵያ የድል ኮከብ ፤

ሐ/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ፤

መ/ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የክብር ኮርዶን ኒሻንና

ሠ/ የዳግማዊ ምኒልክ ፩ኛና ፪ኛ ደረጃ ኒሻን የሚገኙበት ሲሆን ፤

<u>ከውጭ ሀገር ፡—</u>

ከእንግሊዝ መንግሥት ፪ የሁለተኛ ዓለም ጦርነት የአፍሪካ ኮከብ ፩ኛና ፪ኛ ደረጃ ኒሻን ፣ እንዲሁም ከፈረንሣይ ፣ ከፖላንድ ፣ ከናይጄሪያ ፣ ከላይቤሪያ ፣ ከየመን ፣ ከዩጎዝላቪያ ፣ ከስዊድን ፣ ከአሜሪካን ፣ ከግብፅ ፣ ከኔዘርላንድ ፣ ከሳውዲ ዓረቢያ ፣ ከስዊዘርላንድ ፣ ከኬንያ ፣ ከጀርመን መንግሥታት ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ተሸልመዋል

ክቡር ሌ/ጄኔራል ይልማ ሺበሺ ባለትዳር ፣ የ፲ ልጆች እና ሶስት የልጅ ልጆች ባለፀጋ ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ሌ/ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ

## 1912-1967

ክቡር ሌተና ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓ/ም በኤርትራ ውስጥ መንደፈራ ከተማ ዓዲወግሪ ከአባታቸው አቶ ባይከዳኝ ወልደኪዳንና ከእናታቸው ወ/ሮ ሥላስ ተክሉ ተወለዱ ።

ሌ/ ጄኔራል ኃይሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በመንደፈራ ከተማ በሳንጆርጅ ትምህርት ቤት ከተማሩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በዘመኑ የሚሰጠውን ትምህርት ተከታተሉ ።

ሌ/ጄ ኃይሌ ባይከዳኝ በውትድርና ለማገልገል የተመለመሉት በ፲፱፻፴፬ ዓ/ም በ፳፪ ዓመታቸው ነበር ። የውትድርና ትምህርት ለመቀጠል በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት ወደ ገነት ቀ/ኃ/ ሥላሴ ጦር ትምህርት ቤት ተልከው የእጩ መኰንንነት ኮርስ እንዲሳተፉ ተደረገ ። በዚህ ጦር ትምህርት ቤት አንድ ዓመት ያህል የእጩ መኰንንነት ኮርስ ከተማሩ በኋላ በህዳር ፯ ቀን ፲፱፻፴፭ ዓ/ም የም/መ/ አለቃነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

በተከታታይ ባሳዩት ከፍተኛ የሥራ ችሎታ በሰባት ዓመት ውስጥ ከም/የመ/አለቃ ማዕረግ የሌተና ኮሎኔልነት ማዕረግ በ፲፱፻፵፪ ደርሰዋል ።

ሌ/ጄ ኃይሌ ባይከዳኝ በየማሰልጠኛ ጣቢያዎችና የጦር ትምህርት ቤት በመዘዋወር ሠራዊቱን በማሰልጠን ከደከሙት የኢትዮጵያ መኰንኖች አንዱ ነበሩ ። መኰንኑ በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም በሻለቅነት ማዕረግ በገነት ጦር ትምህርት ቤት አሰልጣኝ በነበሩበት ጊዜ ከብሪታንያ ከተላከው አንዱ አሰልጣኝ ቡድን ጋር ተመድበው በሰራዊቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የስታፍ (የመምሪያ) መኰንኖችን ኮርስ አዘጋጅተዋል ።



የጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹም የነበሩት ክቡር ሌ/ጄ ኃይሌ ባይከዳኝ ገና በ፳፪ ዓመት ዕድሜ ጀምረው አገራቸውንና ወገናቸውን በውትድርናና በአሰልጣኝነት ሙያ ለ፴፪ ዓመታት ያገለገሉ ስመጥር መኰንን ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

ሌ/ጄ ኃይሌ ባይከዳኝ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም በሻለቅነት ማዕረግ በጦር ሚኒስቴር (አሁን መከላከያ ሚኒስቴር) ውስጥ የወታደራዊ ትምህርት ዲሬክተር ነበሩ ። ለአምስት ዓመታት ያህል በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ በተለያዩ መምሪያ ሻምበሎች ሲሠሩ ቆይተዋል ። በ፲፱፻፵፮ ዓ/ም ወደ አሜሪካ ተልከው በፎርት ሌቬንወርት (ካንሳስ) ስታፍ (Staff College) ኮሌጅ የከፍተኛ አዛዥነትና የመምሪያ መኰንንነት ኮርስ ተከታትለው ፈተናቸውን በከፍተኛ ማዕረግ በማለፍ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል ።

ከአሜሪካ እንደተመለሱ በጦር ኃይሎች ውስጥ የሰው ኃይል ማደራጃ መምሪያ መኰንን በመሆን ተሾሙ ። በዚህም የሥራ ምድብ ላይ ከፍተኛ የሥራ ውጤት በማሳየታቸው የምድር ጦር የዘመቻ ክፍል መምሪያ መኰንን ሆነው በመሾም ለአራት ዓመታት ያህል አገልግለዋል ። በዚህ መምሪያ ውስጥ በአዛዥነት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፶ ዓ/ም የሙሉ ኮሎኔልነት ማዕረግ አገኙ ።

በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በ፬ኛ ክፍለ ጦር የ፬ኛ ብርጌድ አዛዥ በመሆን በነጌሌ ቦረና የነበረውን ጦር በአስተዳደር ፣ በትምህርትና በዲሲፕሊን ይዞታው እንዲሻሻል ከፍተኛ አመራር ሰጥተዋል ። ለአንድ ዓመት ያህል ብርጌዱን በአዛዥነት ከመሩ በኋላ በ፲፱፻፶፬ ዓ/ም የቀ/ኃ/ ሥላሴ ጦር ት/ቤት አዛዥ ሆነው በመሾም ወደ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ተዛወሩ ። መኰንኑ በገነት ጦር ት/ቤት አዛዥ በነበሩበት ጊዜ በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም የብርጋዲየር ጄኔራልነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

ብርጋዲዮር ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ ፣ በተለያዩ ጊዜያት ወደ አሜሪካ ፣ ምዕራብ አውሮፓና እስያ በመሄድ የጥናት ጉብኝቶች በማድረግ አያሌ ወታደራዊ ድርጅቶችንና ማሰልጠኛ ተቋሞችን ጎብኝተው ለሀገራቸው ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ቀስመው ተመልሰዋል ። እንዲሁም በ፲፱፻፵፮ ዓ/ም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በአሜሪካን አገር ጉብኝት ለማድረግ ከመሄዳቸው በፊት ከአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ለመነጋገር ከሄደው ቡድን ውስጥ ክቡር ብ/ጄኔራል ኃይሌ አንዱ ነበሩ ።

ሌ/ጄ ኃይሌ ባይከዳኝ በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም የሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው በመሾም ለአንድ ዓመት ያህል ክፍለ ጦሩን ሲመሩ ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በሐረር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር አካዳሚ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አዛዥ በመሆን ከነበሩት ከመጨረሻው የአካዳሚው ሕንዳዊ አዛዥ ተረከቡ ። የጦር አካዳሚው አዛዥ በነበሩበት ወቅት ነሐሴ ፲፱፻፷ ዓ/ም የሜጀር ጄኔራልነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

ክቡር ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ በመስከረም ወር ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ከጦር አካዳሚ ወደ ፫ኛ እግረኛ ክፍለ ጦር በመዘዋወር የአንበሳው ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው ተሾሙ ። በጥር ወር ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ሜጀር ጄኔራል ኃይሌ የምድር ጦር ምክትል አዛዥ ሆኑ ።

በታህሣሥ ወር ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የሌተና ጄኔራልነት ማዕረግ ተሰጥቷቸው በአገር መከላከያ ሚኒስቴር የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ማሰልጠኛ ድርጅት አዛዥ ሆነው ተሾሙ ። በዚሁ ዓመት በየካቲት ፳፮ ቀን የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ሆነው ተሹመዋል ።

ሌተና ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያን መንግሥት በመወከል ወደ ተለያዩ የውጭ አገሮች በመሔድ ተደራድረዋል ። በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመከላከያ ኮሚሽን ስብሰባ ላደ የኢትዮጵያን መልእክተኞች ቡድን በመምራት ተካፍለዋል ። በዚሁ ስብሰባ ላይ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመከላከያ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ሆነው በመመረጥ ኮሚሽኑ አምስተኛ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያን መልእክተኞች ቡድን በመምራት ለአፍሪካ የመከላከያ አቋምና አወቃቀር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ።

ሌ/ ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ አገራቸውን በታማኝነትና በቅንነት ለረጅም ዘመን በማገልገላቸው የሚከተሉትን ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ተሸልመዋል ።

፩/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ታላቅ መኰንን

፪/ የዳግማዊ ምኒልክ ፈረሰኛ ማዕረግ ኒሻን

፫/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ፈረሰኛ ኒሻን

፬/ የዳግማዊ ምኒልክ የ፲፭ ዓመት አገልግሎት ሜዳይ

፭/ የዳግማዊ ምኒልክ የረጅም ዘመን አገልግሎት ሜዳይ

አገራቸውን በውትድርና ፣ በአሰልጣኝነትና በመምህርነት ያገለገሉት እኚህ ከፍተኛ የጦር መኰንን በተወለዱ በ፶፭ ዓመታቸው ከሌሎች የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ባለሥልጣኖች ጋር ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በፋሺስቱ የደርግ መንግሥት በግፍ ተገድለዋል ።

ሌ/ጄ ኃይሌ ባይከዳኝ ባለትዳርና የሰባት ልጆች አባት ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

# ሜ/ጀኔራል ጋሻው ከበደ

## 1910 - 1967

ሜጀር ጀኔራል ጋሻው ከበደ ታህሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፲ ዓ/ም በሐረር ጠቅላይ ግዛት በወበራ አውራጃ በደደር ከተማ ተወለዱ ። አባታቸው ባላምባራስ ከበደ ወልደ ገብርኤል ማንቆይህ ፤ እናታቸው ወ/ሮ ጀማነሽ ግዛው ይባላሉ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ትምህርታቸውን በቤተሰቦቻቸው ቤት ካጠናቀቁ በኋላ የዘመናዊ ትምህርት ለመቅሰም ወደ ሐረር ከተማ ሄደው ፈረንሣይ ትምህርት ቤት ገብተው እንዳሉ አገራችን በፋሺስት በመወረሩ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ተወለዱበት ደደር ከተማ ተመለሱ ።

አባታቸው ባላምባራስ ከበደም ከጀግኖች አባቶች ጋር ወደ ኦጋዴን ዘምተው ለጥቂት ዓመታት ሲዋጉ ከቆዩ በኋላ በወራሪው ጦር በቁም እሥር ደደር ከተማ እንዲቆዩ ተደረገ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም መሣሪያ ቀብረሃል ፤ ልትሸፍት አስበሃል በመባል ተከሰው የሞት ፍርድ ስለተፈረደባቸው ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር ተገድለዋል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ ወጣት ጋሻውን በጃንሆይ ሜዳ በተቋቋመው የፖሊስ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ስላደረጓቸው በ፲፱፻፴፬ ዓ/ም በምክትል የመቶ አለቅነት ማዕረግ ተመርቀዋል ።



ክቡር ሜጀር ጀኔራል ጋሻው ከበደ ገና ከ፲፰ ዓመት ዕድሜ ጀምረው የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ በመሆን ለ፴፫ ዓመታት አገራቸውን በትጋት ፣ በታማኝነትና በቅንነት ያገለገሉ መኰንን ነበሩ ።

ክቡር ሜጀር ጀኔራል ጋሻው ከበደ ከ፲፱፻፴፫ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ድረስ ለ፴፫ ዓመታት ውድ እናት አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በተለያዩ የሥራ መደቦችና ክፍለ ሀገሮች በኃላፊነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል ።

— በአዲስ አበባ አስተዳደር ፖሊስ ዋና መምሪያ ፤

— በቤጌምድር አስተዳደር ፖሊስ ዋና መምሪያ ፤

— በወለጋ አስተዳደር ፖሊስ ዋና መምሪያ ፤

— በፖሊስ ሠራዊት አስተዳደር ዋና መምሪያ ፤

— በሐረር አስተዳደር ዋና መምሪያ ፤

— በኤርትራ አስተዳደር ዋና መምሪያ ፤

ማጀር ጀኔራል ጋሻው ከበደ ለአበረከቱት የረጅም ዘመን አገልግሎት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው የማዕረግ እድገት ተሰጥቷቸዋል ።

፩/ ታህሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ/ም የም/መ/አለቅነት ማዕረግ ፤

፪/ ታህሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፻፴፭ ዓ/ም የሙሉ መቶ አለቅነት ማዕረግ ፤

፫/ ታህሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ/ም የሻምበልነት ፤

፬/ ጥር ፳፬ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ/ም የሻለቅነት ፤

www.ethipianorthodox.org

፭/ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ/ም የሌ/ኮሎ ኔልነት ፤

፮/ በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም የሙሉ ኮሎኔልነት ፤

፯/ በ፲፱፻፶፬ ዓ/ም የብርጋዴር ጄኔራልነት ፤

፰/ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም የሜጀር ጄኔራልነት ማዕ ረግ ተሰጥቷቸዋል ።

ለሰጡት ቅን አገልግሎት መታሰቢያ እንዲሆን የሚከተሉትን የክብር ኒሻኖች አግኝተዋል ፡፡

— የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ፤

— የ፲፭ ዓመት አገልግሎት ፤

— የኢዮቤልዩ ፳፭ኛ ዓመት ኒሻን ፤

— የዳግማዊ ምኒልክ ባለአምበል ፤

— የኢትዮጵያ ኒሻን አምበል የሌለው ፤

— ከእንግሊዝ ንግሥት ከዳግማዊት ኤልሳ ቤጥ ፣ ከዩጎዝላቪያው መሪ ማርሻል ቲቶ ፣ ከቡል ጋሪያ ፣ ከፖላንድ ፣ ከኬንያና ከሱዳን መንግሥ ታት ልዩ ልዩ ኒሻኖች በተለያዩ ጊዜ ለፈጸሟቸው መልካም ሥራዎች የምስጋና ደብዳቤዎች አግ ኝተዋል ።

ክቡር ሜጀር ጄኔራል ጋሻው ከበደ በፈረስ ገና ጨዋታና በልዩ ልዩ የስፖርት ዓይነቶች ተካ ፋይ በመሆን ፤ ለፖሊስ ሠራዊት ልዩ ልዩ የዋንጫ ሽልማቶችን አስገኝተዋል ።

ለሠራዊቱ የነበራቸውን ታላቅ ፍቅር በተ ግባር በማሳየት የአሜድላ ክለብ ፕሬዚዳንት ሆነው ሲያገለግሉ ቡድኑን ለአዲስ አበባ ቻምፒዮ ንነት አብቅተዋል ።

ክቡር ሜጀር ጄኔራል ጋሻው ከበደ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ወይዘሮ ሙሉነሽ ሚሊዮንን በሕግ አግብ ተው ከ፳፭ ዓመት በላይ በሆነ የጋብቻ ዘመን ዘጠኝ ልጆችና አሥራ አራት የልጅ ልጆች አፍ ርተዋል ።

ከዚህ ቀጥሎ ክቡር ሜጀር ጄኔራል ጋሻው ከበደን ጨምሮ በወታደራዊው ደርግ በግፍ ለተ ገደሉት ፷ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከባለቤታ ቸው ከወ/ሮ ሙሉነሽ ሚሊዮን የተገጠመው የሐዘን እንጉርጉሮ በአጭሩ ቀንጭበን እናቀር ባለን ።

አልታይም አለኝ ያገሬ ሰማይ
እንግዲህ ሆዴ ቆርጦ ወጥቻለሁ ወይ ?

አገሬ ምን አለኝ ደርጉ ነው ጠላቴ
ከምወደው ባሌ ለየኝ ከካላቴ ።
ጤናም አላገኘሁ ቆሜ በሕይወቴ
ተቆርጠህ ወድቀሃል ግማሽ አካላቴ ።

አይወራ ሞትህ ሞትህ አይወራ
ወዳጅ እንዳያዝን ጠላት እንዳይኮራ ።

ምነው እንደ አልአዛር ሞተህ ብትነሳ
ወዳጅ ጠላትህን ታየው ነበር እሳ ።

አባት የለውም ወይ ወንድም የለውም ወይ
ወገን የለውም ወይ ይኸ ሁሉ ሰው
ቀን እየለቀመ ሌሊት ሲያነደው ።

እስቲ ከቤ ጥራው ወይ ይልህ እንደሆን
እስቲ ፀጋ ጥራው ወይ ይልህ እንደሆን
እስቲ አቤ ጥራው ወይ ይልህ እንደሆን
እፀገነት ጥሪው ወይ ይልሽ እንደሆን
ሰንዬ እስቲ ጥሪው ወይ ይልሽ እንደሆን
ገሊላ እስቲ ጥሪው ወይ ይልሽ እንደሆን
ፋሲል እስቲ ጥራው ወይ ይልህ እንደሆን
ማህፀንተ ጥሪው ወይ ይልሽ እንደሆን

እርብቃ እስቲ ጥሪው ምን ሆኖ አመረረ
እኔንስ እምቢ አለኝ ትንፋሼ እያጠረ ።

ያልተማረ ክፉ ወንድሙን ይገላል
የተማረማ ሰው ስለሰው ይሰዋል

አለመማር ክፉ አለመመልከት
ወንድሙን ይገላል ሥልጣን ለማግኘት

እንዴት ተሰወረ ከሰዎች ሕሊና
እጁን በደም መንከር ሳይመስለው ፈተና

ጲላጦስ ብቻ ነው ይኸንን ያሰበ
ከደሙ ንጹሕ ነኝ ብሎ የታጠበ ።
ስድሳ ስምንቱ እስረኞች ጥይት የፈታችሁ
በግፍ የፈሰሰው ንጹሑ ደማችሁ
እኛ አቅም አጣን ይፋረድ ደማችሁ ።

www.ethipianorthodox.org

# ሜ/ጄኔራል ሥዩም ገድለ ጊዮርጊስ

## 1912 - 1967

ክቡር ሜጀር ጄኔራል ሥዩም ገድለ ጊዮርጊስ ከአቶ ገድለ ጊዮርጊስ አዘነና ከወ/ሮ በለጥሻቸው ግብርዱ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓ/ም በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በሐረር ከተማ ተወለዱ ።

በልጅነታቸው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከአያታቸው ከአለቃ ግብርዱ ቤት ደደር ለጥቂት ጊዜ ከተከታተሉ በኋላ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሐረር ከተማ አጠናቀቁ ። ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ለውትድርና ሞያ በነበራቸው የጋለ ፍቅር በተራ ወታደርነት ተቀጠሩ ። በዚህን ጊዜ ባሳዩት የሥራ ችሎታና ጥሩ ሥነ ምግባር ለመኰንንነት ተመርጠው በሆለታ ገነት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ትምህርት ቤት እንዲገቡ ተደረገ ። ከዚያም ከኮርሳቸው በላቀ ውጤት አንደኛ በመሆን በም/መቶ ዕልቅና ማዕረግ ተመርቀው ከንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ሽልማት አግኝተዋል ። ከዚህም ሌላ በልዩ ልዩ የመምሪያ መኰንንነትና የአዛዥነት ሙያ በአገር ውስጥና በፈረንሣይ አገር ተልከው ሠልጥነው ልዩ ሽልማት በማግኘት በዲፕሎማ ተመርቀዋል ።

ክቡር ሜጀር ጄኔራል ሥዩም በአገር ውስጥና በውጭ አገር በልዩ ልዩ ሥራና ኃላፊነት ተመድበው እንደሚከተለው አገልግለዋል ።

— በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ትምህርት ቤት ፣ በአስተማሪነት ፣ በአሰልጣኝነት ፣ በረዳት መኰንንነትና በአዛዥነት



ክቡር ሜጀር ጄኔራል ሥዩም ገድለጊዮርጊስ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች አገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን በቅንነትና በታማኝነት ከ፴፮ ዓመት በላይ ያገለገሉ ምስጉን መኰንን ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

— በሁለተኛ ክፍለ ጦር የ፳ኛ ብርጌድ የአስተ ዳደር መኰንን

— በምድር ጦር የደሞዝና ሂሳብ መምሪያ የ፫ኛ ክፍለ ጦር ሂሳብ ተቆጣጣሪ

— በ፫ኛ እግረኛ ብርጌድ የሻለቃ ጦር አዛዥ

— በ፫ኛ ክፍለ ጦር የዘመቻና የትምህርት መኰንን

— በመከላከያ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ልዩ ጽሕ ፈት ቤት ሹም

— የ፫ኛ ክፍለ ጦር ኤታ ማዦር ሹም

— በኮሪያ የተባበሩት መንግሥታት የ፭ኛ ቃኘው ሻለቃ የዘመቻ መኰንን

— በኮንጎ የተባበሩት መንግሥታት የ፳፪ኛ ሻለቃ ጦር ዋና አዛዥ

— በአሥመራ የ፪ኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ

— በተጨማሪ ክቡር ሜ/ጄኔራል ሥዩም በአ ሜሪካ ፣ በአውሮፓ ፣ በእሥራኤልና በሌሎች ልዩ ልዩ አገሮች በሥራ፣ በስብሰባና በጉብኝት ተሳትፎ በማድረግ ተልዕኮአቸውን በሚገባ ተወጥተዋል ።

ክቡር ሜ/ጄኔራል ሥዩም በኮሪያና በኮንጎ ቀዳሚ ዘማች በመሆን ለፈጸሙት አኩሪና ጀብዱ ሥራ ከንጉሠ ነገሥቱና ከተባበሩት መንግሥታት ኒሻኖችና ሜዳልያዎች እንዲሁም ሽልማቶች አግኝተዋል ። በአገር ውስጥም በልዩ ልዩ ቦታዎች እንዲሁም በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል በ፲፱፻፶፮ ዓ/ም በተደረገው ጦርነት ላበረከቱት አኩሪና ጀብዱ ሥራ ከንጉሠ ነገሥቱ ኒሻኖችና ሜዳሊያ ዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተቀብለዋል ። ባጠቃላይ ከ፴፬ ዓመት በላይ ላበረከቱት አስተ ዋጽኦ ፲፰ ኒሻኖችና የጦር ሜዳ ሜዳሊያዎች ተሸ ልመዋል ። ከነዚህም ውስጥ ፡—

— የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ታላቅ መኰንን ኒሻን

— የዳግማዊ ምኒልክ ባለአምበል ኒሻን

— የዳግማዊ ምኒልክ የአገልግሎት ሜዳይ

— የቅዱስ ጊዮርጊስ የጦር ሜዳ ጀብዱ ሜዳይ ባለ ፫ ዘንባባ

— ከኢትዮጵያ መንግሥት ፣ የተባበሩት መን ግሥታት የኮንጎ ጦርነት መታሰቢያ ሜዳይ

— የተባበሩት መንግሥታት የኮንጎ ፀጥታ ማስከ በሪያ መታሰቢያ ኒሻን

— ከኢትዮጵያ መንግሥት የተባበሩት መንግሥ ታት የኮሪያ ጦርነት መታሰቢያ ኒሻን

— ከደቡብ ኮሪያ መንግሥት የተባበሩት መን ግሥታት የኮሪያ ጦርነት መታሰቢያ ኒሻን ይገኙበታል ።

ክቡር ጄኔራል ሥዩም ገድለ ጊዮርጊስ ከአ ማርኛ ሌላ አደርኛ ፣ ኦሮምኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ጣሊ ያንኛና እንግሊዝኛ ይናገሩ ነበር ።

ክቡር ጄኔራል ሥዩም በማኅበራዊ ሕይወታ ቸው ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው ደግ ፣ ቅን ፣ ብልህና አርቆ አስተዋይ ነበሩ ። በአለቆቻቸው በበታቾቻቸው እንዲሁም በጓደኞቻቸውና በዘመ ዶቻቸው የተወደዱ መኰንን ናቸው ። ከሥራ ውጭ በአያሌ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተሳትፎ ነበራቸው ። ከብዙ በጥቂቱ የጦር መኰንኖች ክበብ ፕሬዚዳንት ፣ የሆለታ ጦር ትምህርት ቤትና የሐ ረር አካዳሚ የስፖርት ፕሬዚዳንት ነበሩ ። ከዚህ በተጨማሪ ለቤተ ክርስቲያን ፣ ለስፖርት ፣ ለትም ህርት ቤቶች ልዩ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ነበሩ ።

የካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በተደረገው ሕዝባዊ አመጽ በአቋራጭ ስልጣን የያዘው ወታደራዊ ደርግ ለጥያቄ ይፈለጋሉ ብሎ ለአጭር ጊዜ በቁጥጥር ሥር ካቆያቸው በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከሌሎች ፶፱ ከፍተኛ የሲቪልና የጦር ባለሥልጣኖች ጋር ካለፍርድ በግፍ ገድሏ ቸዋል ።

ክቡር ሜጀር ጄኔራል ሥዩም ገድለ ጊዮ ርጊስ ወይዘሮ ንግሥት ኪሮስን በሕግ አግብተው ሁለት ወንዶችና አንድ ሴት ልጅ አፍርተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ሜ/ጀኔራል ታፈሰ ለማ

## 1921-1967

ክቡር ሜ/ጀኔራል ታፈሰ ለማ ከአባታቸው ከቀኛዝማች ለማ በላይነህና ከእናታቸው ከወ/ሮ አዛለች አድማሴ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በየረርና ከረዩ አውራጃ ልዩ ስሙ ቀጨማ በተባለው ሥፍራ ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ/ም ተወለዱ ።

ክቡር ሜ/ጀኔራል ታፈሰ ለማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ናዝሬት አጼ ገላውዴዎስና አዲስ አበባ ደጃዝማች ገብረማርያም ት/ቤት ከአጠናቀቁ በኋላ የስመ ጥሩው የክብር ዘበኛ ጦር ት/ቤት የመጀመሪያው (ከ፲፱፻፴፰—፲፱፻፵፩) ዕጩ መኰንን ምሩቅ ናቸው ። ክቡርነታቸው ከአካዳሚው ከፍተኛ ነጥብ በማምጣት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተፈረመበት የጃንሆይ ፎቶግራፍ ተሸልመዋል ።

መኰንኑ በወታደራዊ ሳይንስ በነበራቸው ከፍተኛ ችሎታ ተመርጠው የሁለተኛውንና የሶስተኛውን የክብር ዘበኛ ጦር ት/ቤት ዕጩ መኰንኖች ከመስከረም ፲፱፻፵፩ እስከ የካቲት ፲፱፻፵፮ ዓ/ም ለ፭ ዓመታት አሰልጣኝ በመሆን አገልግለዋል ። በዚያን ጊዜ በአሳዩት ከፍተኛ የአሰልጣኝነት ችሎታ ከዚያ በፊት በሠራዊቱ ለማንም ተደርጎ የማይታወቅ በግርማዊ ጃንሆይ የተፈረመ "የመልካም መኰንን ሥራ ፍሬ መግለጫ" የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

ሶስተኛ ቃኘው ሻለቃ ወደ ኮሪያ ከመዝመቱ በፊት የጦር ሜዳ የውጊያ ችሎታውን ብቃት ለማሻሻል በተካሄደው ሥልጠና በሻምበል ታፈሰ ለማ አዛዥነት የሰለጠነው አንደኛ ሻምበል በልምምድ ከተወዳዳሪዎቹ ሁሉ አንደኛ ሆኖ በመገኘቱ አዛዡ ሻምበል ታፈሰ ለማ የደረጃ እድገት አግኝተው የሻለቃው አዛዥ አማካሪ በመሆን ወደ ኮሪያ የጦር ሜዳ ዘምተዋል ።

በጦር ሜዳ በያዙት ሥራ ላይ ደርበው የሻለቃው የሁለተኛ መመሪያ መኰንን ሆነው አገልግለዋል ። የኮሪያን ጦርነት ሲመራ ለነበረው ለተባበሩት መንግሥታት ፫ኛ ክ/ጦር ሠራዊት ስለ



ክቡር ሜ/ጄ ታፈሰ ለማ በንጉሠ ነገሥቱ እልፍኝ አስከልካይነት ፣ በጦር አዛዥነት ፣ በሚሊታሪ አታሼነትና በአሰልጣኝነት ሀገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን ለ፳፰ ዓመታት ያገለገሉ ምርጥ መኰንን ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

ጦር እስረኞች አመላለስ የኢትዮጵያ ጦር አገናኝ መኰንን በመሆን በፓንሙንጀም የጦር ምርኮኞች ሠፈር አገልግለዋል ።

የቃኘው ሻለቃ ጦር ወደ አገሩ ተመልሶ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሜዳ ጀብዱና የሥራ ውጤት ጠቅላላ ገለጣ ሲደረግ ክቡር ሜ/ጄኔራል ታፈሰ የኮሪያ ጦርነት የእርቅ ውልና የጦር እስረኞች አለዋወጥን አስመልክተው መግለጫ ሰጥተዋል ። ከዚህም ገለጻቸው ኢትዮጵያዊ ምርኮኛ እንዳልነበረ ታውቋል ።

ክቡር ሜ/ጄኔራል ታፈሰ ለማ ከኮሪያ የጦር ግንባር እንደተመለሱ በክብር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ በትምህርት እና በዘመቻ መኰንንነት በአንደኛ መምሪያ ተመድበው የትምህርት ተቆጣጣሪ መኰንን ሆነው ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም በዚሁ መምሪያ የትምህርትና የዘመቻ መኰንን ሆነው ተሾሙ ። በዚሁ ዓመት ከተወሰኑ የክብር ዘበኛ መኰንኖች ጋር ተመርጠው የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ኤታ ማዦር በማቋቋም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ክቡር ሜ/ ጄኔራል ታፈሰ ለማ በጦር ት/ቤት የዕጩ መኰንኖች አሰልጣኝ ሆነው በጦር ትምህርትና በአስተዳደር ባሳዩት ችሎታና በኮሪያ ጦር ሜዳ አገናኝ መኰንን ሆነው ባሳዩት የዲፕሎማሲ ጥበብ ከአገሪቱ ምርጥ መኰንኖች አንዱ መሆናቸውን በማስመስከራቸው ከዚያ በፊት ላልነበረ አዲስ ሥራ ታጭተው በሌ/ኮሎኔልነት ማዕረግ ግብፅ አገር በካይሮ ሚሊታሪ አታሼ ሆኑ ። እዚያ ለሁለት ዓመት ከሶስት ወር ካገለገሉ በኋላ ከኅዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ጀምሮ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ም/እልፍኝ አስከልካይ ሆኑ ።

ክቡር ሜ/ ጄኔራል ታፈሰ ለማ ቀደም ሲል በክብር ዘበኛ ሠራዊት አባልነታቸው ካካበቱት የጦር ትምህርትና ልምድ በተጨማሪ ታማኝነትንና ታዛዥነትን ፣ የቤተ መንግሥት ሥርዓትና ወግ እንዲሁም በሳል የሕዝብ ግንኙነትንና አስተዳደርን በሚጠይቀው የእልፍኝ አስከልካይነት ሥራ በፈጸሙት አኩሪ ተግባር ተመርጠው የካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ሆነው ተሾሙ ። ለዚህ ከፍተኛ ሹመት ሲበቁ ሜጀር ጄኔራል ታፈሰ ለማ የመጀመሪያው የክብር ዘበኛ ጦር ት/ቤት ምሩቅ ሲሆኑ ይኸም ተማሪዎቻቸውና የቅርብ ጓደኞቻቸው አንድ ቀን የክብር ዘበኛ አዛዥ እንዲሆኑ ይመኙላቸው የነበረው ዕውን ሆነ ።

ለ፳፰ ዓመታት ለአገራቸውና ለመንግሥታቸው ላበረከቱት ከፍተኛ አገልግሎት ሜጀር ጄኔራል ታፈሰ ለማ ከዚህ የሚከተሉትን ሹመትና ሽልማት አግኝተዋል ።

<u>የማዕረግ ዕድገት</u>

የም/መ/አለቅነት ማዕረግ—መስ. ፳/፲፱፻፵፩ ዓ/ም

የሙሉ መ/ አለቅነት ማዕረግ ጥር ፳፪/፲፱፻፵፫ ዓ/ም

የሻምበልነት ማዕረግ — ሰኔ ፳፭/፲፱፻፵፬ ዓ/ም

የሻለቅነት ማዕረግ — ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፶ ዓ/ም

ሌ/ኮሎኔልነት ማዕረግ—ሚያዝያ ፳፯/፲፱፻፶፮ዓ/ም

የብ/ጄኔራልነት ማዕረግ—ጳጉሜን ፬/፲፱፻፶፱ ዓ/ም

የሜ/ጄኔራልነት ማዕረግ — ጥር ፳፰/፲፱፻፷፭ ዓ/ም

የጦር ሜዳ ሜዳሊያዎችና ኒሻኖች ሽልማት

<u>ከኢትዮጵያ መንግሥት :—</u>

፩/ የኢትዮጵያ ክብር ኮከብ ታላቅ መኰንን ኒሻን

፪/ የዳግማዊ ምኒልክ የመኰንን ደረጃ ኒሻን

፫/ የኢትዮጵያ ክብር ኮከብ የመኰንን ደረጃ ኒሻን

፬/ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሜዳ ሜዳይ ባለ ፪ ዘንባባ

፭/ የኮሪያ ጦርነት መታሰቢያ ኒሻን

፮/ የተዋጊ የጠመንጃ ምልክት

<u>ከውጭ ሀገር መንግሥታት :—</u>

፩/ የተባበሩት መንግሥታት ኒሻን ከተባበሩት መንግሥታት

፪/ ብሮንዝ ስታር የጦር ሜዳ የጀብዱ ሜዳይ ከአሜሪካ መንግሥት

፫/ ሲልቨር ስታር የጦር ሜዳ የጀብዱ ሜዳይ ከኮሪያ መንግሥት

፬/ የኮሪያ ጦርነት መታሰቢያ ኒሻን ከተባበሩት መንግሥታት

፭/ የኅብረት ውጊያ ሜዳይ ከአሜሪካ መንግሥት

፮/ የኅብረት ውጊያ ሜዳይ ከኮሪያ መንግሥት

ከእነዚህ በተጨማሪ ሜ/ጄኔራል ታፈሰ ለማ ከውጭ አገር መንግሥታት ፴፱ (ሠላሳ ዘጠኝ) የክብር ኒሻኖች የተሸለሙ ሲሆን በድምሩ አምሳ አንድ የጦር ሜዳ የጀብዱ ሥራ ሜዳዮችና ኒሻኖች የተሸለሙ ምርጥ መኰንን ነበሩ ።

ክቡር ሜ/ጄኔራል ታፈሰ ለማ ለጥያቄ እንደሚፈለጉ በወታደራዊ ደርግ ተጠርተው በቁጥጥር ሥር በዋሉ አራት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከሌሎች ፶፱ ባለሥልጣኖች ጋር ካለፍርድ በግፍ ተገድለዋል ።

ክቡር ሜ/ጄኔራል ታፈሰ ለማ ወ/ሮ የባሌ ወርቅ አውግቸውን በሕግ አግብተው አንድ ወንድና አራት ሴቶች ልጆች ተክተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ብርጋዲዬር ጄኔራል ግርማ ዮሐንስ

## 1919 - 1967



ክቡር ብርጋዲዬር ጄኔራል ግርማ ዮሐንስ በፖሊስ ሠራ ዊት ፳፰ ዓመታት በተለያዩ ደረጃ ያገለገሉ ርህሩህና የተወደዱ መኰንን ነበሩ ።

ክቡር ብ/ጄ ግርማ ዮሐንስ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ/ም በደብረ ብርሃን ከተማ ተወለዱ ። አባታቸው ቀኛዝማች ዮሐንስ ወልደ ማርያም ፤ እናታቸው ወ/ሮ ወርቅነሽ ሞላ ይባላሉ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በደብረብር ሃን ቅድስት ሥላሴ ደብር መንፈሳዊ ትምህርት ሲማሩ ቆይተው በጀግናው አርበኛ ኃይለ ማርያም ማሞ ት/ቤት ዘመናዊ ትምህርት ተከታትለዋል ።

በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም ከትምህርት ቤቱ ተመልም ለው ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ በአዳሪነት ተመዝግበው በወቅቱ ተቋቁሞ በነበረው ክብር ዘበኛ ማሠልጠኛ ት/ቤት የመድፈኛ ትምህርት ተማሩ ።

ዕድልና ፍላጎት ያላገዛቸው በመሆኑ ትም ህርት ቤቱን ለቅቀው በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም በሲቪል ፀሐፊነት በፖሊስ መሥሪያ ቤት ተቀጠሩ ። እዚያም ፫ ወር ያህል እንደሠሩ በነበራቸው አቋም በቋሚነት ተቀጥረው በፖሊስ ሠራዊት ትምህርት ተመረቁ ።

ብ/ጄኔራል ግርማ ዮሐንስ የተፈጥሮ ችሎታ ቸውን በትምህርት ለማጠናከር በአደረጉት ጥረት በ፲፱፻፵፬ ዓ/ም እሥራኤል ሀገር የፖሊስ ትም ህርት ተከታትለው ዲፕሎም አግኝተዋል ። በ፲፱፻

www.ethipianorthodox.org

# ብርጋዴዬር ጄኔራል
# ሙሉጌታ ወ/ዮሐንስ

## 1916-1967



የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አዛዥ የነበሩት ብ/ጄ ሙሉጌታ ወ/ዮሐንስ በተለያዩ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት ለ፴፩ ዓመታት አገራቸውንና መንግሥታቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።

www.ethipianorthodox.org

ብ/ጄኔራል ሙሉጌታ ወ/ዮሐንስ ከአቶ ወ/ዮሐንስ አባይና ከወ/ሮ ይገስግሱ ኃይሉ በ፲፱፻፲፯ ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ አውራጃ ተወለዱ ።

ጄኔራል ሙሉጌታ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ መጀመሪያ በእናት አባታቸው ቤት በአገር ወግና ባህል መሠረት ከዚያም በአካባቢው በሚገኘው ትምህርት ቤት ገብተው ተምረዋል ። የተፈጥሮ ዝንባሌያቸው ወታደር ሆነው አገራቸውንና ወገናቸውን ማገልገል ስለነበር መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ/ም በጦር ሠራዊት ውስጥ ተቀጥረው ነገሌ ቦረና በሚገኘው ፬ኛ ክፍለ ጦር በማገልገል ላይ እንዳሉ ለመኰንንነት ተመልምለው ገነት ጦር ት/ቤት ገብተው በ፲፱፻፴፱ ዓ/ም ም/መቶ አለቃ ሆነው ተመረቁ ። በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም ወደ ፫ኛ ክፍለ ጦር ተዛውረው ሐረር ሐማሬሳ በሚገኘው የጦር ት/ቤት መኰንኖችንና የበታች ሹማምንትን በማሰልጠን አገልግለዋል ።

ከታህሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ/ም ጀምሮ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ ወደ ፖሊስ ሠራዊት ተዛወሩ ። የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስን ለማቋቋም ሲታሰብ ጄ/ ሙሉጌታ ወ/ዮሐንስ ከተመረጡት መኰንኖች አንዱ ነበሩ ። ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ/ም ጄ/ ሙሉጌታ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ፊት ቀርበው "አስፈላጊ መሆናችሁን አውቀን እንድትመጡ አድርገናል ፤ ቀድሞም የነበራችሁበት የሞት ቦታ ቢሆንም ፣ አሁን ደግሞ የተመረጣችሁበት ሥራ የዕለት ሞት ያለበት ስለሆነ ተጠንቅቃችሁና ተግታችሁ እንድትሠሩ በተጨማሪ አደራ እንላችኋለን" የሚል መሪ ቃል በመቀበል ሥራውን ጀምረዋል ።

ወደ ፖሊስ ሠራዊት ከተዛወሩበት ጊዜ አንስቶ ማለትም ፡ ከ፲፱፻፵፯ እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በኢትዮጵያና ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ መሥራችነት ፣ ከ፲፱፻፶፫ እስከ ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ ፖሊስ አዛዥነት ፡ ከ፲፱፻፷ እስከ ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ አዛዥነት ፡ ከ፲፱፻፷፩ እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ/ም በአዲስ አበባ ፖሊስ ዋና መምሪያ ውስጥ ፡ ከ፲፱፻፷፫ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች አገልግለዋል ። በተለይም በፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ግቢ ውስጥ ሠራዊቱ አካሉንና አእምሮውን የሚያዝናናባቸው የሜዳ ቴኒስ ፣ የእግር ኳስና የመረብ ኳስ ሜዳዎች እንዲሠሩ ከማድረጋቸውም በላይ የነዳጅ ማደያ እንዲሠራና የድርጅቱ የተሽከርካሪ ጥገና ክፍሉ እንዲጠናከር አድርገዋል ።

ብ/ጄኔራል ሙሉጌታ ወ/ዮሐንስ ከመጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ/ም እስከ ኅዳር ፴ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ/ም ድረስ ፲፮ ዓመት ከ፱ ወር በጦር ሠራዊት ፣ ከታህሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ድረስ ፳ ዓመት በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ በጠቅላላው ፴፮ ዓመት ከ፱ ወር ውድ እናት ሀገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።

ጄኔራል ሙሉጌታ በዚህ የረጅም ጊዜ አገልግሎታቸው በ፲፱፻፴፱ ዓ/ም የምክትል መቶ አለቅነት ፣ ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ/ም የሻምበልነት ፣ ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ/ም የሻለቅነት ማዕረግ ያገኙ ሲሆን በዚሁ ዓመት ወደ እሥራኤል አገር ሄደው የአየር ወለድ ትምህርት ተምረዋል ። ሰኔ ፯ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ/ም የሌተና ኰሎኔልነት ፣ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም የሙሉ ኰሎኔልነት ፣ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም የብርጋዲዬር ጄኔራልነት ማዕረግ ከማግኘታቸውም በላይ ላበረከቱት መልካምና ቀና አገልግሎት ከተሰጧቸው ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች መካከል የዳግማዊ ምኒልክ የፈረሰኛ ኒሻንና የቀ/ ኃይለ ሥላሴ የብር ሜዳሊያ ይገኙባቸዋል ።

ብ/ጄኔራል ሙሉጌታ ወ/ዮሐንስ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በቁጥጥር ስር ውለው ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ተገድለዋል ።

ጄኔራል ሙሉጌታ ባለትዳርና የአሥራ ሁለት ልጆች አባት ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ኮሎኔል
# ይገዙ ይመኔ

# 1919 - 1967



ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ የአርሚ አቪዬሽን አዛዥና የኮሪያ ጦርነት መኰንን የአየር ኃይሉ አሰልጣኝ በመሆን አገራቸውን ለ፳፮ ዓመታት በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።

www.ethipianorthodox.org

ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ ከአቶ ይመኔ ጠልልና ከወ/ሮ ዘነበወርቅ ሽመልስ በአዲስ አበባ ከተማ በ፲፱፻፲፱ ዓ/ም ተወለዱ ።

በአያታቸው በፊታውራሪ ሽመልስ ሀብቴ ቤት በእንክብካቤ እያደጉ ሳለ የአማርኛን ትምህርት ተማሩ ። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚያን ጊዜ የተፈሪ መኰንን ት/ቤት ይባል በነበረው በዛሬው እንጦጦ አጠቃላይ ት/ቤት ተከታተሉ ።

ኰሎኔል ይገዙ አገራቸውን በውትድርና ለማገልገል በነበራቸው ፍላጎት በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም በክብር ዘበኛ የጦር ት/ቤት ተመልምለው የሚሰጠውን የሶስት ዓመት ወታደራዊ ሳይንስና ልዩ ልዩ ትምህርት በከፍተኛ ውጤት አጠናቀቁ ።

በምክትል መቶ እልቅና ማዕረግ ተመርቀው በክብር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ በማገልገል ላይ እንዳሉ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ጦር በዘመናዊ መልክ ሲቋቋም ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ለአሰልጣኝነት ተመርጠው ተልእኳቸውን በሚገባ ተወጥተዋል ።

ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ በነበረባቸው ከፍተኛ ችሎታና ታታሪነት በማስልጠን ተግባራቸው ብቻ ሳይወሰኑ የአውሮፕላን የበረራ ትምህርት ወስደው በከፍተኛ ውጤት የበራሪነት ክንፍ ተቀብለዋል ።

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት አማካኝነት የሰላም ጥበቃ ወደ ኮሪያ ስትልክ ኰሎኔል ይገዙ የቃኘው ሻለቃ ጦር አንዱ መኰንን ነበሩ ። በጦሩም ውስጥ በፈጸሙት ከፍተኛ የሥራ ውጤት ልዩ ልዩ የምስጋና ጽሑፎች ፤ ሜዳሊያና ሊሻኖች ተሸልመዋል ።

ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ ከኮሪያ ከተመለሱ በኋላ በክብር ዘበኛ ጦር ሠራዊት ውስጥ በማገልገል ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም እንደገና ወደ ኮሪያ ተልከው ለአንድ ዓመት አገልግለዋል ።

ኮሎኔል ይገዙ ይመኔ ለከፍተኛ የአገር ጥበቃና ደህንነት ትምህርት ተመርጠው ወደ ውጭ አገር ተልከው ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ ፤ የቀድሞው የክብር ዘበኛ ሠራዊት በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በተነሳው የመንግሥት ግልበጣ አመጽ ስለተበተነ ወደ ምድር ጦር ተዛውረው እንዲሠሩ ተደረገ ። ከዚያም ቀደም ብለው በቀሰሙት የበረራ ትምህርትና የሥራ ልምድ በመከላከያ ሚኒስቴር የአርሚ አቪዬሽን አዛዥ ሆነው በመሾም ክፍሉን በአዲስ መልክ አሻሽለው በማቋቋም ከፍተኛ ሥፍራ እንዲይዝ አድርገዋል ።

ኮሎኔል ይገዙ ይመኔ ለአከናወኑት ከፍተኛ ተግባርና አገልግሎት ከአገር ውስጥና ከውጭ መንግሥታት ከተሸለሙት ሜዳሊያዎችና ኒሻኖች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

፭/ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሜዳ ሜዳይ

፮/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የፈረሰኛ ደረጃ ኒሻን

፯/ የረዥም ዘመን የአገልግሎት የወርቅ ሜዳይ

፰/ የኮሪያ ዘማች የኢትዮጵያ መታሰቢያ ሜዳይ

፱/ የተባበሩት መንግሥታት የኮሪያ ዘማች መታሰቢያ ሜዳይ

በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የሕዝብ አመጽ ተፈጥሮ ደርግ ሲቋቋምና የራሱን ወንበር ሲያመቻች ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ የሕዝብ ጥያቄ እንዲሟላ ደርግን በግልጽ በይፋ ከመቃወማቸውም በላይ የነበሩበትን ጦር ክፍል በመያዝ ደርግ ሕዝባዊ ምላሽ እንዲሰጥ ለማድረግ ሲታገሉ በጦር ኃይል ተይዘው በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ያለፍርድ ተገድለዋል ።

ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ ለሕዝባዊ ወገናዊነት ቅድሚያ የሚሰጡ በፍትሕና በእኩልነት የሚያምኑ ሕዝባዊ መኰንን ነበሩ ።

ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ሣራ ሣህሌ አንድ ወንድና ሶስት ሴት ልጆች አፍርተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# ኮሎኔል
# የዓለም ዘውድ ተሰማ

## 1918 - 1967

ኰሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ ካሣ ከፊታውራሪ ተሰማ ካሣና ከወ/ሮ ሕብረቱ አብተው በቆላና ደጋ ዳሞት አውራጃ ፡ በሰከላ ወረዳ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ/ም ተወለዱ ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዩ ፈቃድ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር ት/ቤት ገብተው ከነሐሴ ፯ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ/ም ጀምሮ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ/ም በምክትል የመቶ አለቅነት ማዕረግ በዲፕሎም ተመረቁ ።

የአዛዥነትና የመምሪያ መኰንንነት ትምህርት ተከታትለው ሐምሌ ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ/ም በዲፕሎም ተመርቀዋል ።

ኰሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ በውትድርና ዓለም ለ፳፰ ዓመታት ሲያገለግሉ የተሰጣቸው የሥራ መደብና የማዕረግ እድገት ቀጥሎ የተመዘገበው ነው ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር ት/ቤት መምህር
፲፱፻፴፰ እስከ ፲፱፻፴፱
የ፫ኛ ሻለቃ የትምህርት መኰንን (ጂማ)
፲፱፻፵ እስከ ፲፱፻፵፩
የ፪ኛ ሻለቃ ጦር የትምህርት መኰንን (ነገሌ ቦረና) ፲፱፻፵፪ እስከ ፲፱፻፵፫
የ፬ኛ መድፈኛ ሻለቃ ጦር የትምህርት መኰንን
፲፱፻፵፬ እስከ ፲፱፻፵፰



ለ፳፰ ዓመታት በልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች ያገለገሉት ኮሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ ዝናን ያተረፉ የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር አዛዥ መኰንን ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

# ኰሎኔል
# ጣሰው ሞጆ

## 1912 - 1967



ኮሎኔል ጣሰው ሞጆ ለሀገራቸው ፴፱ ዓመት ቅን አገልግሎት የሰጡ የአምስት ዓመት ጀግና አርበኛና የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንጋች ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

ኰሎኔል ጣሰው ሞጆ ከባላንባራስ ሞጆ ሰን በቶና ከወ/ሮ መደምደሚያ ተስፋዬ በ፲፱፻፲፪ ዓ/ም በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በምንጃር ወረዳ ተወለዱ ። ኰሎኔል ጣሰው ሞጆ የአማርኛ ትምህርት የተማሩት በአባትና በእናታቸው ቤት በወግና በሥርዓት በሚያድጉበት ጊዜ ነበር ።

ፋሽስት ኢጣሊያን አገራችንን በ፲፱፻፳፰ ዓም በወረረበት ጊዜ ኰሌኔል ጣሰው በወጣትነት ዕድሜያቸው ከጀግኖች አርበኞች ጋር በመሆን በቡልጋ በረሃዎች ገብተው ጠላትን ተፋልመዋል። በወቅቱ በአርበኝነት ጎራ ግንባር ቀደም መሪ ከነበሩት ከፊታውራሪ አማረ ሻውል አባዘልስ ጋር ሆነው በሸንኮራ ፤ በቡልጋ ፤ በበሪኸት ፤በአሪርቴ ፤ በብቻሽ ፤ በዶዶታ ፤ በስቻትና በቅርጡ እየተዘዋወሩ እለት በእለት ጠላትን መግቢያና መውጫ ያሳጡ ጀግና ተዋጊ ነበሩ ።

ኰሌኔል ጣሰው ሞጆ ስለአገራቸው ክብርና ስለወገናቸው ፍቅር የታገሉ ፤ በየጦር ሜዳው ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ ቆራጥ መኰንን ናቸው። በሸንኮራ ወረዳ በጉጂ ኪዳነምህረት ፤ በብቸሽ ፤ በነጭ ድንጋይ ፤ በስቻት ፤ በቡልጋ ዶፋ ሚካኤልና በጉራም ላይ በተደረጉት አያሌ ጦርነቶች በአስደናቂ ሁኔታ ተዋግተው ታላቅ ጀብዱ ሠርተው ከፍተኛ ዝናን አትርፈዋል ።

የክፍል መሪያቸው የነበሩት ፊታውራሪ አማረ ሻውል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አርበኛው ጦር በሙሉ ወደ ደጃዝማች ከበደ ካሣ ሲቀላቀል ኰሌኔል ጣሰው ሞጆም ወደዚያው ተዛውረው በተድላ ማርያም ፤ በበረኸት ፤ በሰጠን ፤ በቤሎና መጠቅለያ ፤ በወሲልና ፤ በጉታ ገደል በተደረጉት እጅግ የሚዘገንኑ ጦርነቶች ወደር በሌለው ጀግንነት ተዋግተዋል ።

ፋሽስት ኢጣልያ ከኢትዮጵያ ተባርሮ ከወጣ በኋላ ኰሌኔል ጣሰው አገራቸውን በውትድርና ለማገልገል ከፍተኛ ፍላጎት ስላደረባቸው በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በጦር ሚኒስቴር የሠራዊቱ ባልደረባ ሆነው ተቀጠሩ ።

ወዲያው በውትድርና ሙያ ባሳዩት ብስለትና ብቃት የ፶ አለቃነት ማዕረግ አገኙ ። ቀጥሎም በ፲፱፻፴፯ ዓ/ም የም/መቶ አለቃ ሆኑ ።

ኰሌኔል ጣሰው ሞጆ በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ከክፍል ወደ ክፍል እየተዘዋወሩ በኃላፊነት ቦታ በመመደብ የረጅም ዘመን ቅን አገልግሎት ሰጥተዋል ።በዚህም ረጅም አገልግሎታቸው ከሃምሳ አለቃነት እስከ ኰሌኔል ማዕረግ ደርሰዋል ።

በመጨረሻም በነበራቸው ፍጹም የሆነ ታማኝነትና ሐቀኝነት በአለቆቻቸው ተመርጠው የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንጋች በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተው ። በደርግ ቁጥጥር ስር እስከዋሉበት ጊዜ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ አገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ።

ኰሌኔል ጣሰው ሞጆ ለአርበኝነት ተጋድሏቸውና ለረጅም ዘመን ግልጋሎታቸው ፤

— የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን

— የኢትዮጵያ የብር ኮከብ ኒሻን

— የአርበኝነት ሜዳይ ባለ አምስት ዘንባባ

— የድል ኮከብ ሜዳይ

— የመልካም አገግሎት ሜዳይ

— የአሥራ አምስት ዓመት አገልግሎት ሜዳይ

— የሃያ ዓመት አገልግሎት የወርቅ ሜዳይ

— በአንገት የሚጠለቅ የወርቅ ኒሻንና ሌሎች አራት ልዩ ልዩ ኒሻኖችና ሜዳልያዎች በጠቅላላው ፲፪ ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ተሸልመዋል ።

ኰሌኔል ጣሰው ሞጆ በአረመኔውና በፋሽስቱ ደርግ ተይዘው በቁጥጥር ሥር ከቆዩ በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ ም በግፍ ተገድለዋል ።

ኰሎኔል ጣሰው ሞጆ ወ/ሮ አበበች ተሰማን በሕግ አግብተው አራት ወንዶችና አምስት ሴቶች ልጆች ተከተዋል ።

www.ethipianorthodox.org

# ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ

## 1934-1967

ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ ታህሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ/ም በኢሊባቦር ክፍለ ሀገር መቱ ከተማ ተወለዱ ። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በቤተሰቦቻቸው ወደ አዲስ አበባ ተልከው (በባላባት ትምህርት ቤት) መድኃኔዓለም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው ፩ኛና መለስተኛ ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታተሉ ። በኋላም በአባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ለእጩ መኰንንነት ትምህርት ለ፲ኛ ኮርስ ተመዝግበው ፈተናውን ስላለፉ የቀለም ትምህርታቸውን አቋርጠው አባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ገቡ ።

በ፲፫/፱/፲፱፻፶፩ ዓ/ም በኮሌጁ የሚሰጠውን ትምህርት ፈጽመው የፖሊስ ሠራዊት ለ፲ኛ ጊዜ ካስመረቃቸው መኰንኖች አንዱ ሆነው ተመረቁ ።

ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ ያቋረጡትን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከሥራቸው ጋር አጣምረው በመማርና በማጠናቀቅ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተው የሕግ ዲፕሎማ አግኝተዋል ።

ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ በሠራዊቱ ከተቀጠሩ ጊዜ ጀምሮ ቃል የገቡበትን ዓላማ ሳይዘነጉ ሀገራቸውን ፣ መንግሥታቸውንና ወገናቸውን በቅንነት ያገለገሉ ታማኝ ዜጋ ነበሩ ።

ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ ለቅን አገልግሎታቸው በተለየዩ ጊዜያቶች የሜዳሊያ ሽልማቶች ፣ የምስክር ወረቀቶችና የምስጋና ደብዳቤዎች ከመንግስትና ከተለያዩ ቦታዎች አግኝተዋል ።

ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ ለአስቸኳይ ሥራ ትፈለጋለህ ተብለው በስልክ ከተጠሩ በኋላ መጀመሪያ በኮልፌ ፈጥኖ ደራሽ ማሰልጠኛ ታሰሩ ፣ ከኮልፌ ወደ ፪ኛ ክፍለ ጦር ሠፈር ፣ ከዚያም ወደ ቤተመንግሥት ተወስደው በእስራት ሲንገላቱ ከቆዩ በኋላ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በደርግ ጥይት በመገደል የግፈኞቹ ፋሽስቶች ሰለባ ሆነዋል ። ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ ባለትዳርና የሦስት ወንዶችና የሦስት ሴት ልጆች አባት ነበሩ ።



የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ዲፕሎም ምሩቅና የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ የነበሩት ሻለቃ ብርሃኔ ሜጫ ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን ለ፲፯ ዓመታት በቅንነት ያገለገሉ መኰንን ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ሻምበል
# በላይ ጸጋዬ አብርሃ
# 1936-1967



የሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቅና በአርሚ አቪዬሽን የሄሊኮ ፕተር አብራሪ የነበሩት ሻምበል በላይ ፀጋዬ የ፴፩ ዓመት ወጣት መኰንን ነበሩ ።

ሻምበል በላይ ፀጋዬ አብርሃ ከአባታቸው ከአቶ ፀጋዬ አብርሃና ከእናታቸው ከወይዘሮ ካሣ ጥቅምት ፱ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ/ም በአሥመራ ከተማ ተወለዱ ።

እድሜአቸው ለትምህርት እንደደረሰ አሥመራ ከተማ እስከ ፯ኛ ክፍል ተምረዋል ። ኋላም ከአ ባታቸው ጋር ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር ሄደው ደብረ ማርቆስ ከተማ በሚገኘው ንጉሥ ተክለ ሃይማ ኖት ትምህርት ቤት ለሁለት ዓመታት ተከታት ለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ፈጸሙ ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በደጃዝማች ወንድራድ ትምህር ት ቤት በአዳሪነት ተመዝግበው ለሁለት ዓመ ታት ከተከታተሉ በኋላ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተዛውረው የሁለተኛ ደረ ጃ ትምህርታቸውን በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም አጠናቀቁ ።

በኋላም ፤ በሐረር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር አካዳሚ በእጩ መኰንንነት ተመልምለው ወታደራዊ ሣይንስና አካዳሚክ ትምህርት ለሶስት ዓመታት ተከታትለው በጥቅምት ወር ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በዲፕሎም በመመረቅ የምክትል መቶ አለቃነት ማዕረግ አገኙ ።



www.ethipianorthodox.org

ም/መ አለቃ በላይ ፀጋዬ ደብረዘይት በሚ ገኘው የምድር ጦር አየር ወለድ ት/ቤት ሰል ጥነው የመጀመሪያ ደረጃ የአየር ወለድ ክንፍ ተቀብለዋል ።

ከዚያም በምድር ጦር አየር ክፍል (አርሚ አቪዬሽን) ተመድበው የመጀመሪያ ደረጃ የበረራ ትምህርት ከፈጸሙ በኋላ በአብራሪነት (ፓይለ ትነት) አገልግለዋል ።

ታታሪው መኰንን በሥራቸው ላይ ባሣዩት ብቃት በሐምሌ ወር ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ሙሉ የመቶ እልቅና አገኙ ። የመቶ አለቃ በላይ ፀጋዬ በ፲፱ ፻፷፫ ዓ/ም ለሄሊኮፕተር በረራ ትምህርት ወደ አሜሪካን አገር ተልከው ትምህርታቸውን በሚ ገባ አጠናቅቀው ከተመለሱ በኋላ በሄሊኮፕተር አብራሪነት አገልግለዋል ።

በምድብ ሥራቸው ላይ ባሣዩት ከፍተኛ ችሎታና ሥነ ምግባር በጥር ወር ፲፱፻፷፭ ዓ/ም የሻምበልነት ማዕረግ እድገት ተሰጣቸው ።

ሻምበል በላይ ፀጋዬ ከፍተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት የነበራቸው ወጣት መኰንን ከመሆናቸ ውም በላይ ወታደራዊ መንግሥት የሕዝቡን ሥልጣን በኃይል ቀምቶ ከመያዙ በፊት የተማ ሪዎች እንቅስቃሴ ደጋፊ ነበሩ ።

መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ደርግ በመሣሪያ አፈሙዝ ሥልጣን ሲጨብጥ ፤ ሻምበል በላይ ለደርግ መንግሥት ያላቸውን ተቃውሞ በግልጽ አሰምተዋል ። ደርግ ወደ ሙሉ ወታደራዊ አምባገነንነት ሲያመራ ወታደራዊ ክፍሎች ሁኔ ታውን በመቃወማቸው ፤ የደርግን እንቅስቃሴ በቅርብ ሆነው እየተከታተሉ ሁኔታዎችን ለጦር ክፍላቸው የሚያሳውቁ አባላት በየጦሩ ክፍሎች ተመረጡ ። የምድር ጦር አየር ክፍል ባልደረቦች ለዚህ ከፍተኛ ኃላፊነት ከመረጡዋቸው የሕዝብ ታማኝ ከሆኑ ሰዎች አንዱ ሻምበል በላይ ፀጋዬ ነበሩ ።

ደርግ ሻምበል በላይን ከጎኑ ለማሰለፍ ከፍ ተኛ ሙከራ ቢያደርግም ፤ ሻምበል በላይ እንዲ ቋቋም የፈለጉት ወታደራዊ ጁንታ ሣይሆን "ሕዝባዊ መንግሥት" በመሆኑ የደርግን ፍላ ጎት ማሟላት አልፈለጉም ። በዚህም ምክንያት ደርግን በግምባር ቀደምትነት ከሚመሩት መኰ ንኖች ጋር ከፍተኛ አለመግባባት ተፈጠረ ።

በዚሁ የከረረ ቅራኔ የተነሣ መኰንኑ መስ ከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በደርግ ቁጥጥር ሥር ውለው ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በግፍ ተገድለዋል ።

ሻምበል በላይ በምድብ ሥራቸው ላይ ትጉ ህና ታታሪ መኰንን ከመሆናቸውም በላይ መጻ ሕፍት የማንበብ ከፍተኛ ፍቅር የነበራቸውና በጓ ደኞቻቸው ዘንድ በጣም ተወዳጅ መኰንን ነበሩ።

ሻምበል በላይ የሰው ደም በጠማቸው ሥል ጣን ፈላጊ በሆኑት አረመኔ የደርግ ፋሽስቶች ውሣኔ በግፍ ቢገደሉም ሕይወታቸውን አሳል ፈው የሰውት "የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደርና የመምራት" ሥልጣን እንዲኖ ረው በመታገል በመሆኑ የቆሙለት ክቡር አላማ ሕያው ሆኖ ይኖራል ።



www.ethipianorthodox.org

# የመቶ አለቃ ተስፋዬ ታከለ 1942-1967

የመቶ አለቃ ተስፋዬ ታከለ ከወ/ሮ ታቦቴ ካሣሁንና ከባላምባራስ ታከለ ጣሰው በደሴ ከተማ መጋቢት ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ/ም ተወለዱ ።

እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በባህሉ መሠረት በቄስ ትምህርት ቤት ፊደል ቆጥረው ፤ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም በተፈሪ መኰንን ት/ቤት አጠናቀቁ ። ከዚያም አዲስ አበባ በሚገኘው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ገብተው የቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ትምህርት (የንግድ ትምህርት) በመከታተል ላይ ሳሉ ፤ ወታደራዊ ትምህርት ለመማር በነበራቸው ፍላጎትና ከፍተኛ ዝንባሌ ተገፋፍተው በ፲፱፻፷ ዓ/ም ሐረር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር አካዳሚ ገቡ ። በአካዳሚው ለሶስት ዓመት የሚሰጠውን የዕጩ መኰንንነት ኮርስ ፈጽመው በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም በምክትል መቶ አለቅነት በከፍተኛ ማዕረግ ተመረቁ ።

ከዚያም አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው አቪዬሽን እንዲሰሩ ተመድበው የአውሮፕላን አብራሪነት ትምህርት ሲከታተሉ ቆዩ ። ወጣቱ መኰንን በፈረንሳይ ፤ በየመን ፤ እንዲሁም በቻይና በአቪዬሽን ማእከላት ልምድ ካካበቱ በኋላ በሙሉ የመቶ እልቅና ማዕረግ የምድር ጦር አውሮፕላን አብራሪ ሆነው ተመደቡ ።

መኰንኑ ከልጅነት እድሜያቸው ጀምሮ በስፖርት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፏቸው ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ፤ በአካዳሚው ውስጥም በልዩ ልዩ የስፖርት ዓይነቶች ተሸልመዋል ።



የመቶ አለቃ ተስፋዬ ታከለ የአርሚ አቪየሽን አውሮፕላን አብራሪ ፣ የሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቅና በእስፖርትና በአካዳሚ ትምህርት የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ የ፳፬ ዓመት ወጣት ነበሩ ።

የመቶ አለቃ ተስፋዬ ታከለ በ፲፩ኛ ዕጩ መኰንኖች ኮርስ በተመረቁበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሽልማቶች ተቀብለዋል ።

በኮርሱ ወቅት በጠቅላላ ውጤት አንደኛ በመናሆቻቸው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የብር ዋንጫና የወርቅ ሜዳልያ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ተቀብለዋል ።

በኮርሱ ወቅት በአጠቃላይ በውድድሩ በሁለገብነት ብልጫ በማግኘታቸው በወቅቱ ኢትዮጵያን ይጎበኙ ከነበሩት ከሱዳኑ መሪ ፕሬዚዳንት ኒሜሪ የሻምላ ሽልማት ተቀብለዋል ።

በወታደራዊ ትምህርት ሁለተኛ በመሆን ከቀ/ኃ/ሥ የመጽሐፍ ተሸላሚ ሆነዋል ።

በአካዳሚክስ ትምህርት ሁለተኛ በመሆን ከቀ/ኃ/ሥ የመጽሐፍ ተሸላሚ ሆነዋል ።

በ፰፻ ሜትር ሩጫ አንደኛ በመውጣት የምስክር ወረቀት አግኝተዋል ።

በ፬፻ ሜትር ሩጫ ውድድር አንደኛ በመሆን የምስክር ወረቀት ተሸልመዋል ።

በ፻፲ ሜትር ነጠላ ሩጫ ውድድር ሁለተኛ ሆነው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

በዝላይ ውድድር ሁለተኛ ወጥተው የምስክር ወረቀት ተሸልመዋል ።

በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም መቶ አለቃ ተስፋዬ ታከለ የምድባቸው የጦር ኃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ሆነው ሲሰሩ በወቅቱ በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የአርሚ አቪዬሽንና የምድር ጦር መሐንዲስ የተቃውሞ ንቅናቄ በማድረጋቸው መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በቁጥጥር ሥር ዋሉ ።

የመቶ አለቃ ተስፋዬ ታከለ የአንድ ልጅ አባት ሲሆኑ ፤ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከ፷ ሰማዕታት አንዱ በመሆን ገና በአፍላ እድሜያቸው በግፍ ተገድለዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# የመቶ አለቃ
# በቀለ ወ/ጊዮርጊስ

## 1945-1967

የመቶ አለቃ በቀለ ወልደጊዮርጊስ ከአባታቸው ከአቶ ወልደጊዮርጊስ ጁሌና ከእናታቸው ከወ/ሮ ቦጋለች አምበሬ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፭ ዓ/ም አዲስ አበባ ተወለዱ ።

ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ መንግሥት ትምህርት ቤት ገብተው እስከ ፲፪ኛ ክፍል ተምረዋል ።

የመቶ አለቃ በቀለ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም በምድር ጦር መሐንዲስ መምሪያ ተቀጥረው እስከ ፲፱፻፷፮ አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ፤ እንዲሁም ከጓደኞቻቸው ጋር በመግባባት እየሰሩ ሳለ መምሪያው በደርግ ላይ አመጸ በሚል ሰበብ መኰንኑ በቁጥጥር ስር ውለው ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ከሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በ፳፪ ዓመታቸው በግፍ ተረሸነዋል ።

የመቶ አለቃ በቀለ የሥነጽሁፍ ችሎታ ስለ ነበራቸው በትምህርት ቤትም ሆነ በተቀጠሩበት የምድር ጦር መሐንዲስ መምሪያ በርካታ ጽሑፎችንና ግጥሞችን እንደጻፉ ይነገርላቸዋል ።

የመቶ አለቃ በቀለ ወልደጊዮርጊስ ያላገቡና አባታቸው በልጅነታቸው ስለሞቱ ያሳደጓቸውን እናታቸውን ፤ ታናሽ እህቶቻቸውንና ወንድሞቻቸውን የሚረዱና የሚንከባከቡ ሩህሩህ መኰንን ነበሩ ። መኰንኑ በቤተ ዘመዶቻቸውና በሚያውቋቸው ሰዎች ዘንድ በትህትናቸው የተወደዱም ነበሩ ።



ሩህሩህና የአባት አልባ ቤተሰብ አለኝታ የነበሩት የመቶ አለቃ በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ ገና በ፳፪ ዓመታቸው በወታደራዊ ደርግ ሕይወታቸው በአጭሩ ሊቀጭ ችሏል ።

www.ethipianorthodox.org

# ም/አስር አለቃ ተክሌ ኃይሌ

## 1949-1967

ምክትል አሥር አለቃ ተክሉ ኃይሉ ከአባቱ ከአቶ ኃይሉ ተክሌና ከእናቱ ከወ/ሮ ማሚቴ በቀለ በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም/ በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ ።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ይርጋዓለም በሚገኘው የራስ ደስታ ትምህርት ቤት ከጨረሰ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንና የአውቶ ሜካኒክነት ሙያ አዲስ አበባ ተግባረዕድ ትምህርት ቤት አጠናቋል ።

በምድር ጦር የመሀንዲስ ክፍል በሚያገለግልበት ወቅት ለወታደራዊ ምህንድስና ሙያ ወደ አሜሪካ አገር ተልኮ ኮርሱን ተከታትሎ ተመልሷል ።

በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም/ ሰኔ ወር ላይ በበታች መኰንኖችና ተራ ወታደሮች ተቋቁሞ ለነበረው አስተባባሪ ኮሚቴ (ወታደራዊ ደርግ) ተመርጦ ወታደራዊው ክፍል ስልጣን ይዞ መቆየት እንደሌለበትና ለሕዝቡም ማስረከብ እንደሚገባው ለኮሚቴው አባሎች በማስረዳቱና በመታገሉ በቁጥጥር ሥር ውሎ በግፍ የተገደለ ወጣት ነው ።



የ፲፰ ዓመቱ ተክሉ ኃይሉ ፣ የተግባረ ዕድ ት/ቤት ምሩቅ ፣ የምድር ጦር የምሕንድስና ክፍል ባልደረባ ፣ "ወታደሩ ሥልጣን ይዞ መቆየት የለበትም ፣ ሥልጣን ለሕዝቡ መመለስ አለበት" በማለቱ ከ፳ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በግፍ የተገደለ ወጣት ነው ።



www.ethipianorthodox.org

## ሐምሌ ፣ ፫ ፣ ፭ ፣ ፯ ፣ እና ፲ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ተወስደው የተሰዉ ሰማዕታት አጭር የሕይወት ታሪክ

በሐምሌ ወር ፲፱፻፷፯ ዓ/ም/ ደርግ አን ዳንድ እስረኞችን ቀድሞ ከነበሩበት መውሰድ ጀመረ ። ለቤተሰብ የሚነገረው ወደ ሌላ ቦታ ተዛውሯል የሚል ነበር ።

ከታላቁ ቤተመንግሥት እስር ቤት መው ሰድ የተጀመረው ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በ፰ ሰዓት ላይ ነበር ። በዚሁ ዕለት ሁለት እስ ረኞች ከ፪ ቁጥር ተጠሩ ። እንዳጋጣሚ ቤተሰብ ስለነበሩ ዘመድ አስጠርቷቸዋል በሚል ግምት ክፉውን የጠረጠረ እስረኛ አልነበረም ።

አሥር ሰዓት ድረስ ባለመመለሳቸው የቀ ሩት እሥረኞች መጠራጠር ሁኔታውንም ማው ጣት ማውረድ ጀመሩ ። ሁሉም በር በሩን ሲመ ለከቱ ፲፪ ሰዓት ሆነ ። በሩን የዘጉት ወታደሮች ተጠይቀው ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረዋል የሚል መልስ ሰጡ ።

ስለተወሰዱት ጓደኞቻቸው እስረኞች አዝ ነው ሳለ ሐምሌ ፭ ቀን ሐሙስ መጣ ። ፭ ሰዓት ተኩል ላይ ቀዩ ደወል ያለወትሮው ተደወለ ። እስረኞቹም በየክፍላቸው እንዲገቡ ታዘዙ ። እስ ረኛው የበለጠ ተደናገጠ ። የአንድ ቁጥርና የሁ ለት ቁጥር ሀላፊዎች ተጠሩ ። የሁለት እስረኞች ስም ከተጠራ በኋላ ብርድ ልብስና የሽንት ቤት ወረቀት ይዘው በአስቸኳይ እንዲወጡ ተነገረ ። ከተጠሩት እስረኞች አንዱ ትዕዛዙን የተቀበለው የቁጥር ፪ አለቃ ራሱ ነበር ። ሁለቱም እስረኞች ከቁጥር ፪ ነበሩ ።

ከዚያን ቀን ጀምሮ እያንዳንዱ እስረኛ እቃ ውን ማደራጀት ጀመረ ። ኑዛዜውን ማስታወሻ ውን ፣ መልዕክቱን እየጻፈ በሕይወት ከተረፍክ ለሚስቴ ፣ ለልጄ ለአባቴ ለእናቴ አድርስ በመባባል ከሞት ጋር ቀጠሮ ያዘ ። ሐምሌ ፯ ቀን እስረኛው ተራውን ሲጠባበቅ ቢውልም ማንም ሰው ሳይጠራ አለፈ ።

ሐምሌ ፯ ቀን በተለመደው ሰዓት ተደ ወለ ። ወታደሮቹ የእስር ቤቱን በር ዘጉ ። አለቆቹ ተጠሩ ።የአራት እስረኞች ስም ተነገራቸው ብርድ ልብስና የሽንት ቤት ወረቀት ይዘው በአስ ቸኳይ እንዲወጡ ተባለ ። ከቁጥር ፪ አንድ ከቁ ጥር ፩ ሦስት ሰዎች ነበሩ ።

የቅዳሜው ጥበቃ ጠንከር ያለ ነበር ። ከእስር ቤቱ አጥር ውጭ መሳሪያ የያዙ ወታደሮች ግራና ቀኝ ተሰልፈው ይጠብቁ ነበርና እየተሰነባበቱ መለያየቱ እንደሚቀጥል የተሰማው እሥረኛ ዝግጅቱን ቀጠለ ። ብርድ ልብስ ከቤት እንዲ መጣለት እስከመጠየቅ ።

ሐምሌ ፰ እና ሐምሌ ፱ አለፈ ። ሐምሌ ፲ ቀን ግን በተለመደው ሰዓት ደወል ተደወለ ። እስረኞች ወደየክፍላቸው እንዲገቡ ተነገረ ። አለቆች ተጠሩ ። ከቁጥር አንድ አንድ እሥረኛ ተወሰዱ ።

የሄዱት እሥረኞች ወደ ሌላ ቦታ ተዛው ረዋል በማለት ዕቃቸው ተዘጋጅቶ እንዲወጣ አለ ቆች ትእዛዝ ተሰጣቸው ።

በዚያኑ ሰሞን ከአራተኛ ክፍለ ጦር እና ከሌሎች እስር ቤቶች በመሰል ሁኔታ የተወሰዱ እስረኞች ነበሩ ። ሆኖም ስለሁሉም አገዳደል ደርግ የተወው የጽሁፍ መረጃ ስለመኖሩ እስከ ዛሬ አንዳችም ፍንጭ ስላልተገኘ ሁኔታው ተዳ ፍኖ ቀርቷል ።

የአይን ምስክር ነን የሚሉ አንዳንድ ሰዎች በሐምሌ ወር ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የተወሰዱት እስረ ኞች የተገደሉት እንጦጦ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ መኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በሽቦ እየ ታነቁ መሆኑን ይናገራሉ ። በእርግጥም አጽማ ቸው የተገኘው በተባለው አካባቢ ነው ።

ሐምሌ ፫ ፣ ፭ ፣ ፯ እና ፲ ከታላቁ ቤተ መንግ ሥት እና ከአራተኛ ክ/ ጦር የተወሰዱት እስ ረኞች የሕይወት ታሪክ እንደሚከተው ቀርቧል ።



www.ethipianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

## 1902-1971



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሚያዝያ 16 ቀን 1902 ዓ.ም. በጎጃም ክፍለ ሀገር ደብረ ኤልያስ ተወለዱ ፤ ብፁዕነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሁለተኛ ፓትሪያርክ ነበሩ ።

ብፁዕ አቡነ ተዎፍሎስ ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም. ከታላቁ ቤተመንግሥት እስር ቤት ተወስደው ባልታወቀ ቀን ተገድለዋል ።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አፅም በመካነሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አርፏል ።

www.ethipianorthodox.org

# ጸሐፊ ትዕዛዝ
# ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ

## 1898 - 1971



ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ በሚኒስትርነት ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ፀሐፊና የዘውድ ምክር ቤት አባል በመሆን ሀገራቸውን ለ፴፫ ዓመታት ያገለገሉ ታላቅ ሰው ነበሩ ።

ሠላሳ ሶስት ዓመት ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን በቅንነት ያገለገሉት ክቡር ፀሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ ከእመት ደጅይጥኑ ጋረደውና ከአቶ ኪዳነ ወልድ ቢሰውር በአዲስ አበባ ከተማ "አጣሪ ሠፈር" ይባል በነበረው አካባቢ በ፲፰፻፺፰ ዓ/ም ተወለዱ ።

በዚሁ ከተማ በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የአማርኛና መንፈሳዊ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ በስዊድን ወንጌላዊት ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብተው በአዳሪነት ዘመናዊ ትምህርትና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተምረዋል ። በእንግሊዝ አገር በስደት ላይ በነበሩበት ዘመንም ከሎንደን ከተማ ፒትማን ኮሌጅ ገብተው የቀለም ትምህርት ተከታትለዋል ።

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ ለአጭር ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደሠሩ ወደ እንግሊዝ ለጋሲዮን ተዛውረው በአስተርጓሚነት ተቀጠሩ ። በዚሁ ሥራ ላይ እንዳሉ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ/ም ግራሲያኒ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ለአዲስ አበባ ሕዝብ ንግግር ለማድረግ ሲሞክር በአገር ወዳዶች በተጣለው የቦንብ አደጋ አፀፋ የፋሺስቱ ወታደሮች በሰላማዊ ሰዎችና በተማሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ባደረሱት ጭፍጨፋና እስር ክቡርነታቸውም የሴራው ተባባሪ ናቸው በሚል ሰበብ በድንገት ተይዘው ሲታሠሩ ከፍተኛ ምርመራና ስቃይ ደርሶባቸዋል ። ምርመራቸው የተካሔደው በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በአሥመራና በምጽዋ ጭምር ነበር ።

ከየካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፱ እስከ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ በአዲስ አበባ ፣ በኢዚናራ ፣ በሌንጌ



www.ethipianorthodox.org

ቦኮና በናፖሊ በእሥራት ላይ ቆዩ ። በኋላም በእን ግሊዝ መንግሥት ጥያቄ ከእስር ተለቀው ወደ ሎንዶን ተሰድደው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ ሀገራቸው ሊመለሱ በቅተዋል ።

ክቡር ፀሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ከጠላት ወረራ በኋላ ከ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ጀምሮ ፤

ሀ/ የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ፀሐፊ ፤

ለ/ ፀሐፊ ትእዛዝ ተብለው የጽሕፈት ሚኒስትር

ሐ/ የግቢ ሚኒስትርና

መ/ በመጨረሻም የዘውድ ምክር ቤት አባል በመሆን በከፍተኛ ማዕረግና ኃላፊነት እስከ የካቲት ወር ፲፱፻፷፮ ድረስ ለ፴፫ ዓመታት አገራቸውን በቅንነትና በታ ማኝነት አገልግለዋል ።

ፀሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ ከ፲፱፻፴፫—፲፱፻፵፯ ዓ/ም የግርማነታቸው ልዩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሆነው ሳለ ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል በጊዜው በውጭ አገር ሰዎች ይካሄድ የነ በሩ እንደ ቤት ሳይዳ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስ ፒታል ፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ፣ የግርማዊት እቴጌ የእጅ ጥበብ ትምህርት ቤትና የሐረር ጦር አካዳሚ የቴክኒክ መሥሪያ ቤቶች በማስተባበር የቅርብ ባልደረባ ሆነው ሥራቸው እንዲቃና አድርገዋል ።

የጽሕፈት ሚኒስትር በነበሩበት ከ፲፱፻፵፯— ፲፱፻፶፪ ዓ/ም ባለው ጊዜ መንግሥታዊ ትእዛዞችን በማስተላለፍ ፣ ሕግ በማወጅና ሹመት ሽልማት በመስጠት ሌላም መንግሥታዊ ተግባራት ከማከናወናቸውም በላይ የተሻሻለው ሕገ መን ግሥት በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም ሲታወጅ በታላቁ ማኅተም ጠባቂነታቸው በፓርላማ ውስጥ በተደረገው የተ ለየ ሥነ ሥርዓት ላይ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በሕገ መንግሥቱ ላይ ፈርመዋል ። በልዩ ፀሐፊነታቸው ዘመናትም ሆነ ከ፲፱፻፶፪—፲፱፻፷፮ ዓ/ም የግቢ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ የቤተ መንግሥቱ ሕግና ሥርዓት እንዲከበር በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ።

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ ከምድብ ሥራቸው ሌላ ለረጅም ዘመናት የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው በበጎ ፈቃደኝነት ማህበራዊ አገልግሎት አበርክተዋል ። በተጨማሪም የል ዕልት ፀሐይና የልዑል መኰንን መታሰቢያ ሆስፒ ታሎች ለማቋቋም በተደረገው ጥረት የሁለቱም ድርጅቶች የእርዳታ አሰባሳቢ ቦርድ ሰብሳቢ በመሆን የእርዳታ ገንዘብ አሰባስበዋል ።

የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ረዳት በመሆንና በልዩ መልእክተኛነትም ከአምሳ ያላነሱ አገሮችን ጎብኝተዋል ። በነዚሁም አገሮች በተደረጉ ንግ ግሮች ተካፍለዋል ። በተለያዩ የፕሬስና የሰላም ጉባኤዎች ከኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን አባሎች አንዱ ሆነው ከመካፈላቸውም ሌላ የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ መልእክተኛ ሆነው በፕሬዚዳንት ንክሩህማና በፕሬዚዳንት አይዘናወር የቀብር ሥነ ሥርዓት ፣ በፕሬዚዳንት ታብማን መታሰቢያ ምረቃ ሥነ ሥርዓት ፣ በሱዳንና በታንዛኒያ የነፃነት ክብረ በዓላት ላይ ተገኝተው ከየመንግሥታቱ መሪዎች ጋር አገራችንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በቅርብ ተነጋግረዋል ።

ክቡርነታቸው ላገራቸውና ለመንግሥታቸው ላበረከቱት መልካም ሥራና የአርበኝነት ተግባር የሚከተሉትን ኒሻንና ሜዳይ ተሸልመዋል ።

፩/ የምኒልክ ኮርዶን ፤

፪/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኮርዶን ፤

፫/ የምኒልክ ታላቅ መኰንን ፤

፬/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ታላቅ መኰንን ፤

፭/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የመኰንን ደረጃ ፤

፮/ የሥላሴ የፈረሰኛ ደረጃ ፤

፯/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ፈረሰኛ ደረጃ

፰/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ባለአምበል ፤

፱/ የውስጥ አርበኛ ሜዳይ ፤

፲/ የድል ኮከብ ሜዳይ ፤

፲፩/ የ፳፭ኛው የድል በዓል ሜዳይ ተሸልመ ዋል ።

እንደዚሁም ከእንግሊዝ ፣ ከፈረንሣይና ከሌ ሎች ሃያ ሰባት የውጭ አገር መንግሥታት ከፍ ተኛ የክብር ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

እኒህን የ፹፫ ዓመት አዛውንት የደርግ መን ግሥት ከአምስት ዓመታት በላይ በእስር ካቆያቸ ው በኋላ ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ከእስር ቤት ወስዶ የት እንዳደረሳቸው ሳይታወቅ ቆይቶ ነበር ። በመጨረሻም በልዑል አሥራተ ካሣ ግቢ ውስጥ ገድሎ የቀበራቸው መሆኑ በክትትል ስለተደረሰ በት አጽማቸው ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ከተጣለበት ወጥቶ በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያ ያን በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል ።

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ ሁለት ሴት ልጆች ተክተዋል ።

www.ethipianorthodox.org

# ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም

## 1924-1971

ክቡር ደጃዝማች ካሣ ከደጃዝማች ወልደ ማርያም ኦዳ እና ከወ/ሮ አስካለ ማርያም ጀቴ በጋሞጎፋ ክፍለ ሀገር ፣ በልታ ከተማ መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ/ም ተወለዱ ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ አባታቸው ደጃ/ወልደ ማርያም በሰሜን ግንባርና በማይጨው በአዝማችነት ከተዋጉ በኋላ ከማይጨው መልስ በደቡብ ዘመቻውን የቀጠሉ ቢሆንም በተዋጊዎች መካከል ቁስለኛና ታማሚ በመብዛቱና ሕክምና በመታጣቱ በኅዳር ወር ፲፱፻፴ ዓ/ም መላ ቤተ ሰባቸውን ይዘው ወደ ኬንያ ተሰደዱ ።

የጦርነቱ ወላፈን ፣ የጊዜው ወጀብ ፣ የስደቱ ወቅት ውሽንፍርና መከራ በዚያን ጊዜ ዕድሜያቸው ፮ ዓመት ያህል ለነበረ ለጋ ልጅ አእምሮ ዕትሙን ሳይተው አላለፈምና ደጃ/ካሣ ወ/ማርያም በሕይወት ዘመናቸው ላሳዩት ጥልቅ የሀገር ፍቅርና የኃላፊነት ስሜት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ አልቀረም ።

ደጃ/ካሣ ወልደ ማርያም በኬንያ የኢትዮጵያ ስደተኞች ት/ቤት የጀመሩትን የአንደኛ/ደረጃ ትምህርት በ፲፱፻፴፯ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በአዲስ አበባ ሊሴ ገብረማርያም ት/ቤት አጠናቀቁ ። የ፪ኛ ደረጃ ትምህርት በጄኔራል ዊንጌት ት/ቤት ከፈጸሙ በኋላ ወደ ካናዳ ሄደው በዓለም አቀፍ ሕግ የባችለር ዲግሪ ፣ ከዚያም በአሜሪካን አገር ከዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ በሕዝብ አስተዳደር በማስትሬት ዲግሪ ተመርቀዋል ።

ክቡር ደጃ/ካሣ ወልደ ማርያም የዕውቀት መሣሪያ ይዘው ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ ፣

ሀ/ ከ፲፱፻፶፩—፲፱፻፶፫ ዓ/ም በግርማዊነታቸው ልዩ ጽ/ቤት በረዳት ልዩ ፀሐፊነት፣



ክቡሮ ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም በእርሻ ሚኒስትርነት ፤ በወለጋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴነት ፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትነት ፤ እና በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጽ/ቤት ልዩ ጸሐፊነት ሀገራቸውን ያገለገሉ ፤ በዕውቀት የበሰሉ ፤ በአገራቸው ባሕል የበለፀጉ ፤ በሀገር ፍቅርና በኃላፊነት ስሜት የዳበሩ ምሁር ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

ለ/ ከ፲፱፻፶፫—፲፱፻፶፬ በዚሁ ጽ/ቤት የማዕረግ እድገት አግኝተው በልዩ ፀሐፊነት ፤

ሐ/ ከ፲፱፻፶፬—፲፱፻፷፩ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ፤

መ/ ከ፲፱፻፷፩—፲፱፻፷፮ በደጃዝማችነት ማዕረግ የወለጋ ክ/ሀ አስተዳዳሪ ፤

ሰ/ ከ፲፱፻፷፮—፲፱፻፷፯ የእርሻ ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል ።

ክቡር ደጃ/ካሣ ከላይ በተዘረዘሩት የሥራ ክፍሎች ሁሉ ቅን አገልግሎታቸውን በትጋትና በሙሉ ችሎታ የሰጡ ሀገር አፍቃሪ ፣ የሕዝብ አገልጋይ ነበሩ ።

ለሀገራቸው ከአበረከቱት ቅን አገልግሎት ጎልቶ የሚታየው በሀገራችን የመጀመሪያው በሆነው ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ጊዜ ለተቋሙ ሥራ መልካም አጀማመር ያደረጉት ጥረት ነበር ። ዩኒቨርስቲው የእውቀትና የምርምር ምንጭ እንዲሆን ፣ በትምህርት ዓይነትና ደረጃ ፣ እንዲሁም በሥነ ሥርዓት አጠባበቁ ከጅምሩ አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረው በልዩ ጥንቃቄና ትጋት ፣ ትዕግሥት ባልተለየው ቆራጥነት ያበረከቱትን አገልግሎት የሙያ ጓደኞቻቸው ሁሉ ሲያስታውሱት ይኖራሉ ።

ደጃዝማች ካሣ ሀገራችን ወደፊት በሕክምና አገልግሎት ራስዋን ትችል ዘንድ ኢትዮጵያውያን ሐኪሞች ሙያውን የሚቀስሙበትን የሕክምና ፋኩልቲ ፣ ለሰላማዊ ኑሮ አስፈላጊ የሆነው የሕግ ሥርዓት የበለጠ ይሰፍን ዘንድ የሕግ ባለሞያዎችን የሚያፈራና በሥራ ላይ የሚገኙትም ዳኞች ፣ ጠበቆችና አቃብያነ ሕግ የእውቀት አድማስ የሚያዳብሩበት የሕግ ፋኩልቲ እንዲሁም በንግድ ፣ በኢንዱስትሪና በፋይናንስ ማኔጅመንት ዘዴና ስልት ዘመናዊ እውቀት የሚያቀዳጅ የቢዝነስ ኮሌጅ ተቋሞችን ዩኒቨርስቲው እንዲጎናጸፍ አድርገዋል ።

ጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ወግና ባሕል ተመርምሮ ፣ ተሰብስቦና ተመዝግቦ ለትውልድ እንዲተላለፍ የኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት በዩኒቨርስቲው የተቋቋመው በዚሁ በደጃ/ካሣ ፕሬዚዳንትነት ወቅት ነበር ። የአገሪቱን የድራማና የሙዚቃ ችሎታ ለማበልጸግ ባሕላዊ ሙዚቃንም ፈልፍሎ አውጥቶ ማዳበር እንዲቻል ባሕል ማዕከል በዚሁ ወቅት ተቋቋመ ። ሌላው በዩኒቨርስቲው እንዲቋቋም ከተደረጉት አዳዲስ ተቋማት በዕደ ማርያም ት/ቤት መምህራን የመማር ማስተማርን ዘይቤ የሚለማመዱበትና የሚመራመሩበት ነበሩ ።

የመማር የማስተማርን ሂደት ለማገዝና የተማሪዎችንና የመምህራንን የምርምር ፍላጎት ለማጎልበት የተቋቋመው ሌላው አዲስ ተቋም ኬኔዲ መጻሕፍት ቤት ነበር ።

ተማሪዎቻቸውን በዲፕሎም ብቻ ያስመርቁ የነበሩት የጎንደር ጤና ጥበቃ ኮሌጅ ፣ ስኩል ኦፍ ሶሻል ሳይንስና የሕንፃ ኮሌጅ የመማር ማስተማር ደረጃቸው ወደ ዲግሪ ከፍ ብሎ የአገሪቱን የተማረ ኃይል ለማጎልበት ችለዋል ።

በዋነኛነት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አዳዲስ ተቋማት ለማቋቋም ፣ ነባሮቹን ለማስፋፋትና እያደገ ከመጣው የተማሪዎች ቁጥር ጋር የተመጣጠነ አገልግሎት ለማበርከት እንዲቻል የአርት ፣ የቴክኖሎጂና የኬኔዲ መጻሕፍት ቤት ሕንፃዎች በስድስት ኪሎና አምስት ኪሎ ቅጥር ግቢዎች ተሠርተዋል ።

ክቡር ደጃ/ካሣ ወልደ ማርያም የዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት በነበሩበት ጊዜ የመማር ማስተማርን ሂደት ለማጎልበት እንዲቋቋምና እንዲስፋፋ ላደረጉት አዲስና ነባር ተቋማት ሕንፃዎች ማሠሪያ ገንዘብ እንዲሁም መምህራን ከውጭ አገር መንግሥታት በእርዳታ እንዲገኙ ፣ ከአገር ውስጥም መንግሥት ተገቢውን በጀት እንዲመድብ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ጅምራቸው ውጤታማ እንዲሆን ረድተዋል ።

ደጃ/ካሣ ወ/ማርያም የትምህርት አድማስ በዩኒቨርስቲ ደረጃ እንዲስፋፋና እንዲጎለብት ፣ የመማር ማስተማርና የምርምር ተግባሮች ፈር እንዲይዙ ከማስቻላቸውም ሌላ ተማሪዎች በገጠርና በከተማ መካከል ያለውን የኑሮ ልዩነት ተገንዝበው በሥራ ዓለም ሲሰማሩ የሚገጥማቸውን ችግር በመቋቋም ጠቃሚ አገልግሎት ለሀገራቸው ማበርከት ይችሉ ዘንድ ለአንድ ዓመት በገጠር ተሰማርተው የሕዝቡን ሕይወት እየኖሩ እውቀታቸውን እንዲያካፍሉ የቀየሱት ፕሮግራም የተማሪውን የማህበራዊ ኑሮ አድማስ ለማስፋት ከመርዳቱም በላይ ማይምነትን ለመቅረፍና የመምህራንን እጥረት ለመቋቋም አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ባጠቃላይ ክቡር ደጃ/ካሣ ወልደማርያም የመማር ማስተማር ሂደት እንዲጎለብት ባደረጉት ተከታታይ ጥረት ዩኒቨርስቲው በዓለም አቀፍ ዩኒቨርስቲዎች ዘንድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታዋቂነትና ተቀባይነት እንዲያገኝ አስችለዋል ። ከዚህ ሌላ በአፍሪካ ዩኒቨርስቲዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት ተፈጥሮ የምርምር ፣ የመምህራንና የተማሪዎች ልውውጥ እንዲኖር ባደረጉት ጥረት የተቋቋመው የአፍሪካ ዩኒቨርስቲዎች ማህበር ዛሬ የሚያስመሰግኑ አያሌ የጋራ ጥቅም ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል ።

www.ethipianorthodox.org

ደጃ/ካሣ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ሆነው የነቀምቴ ከተማን መንገድና በክፍለ ሀገሩ ሌሎች መንገዶችን በማስከፈት እንዲሁም የውጭ አገር እርዳታን በመጠየቅ መሬት የሌላቸውን ገበሬዎች በማስፈር አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ያደረጉት ጥረት ሌሎች የሚጠቀሱ ክቡር ተግባሮች ናቸው ።

ደጃ/ካሣ በዚህ ክፍለ ሀገርና በሌሎችም በአገለገሉባቸው መ/ቤቶች ሁሉ በቅንነታቸውና በሥራ ችሎታቸው የታወቁ ፣ በሥራ ባልደረቦቻቸውና በሕዝቡም ዘንድ መወደድና አክብሮትን ያተረፉ ስመጥር ምሁር ነበሩ ።

ደጃዝማች ካሣ ወ/ማርያም ለእርሻ ሚኒስትርነት ሲመረጡ ለአገር እድገት የነበራቸውን ጽኑ ምኞትና የሕዝብ ፍላጎት ወደፊት ለማራመድ የሚያስችል ዓይነተኛ ዕድል የገጠማቸው መስሏቸው ጥሪውን የተቀበሉት በደስታ ነበር ። በዚያ ሥራ ላይ ባሳለፉት አጭር ጊዜ ለዘላቂ የእድገት እቅድ መቃናትና መፋጠን ከአደረጉት አስተዋጽኦ ሌላ ፣ በተለይም በጊዜው የተከሰተውን የድርቅ ችግር ማቃለል የሚያስችል እርዳታ ለመጠየቅ ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ጥረት በማድረግ ላይ ሳሉ የ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የመንግሥት ለውጥ ተደረገ ።

በዚህ ጊዜ የለውጡ አካሄድ የተሳሳተ አቅጣጫ ስለያዘ ፣ እስኪስተካከል ድረስ በውጭ እንዲቆዩ ምክር ቢደርሳቸውም የልብ ቅንነትና የሀገር ፍቅር ስላሸነፋቸው ከፉም ነገር ቢሆን በሀገራቸው ላይ ሆነው መቀበልን በመምረጥ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ። እንደተፈራውም የሥልጣን ፍላጎት ያሰከረውና ራስ ወዳድ የሆነው ወታደራዊ ደርግ ከራሱ በስተቀር ሌላውን ሁሉ ፈልጎ ማጥፋትና ዓላማው አድርጎ የተነሳ በመሆኑ እኒህን ውድ የኢትዮጵያ ልጅ ወደ አገራቸው እንደተመለሱ ሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ተይዘው በቁጥጥር ሥር እንዲቆዩ አደረገ ።

በእውቀት የበሰሉ ፣ በሀገራቸው ባሕል የበለፀጉ ፣ በግብረገብነት የታነጹት እኒህ ምሁር ራሳቸው የዚያ የመራራ እሥር ቤት ሕይወት ምርኮኛ ሆነው ሳለ ፤ የሌሎችን ችግርና ሸክም ለማቃለል ማናቸውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጠው የተነሱ ስለነበር በሚናገሩት ፣ በሚሠሩትና በየዕለት ኑሯቸው የሚያሳዩት ምሳሌ ለሌሎች ጽናትና ደስታን የማስተላለፍ ኃይል ነበረው ።

በእስረኞች ሁሉ ላይ የሞት ጥላ ባንዣበበበት በዚያ የጨለማ ወቅት ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፷፯ የደርግ የሞት መልእክተኞች ከያዙት የእስረኞች ስም ዝርዝር የእርሳቸው ስም ሲጠራ በረጋ መንፈስ የኅሊና ፀሎት አድርሰው ፣ ወዲያው ተከታትሎ ስማቸው የተጠራውን የፓትርያርኩን መስቀል ተሳልመው ፣ በቆራጥነት መንፈስ ወደ ተጠሩበት ቦታ አመሩ ። ይህም አድራጎታቸው የእውነተኛ አማኝ ተጓዥ ምሳሌ አድርጓቸዋል ።

ደጃዝማች ካሣ ከምድራዊው ሕይወት ከመለየታቸው በፊት ፣ በእስር ቤት እያሉ ለሌሎች አገልግሎት ከሚያውሉት የሚተርፋቸውን ጊዜ ቁም ነገር ላይ በማዋል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስተያያ (Bible Concordance) ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉመው ረቂቁ ለኅትመት ዝግጁ ሆኖ በእጃቸው ይገኝ ነበረ ። ለስማቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ መጽሐፉ እንደሚታተም ተስፋ ተደርጓል ።

ክቡር ደጃዝማች ካሣ ለመልካም አገልግሎታቸው ከአገራቸውና ከውጭ አገር መንግሥታት ምስክር የሚሆኑ አያሌ የክብር ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች ተሸልመዋል ።

ክቡር ደጃ/ካሣ ወልደ ማርያም ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፱ ከልዕልት ሰብለ ወንጌል ደስታ ጋር በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በተክሊል ተጋብተው እስከ ዕለተሞታቸው በሕገ እግዚአብሔር ፀንተው ኖረዋል ።

ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በተወለዱ በ፵፯ ዓመታቸው በግፍ በወታደራዊ ደርግ በድብቅ ተገድለው ከዚህ ዓለም ሲለዩ ከውድ ባለቤታቸው ከልዕልት ሰብለ ደስታ አራት ሴት ልጆችና አንድ ወንድ ልጅ አፍርተዋል ።



www.ethipianorthodox.org

# አቶ
# ሰይፉ ማህተመ ሥላሴ

## 1916-1971



ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ የኢትዮጵያን የመብራትና የኃይል ምንጭ መሠረት የጣሉና የኢትዮጵያን ሥርዓተ ትምህርት በመለወጥ የሕዝቡን ምርታማነት ለማሳደግና ሥራ አጥነትን ለማስወገድ ጥረት ያደረጉ ሚኒስትር ነበሩ ።

ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመ ሥላሴ ከቡልጋው ተወላጅ ከክቡር ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀልና ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የዘር ሀረግ ከሚወለዱት ከክብርት አምሳለ ወርቅ ከፈተው የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፲፮ ዓ/ም አዲስ አበባ ተወለዱ፤

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በእናት አባታቸው ቤት በቀድሞው ወግና ሥርዓት መሠረት አስተማሪ ተቀጥሮላቸው የግብረገብና የአማርኛ ትምህርት ተማሩ ፤ ዳዊትንም ደገሙ ። ከዚህ በኋላ ዘመናዊ ትምህርት ለመማር በመጀመሪያ ተፈሪ መኰንን ት/ቤት ፤ ከዚያም አምቦ የእርሻ ት/ቤት እንዲሁም ደሴ በሳላይሽ ት/ቤት ገብተው ልዩ ልዩ የቀለምና የእርሻ ሙያ ትምህርት ከመከታተላቸውም በላይ የእንግሊዝኛና የፈረንሣይኛ ቋንቋዎችን ፋሺስት ኢጣልያ አገራችንን እስከወረረበት ጊዜ ድረስ ተምረዋል ። ከየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ/ም እልቂት በኋላ አዲስ አበባ በመጡ እንደተረጋጋች በፕረንቸፒ ዲፒዮሞንቴ ኢጣልያ ት/ቤት ገብተው የኢጣልያንኛ ቋንቋ ተከታትለዋል ።

ፋሽስት ኢጣልያ ከሀገራችን ከተባረረ በኋላ በልዑል መርዕድ አዝማች አስፋወሰን ኃይለ ሥላሴ ግቢ በእልፍኝ አሽከርነት ተመልምለው አገልግለዋል ። በዚህ የአገልግሎት ጊዜ ደሴ በሆጤ የውትድርና ካምፕ ገብተው የተመደበላቸውን የውትድርና ኮርስ በመፈጸማቸው የመቶ አልቅና ማዕረግ ከልዑልነታቸው ተቀብለዋል ።

በቅን ለአገለገለ ሠራተኛ ምን ጊዜም ውለታ መላሽ የሆኑት ልዑል አልጋ ወራሽ የወጣቱን የሰይፉን ትጋትና አስተዋይነት በመመልከት በቀለም ትምህርት እንዲገፉ አደረጉ ። አቃቂ አድቬንቲስት ሚሲዮን ት/ቤት ገብተው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመቀጠል ላይ እንዳሉ በትጋታቸው

www.ethipianorthodox.org

ተመርጠው ከልዑልነታቸው ልዩ ግምጃ ቤት እየተከፈላቸው ከፍተኛ ትምህርት እንዲማሩ አሜሪካን አገር ተላኩ ።

በ፲፱፻፴፱ ዓ/ም አሜሪካን አገር ሄደው መጀመሪያ በዩኒየን ኮሌጅ ፣ ኔብራስካ ፤ ከዚያም በጉስታቭ አዶልፉስ ኮሌጅ ፣ ሚኒሶታ ገብተው በኤሌትሪካል ኢንጂኔሪንግ የባችለር ዲግሪ በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም ተመረቁ ።

በ፲፱፻፵፬ ዓ/ም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን ሚኒስቴር በኤክስፐርትነት ተመድበው በማገልገል ላይ እንዳሉ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መስከረም ፭ ቀን ፲፱፻፵፭ ዓ/ም የመብራት ኃይል ባለሥልጣን ዋና ዲሬክተር ሆነው ተሾሙ ። በጥር ወር ፲፱፻፶ ዓ/ም የዚሁ መ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኑ ። ከዚያም በኅዳር ወር ፲፱፻፶፬ ዓ/ም የም/ሚኒስትርነት ማዕረግ አገኙ ።

ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ የመብራት ኃይል ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው በርካታ ትላልቅ ሥራዎች እንዲከናወኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ከእነዚህም የቆቃ ግድብ፣ የአዋሽ ሸለቆ የሁለተኛና ሶስተኛ ግድብ ፣ በባሕርዳር ከተማ በስተደቡብ የተሠራው የጭስ አባይ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ይገኙበታል ። ለዚህ ተግባራቸው ከግርማዊ ጃንሆይ ከፍተኛ ምስጋና አግኝተዋል ።

የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ/ም የውኃ ሀብት ልማት ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ ። በዚህ ሚኒስቴር ብዙም ሳይቆዩ መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ/ም የትምህርት ሚኒስትር ሆኑ ። በትምህርት ሚኒስቴር እስከ ፲፱፻፷፮ በቆዩበት ጊዜ ፤

ሀ/ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ምስጉን መምህራን እየተመረጡ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን በመቅረብ የምስክር ወረቀት እንዲቀበሉና እንዲመሰገኑ በማድረግ ለመምህራኑ የማበረታቻና የማነቃቂያ ፕሮግራም ዘርግተዋል ።

ለ/ የኢትዮጵያ የሥራ ቋንቋ የሆነው አማርኛ በስፋትና በጥልቀት እንዲዳብርና እንዲበለጽግ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ማደግ አስፈላጊ በመሆኑ የአማርኛ መርሀ ልሳን አካዳሚ እንዲቋቋም ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ። ለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታ ናቸው ።

ሐ/ ከ፲፱፻፴፬ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ድረስ የነበረው የኢትዮጵያ የትምህርት ፕሮግራም በስፋትና በጥልቀት ከተገመገመ በኋላ አዲስ የትምህርት እቅድ እንዲዘረጋ በማስፈለጉ አጠቃላይ የትምህርት ጥናት (ሴክተር ሪቪው) በመጀመሪያ ፹ ሊቃውንት እንዲያጠኑት ተደርጎ ፣ ከዚያም የኢንተናሽናል ድርጅት ተጠሪዎችና ፩፻፴፭ የሀገርና የውጭ አገር ሊቃውንት በአፍሪቃ አዳራሽ በተገኙበት በጥልቀት ከተመረመረና በመንግሥት ከጸደቀ በኋላ በሥራ ላይ እንዲውል ተፈቀደ ።

ይህ ጥናት የተደረገው ክቡር አቶ ሰይፉ የትምህርት ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ በመሆኑ ደርግበአቋራጭ ሥልጣን ነጥቆ በያዘበት ወቅት ይህን የዓለም ሊቃውንት ያደነቀውን የትምህርት አጠቃላይ ጥናት በመጥፎ በመተርጎም ሕዝብ እንዲቃወመው በሀሰት ፕሮፓጋንዳ ጥላቻን ዘርቶ በፈጠረው ተንኮል ለሕይወታቸው መጥፊያ ተቀዳሚ መከሰሻ ሆኖ ከ፳ ዓመት እስራት በኋላ ያለፍርድ ተገድለዋል ። ይሁን እንጂ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ሕያው አምላክ የንጹሐን ደም በከንቱ መፍሰሱን አይቶና መዝኖ ግፈኛው ደርግ በአጸፋው ተንኮታኩቶ እንዲወድቅና የሠራውን እንዲያገኝ ፍርዱን ሰጥቷል ።

ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ ለውድ ሀገራቸው በቅንነትና በታማኝነት ላበረከቱት አገልግሎት ከግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

ክቡር አቶ ሰይፉ ወ/ሮ ሶፊያን በሕግ አግብተው የሁለት ወንዶችና የሁለት ሴት ልጆች አባት ሲሆኑ ውድ ሀገራቸውን በቅን በማገልገል ላይ በነበሩበት ጊዜ ስለ መልካም ሥራቸው ከግርማዊ ጃንሆይ ቁጥራቸው በዛ ያሉ የከፍተኛ ማዕረግ ኒሻኖች ተሸልመዋል ።



www.ethipianorthodox.org

## ደጃዝማች

## ሐረጐት አባይ

## 1901-1967



ክቡር ደጃዝማች ሐረጐት አባይ በሐምሌ ወር 1901 ዓ.ም በአማሴን አውራጃ በአስመራ ከተማ ተወለዱ ።

በኤርትራ የፌዴራል መንግሥት ሲቋቋም የፍርድና ፍትህ ሚኒስትር ቀጥሎም የኢኮኖሚ ሚኒስትር በመሆን አገልግለዋል ። ከ1965 ዓ/ም ጀምሮ የአስመራ ከተማ ከንቲባ ነበሩ ።

**የክቡር ደጃዝማች ሐረጐት አባይ**
**የቀብር ሥነሥርዓት በአሥመራ ተፈጽሟል**

www.ethipianorthodox.org

# ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ

## 1912-1971



ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ በጦር መኰንንነትና በሕግ መወሰኛ ም/ቤት አማካሪነት ሀገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን ለ፴፫ ዓመታት በቅንነትና በታታሪነት አገልግለዋል ። በዚህም ረጅም የሥራ ዘመን የጦር ሠራዊቱን ልዩ ልዩ ክፍል በድርጅት ለመገንባትና ይዞታውን አደላድሎ ለማሻሻል ከፍተኛና ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት መኰንኖች አንዱ ነበሩ ።

ክቡር ብ/ጄኔራል ሣሙኤል በየነ ከፊታውራሪ በየነ ሠራዊቱና ከወ/ሮ አስካለ በላቸው አባፍታው በ፲፱፻፲፪ ዓ/ም አዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ ።

በጊዜው በነበረው ሥርዓት መሠረት በወላጆቻቸው ቤት በእንክብካቤ ተኰትኩተው አደጉ ። የአማርኛን ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ መጀመሪያ በአሊያንስ ፍራንሲዝ ፤ ቀጥሎም በተፈሪ መኰንን ት/ቤት ገብተው ዘመናዊ ትምህርት ተምረዋል ።

አባታቸው ፊታውራሪ በየነ ሠራዊቱ በማይጨው ጦር ግንባር ከጠላት ጋር ሲፋለሙ በጀግንነት ተሰው ። ወጣት ሳሙኤል የአባታቸውን ጋሻ በማንሳት የጠላት ጦር ድል ተመትቶ ከኢዮጵያ በ፲፱፻፴፫ ሲባረር በውትድርና ተግባር ተሠማሩ ።

ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ ከ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ጀምሮ በመከላከያ ሚኒስቴር የሠራዊቱ ባልደረባ በመሆን እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ድረስ በተለያዩ ደረጃዎችና ክፍሎች አገራቸውንና መንግሥታቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል ። በእዚህ ረጅም ሠራዊቱን የማቋቋምና የመገንባት ዘመን ብ/ጄኔራል ሣሙኤል በየነ አገልግሎታቸውን ካበረከቱባቸው የሥራ መስኮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ፡—

— የልዑል አልጋ ወራሽ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለሥላሴ እልፍኝ አስከልካይ ፤

— የምድር ጦር መሐንዲስ ክፍል ዲሬክተር ፤

— የምድር ጦር ማመላለሻ መምሪያ አዛዥ ፤

— የምድር ጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት አዛዥ ፤

— የምድር ጦር ስንቅና ትጥቅ መምሪያ አዛዥ ፤

— በመከላከያ ሚኒስቴር የመምሪያ መኰንን



www.ethipianorthodox.org

በእነዚህ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች በተለያየ ማዕረግና ደረጃ ሲያገለግሉ የግል አስተዋጽኦዋ ቸው በተለይ ጎልቶና ዘላቂነትን ያስመሰከረው ከብዙ በጥቂቱ በሚከተሉት መስኮች ነው ።

፩/ የማመላለሻ የጦር ሠፈር ለሥራ ክልል ለመ ኪና ጋራዥና ለጦር አባላት መኖሪያ ሠፈር ተደልድሎ እንዲሠራ አድርገዋል ።

፪/ በዘልማድ ጥይት ቤት የሚባለውንና ከጥንት ተያይዞ የመጣውን ይዞታ የፈንጂና የጥይትን አደገኛነት በማጤን ቦታውን ለመቀየር በልዩ ልዩ ምክንያት ባይቻልም ባለበት ይዞታ ማከ ማቻውንና አቀማመጡን የጊዜው ቴክኖሎጂ በሚፈቅደው መሠረት በኤክስፐርት አሰ ጠንተው በጀት አስፈቅደውና ሂደቱን በመ ቆጣጠር ሥራውን በአስተማማኝ ሁኔታ አሰ ርተዋል ።

፫/ የሠራዊቱ አባላት ልጆች ፍላጎታቸው ሲ ሆን ወደ ሠራዊቱ የሚገቡበትን ፣ በሠራዊ ቱም እየሠለጠኑ የሚያድጉበትን መንገድ በማቃናት ፣ በማመቻቸትና በማስፈቀድ በተ ግባር አውለዋል ።

ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ በገነት ጦር ትምህርት ቤት ይሰጥ በነበረው የመሪነት ኮርስ ከመካፈላቸውም በላይ የአመራር ችሎታቸ ውን ለማዳበር በመከላከያ ሚኒስቴር አዘጋጅነትና አስተባባሪነት በቡድን በመሆን የአሜሪካንና የእ ሥራኤልን የምድር ጦር ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች በተለያዩ ወቅት ጎብኝተዋል ። በተጨማሪም የአስተያየታቸውን አድማስ ለማስፋት በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት ከቤተሰባቸው ጋር በመሆን አውሮ ፓን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል ።

ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ ራስንና ወገንን ለመርዳት አገርን በጋራ ለማልማትና ለማበልጸግ በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት መደበኛ ሥራቸው ላይ ደርበው በየረርና ከረዩ አውራጃ በሶደሬ ዘመናዊ እርሻ በማልማት ለብዙዎች መልካም አርአያ ሆነዋል ።

ጄኔራል ሳሙኤል ርህሩህ ፣ ለሰው አዛኝ ፣ ለጋስ ፣ የሰውን ሁሉ መሻሻልና እድገት ፣ የራሳ ቸውንና የቤተሰባቸውን መልካምና የተደላደለ ኑሮ የሚወዱ ነበሩ ። አካባቢያቸውን ለማሻሻል ፣ ለማሳመር ፣ አዲስ ነገርን በተለይ ቴክኖሎጂን ለማ ወቅና ለመሞከር ጉጉት የነበራቸውና ጥረት የሚ ያደርጉ እንዲሁም በመልካም አርአያነታቸው ለወ ዳጅ ዘመድ ቤዛና አለኝታ የነበሩ መኰንን ናቸው ።

ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ የሕግ መወ ሰኛ ምክር ቤት አባል እንዲሆኑ በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ተሹመው በወትሮው ታታሪነታቸው እያገለገሉ ሳሉ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በፋሺስት ደርግ በቁጥጥር ሥር ዋሉ ። ለይስሙላ ያህል ጉዳያቸው በፍርድ ቤት (በጊዜያዊ ወታደራዊ ጦር ፍርድ ቤት) ይጣ ራል ፣ የፍትሕም ውሳኔ ይሰጠዋል በማለት ጉዳዩ ሲሰማና የተደጋገመ ቀነ ቀጠሮ ሲሰጠው ቆየ ። በወቅቱ የነበሩትን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ያለ ፍርድ ማጥፋት የተለመደ ተግባሩ ያደረገው ወታ ደራዊው የፋሺስቶች ቡድን ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ከአምስት ዓመት እስራት በኋላ ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነን በግፍ በኢሰብአዊነት በሚስ ጢር ገደለ ።

ደርግ ኢሰብአዊና ፍትሕ አልባ የሆነ ድርጊ ቱን በሚስጢር አፍኖ ይዞ ቋሚ ቤተሰቡን ዘመድንና ወዳጅ በመንፈስ ጭንቀት ፣ በሕሊና ፀፀት ፣ እንዲሁም ሀብት በማራቆትና በማመና መን የፈጸመው ግፍ ኢሕአዲግ መንግሥቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ይፋ ሊወጣ ችሏል ። ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነም ከሌሎች አሥር የሥራ ጓደኞቻቸው ጋር በድብቅ ከተቀበሩበት ከልዑል ራስ አሥራተ ካሣ ግቢ አጽማቸው ተቆፍሮ ወጥቶ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የአገር ውስጥና የውጭ መንግሥታት ተወካዮች ወዳጅ ዘመድና ቤተሰቦቻቸው በተገኙ በት ከሌሎች ፳፯ ሰማዕታት ጋር አጽማቸው አርፏል ።

ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ ለአገራቸው በቅንነት ፣ በታማኝነትና በታታሪነት ላበረከቱት አገልግሎት ከአገር ውስጥና ከውጭ መንግሥታት ከተሸለሙት አያሌ ሜዳዮችና ኒሻኖች የሚከተ ሉት ይገኙበታል ።

፩/ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የአንገት ከነ ፕላኩ ፤

፪/ የዳግማዊ ምኒልክ የመኰንን ደረጃ ፤

፫/ የረጅም ዘመን አገልግሎት የወርቅ ሜዳይ ፤

፬/ የ፲፭ ዓመት አገልግሎት ሜዳይ ፤

፭/ የድል ሜዳይ ፤

፮/ የአፍሪካ ስታር ኮከብ ፤

፯/ ከዩጎዝላቪያ መንግሥት የመኰንን ደረጃ ፕላክ

ክቡር ብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ወ/ሮ መሰሉ ሳልባቶርን አግብተው የሁለት ወንዶችና የሁለት ሴቶች አባት ነበሩ ።



www.ethipianorthodox.org

# ፊታውራሪ ክፍሌ እንቁሥላሴ

## 1916 - 1971

ክቡር ፊታውራሪ ክፍሌ እንቁሥላሴ ከአባታቸው ከግራዝማች እንቁሥላሴ ባንትይዳኝና ከእናታቸው ከወ/ሮ ፍቅርተ ኃይለ ሥላሴ ሐምሌ ወር ፲፱፻፲፮ ዓ/ም በሸዋ ክፍለ ሀገር በሙጢገላ ተወለዱ ።

የአማርኛ ትምህርታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ በጨዋ ልጅ ማእረግ እንዲያድጉ ለቤተ መንግሥት ተሰጡ ። ጠላት ኢትዮጵያን በግፍ እስከወረረበት ጊዜ ድረስ በቤተ መንግሥት ከቆዩ በኋላ ገና ከ፲፫ ዓመት እድሜያቸው ጀምሮ በአምስቱ ዓመታት የኢጣሊያን ወረራ ከአባታቸውና ከወንድሞቻቸው ጋር በመሆን በአርበኝነት ታግለዋል ። በዚህም ጊዜ እስከ መቶ አለቃነት ማእረግ ደርሰዋል ።

በሥራ ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮ በልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች አገልግለዋል ። በቤተ መንግሥት ባለሟልነት ፡ በከፋ ክፍለ ሀገር የጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም ፡ በሲዳሞ ክ/ሀገር የአዶላ ማዕድን ኃላፊና በሸዋ ክፍለ ሀገር የማዘጋጃ ቤት ሹም በመሆን በታማኝነትና በታታሪነት ሠርተው የፊታውራሪነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

ግፈኛው የደርግ መንግሥት አምስት ዓመት ከአሰራቸው በኋላ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ከእስር ቤት ወስዶ በስውር ስለገደላቸው ፡ ሬሣቸውም የወደቀበት ባለመታወቁ ፡ ለቤተሰባቸው ታላቅ ሐዘንና የመንፈስ ጭንቀት ሆኖ ቆይቷል ።

አጽማቸው ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በልዑል ራስ አሥራተ ካሣ ግቢ ስለተገኘ ህዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በወታደራዊው ደርግ በግፍ ከተገደሉት ፷ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አጽም ጋር ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በቅድስት ሥላሴ ቅጥረ ግቢ በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል ።



የማዘጋጃ ቤቶች ሹምና የአዶላ ወርቅ ማዕድን ኃላፊ ሆነው እንዲሁም በተለያዩ ክፍላተ ሀገር ሲያገለግሉ የነበሩት ፊታውራሪ ክፍሌ እንቁሥላሴ በልጅነት ዕድሜያቸው ለአምስት ዓመት ለኢትዮጵያ ነፃነት በአርበኝነት ተፋልመዋል ።

www.ethipianorthodox.org

# አቶ
# አበበ ከበደ ወ/ጊዮርጊስ

## 1924-1971

አቶ አበበ ከበደ ከስመ ጥሩ አርበኛ ከፊታ/ ከበደ ወልደጊዮርጊስና ከወ/ሮ አመለወርቅ ኢየሱስ በ፲፱፻፳፬ ዓ/ም አርሲ ክ/ሀገር ተወለዱ ።

እንደ ብዙዎች የአርበኞች ልጆች ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የአርበኛ አባታቸውን ውለታ በማስታወስ በቀድሞው ተፈሪ መኰንን ት/ቤት በአዳሪነት እንዲማሩ አደረጉ ። በዚሁ ት/ቤት እስከ ፲፱፻፵፬ ዓ/ም ድረስ ከተማሩ በኋላ ሐረር መምህራን ማሠልጠኛ ት/ቤት ገብተው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

አቶ አበበ ቀ-ኃ-ሥ ኮከበ ጽባሕ ይባል በነበረው ት/ቤት ተመድበው ሲያስተምሩ ባሳዩት ችሎታና ቅን አገልግሎት ለከፍተኛ ትምህርት ተመርጠው ወደ አሜሪካ ተላኩ ። ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቅቀው ወደ ሀገራቸው እንደ ተመለሱ በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ተመድበው በመጀመሪያ የዕደ ጥበብ ማዕከል ኃላፊ ቀጥሎም የአሁኑ ብሔራዊ ቴያትር (የቀድሞው የቀ.ኃ.ሥ. ቴያትር) ዲሬክተር በመሆን አገልግለዋል ። ኃላፊነታቸውን በሚያስመሰግን ሁኔታ መወጣታቸው በጉልህ ስለታየ ፤ በታላቋ ብሪታንያ የትምህርት አታሼ ሆነው ተሾሙ ። በዚህም ኃላፊነታቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ አበይት ተግባራትን በማቀድና በማከናወን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

ቅን አገልግሎታቸውና ታታሪነታቸው ከፍ ላለ ኃላፊነት ስለአስመረጣቸው ከየካቲት ፲፬ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ/ም ጀምሮ የቀ- ኃ- ሥ በጎ አድራጎት ድርጅትን በኃላፊነት እንዲመሩ ተደረገ ።

ይህንንም ከፍተኛ ኃላፊነት ከተረከቡ በኋላ በድርጅቱ ሥር ይተዳደሩ የነበሩትን

ሀ/ በደብረ ሊባኖስና በሐረርጌ የሚገኙ መጦሪያ ቤቶች በተሻሻለ ሁኔታ እንዲያገለግሉና እንዲስፋፉ ፤

ለ/ እናት አባት የሌላቸው ሕፃናት በልዩ ልዩ እንክብካቤ የሚያድጉባቸው ቤተ ሕፃናት እንዲያስፋፉ ፤ ወጣቶቹም በቀለምና በሙያ ትምህርት በተሻለ ሁኔታ እንዲማሩና እንሰለጥኑ ፤

ሐ/ ረዳትና ወገን የሌላቸው ደካሞች ፣ ጤናቸው የሚጠበቅበትና የሚታከሙባቸው ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች እንዲሻሻሉና እንዲስፋፉ ፤

መ/ በተፈጥሮና በልዩ ልዩ እክል ምክንያት ብርሃናቸውን ያጡ ዓይነ ስውራን በልዩ እንክብካቤ ተይዘው እውቀትና ከፍተኛ ሙያ የሚገበዩባቸው ትምህርት ቤቶች ዘመናዊና ዘላቂነት ባለው መንገድ እንዲደራጅና እንዲስፋፉ በማድረግ እጅግ ብዙ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን መገልገያ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስዋጽኦ አድርገዋል ።

አቶ አበበ ከበደ በእነዚህና በተመሳሳይ መስኮች ዘላቂነት ያለው ሥራ የፈጸሙት ተግባር በአገር ውስጥና በውጭ ዓለም ከፍተኛ ታዋቂነት እንዲያገኙ አድርገዋል ።

በድርጅቱ ሥር ከነበሩት ሕፃናት ማሳደጊያዎችና ከመርሐ ዕውራን ት/ቤት ጀምረው በልዩ



"- - - መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለው አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ - - - (ማቴ ፭፥፲፮)

አቶ አበበ ከበደ ለ፳፭ ዓመት አገራቸውን ያገለገሉ ፤ በተፈጥሮ የታደሉትን ችሎታና እውቀት ፤ በትምህርት ከቀሰሙት እውቀትና ሙያ ጋር አዋህደው ለታረዙ ፣ ለተራቡ ፣ ለታመሙ ፤ ለደከሙና ረዳት ለሌላቸው ፣ ብርሃናቸውን ላጡና ለዕጓለማውታን ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሰው ግብረገብ የተላበሱ ታላቅ ሰው ነበሩ ።

www.ethipianorthodox.org

ልዩ ሙያ ሠልጥነው ዛሬ ሀገራቸውንና ወገኖቻቸውን በብቃትና በኩራት የሚያገለግሉ ጥቂቶች አይደሉም ። በአሁኑም ወቅት በስፋት አገልግሎት ከሚሰጡት ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች መሐከል ቅ/ጳውሎስ ሆስፒታልን ፣ ወ/ሮ በለጥሻቸው ክሊኒክ ፣ የአክሱም ቅ/ማርያም ሆስፒታል ፣ ወዘተ ለአብነት ያህል የሚጠቀሱ በአቶ አበበ ከበደ አማካይነት የተሠሩና የተደራጁ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ናቸው ።

በአገራችን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አካለ ስንኩላን ፣ ብርሃናቸውን ያጡ ዓይነ ስውራን ፣ ደካሞች ወዘተ በዘመናዊ አቋም ተደራጅተው ፣ ተባብረውና በአንድነት ሠርተው ሕይወታቸውን መምራትና ከሁሉም ጋር በእኩልነት መኖር እንዲችሉ የታየበትና የተመሰከረበት "የተዋህዶ ጥበብ የጃንጥላና የባትሪ ድንጋይ ፋብሪካ" በእሳቸው መሪነት የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነበር ። ይህም በአርአያነቱ የውጭ አገር አጥኚዎችን ሳይቀር የሚስብና የሚጎበኝ ድርጅት ነበር ።

አቶ አበበ በተፈጥሮ የታደሉትን ችሎታና እውቀት ፣ በትምህርት ከቀሰሙት እውቀትና ሙያ ጋር በማዋሐድ ፣ በሃይማኖትና በቆራጥ የሥራ ወዳድነት ፣ እየታገሉ ለታረዙ ፣ ለተራቡ ፣ ለታመሙ ፣ ለደከሙና ረዳት ለሌላቸው ፣ ብርሃናቸውን ላጡና ዕጓለማውታ ፣ ወዘተ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሰው ታላቅ የግብረገብ ሰው ነበሩ ።

አቶ አበበ ከበደ በተፈሪ መኰንን ት/ቤት በነበሩበት ወቅት በሃይማኖታቸውና በግብረገብነታቸው በጓደኞቻቸው መሐል የታመኑና የተወደዱም ነበሩ ። የተጣሉትን በመምከርና በማስታረቅ፣ የወንጌልም ቃል እንዲስፋፋ በመቀስቀስ ይሳተፉ ነበር ። በ፲፱፻፴፱ ዓ/ም ከት/ቤት ጓደኞቻቸው ጋር የጀመሩት "የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን" ለዛሬው "የተምሮ ማስተማር ማኅበር" የመሠረት ድንጋይ ጥሏል ።

በዚህ ሁኔታ በት/ቤት የተጀመረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በአቶ አበበ ከበደ አስተባባሪነትና መሪነት በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤ/ክ ቅጽር ግቢ ውስጥ እንዲቀጥል ሆኗል ። ይኸው እንቅስቃሴ ከፍተኛ የሰንበት ትምህርት ማስተማሪያ በመሆኑ በየእሁድ ጠዋት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በእቅድና በሥነ ሥርዓት የሚከናወን ሰፊ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጥበታል ።

በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም "ተምሮ ማስተማር ማኅበር" ተብሎ የተጀመረው ማኅበር አቶ አበበ እውቀታቸውን ፣ ገንዘባቸውንና ትርፍ ጊዜአቸውን መስዋዕት አድርገው በማደራጀታቸው እስከዛሬ ድረስ ዓላማውን ሳይስትና ሳይፋለስ እንቅስቃሴው ሳይዳከምና ሳይታጎል እጅግ ብዙ ለሆኑ ወጣቶች ምዕመናን መንፈሳዊ አገልግሎት ከመስጠቱም በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤቶች በጀማሪነቱና በዘላቂነቱ ቋሚ አርአያ ለመሆን በቅቷል ።

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ መኩሪያ የነበሩት አቶ አበበ ከበደ ያበረከቱት አገልግሎት በዚህ ሳያበቃ የምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ዘመናዊ አደረጃጀትና አመራር እንዲያገኝ እንዲሁም ቋሚ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው ፣ በገዳሙ ስርም ዘመናዊ ት/ቤት ተመስርቶ አኩሪ ደረጃ ላይ እንዲደርስ መነሻውንና መድረሻውን ቀይሰው እንዲመሠረት በማድረግ ከፍተኛ ድርሻና አስተዋጽኦ አበርክተዋል ።

እነዚህን በመሳሰሉ በጎ ሥራዎች በመሳተፋቸውና በመደበኛው ሥራቸውም አኲያ ያበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመታወቃቸው ፣ ጄኔቭ የሚገኘው የዓለም አብያተ ክርስቲያናትና ናይሮቢ ኬንያ ላለው የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች ቋሚዬ የምክር ቤት አባል ሆነው በመመረጥ አገልግለዋል ።

አቶ አበበ ከበደ ለፈጸሙት በጎ ሥራዎችና ለአገራቸው ለሰጡት ሰፊ አገልግሎት የዳግማዊ ምኒልክ የመኰንን ደረጃና የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የታላቅ መኰንን ኒሻኖች ተሸልመዋል ።

አቶ አበበ ከበደ ከወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋው ጋር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ደንብና ሥርዓት በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም በተክሊል ተጋብተው ቆርበዋል ። በፍቅርና በሰላም ፣ በመተጋገዝ በመረዳዳት ፣ መልካም የቤተሰብ መሪነታቸውን ከማስመስከራቸውም በላይ የሁለት ሴቶች ልጆች አባት ነበሩ ።

አቶ አበበ ከበደ ከዚህ ዓለም አልፈዋል ፤ ለሀገርና ለወገን መገልገያ እንዲሆኑ ያነጹዋቸው ተቋሞች ግን ዘለዓለም ይኖራሉ ። አቶ አበበ እንደ አንድ ሻማ ሆነው በርተውና ተቃጥለው ጨለማውን ያስወገዱላቸው ማኅበራት ግን ለሌሎች የሚያበሩ የብርሃን ምንጮች ሆነዋል ። በመልካም ሥራዎቻቸው ለዘለዓለም ሲታወሱ ፣ ሲመሰገኑና ሲከበሩ ይኖራሉ ።

"- - - መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ፤ ሩጫዬንም ፈጽሜያለሁ ፣ ሃይማኖቴንም ጠብቄያለሁ ፣ እንግዲህስ እውነተኛ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያዘጋጀልኝን የጽድቅ አክሊል ይሰጠኛል" ማቴ ም ፬ ቁ ፯



www.ethipianorthodox.org

## የሰማዕታቱ ፍልሰተ አጽምና የቀብር ሥነ ሥርዓት

የካቲት ፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ የሽግግር መንግሥት በቴሌቪዥን ያወጣው መግለጫ "የንጉሠ ነገሥቱና የ፷ዎቹ ሚኒስትሮቻቸው የተቀበሩበት ቦታ ስለተገኘ መንግሥት አጽማቸውን አስወጥቶ ለቤተዘመድ ለመስጠት ዝግጅት ተጠናቋል" የሚል ነበር ። ስለሥርዓቱ አፈጻጸም መጀመሪያ የንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ የሚኒስትሮችና የጦር ባለስልጣኖች አጽም አርብና ቅዳሜ በቅደም ተከተል የሚ ሰጥ መሆኑን ተገለጠ ።

የካቲት ፬ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም የ፷ዎቹ ሰማ ዕታት ቤተሰቦች ከአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ጋር ከተነጋገሩ እና ቀብሩ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እንዲሆን ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህ በርና ከካቴድራሉ ጽሕፈት ቤት ፈቃድ ከተገኘ በኋላ ዝግጅቱ ቀጠለ ።

መንግሥት የአጽሙን ፍለጋ ቆፍሮ የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ዘመድ ወዳጅ በተገኘበት አስጀመረ ። ቅዳሜና እሁድ የቀጠለው ቁፋሮ ከሰዓት በኋላ ተጠናቀ አጽሙ በ፮ ሳጥኖች ሆኖ በወህኒ ቤት ውስጥ ከሚገኘው ሚካኤል ቤተክርስ ቲያን አረፈ ። በዚያው የፍትሐት ፀሎት ሲደረግ አድሮ በማግሥቱ የሰማዕታቱ አጽም በሟች ቤተሰቦች ዘመዶችና እንዲሁም ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ካህናት ታጅቦ ወደ መንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተጓዘ ። እዚያም ሲደ ርስ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በለቅሶና ዋይታ ፤ ሊቃነ ጳጳሳት የደብር አለቆችና የካቴድ ራሉ ካህናት በጸሎትና ዝማሬ ከተቀበሉት በኋላ በጊዜያዊነት ወደ ተዘጋጀው ሥፍራ አረፈ ።

ቀጥሎ ቤተሰቡ ስለ ሐውልቱ ሥራ የሚያ ስፈልገውን ሁሉ አጠናቆ ሥራውን አስጀመረ ። የሐውልቱ ሥራ በመካሄድ ላይ እንዳለ አጽሙ በጊዜያዊ ከሚገኝበት ቦታ ቋሚ ወደሆነው ማረ ፊያው እንዲዛወር በተለይ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ቤተሰቦች በመጠየቃቸው የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም/ እንዲሆን ተወስኖ ዝግጅቱ ቀጠለ ።

እንዲሁም ደርግ በድብቅ ወስዶ የት እንዳ ደረሳቸው ስላልታወቁት ባለሥልጣኖች ጉዳይ ቤተሰቡ ለሽግግር መንግሥት የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር አመልክቶ መልስ እየጠበቀ እንዳለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ጨ ምሮ የተጠቀሱትን ባለስልጣኖች ደርግ የገደ ላቸው እና የተቀበሩትም ልዑል አሥራተ ካሣ መኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ መሆኑን በማስ ታወቅ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር በግንቦት ወር መግለጫ አወጣ ።

ወዲያውኑ በቤተክህነት ጽ/ቤት አስተባባ ሪነት በተጀመረው ፍለጋ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አጽም መገኘቱ ተነገረ ። የአገር ው ስጥ ጉዳይ ሚኒስቴርና ቤተሰቡ በመተባበር የቀሩት ፱ ባለስልጣኖች አጽም ፍለጋ ቁፋሮ ተጀመረ ። ለአንድ ወር ያህል በተደረገ ቁፋሮ የ፲፪ ሰው አጽም ተገኘ ። ስምንቱ ከታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት በሐምሌ ወር የተወሰዱት ባለሥልጣኖች አጽም መሆኑ ሲረጋገጥ ፤ አንዱ ደግሞ ከአራተኛ ክፍለ ጦር እስር ቤት የተወሰ ዱት የፊታውራሪ ክፍሌ እንቁሥላሴ አጽም መሆኑ ታወቀ ። ከቀረው ሶስት አጽም ሁለቱ የሴቶች አንድ ደግሞ የአንድ መኰንን መሆኑን ለይተው ቤተሰቦች ወሰዱ ።

የዘጠኙ ባለሥልጣኖች አጽም ተለይቶና በሶስት ሳጥን ሆኖ ለጊዜው በእንጦጦ ገነተ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን እንዲያርፍ ከተደረገ በኋላ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም በቤተሰቦቻቸውና በዘመድ አዝማድ ታጅቦና ወደ መንበረ ቅድ ስት ሥላሴ ካቴድራል ተወስዶ ከጓዳኑ ሰማዕታት አጽም ጋር እንዲያርፍ ተደረገ ። በዚህ አኳኋን የሁሉም የቀብር ሥነሥርዓት ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም የሟቾች ባለቤቶችና ልጆች

www.ethipianorthodox.org

ዘመድ ወዳጅ ፤ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፤ የውጭ አገር አምባሳደሮች ፤ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው ሌሎች እንግዶች በተገኙበት ተፈጸመ ።

የዕለቱን ፀሎት የመሩትና ቡራኬ የሰጡት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ነበሩ ። በቀብሩ ስነሥርዓት ላይ የቤተሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ ተወካይ ፤ በሕይወት የሚገኙና አብረው ታስረው የነበሩ ሰዎች ተወካይ ፤ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ተወካይ ፤ የባለቤቶቻቸው ተወካይ ፤ የወንድ ልጆቻቸው ተወካይ ፤ የሴት ልጆቻቸው ተወካይ ፤ በቅደም ተከተል ንግግር አድርገዋል ።

ለዕለቱ ማስታወሻ ይሆንም ዘንድ የሰማዕታቱን ፎቶግራፍና አጭር ታሪክ ያካተተ መጽሔት ተዘጋጅቶ ለቤተሰቡና በበዓሉ ላይ ለተገኙ የክብር እንግዶች ታድሏል ።



ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም የሰማዕታቱ አጽም
በጊዜያዊ ካረፈበት ቦታ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ።



ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም
የሰማዕታቱ አጽም ከመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሲወጣ



www.ethipianorthodox.org

## በ፲፰ ቀዳሚ ሰማዕታት አጽም ዕረፍት ሥነ ሥርዓት ላይ
## የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ተወካይ
## በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያደረጉት ንግግር

— ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፤
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፤
— ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፤
— ክቡራን የመንግሥታቱ አምባሳደሮች ፤
— ክቡራትና ክቡራን ሐዘንተኞች ፤
— የተከበራችሁ የቤተሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበርና አባላት ፤
— እንዲሁም የሐዘኑ ተካፋዮች ፤

ሞት የተፈጥሮ ባሕርይ አይቀሬ ክስተት ነው፤

ፍጡር የሆነ ሁሉ ይሞታል ፤ የሰብአዊ ፍጡር አሟሟት ግን በደመ ነፍስ ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረታት የተለየ የነፍስም ሆነ የሥጋ ታሪካዊ ምስጢርነት አለው ።

የሰው ልጅ የዓለም ጌጥ የሆነ ባለ አእምሮ ፍጡር በመሆኑ ለሃይማኖታዊ እምነቱ ፣ ለታሪካዊ ተግባሩ ፣ ለሀገሩ ክብርና ፣ ለነፃነቱ እንዲሁም ለሰብአዊነትና ለሐቅ በሚከፈለው መስዋዕትነት የዚህ ተቃራኒ በሆኑ ኢሰብአዊያን ቢገደል በታሪክም ሆነ በነፍሱ ያለው ክብርና ዋጋ ሕያው ነውና እንደሞተ አይቆጠርም ።

በኢሰብአዊ ድርጊታቸው ንጹሐንን አጥፍተው የሚጠፉ ግን የታሪክም ሆነ የነፍስ ሙታን ናቸውና ፣ ሥጋዊ መታሰቢያቸው የተዋረደ ፣ የሁለት ዓለም ፍርደኞች በመሆናቸው ለታሪካዊ ክብር ከሚሞቱ ሰማዕታት አሟሟት ጋር ይለያሉ ።

የሰው ልጅ በዚህ ዓለም የሚቆየው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ መሆኑ የሚታወቅ ነው ። ይሁንና አንዳንድ የፖለቲካ ሥልጣን መሪነት በአጋጣሚ በእጃቸው ሲገባ ዘለዓለማዊ ዕድሜ ያገኙና የማይለወጡ ይመስል ሥልጣኑን ለበቀል ፤ ለግል ክብርና ዝና እየተጠቀሙበት የሀገር ዕዳ ፣ የወገን ፍዳ በመሆን ታሪክና ትውልድ ይቅርታ የማያደርግላቸው ቀሳፊና አደራ በል ዘራፊ ይሆናሉ ። ሌሎች ደግሞ የመሪነትን ሥልጣን ፣ የሀገር ተስፋ ፣ የወገን ቤዛ አድርገው ፣ ለተከታይ ትውልድ የሚጠቅሙ መሠረቶችን በመጣልና በመገንባት ለሀገር እድገትና ለሕዝብ ብልጽግና በማጎናጸፍ ሕዝባዊ አደራቸውን የሚወጡና ራሳቸውን ለሕዝብ ሰጥተው የማይሞት የታሪክ ምስክርነት ያተርፋሉ ። እሩቅ ሳንሄድ ከሀገራችን ልምድ የሁለቱን ተቃራኒ የአመራር ባህርያት መመልከት ይቻላል ። ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን ወደ ዘመናዊ ሥልጣኔ እንድትሸጋገር በር በመክፈትና ለሀገር አንድነት መጠናከር ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደናቂነትና ታዋቂነትን ከማትረፋቸውም በላይ ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ የተማሩ ባለሙያዎችን አፍርታ በሠለጠነ የወገን ባለሙያዎች እንድንገለገል አስችለዋል ። ግርማዊነታቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ ሥነ ምግባራትንና ሰብአዊነት በማበልጸግ ፣ ሀገሩን ላገለገለና ለተማረ ሰው ተገቢውን ክብርና ደረጃ በመስጠት ፣ በሀገር ውስጥ አመራራቸው የተወደዱ ፣ በውጭ ዓለምም እጅግ ከበሬታን ያገኙ ፣ ሀገራቸውን አኩርተውና አስከብረው ገናና የታሪክ ሰውነትን ያተረፉና በውጭ ሕብረተሰብ እስከ መመለክ የደረሱ ታላቅ መሪ ነበሩ ። በተቃራኒው የሀገር ከሐዲውና እምነተ ቢሱ ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አፍራሽና ፀረ ምሁር ፣ የወገን ባለሙያ አጥፊ ፣ የሕዝብ የበላይነትን እረጋጭና ኮሚኒስታዊ አምባገነን መሪ ነበር ።

የተከበራችሁ ሐዘንተኞችና የሐዘኑ ተካፋዮች ፤

ክቡር ሥጋቸው እንደጉድፍ የትም ከተጣለበት ተሰብስቦ ዛሬ ሥርዓተ ቀብር ከሚፈጸምላቸው ፲፰ ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት መካከል ብዙዎች ሀገራችን በኢጣልያን ፋሽስት በተወረረችበት ወቅት ለሀገራቸው ነፃነትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነት በአርበኝነት በየጦር ሜዳው የተዋደቁ ፣ በውስጥ አርበኝነትና በስደት ሆነው በፖለቲካ ታግለው ሀገራቸውን ከቅኝ ገዥ መንጋጋ ያላቀቁ ቢሆንም ለጊዜው በጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ስማቸው በክብር መዝገብ ተመዝግቦ የተገኘው ፤

፩/ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ
፪/ ክቡር ራስ መስፍን ስለሺ
፫/ ክቡር ሌ/ጀኔራል አቢይ አበበ
፬/ ” ” ከበደ ገብሬ
፭/ ” ” ደበበ ኃይለ ማርያም
፮/ ” ኰሎኔል ታምራት ይገዙ
፯/ ” ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ
፰/ ” ደጃዝማች ክፍሌ ዕርገቱ
፱/ ” ሌ/ጀኔራል ይልማ ሺበሺ
፲/ ” አቶ አካለ ወርቅ ሀብተወልድ
፲፩/ ” ፊታውራሪ ክፍሌ እንቁ ሥላሴ
፲፪/ ” ኰሎኔል ጣሰው ሞጆ ናቸው ።

የነዚህ ፲፪ ጀግኖች በስማቸውና በፎቶግራፋቸው አቀማመጥ ልዩ ክብር እንዲሰጣቸው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር አስቀድሞ ውሳኔ ያሳለፈ ቢሆንም ሁሉም በቀላሉ የማይተኩ ፣ በትምህርት የበሰሉ ፣ ሀገራቸውን በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በማህበራዊ ኑሮ ፣ በአስተዳደር እና በጦር ሙያ ዘርፍ ያገለገሉ ፣ ሚኒስትሮች ፣ አምባሳደሮች ፣ ከፍተኛ የጦር መሪዎች ፣ የቴክ

www.ethipianorthodox.org

ኒክ ባለሙያዎች ፣ አስተዳዳሪዎችና ምሁራን የነበሩ ፣ ዓለም አቀፍ ታዋቂነትን ያተረፉ ታላላቅ ሰዎች እንደሆኑ ማንም የሚያውቀው ነው ።

ነገር ግን እኒህ የሀገሪቱ ታላላቅ ሰዎች ለውጭ ፋሺስት ያልተበገሩ ፤ ድል አድራጊ ጀግኖች ፣ አስመሳይና አታላይ በሆነው የወገን ፋሽስታዊ አምባገነን ደርግ ተዘናግተው ከየሥራ ቦታቸውና ከየመኖሪያ ቤታቸው ተወስደው የፀሐይ ብርሃን በማይገኝበት ቀዝቃዛ ምድር ቤት ውስጥ ታጉረው በሰቆቃ ረጅም ጊዜ ከቆዩ በኋላ ያለፍርድ ፣ ከሰብአዊ ርህራሄ ውጭ በአውቶማቲክ ጠብመንጃ በመጨፍጨፍ ፣ የሕይወታቸው ማለፍ በውል ሳይረጋገጥ በግሬደር በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ እንደውሻ ሬሳ ተጥለዋል ። ይህ አድራጎት በኢሰብአዊነቱም ሆነ በፖለቲካ ቅሌቱ ተወዳዳሪ የሌለው ወራዳ አፈጻጸም በመሆኑ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ድርጊቱን ቃላት ሊገልጡት በማይችሉ ከፍተኛ የሐዘን ስሜት ያወግዛል ። በዚያ ፋሽስታዊና አረመኔአዊ እልቂት አንጀቱ ያረረው ቤተሰብና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትሐዊና ወገናዊ በሆነ ተቆርቋሪነት ከዚያም አልፎ በደም መላሽነት የእነዚህ የሀገሪቱ ታላላቅ ሰዎች አጽም በስውር ከተጣለበት አልባሌ ቦታ በረቀቀ ምርምር እንዲደረስበት ያላሰለሰ ጥረት አድርጎ የእምነት ፣ የኢትዮጵያዊነትና የባለውለታነት ክብሩን በማስገኘት በዚህ የአርበኞች ፣ የውስጥ አርበኞችና የስደተኞች አጽም ማረፊያ እንዲሆን መንግሥት በመደበው ታላቅ ካቴድራል ቅጽር ግቢ ውስጥ ሐውልት አዘጋጅቶ እንዲያርፍ በማድረጉ በመላ የኢትዮጵያ አርበኞች ስም ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ከዚህም በቀር የዛሬው ዕለት የ፷ቱ ሰማዕታት ውለታና ክብር ተሐድሶ ያገኘበት በመሆኑ የሟች ቤተሰቦች ፣ ወዳጆችና ወገናዊ ተቆርቋሪዎች ሁሉ ልንጽናናበት እንጂ ሐዘኑን አገርሽተን ልንመለሰበት አለመሆኑን ለማስታወስ እወዳለሁ ።

ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ኃያሉ እግዚአብሔር ለሟቾች መንግሥተ ሰማያትን ፣ ለቤተሰብ ጽናቱን እንዲሰጥ በመላ የኢትዮጵያ አርበኞችና በሥራ አመራር ምክር ቤት አባላት እንዲሁም በራሴ ስም እመኛለሁ ።

ስላዳመጣችሁኝ እግዚአብሔር ይስጥልኝ

ግራዝማች ዓለማየሁ በላይ
የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት

አዲስ አበባ

ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም

---

## በ፷ቹ ቀዳሚ ሰማዕታት አጽመ ዕረፍት ሥነሥርዓት ላይ የቤተሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያደረጉት ንግግር

---

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፤
ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፤

ክቡራን አምባሳደሮችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተጠሪዎች
ክቡራን ቤተሰቦችና እንግዶች ፤

የሥራ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ የሐዘናችን ተካፋይ ለመሆን በመካከላችን ስለተገኛችሁ በሙዋች ቤተሰቦች ፣ በቤተሰብ አስተባባሪ ኮሚቴና በራሴ ስም ምስጋና አቀርባለሁ ።

ዛሬ ደርግ መጀመሪያ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ፷ውን ፣ ቀጥሎ ከአምስት ዓመት በኋላ ደግሞ በሐምሌ ወር ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ፲ሩን በድምሩ ፸ውን ያለፍርድ በግፍ የገደላቸውን ከፍተኛ የቀድሞ ባለሥልጣኖች አጽም በክብር የምናሳርፍበት ፣ የደርግን ኢሰብአዊነትና አውሬነት የምናስታውስበት ፣ "ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም" እያለ ተነስቶ አሥራ ሰባት ዓመት ሙሉ የዜጎችን ደም ያፈሰሰበትን ሁኔታ ፣ የምናስብበት ዕለት ነው ።

በዛሬው ቀን በተለይ ማስታወስ የምንፈልገው የቀድሞዎቹን ስድሳ ባለሥልጣኖች መገደል በወቅቱ ደርግ ስማቸውን ዘርዝሮ ሲያውጅ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለተገደሉት ፲ ባለሥልጣኖች በሕይወት መኖር ወይም አለመኖር ማረጋገጥ የተቻለው ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ አጽማቸው ከተጣለበት እየተቆፈረ ከወጣ ወዲህ መሆኑን ነው ። ስለዚህ በቅርብና በሩቅ የሚገኝ ዘመድ አዝማድ ሁሉ እርሙን ያወጣ ዘንድ ስማቸውን ቀጥሎ መዘርዘር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል ።

፩ኛ/ ክቡር ፀሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ

፪ኛ/ ክቡር ደጃ/ካሣ ወልደማርያም

፫ኛ/ ክቡር አቶ ሠይፉ ማህተመሥላሴ

፬ኛ/ ክቡር አቶ ዮሐንስ ኪዳነማርያም

፭ኛ/ ክቡር ብ/ጄ ሳሙኤል በየነ

፮ኛ/ ክቡር ደጃ/ሐረጎት አባይ

፯ኛ/ ክቡር አቶ አሰፋ ድፋዬ

፰ኛ/ አቶ አበበ ከበደ እና

፱ኛ/ ፊታ/ክፍሌ ዕንቁሥላሴ ናቸው

የቤተሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ የስድሳውን ሰማዕታት አጽም ከተረከበበት ከየካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ጀምሮ የተቀሩትን ባለሥልጣኖች አጽም ፈልጎና ቆፍሮ እስካወጣበት ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ድረስ እንዲሁም የመጨረሻው ማሳረፊያቸው በዚህች የተቀደሰች ቦታ እንዲሆን



www.ethipianorthodox.org

ብዙ ደክሟል ። በእግዚአብሔር ቸርነት አንዳንድ ችግሮችን አሳልፈን የመታሰቢያው ሐውልት ሥራ የተጀመረ ሲሆን የአጽሙ ማሣረፊያ ቦታ ግን ተደራጅቶ አልቋል ።

የውስጥ ዝግጅት ጭምር በሚቀጥሉት ፫ ወራት የሚጠናቀቅ በመሆኑ ፷ው ሰማዕታት በጥይት ተደብድበው በግፍ የተገደሉበትን ቀን በምናስብበት ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ሐውልቱን ለማስመረቅ አቅደናል ።

የዘመዶቻችን አጽም ከያለበት እንዲሰባሰብ የሽግግሩ መንግሥት ላሳየው በጎ ፈቃድና ላደረገልን እርዳታ የተለየ ምስጋና እናቀርባለን ። እንዲሁም በሥራችን ለተባበሩንና ለረዱን ሁሉ በተለይ ለሽግግሩ መንግሥት የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ፣ ለጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፣ ለመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጽ/ቤት ፣ ለአሊያንስ ፍራንሲስ ትምህርት ቤት አስተዳደርና ለሌሎች ግለሰቦችና ድርጅቶች የቤተሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ ወሮታ እጅግ የላቀ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ ።

ከሀገር ተሰደው በውጭ አገር የሚኖሩ ፶፪ የሙታን ባለቤቶች ፣ ልጆቻቸውና የቅርብ ቤተሰቦች በመካከላችን ለመገኘት በመቻላቸው እንኳን ለቀብሩ ሥርዓት አበቃቸው እንላለን ።

የዛሬው ፕሮግራም የተዘጋጀው የአየር ሁኔታን በማሰብ አጠር ያለ ነው ። በመሆኑም ቀደም ብሎ ታቅዶ የነበረው የውሎ ለቅሶ በዛሬው ዕለት ሊፈጸም አልቻለም ።

ቤተሰብ የዛሬውን ዕለት የሚያሳልፈው በለቅሶና በዋይታ ሳይሆን፣ ፲፯ ዓመት ሙሉ የደረሰበትን ተጽእኖ ፣ ፈተናና ጭቆና ፣ ታፍኖ የቆየውን ሐዘኑን እንዲሁም ችግሩንና ብሶቱን በተመስጦ በሕሊናው በማሰብ ይሆናል ።

የተከበራችሁ እንግዶቻችን

የዛሬው ዕለት ያለፈውን ሐዘናችንን ፣ ሰቆቃን ፣ ችግራችንንና ተጭኖብን የነበረውን የሕሊና ተጽዕኖ በጥሞና የምናስብበት ይሁን ። እንዲሁም ያለስጋት ለማሰብ ለመናገርና ለመፈጸም ላበቃን ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋና የምናቀርብበት ዕለት ያድርግልን ።

አሸናፊ ሽፈራው

የቤተሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር

ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

---

## በ፷፷ ቀዳሚ ሰማዕታት አጽመ ዕረፍት ሥነሥርዓት ላይ የእሥረኞች ተወካይ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያደረጉት ንግግር

---

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ፤

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፤

ክቡራን አምባሳደሮች ፣ የድርጅቶች ተጠሪዎች ፣

ቤተሰቦችና ወዳጆች ፤

የሐዘናችን ተካፋይ ለመሆን የተገኛችሁ ሁሉ ፤

በዛሬው ዕለት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል (ዓውደ ምሕረት) ያለሥጋት በነፃነት ተሰብስበን በአመጸኛው ወታደራዊ ደርግ የአምባገነንነት ዘመን በግፍ የተገደሉ ቀዳሚ ሰማዕታት መታሰቢያ ስናከብር ሐዘንና ደስታ በተቀላቀለበት ስሜት ነው ። ሐዘናችን ወንድሞቻችን በቁማቸው የተቀበሉትን መከራና የግፍ አገዳደል በማሰብ ሲሆን ፣ ደስታችን ደግሞ የእግዚአብሔር የምሕረት ጊዜ ደርሶ ለስማቸው መታደስ ፍትሕ በመስጠቱ ነው ።

በወታደራዊ ደርግ ውሳኔና ትእዛዝ መጀመሪያ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በታላቁ ቤተ መንግሥትና በሌሎችም ሥፍራዎች በጥበቃ ሥር ከነበሩት የፖለቲካ እሥረኞች መካከል ተለይተው ተወስደው በግፍ የተገደሉት የ፷ ባለሥልጣኖችና ፪ኛ ከአምስት ዓመት እሥራት በኋላ ከሐምሌ ፫ እስከ ፲ ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በየቀኑ ከየእሥር ቤቱ ተወስደው ወዴት እንዳደረሱዋቸው ሳይታወቅ ቆይቶ በአለፈው ዓመት ደርግ በውርደት ሲባረር መሞታቸው ታውቆ በብዙ ጥረት መቃብራቸው የተገኘው የ፲ ባለሥልጣኖች አጽም ከተጣለበት ሥፍራ ተሰብስቦ ለሙታን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎላቸው አጽማቸው የክብር ቦታውን ሲይዝ ለማየት በቅተናል ።

ቤተሰብ አባሎቻቸውና ወዳጆቻቸውም ጋር ግፍን አብረን የተቀበልን ኀዘኑንና ደስታውንም የተካፈልን ሁሉ ለኃያል አምላክ ምስጋና ለማቅረብ በቅተናልና የእግዚአብሔር ስሙ ለዘለዓለም ይመስገን እላለሁ ።

የሁሉ ዳኛ ፣ የምሕረትና የፍቅር አምላክ እሱ ራሱ "በቀልን ለእኔ ተው ፣ የምበቀል እኔ ነኝ" ብሏልና የሰው ጥበብ ሳይሆን የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ በታየበት በዛሬው ዕለት በቂም በቀል መንፈስ መመራት ደካማነት ስለሚሆን ፣ ይህ በሐሳባችን እንዲመላለስ አንፈቅድለትም ።

ስለዚህ ፣ ግድ ሆኖብን በዚህ ጊዜ አንዳንድ ድርጊቶችን ብናነሳም ፣ የእሥረኞች ሕይወት ያለፈበትን አስከፊ መልክ በማሳየት ፣ የወደፊቱን



www.ethipianorthodox.org

የሕዝብ ኑሮ ለማቃናት በትምህርትነቱ ጠቃሚ ይሆናል በማለት ብቻ ነው ።

እነዚህ የሕዝብ አገልጋዮች በጊዜያቸው በሰላማዊ አገልግሎት ወይም በውትድርና ፣ ችሎታቸው በፈቀደው መጠን ድርሻቸውን ያበረከቱ ፣ የሚከተለውም ትውልድ በመከበር በሰላም ይኖር ዘንድ ብዙ ዓይነት መስዋዕት የከፈሉ በመሆናቸው የተፈጸመባቸው የውለታ ቢስነትና የአረመኔነት ሥራ ሲታወስ የሚኖር ነው ።

እነዚህ ወንድሞቻችን ለሀገርና ለወገን ኑሮ መሻሻል ለሚታመንባቸው የለውጥ ሂደቶች ተቃዋሚ አልነበሩም ።

እጃቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁም በቅንነት ወደተጠሩበት እየሄዱ እጃቸውን ሰጡ ። ምክንያቱም "ሥልጣናቸውን መከታ አድርገው አስተዳደር አዛብተዋል ፣ ዳኝነት አጉድለዋል ፣ አለ አግባብ በልጽገዋል" የሚለው የተጋነነ አሉባልታ እንዲጣራ መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ ስለነበር "ክሱ በሕግ አግባብ ይጣራል" ብሎ በማመን ነበር ።

በግፍ ከተገደሉት ወንድሞቻችን መካከል አንዱ ይህንኑ ሁኔታ በተመለከተ የዘረፉት ጉባኤ ቃና ቅኔ ፤

"ሠራዊተ ኢትዮጵያ ኵሎሙ ዘበትሕትና
ተንሥኡ

ወልታ ወሐፀ እምአበዊሆሙ ነሥኡ ።"
የሚል ነው ።

በአገራችን ልማድ ሽማግሌዎች ከአንድ ሰው ቤት በእንግድነት ሲገቡ ወጣቶቹ ተነስተው በአክብሮት ጋሻና ጦራቸውን ተቀብለው በክብር ሥፍራ ያስቀምጧቸዋል ። ቅኔው በዚህ መንፈስ የተመራ የቆየውን ተወዳጅ ባህላችንን የሚገልጽ ሲሆን ፣ ግምቱ ግን የተሳሳተ መሆኑን ተከታትሎ የተፈጸመው ድርጊት አሳውቆታል ።



ደርግ ከእንደዚህ ያለ ጨዋነት የተራቆተ አጥፊ የሆነ የክፋት መሣሪያ በመሆኑ ፣ አማካሪዎቹም በምግባር ያልተሻሉ (ሞኝ ምሁራን) ሆነው በመገኘታቸው "የጥበብ መጀመሪያ ፈሪሃ እግዚአብሔር ነው" የተባለውን መለኮታዊ ትእዛዝ ተከትለው ተስፋ ያለው አመራር ሊሰጡ ባለመቻላቸው የተጠበቀው ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ምልክቱም አልታየም ። በዚህ ፋንታ ደርግ ያሳየው ባሕሪ የትዕቢተኛነት ፣ የምቀኝነት ፣ ከሁሉም ይበልጥ የተበቃይነት ክፉ መንፈስ ነበር ። ከግብሩ እንደታየው ፣ ትንሽነትና አለአዋቂነት ይሰማው ስለነበረ ፣ ከዕውቀቱና ከችሎታው በላይ የሆነውን ሰው ሁሉ ማዋረድና ማጥፋት የተገባ ተግባር ነው ፤ ብሎ ተያይዞት ነበር ። በዚህ በጎስቋላ መንፈስ በመመራት ፣ በእሥረኞች ላይ እንኳ በጊዜ እጥረት ምክንያት ሊዘረዘር የማይቻል ፣ ብዙ ፈተና እና ውርደት አድርሷአል ።

ይህም ሁሉ ተደርጎ በዚህ መራራ ሕይወታችን የእግዚአብሔር ረድኤት ስላልተለየን ካህናትን ከመካከላችን አላሳጣንም ነበርና እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ጸሎትና ምሕላ ሳይታጎል ፣ የወንጌል ስብከትም ሳይቋረጥ ቆይቷል ። በዚህም ጊዜ ለምርመራ የምንሄድ እሥረኞች ሁለት እጆቻችን በብረት ማነቆ (ዛንጅር) እየታሠርን ፣ ሳንጃ በደገኑ ወታደሮች እየታጀብን ምርመራ ኮሚሽን ችሎት ስንመላለስ ቆይተን ውጤትን በመጠባበቅ ላይ ነበርን ።

የእሥረኝነት ጊዜ ሕይወታችን በዚህ ዓይነት ሲቀጥል የግፍ ጽዋ ከተቀበሉት ወንድሞቻችን ጋር ኅዳር ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤልን በዓል አብረን ለማክበር በቅተን ነበር ።

እንደማስታውሰው በጸሎቱ ሥርዓት ላይ የተዘመረው ምስባክ ፤

"እስመ በእንቲአሁ ይቅትሉነ ኵሎ አሚረ
ወኮነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሁ
ንቃህ እግዚኦ ለምንት ትነውም"
ይህም ወደ አማርኛ ሲተረጎም
"ስለ አንተ ሁልጊዜ ተገድለናል
እንደሚታረዱም በጎች ሆነናል
አቤቱ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ" የሚል ነው

ዘማሪው ዲያቆንም አቶ አካለ ወርቅ ሀብተወልድ ነበሩ ።

ይህ ኅዳር ፲፪ ቀን የተዘመረው ምስባክ ግድያው ከደረሰ በኋላ ግልጽ እንደሆነው "ትንቢትሰ ይቀድም ለነገር" እንደተባለው ፣ ኅዳር ፲፬ ቀን የተፈጸመውን የግፍ ግድያ አስቀድሞ የሚያመለክት ኖሯል ። እንግዲህ በታሪክ ሲታወስ የሚኖረው ድርጊት መግለጫው ጊዜ መድረሱ ነው ።

ደርግ በተባለ የአንድነት ስም የተሰባሰቡና ለሥልጣን የጓጉ የበታች መኰንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ/ም የሬዲዮ ጣቢያውን ይዘው ሕዝቡን ለጥላቻና ለቁጣ አነሳሱ ። ተቃዋሚ ይሆናሉ ተብለው የሚያሰጉትንም ባለሥልጣኖች እና ከፍተኛ መኰንኖች በብረት ለበስ የጦር መኪናዎች እየሰበሰቡ ቆይተው በመጨረሻ ንጉሠ ነገሥቱን መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከዙፋናቸው አውርደው ሥልጣን ያዙ ። በዚሁ ዓመት ኅዳር ፲፬ ቀን ከፖለቲካ እሥረኞች መካከል በ፷ው ላይ የግፍ አገዳደል ፈጸሙባቸው ። በተለይ ያቋቋሙትን ፍርድ ቤት እንኳን ባለማመን ከሕግ አሠራር ውጭ በችኮላ በተደረገ ውሳኔ በማግሥቱ ጠዋት ትዕቢት በተሞላበት ቋንቋ "አብዮታዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል" የሚል መግለጫ በሬዲዮ አናገሩ ። በተጨማሪም የፈጠራ የወንጀል ክስ በጋዜጣ ታትሞ ወጣ ።

www.ethipianorthodox.org

በዚሁ ዕለት ሁለት የደርግ አባላት ወደ እሥር ቤቱ መጥተው የወንድሞቻችንን ሞት ሲያረዱን ፣ ወደፊት ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ በዚህ ዓይነት "አብዮታዊ እርምጃ" የማይወሰድ መሆኑን ለማረጋገጥ ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት ቃል ገቡልን እኛ ግን ከማፌዝ ነው የቆጠርነው ። ይህም እውነት ይሆን ዘንድ አከታትለው የፈጸሙት ድርጊት መስክሮባቸዋል ።

በዚህ ዕለት በሁለት ክፍሎች የነበርን እሥረኞች ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ክፍል ውስጥ ተገናኝተን ከተላቀስን በኋላ ካህናቱም ጸሎተ ፍትሐት አድርሰው ወደየክፍላችን ተመለስን ። ድርጊቱንና አደራረጉ እኛን ቀሪዎቹን ጥልቅ ኀዘን አሳደረብን ። "አልሞትኩም ብየ አልዋሽም" ተብሎ በአንድ አጋጣሚ የተነገረው በዚህ ጊዜ የሚታወስ ነው ። ይሁን እንጂ ኀዘኑ እጅግ ከባድ ቢሆንብንም ራሳችንን ለእግዚአብሔር አደራ በመስጠት ወደፊት የሚደርስብንን በትዕግሥት ለመቀበል ቆርጠን የእሥረኝነት ሕይወታችንን ተያያዝነው ። በዚያው ሰሞን ጋዜጣ እንዲገባልን ስለተፈቀደ የየዕለቱን ድርጊት በመከታተል የሕዝቡን የመከራ ኑሮ በመንፈስ ተካፍለናል ።

በተፈጸመው የግፍ ግድያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን እንደተሰማው ማወቂያ መንገድ አልነበረንም ። ከተባራሪ ወሬ እንደሰማነው መቆጣት ባይችልም ፣ ማዘኑና መደንገጡን የተረዳነው ፣ ደርግ እንደጠበቀው በጭብጨባ ሳይቀበሉት በየቤቱ በለቅሶና በዋይታ በማሳለፉ ነው ። ድርጊቱ እንኳን ኢትዮጵያውያንን የውጭውንም ዓለም አስደንግጧል ። ነፃነት በአለበት አገር ፣ በመንግሥት ሥራ ላይ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ፣ "በሰላምና ፍትሕ ወዳድነት ተለይታ በምትታወቅ በኢትዮጵያ ይህን የመሰለ ሕገ ወጥ ሥራ ተፈጽሞና ተሰምቶ አይታወቅምና ከዛሬ ጀምሮ የዚህ አመጽ ተባባሪ አይደለንም" ሲሉ ሥራ የለቀቁ ፣ በጽሑፍ የተቃወሙና ከአገር የወጡ ብዙዎች ነበሩ ።

በዚያ ጊዜ ለእኛ ለእሥረኞች የገረመንና እጅግ ያሳዘነን ፣ ያቺ ስሟ የገነነው ቤተ ክርስቲያናችን ውርደቱ በራስዋ ላይ በኋላ በቀጥታ መድረሱ ላይቀር ፣ ይህን የመሰለ ከሕግ ውጭ የሆነ የአረመኔነት ሥራ ሲፈጸም እያየችና እየሰማች ዝም ማለቷና የተጎዳውም ወገን አጽናኝ ያጣበት ጊዜ በመሆኑ ነበር ። ቅዱስነታቸው የቀድሞው ፓትርያርክም ብዙ ሳይቆዩ ከእሥረኞች ጋር በተቀላቀሉ ጊዜ ተነጋግረንበት ስለነበረ ራሳቸው ጸሎቱን በመሩበት በመጀመሪያ ዕሑድ የጋራ ጸሎት ከመደረጉ በፊት ይቅርታ ጠይቀው ፣ ተላቅሰን ከልብ ይቅር ብለን ፣ ከእናት ቤተ ክርስቲያናችን መሪዎች ጋር ያለንን መገናኛ ማስተካከላችንን ዛሬ ስንገልጽ ያለአንዳች ቅሬታ ነው ።

በዛሬው ዕለት በዚህ ቤተ ክርስቲያን የሚነገረው ሁሉ ግፍ የተፈጸመባቸውን ሰማዕታት ይረዳል ለማለት ሳይሆን ፣ የነገው ሰው አደጋው በራሱ ላይ እስኪደርስ ከመጠበቅ ፣ በሩቅ ለመከላከል የሚችል የማይበገር ጽኑ ጠባይ ባለቤት ለመሆን የሚያነሳሳ ይሆናል ብዬ በማመን ነው ።

ከደረሰ ወዲያ ዋይታ የሚጠቅም አለመሆኑን ያለፈው ድርጊት አስተማሪ ሊሆን ይችላል ።

ወዳጆቼ ፣ ወገኖቼ ፤

የእሥረኞቹን ቤተሰብ በዚህ ጊዜ አለማስታወስ ሐቀኝነት የተለየው ውለታ ቢስነት ይሆናልና ይህን ተግባር ባልፈጽም ኅሊናዬ ይወቅሰኛል ። የእሥረኞች ቤተሰቦች በውርስ ከተራቆቱ ባዶ ቤት ስንቅ ለማቀበል ከሚደርስባቸው ጭንቀት በላይ ፣ በልጆችና በመላ ቤተሰብ ጭምር ይደርስ የነበረውን ስድብና ውርደት ማስታወስ የሚያሳዝንና የሚዘገንን ነው ። ይህን ሁሉ ታግሰው ያሳለፉ መሆናቸው በማኅበረሰቡ ዘንድ ባለውለታ ሊያደርጋቸው ይገባል ብየ አምናለሁ ።

በበኩሌ የውለታው ተጠቃሚ በመሆኔ በራሴና በሁሉም እሥረኞች ስም ሆኜ ከልብ ጥልቀት የመነጨ ምስጋና ከሽምግልና ምርቃቴ ጋር በማቅረብ ፣ በዚያ በችግራችን ጊዜ በመንፈስም ሆነ በሚያስፈልግ ሁሉ እርዳታ ላደረጉልን ልዑል እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ ።

በዛሬው ዕለት በዚህ ቅጥር ቤተ ክርስቲያን የ፷፫ቱ ሰማዕታት አጽማቸው በክብር ሥፍራ በሚያርፍበት ወቅት ከአሁን በፊት ተላቅሶ ለመቅበር እንኳ ዕድል ላልነበራችሁ ቤተሰቦች ሁሉ እግዚአብሔር ጽናቱን ይስጣችሁ እላለሁ ። በሥነ ሥርዓቱ ለመካፈል ከቅርብም ፣ ከሩቅም ለመጣችሁት ሁሉ ምስጋና ይግባችሁ ።

ለዚህ ያበቃን አምላክ ስም አሁንም ይክበር ይመስገን ። አ ሜ ን !

ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት

የእሥረኞች ተወካይ

ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም

www.ethipianorthodox.org

## በ68 ቀዳሚ ሰማዕታት አጽመ ዕረፍት ሥነ ሥርዓት ላይ የሚስቶች ተወካይ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያደረጉት ንግግር

ክቡራትና ክቡራን እንግዶቻችን

አባቶች ፣ እናቶች ፣ ወንድሞችና ልጆቻችን

ከሁሉም አስቀድመን የደርግ መንግሥት ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ፍትሕ በጎደለው ውሳኔ የተገደሉትን የባሎቻችንና የቤተሰቦቻችንን የቀብር ሥነ ሥርዓት ከምናከብርበት ከዛሬዋ ታሪካዊ ዕለት በሕይወት ተገኝተን ለዚህ ላበቃን ልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰው እያልን በወከሉን ቤተሰቦችና በራሴም ስም ሲቃ የተሞላበትን ደስታ በታላቅ ክብር እገልጻለሁ ።

ደርግ በግፍ የገደላቸውን ባሎቻችንና ቤተሰቦቻችንን አስከሬን አግኝተን አልቅሰን እንዳንቀብር በመከልከሉ እነሆ ለ፲፯ ዓመታት በግልጽ ሐዘናችንና እርማችንን እንዳናወጣ ታፍነን ውስጣዊ ሐዘን አንጀታችንን ሲያቃጥል ቆይቷል ። ሁሉን ማድረግ የሚችል ልዑል እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ባለመኖሩ በራሱ ጥበብና ቸርነት ያንን ሁሉ መከራና ጭንቅ አሳልፎ የእነዚያ ንጹሐን ዜጎች አጽም ከተጣለበት የወል ጉድጓድ ወጥቶ በዛሬዋ ዕለት ዘመድ አዝማድ ፣ ወዳጅና ሕዝብ በተሰበሰበበት የቀብራቸውን ሥነ ሥርዓት ለመፈጸም እዚህ ቦታ እንገኛለን ።

ክቡራትና ክቡራን ፤

የዛሬ ፲፰ ዓመት የደርግ መንግሥት "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን መፈክር ሲያስተጋባ ፣ ባሎቻችን ፍትሕና ሕግ አለ ብለው ኢትዮጵያ አገራቸውን በማስቀደም ደም ላለማፋሰስ እጃቸውን በመስጠት መስዋዕት የሆኑ አገር ወዳዶች ፣ ጀግኖች በግፍ ያለፍርድ ተገድለዋል ።

ቤተሰቦችም ያለፍርድ ታስረን ፣ ልጆቻችን ተገደሉ ፣ ከሞት የተረፉትም ከእኛው ጋር በየወህኒ ቤቱ ለረጅም ዘመናት ተሰቃዩ ፣ ከባድ በሽታ ላይም ወደቅን ። አብዛኞቻችንም የሞራል ውድቀት ደረሰብን ።

በዕድሜያቸው ምክንያት ከመታሰር ያመለጡት ሕፃናት ፣ አባቶቻቸው በመገደላቸውና እኛም እናቶቻቸው በመታሰራችን ያለአሳዳጊ ባዶ ቤት ውስጥ ቀሩ ። ለአካለ መጠን የደረሱት አልፎ አልፎ ሥራ ሲያገኙ የአድኃሪያን ልጆች ናቸው እየተባሉ ለስቃይ ተዳረጉ ። አብዛኞቹም ሥራ እንዳይሰጣቸው በመታገድ ሕልውናቸውና የዜግነት መብታቸው ተገፎ በችግር ሲማቅቁ እንዲኖሩ ካለሕግ ተፈረደባቸው ።

ክቡራትና ክቡራን

ያንን ሁሉ የረጅም ዘመን መከራና መራራ ሐዘን አሳልፈን በዛሬዋ ዕለት በሕይወት በመገኘት በግፍ የተገደሉትን የባሎቻችን አጽም በዚህ ሥፍራ ሲያርፍ ለማየት በመብቃታችን ዕለቷ የትንሣኤ በዓላችን ናት እላለሁ ። ባሎቻችንም በግፍ ተገድለው ከእኛ ከቤተሰቦቻቸውና ከወገኖቻቸው የተለዩ ቢሆንም ለሀገራቸውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከወጣትነት ጊዜ ጀምረው እስከ ወደቁባት ዕለት ድረስ የሚያኮሩ ተግባራትን የሠሩ መሆናቸውን ታሪክ ስለሚመሰክርላቸው ሕያዋን ናቸው ብለን ከሐዘናችን እንጽናናለን ። ለደረሰብን ግፍ ግን እውነተኛ ፍርድ እንዲሰጥ ለእግዚአብሔርና ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንተዋለን ።

በመጨረሻም በዛሬው ቀን የሐዘናችን ተካፋዮች ለሆናችሁ ሁሉ በሚስቶች ስም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። አመሰግናለሁ ።

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ
የሚስቶች ተወካይ

ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም

## በ68 ቀዳሚ ሰማዕታት አጽመ ዕረፍት ሥነ ሥርዓት ላይ የወንዶች ልጆች ተወካይ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያደረጉት ንግግር

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ጳውሎስ

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት

የተከበራችሁ አምባሳደሮች

የተከበራችሁ እናቶቻችን ፣ አባቶቻችን እህቶቻችንና ወንድሞቻችን የሐዘናችን ተካፋይ የሆናችሁ እንግዶቻችን ክቡራንና ክቡራት ፤

ዛሬ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተሰብስበን ያለፍርድ በግፍ የተፈጁትን የውድ አባቶቻችንን አጽም አሰባስበን በክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እንድንሰናበታቸው ላስቻለን አምላክ ክብርና ምስጋና እናቀርባለን ።

በአባቶቻችን መታሰርና ሕልፈት በእኛና በቤተሰቦቻችን ላይ ጀምበር ስትጠልቅ ፣ የደረሰብንን ሁሉ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናስታውሰው ቀሪን ያስገርመዋል ። ገና ከማለዳው የደረሰብን መራብ ፣ መራቆት ፣ ብቻ አልነበረም ፤ መዋረድ ፣ ማፌዣ መሆንም እንጂ ። ደርግ አፍኖ በሚያስቃያቸው አባቶቻችን ላይ ከሚነዛው የሐሰት ፕሮፓ



www.ethipianorthodox.org

ጋንዳ የተነሳ ፣ የመንደር ልጆች ብቻ ሳይሆኑ የትምህርት ቤት ጓደኞቻችንም ሳይቀሩ ፣ መዘባበቻ ያደርጉን ነበር ። ይህም ሕሊናችንን ስለሚያቆስለው ብዙዎቻችን ትምህርታችንን በደንቡ ለመከታተል አልቻልንም ነበር ።

በዚህ በፈተናችን ዘመን የረዳን ከአባቶቻችን ያገኘነው የመንፈስ ጥንካሬና አባታዊ ምክር ነበር ።

ይባስ አታምጣ እንዲሉ ደርግ አሰቃይቶ በእስር ከአጉላላቸው በኋላም ፣ በኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም አባቶቻችን ያለፍርድ ተገደሉብን ። በተጨማሪም ከአምስት ዓመት እስር በኋላ ከሐምሌ ፫ ቀን እስከ ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ባለው ጊዜ አባቶቻችን ከእስር እየተወሰዱ የትእንደ አደረሷቸው እንኳን ሳይነገረን ቀርቷል ።

ይህ አረመኔያዊ ድርጊት አባታዊ እንክብካቤአቸውን ብቻ አይደለም ያሳጣን ፤ ያለልቅሶ መቅበርንና የወደቁበትን ትክክለኛ ሥፍራ ለይቶ የማወቅ መብታችንን እንኳን ሳይቀር ነፍጎናል ። ለመከራ አድሎን የኛ መከራ በዚህ ብቻ አላበቃም ። በቀበሌ መታሰር ፣ መገረፍም ደርሶብናል ። ከመካከላችን በአባቶቻቸው ደፍ የተገደሉም አሉ ። ከቀበሌ ስቃይ የተረፍነው ደግሞ ያለጥፋት በደርግ ታስረናል ፤ የመማር ፣ በሰላም የመኖር ፣ የመሥራት ፣ ከአገር የመውጣት እድልም ተነፍገናል ። በዚህም ምክንያት ብዙዎቻችን ከኢትዮጵያ እንድንሰደድ ተገድደናል ፤ በእግር ጉዞ ወደ ጎረቤት አገሮችም መሄድ የማይቀር ሆኗል ።

በጉዞ ላይ የአውሬ ራት የሆኑ ፣ በረሀብና በደርግ ጥይት የሞቱ ፣ በዱር በገደል የወደቁም አሉ ። እነዚህን ወንድሞቻችንን እንደዚሁም በደርግ የተጨፈጨፉትን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ሁሉ በዚች ሰዓት በሰቀቀን እናስታውሳቸዋለን ። ከሞት ተርፈን ከጎረቤት አገሮች የደረስነውም ካምፕ በስደተኛነት ማቀናል ።

ሆኖም ለአምላክ ክብር ምስጋና ይድረሰውና ብዙዎቻችን በአፍሪካ ፣ በምዕራብ አውሮፓና በአሜሪካ በሰብአዊ ርህራሄ ጥገኝነት ተሰጥቶን የመኖር ፣ የመማርና የሠርቶ የማደር ዕድል አግኝተናል ። ለዚህ ለአበቁን ለምዕራብ አውሮፓ ፣ አሜሪካና አፍሪካ መንግሥታት ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን ።

በመንፈስ እንጂ በአካል ለማያዩን ዛሬ በዚህ ቅዱስ ሥፍራ አጽማቸው ለሚያርፈው አባቶቻችን ፍቅራችንንና የመንፈስ ጥንካሬያችንን በኩራት እንገልጽላቸዋለን ።

በዚህ ወቅት ለነፃነትዋ ፣ ለአንድነትዋ ፣ ለሰላምዋ ፣ በዓለም ለመታወቅዋ ፣ ለመፈራትዋ ፣ ለክብሯም ሲሉ ደማቸውን ያፈሰሱላትን ፣ በዓለም አቀፍና በአገር ውስጥ መድረኮች በፖለቲካውና በዲፕሎማሲውም ዓለም የተከራከሩላትንና የቆሙላትን አባቶቻችንን ፣ እናት አገር ፣ ኢትዮጵያን በቅንነት ለማገልገልና ለሕልውናዋም ለመሰዋት ፣ ምን ጊዜም ዝግጁ መሆናችንን በማረጋገጥ ቃል ኪዳን እንገባላቸዋለን ። ይህንንም ፈጽሞ ለመገኘት ኃያሉ እግዚአብሔር ይርዳን ።

በመጨረሻም የአባቶቻችንን አጽም ቆፍሮ በማውጣትና በማስረከብ ለዛሬው ሥነ ሥርዓት አመቺ ሁኔታ የፈጠረልንን የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት እናመሰግናለን ። እንዲሁም አጽማቸው በዚህ ቅዱስ ሥፍራ እንዲያርፍ ለተባበሩን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤትና ለጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች ማኅበር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን ።

ዶ/ር አስፋ ወሰን አሥራት  
የወንዶች ልጆች ተወካይ  
አዲስ አበባ ፤ ሐምሌ 20 ቀን 1984 ዓ/ም

## በ68 ቀዳሚ ሰማዕታት አጽመ ዕረፍት ሥነ ሥርዓት ላይ<br>የሴቶች ልጆች ተወካይ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያደረጉት ንግግር

ብፁዕ አባታችን  
የተከበራችሁ የሐዘናችን ተካፋዮች  
እናቶችና አባቶች ፣ እህቶችና ወንድሞች ፤

በዚህ በዛሬዋ የሐዘንና የደስታ ቀን የአባቶቻችንን አጽም በክብር ለማሳረፍ ላበቃን ልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰው ።

ከ፲፯ ዓመት በፊት ያለፍርድ በግፍ የተገደሉትን አባቶቻችንን አጽም ከተጣለበት ቦታ አሰባስበን ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰናበት በዛሬዋ ዕለት በዚህች ቦታ እንገኛለን ። ሕይወታቸው ያለፈበትን ሁኔታ መላው የዓለም ሕብረተሰብ ያወገዘው ቢሆንም ለእኛ ለልጆቻቸው የረጅም ጊዜ መራር ሐዘን ሆኖብናል ።

ይህን የሐዘን ጊዜ ያሳለፍነው በእስር ቤትና በስደት ላይ ሲሆን ከልጆችም መካከል እንዳባቶቻቸው ያለፍርድ የሞትን ጽዋ የተቀበሉ አሉ ። በዚህ ብቻ አልበቃም ። በተከታታይ የያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሕይወት ኑሮ ባጠፉት ጥቂት ወታደሮች ቡድን መላው የሀገሪቱ ሕዝብ ሐዘንተኛ ሊሆን ተገዷል ።

አባቶቻችን ከሁሉም በላይ አገራችንን እንድንወድ አስተምረው አልፈዋል ። ለዚህም ነው በማንኛውም አገር ስደተኛ ሆነን መኖር አስቸጋሪ የሆነብን ። አባቶቻችን ባህላችንን ጠንቅቀን እንድናውቅና እንድንኮራበትም ስላስተማሩን ፍጹም ኢትዮጵያዊ አድርጎናል ። ለነፃነት ያደረጉትን ተጋድሎ ስናስታውሰው በጣም ያኮራ

ናል ፤ እናደንቃቸዋለንም ። አባቶቻችን ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው እውነተኛ ነበሩ ። ድሮም ታስረውም ፣ ተገድለውም ፣ ዛሬም ፣ ለወደ ፊትም የምንመካባቸውና የምናፈቅራቸው አባቶ ቻችን ናቸው ። ዳግም መወለድ ቢቻል ኖሮ ከነርሱ እንደገና ለመወለድ እንኮራባቸዋለን ። ከነርሱ ባገኘነው ትምህርትና የሞራል ጥንካሬ አሁን ላለንበት ቀንና ቦታ ደርሰናልና ።

አባቶቻችንን በመስዋዕትነት የከፈልንባትን አገራችንን ከሁሉም ነገር በቀደምትነት እንድ ንወዳትና የአባቶቻችንን አርማ ይዘን ምትክ ልንሆን ፣ ወገኖቻችን ኢትዮጵያውያንን በፍቅር የማገልገል ግዴታ አለብን ። የሀገራችንን ነፃነትና አንድነት ለመጠበቅ ለሀገሪቱም እድገት ግዴታ ችንን መወጣት እንዳለብን የአባቶቻችን አጽም ጥሪ ስለሆነ ተገቢውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ሆነን መገኘት ይኖርብናል ።

ዛሬ አጽማቸውን የምናሳርፈው አባቶቻችን የሀገር ባለአደራዎች ስለነበሩና ግዴታቸውንም በሚገባ የተወጡ በመሆኑ እንኮራባቸዋለን ። በሕግ ላይ በነበራቸው እምነት ምክንያት ሕይወ ታቸው በማለፉ ስማቸው በሰማዕታትነት ሲወሳ ይኖራል ።

በዚህ አጋጣሚ እናቶቻችን ፣ የደረሰባቸውን ከባድ ሐዘን ፣ እስራትና ችግር ተቋቁመው ፣ ለዚች ቀን እንድንደርስ በማድረጋቸው በአድናቆት እና ስታውሳለን ፣ ከልብም እናመሰግናቸዋለን ።

በመጨረሻም ሁሉን የሚችል ሕያው እግዚ አብሔር ነፍሳቸውን በፍቅር እጁ እንዲረከብልን እንማፀነዋለን ።

እዚህ በመገኘት ሐዘናችንን የተካፈላችሁትን በሙሉ አመሰግናለሁ ።

ወ/ሮ ሂሩት መስፍን

የቤት ልጆች ተወካይ

ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም



## እንጉርጉሮ

እናንት መሳፍንቶች መኳንንቶችና የጦር ኃይል አዛዦች ማን ማን እንበላችሁ ፤
ተለያይተን ቆየን ተረሳን ስማችሁ ፤
ከቃላት ይበልጣል ይመስክር ሥራችሁ ።

እናንተ መሳፍንቶች መኳንንቶችና የጦር ኃይል አዛዦች የሠራችሁ ለሀገር ፤
ስጦታ አገኛችሁ ሽልማት የእጅ አንባር ።

በምን ይታወቃል የማዕረግ ክብራችሁ ፤
ሁላችሁ አንድነት በእጅ አንባር ጌጥና በመርገፍ ላይ ናችሁ ።

ልባዊት ፣ ነባቢት ፣ ሕያዊት ሰውነት የነበራችሁ ፤
ወደ ግዑዝነት ምን ለወጣችሁ ።

አሥራ ሰባት ዓመት ጭቃ ሹም ሆናችሁ ፤
እንግዲህ ይበቃል ካቡን በላይ ናችሁ ።

ራስ ፣ ደጃዝማች ፣ መሳፍንት መኳንንት ፣ የጦር መኰንኖች አንድ ላይ ሆናችሁ ፤
ሀገር ዲና ስትሆን ምነው ፀጥ አላችሁ ።

እናት ሀገራችን መንገዱ ጠፍቷት ፤
ወደ ኋላ ሄደች ወደፊት መስሏት ።

ነጭ ጤፍ ሠላሳ ተሸጦ እንዳልነበር ፤
እጅ ተስሞ ነው በቆሎ መቶ ብር ።

ሀገራችን ደማች ቆሰለች በጣም ፤
መድኃኒት የሚሰጥ ካልመጣ ሐኪም ።

ፊታውራሪ ገብረሕይወት ወልደሐዋርያት

www.ethipianorthodox.org